# መጽሐፈ መሳፍንት

## መግቢያ

### አሰያየሙ

የዚህ መጽሐፍ አሰያየም ከኢያሱ ዘመን አንሥቶ ንጉሣዊው አገዛዝ እስከ ተጀመረበት ጊዜ ድረስ
በእስራኤል ስለ ነበሩት መሪዎች ይገልጻል:: የመጽሐፉ ዋና ዐላማ በ2፥16 ላይ በግልጽ ተጠቅሶአል::
የእስራኤል መጨቈንና የሚታደጓት ሰዎች መነሣት በእግዚአብሔር ፈቃድ የመጣ ስለ ሆነ መስፍኗና
ነጻ አውጪዋ ራሱ እግዚአብሔር ነበረ (11፥27 እና እግዚአብሔር የእስራኤል እውነተኛ መሪ እንደሆነ
የተነገረበት 8፥23 ይመ)::

### ጸሓፊውና የተጻፈበት ጊዜ

ሳሙኤል መጽሐፉን እንደ ጻፈው በትውፊት ቢነገርም፣ በእርግጠኝነት ማን እንደ ጻፈው ግን
አይታወቅም:: ሳሙኤል ከመሳፍንት ዘመን ጀምሮ የነበረውን መረጃ ሊያሰባስብ እንደሚችል ቢገመ
ትም፣ በዳዊት መንግሥት የነበሩት እንደ ናታንና ጋድ ያሉ ነቢያት መጽሐፉን ቅርጽ የማስያዝና የማ
ስተካከል ዕድል እንደነበራቸው ይታሰባል (1ዜና 29፥29 ይመ):: መጽሐፉ የተጻፈበት ትክክለኛ ጊዜ
ባይታወቅም በነገሥታት ዘመን እንደ ተጻፈ አጠራጣሪ አይሆንም:: በተደጋጋሚ "በዚያን ዘመን በእስራ
ኤል ንጉሥ አልነበረም" የሚለው ዐረፍተ ነገር (17፥6፤18፥1፤19፥1፤21፥25)፣ መጽሐፉ እስራኤል
በንጉሥ መመራት ከጀመረች በኋላ እንደ ተጻፈ ያመለክታል:: በወቅቱ ኢየሩሳሌም ገና በኢያቡሳውያን
እጅ መሆኗ (1፥21)፣ ዘመኑ ዳዊት በ1000 ዓ.ቅ.ክ. አካባቢ ከተማዋን ከመያዙ በፊት መሆኑን ይጠቍ
ማል (2ሳሙ 5፥6-10):: በም 17-21 እንደ ተጠቀሰው በእስራኤል የተከሠተው አዲስ ሁኔታ ግን የዳ
ዊት መንግሥት በሚገባ ከተመሠረተ በኋላ ያለውን ጊዜ ያመለክታል::

### መሪ ሐሳቡና ትምህርተ መለኮቱ

መጽሐፈ መሳፍንት ከኢያሱ ሞት እስከ ንጉሣዊ አስተዳደር ጅማሬ ድረስ የእስራኤል ሕዝብ
በተስፋዪቱ ምድር የነበረውን ኑሮ ያመለክታል:: በአንድ በኩል ዐመፀኝነት በመብዛቱ በሕዝቡ ላይ
የደረሰውን የእግዚአብሔርን ቅጣት፣ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር በመከራና በጭንቀት ጊዜ ለቀረበለት
የርዳታ ጩኸትና ልመና ምላሽ በመስጠት የተለያዩ መሪዎች (መሳፍንትን) አስነሥቶ የሕዝቡን ጠላት
እንደ መታና ሰላምን እንዳሰፈነ ይተርካል:: ከዚህም ሌላ መጽሐፉ እስራኤላውያን በኢያሱ መሪነት
ለአባቶቻቸው የተገባላቸውን የተስፋ ምድር እንደ ወረሱና እስራኤልም እንደ እግዚአብሔር መንግሥት
በምድር ላይ እንደ ተመሠረተች ይናገራል:: ነገር ግን እስራኤል ከነዓን ከገባች በኋላ እግዚአብሔር
ያደረገላትን ሁሉ ወዲያው ረሳች:: ከከነዓናውያን ጣዖታትና እምነት ጋር ራሷን አጠላለፈች::

የመጽሐፈ መሳፍንት መሠረታዊ ጕዳይ እግዚአብሔር የእስራኤል ጌታ መሆኑን መግለጽ ነው::
እግዚአብሔርን በእስራኤል ላይ ጌታና ንጉሥ መሆኑ በመጀመሪያ በሲና ተራራ በተገባው ኪዳን (ዘፀ
19-20)፣ በኋላም በሞዓብ ምድር በሙሴ አማካይነት (ዘዳ29)፣ እንዲሁም በሴኬም በኢያሱ አማካይነት
በተደረገው የኪዳን ተሐድሶ ውስጥ ተገልጾአል (ኢሱ24):: ይሁን እንጂ እስራኤል የእግዚአብሔርን
ንጉሥነት ባለመቀበሏ ጸሓፊው ደጋግሞ ይወቅሳታል:: በም17-21 ላይም በተደጋጋሚ የተወሣው ሰቈቃና
ክስ "በዚያ ዘመን እስራኤል ንጉሥ አልነበራትም፤ እያንዳንዱም በፊቱ መልካም የመሰለውን ያደርግ
ነበር" የሚል ነው (የ17፥6ማብ ይመ):: ይህም በቅድሚያ ሰብዓዊ ነገሥታትን የሚያመለክት ቢሆንም፣
በውስጠ ታዋቂነት ግን እስራኤል ሰማያዊ ንጉሥዋን አለመቀበሏን የሚያሳይ ነው::

እግዚአብሔር በሉዓላዊ ሥልጣኑ ባዕዳን ወራሪዎችን ተጠቅሞ ሕዝቡን በመቅጣት፣ በዚህም በኪዳኑ
የተጠቀሱትን ርግማን በመፈጸም (ዘሌ26፥14-45፤ዘዳ28፥15-68) እንዲሁም ሕዝቡ ተጨንቆ ወደ እርሱ
በሚጮኽበት ጊዜ፣ ነጻ አውጪ መልእክተኞች በመላክ በእስራኤል ላይ ያለውን ንግሥና ይጠብቅ
ነበር፤ የተመሠረተውም አዲስ መንግሥት እንዳይጠፋ ይከላከል ነበር:: ምድሪቱ ከመልክዐ ምድራዊ አቀ
ማመጧ የተነሣም በየጊዜው በተለያየ አቅጣጫ ከተሠነዘረባት የጠላት ወረራ ይታደጋት ነበር::

የሕዝቡ አለመታዘዝ፣ የባዕዳን ጭቈና፣ የርዳታ ጩኸትና ለሕዝቡ የተደረገው ትድግና፣ እግዚአብሔር
ኪዳኑን በታማኝነት እንደሚጠብቅ ያመለክታሉ (2፥11-19፤ነህ 9፥26-31):: መረጋጋት በሌለበት በዚህ
ጊዜ፣ አስደናቂ የሆነው የእግዚአብሔር ትዕግስት ግልፅ በሆነ መንገድ ታይቶአል:: ከሙሴና ከኢያሱ ነጻ
የማውጣት አመራር ቀጥሎ የተከሠተው የእስራኤል ውድቀት፣ መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ዘመን
የከፈተውን ልዩ የአሠራር መንገድ ያሳያል:: የእግዚአብሔርን መንግሥት ተቀናቃኝ ኀይሎች
ለመምታትና የጌታን ቅዱስ ጦርነት ለሚዋጉ ሰዎች የእግዚአብሔር መንፈስ ኀይልን በመስጠት በድል
ያራምዳቸው ነበር (3፥10፤6፥34፤11፥29፤13፥25፤14፥6:19፤15፥14 እና 1ሳሙ 10፥6:10፤11፥6፤16፥3 ይመ)::
ከሁለተኛው ኢያሱ (ከኢየሱስ) የማዳን ሥራ በኋላም በቤተ ክርስቲያን ላይ በመፍሰስ ወንጌልን ለሕዝቦች ሁሉ
የመስበክ ኀላፊነት ለመወጣትና የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት የእግዚአብሔርን ሕዝብ በኀይል
ሞልቶአል (የሐሥ1፥2:8 ማብ ይመ)::

**ታሪካዊ ጻራው**

መሳፍንት የነበሩበትን ትክክለኛ ዘመን ለመናገር አዳጋችና ውስብስብ ነው::⁄ የታሪኩ የዘመን አቈጣጠር በዘፀአትና በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት አራተኛ ዓመት መካከል ያለውን 480 ዓመት በሚናገረው በ1 ነገ 6፥1 ላይ የተመሠረተ ነው:: ይህም ዘፀአትን 1446 ዓ.ቅ..ክ ላይ፣ የመሳፍንትን ዘመን ደግሞ በ1380 ዓ.ቅ..ክ እና ሳኦል በነገሠበት 1050 ዓ.ቅ.ክ መካከል መሆኑን ያመለክታል:: እስራ ኤል የሐሴቦንን ምድር ለ300 ዓመት (11፥26) ይዛ እንደ ነበር የሚናገረው የዮፍታሔ ዘገባ፣ ከእነዚህ ዘመናት ጋር የሚስማማ ነው::

**ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያቱ**

መጽሐፈ መሳፍንት ሦስት መሠረታዊ ገጽታዎች አሉት፤ 1) መግቢያ (1፥1-3፥6)፤ (2) ዋና ክፍል (3፥7-16፥3) እና (3) መደምደሚያ (17-21):: ይህም በጥልቀት ሲጠና ውስብስብ የሆነ የጽሑፍ መዋቅርና በዘመናት ያለውን ባሕርያት ጠቅለል ባለ መልኩ የሚያቀርብ ሆኖ ይገኛል::

መግቢያው የተለያየ ዐላማ ያላቸው ሁለት ክፍሎች አሉት፤ ሁለቱም በጊዜ ቅደም ተከተል የማይ ገናኙና የጊዜ ቅደም ተከተልን የማያመለክቱ ናቸው:: የመጀመሪያው ክፍል (1፥1-2፥5) እስራኤል የተስፋዪቱን ምድር ከወረሰችበት ጊዜ አንሥቶ ባለመታዘዟ ወድቃ እስከ ተገሠጸችበት ጊዜ ድረስ ያለውን ሁኔታ ይገልጻል፤ ሁለተኛው ክፍል (2፥6-3፥6) ከኢያሱ አንሥቶ እስከ መሳፍንት አገዛዝ ጅማሬ የነበረውን ታሪክ የሚያካትት ሲሆን፣ ይህም የክህደት፣ የጭቈና፣ የሰቆቃና የእግዚአብሔር የጸጋ ትድግና በተደጋጋሚ የታየበት ጊዜ ነው:: ጸሓፊው በዐመፀኛው ሕዝብ ላይ ስለ ደረሰው የእግዚአብሔር ፍርድ ሲተርክ፣ እግረ መንገዱን አንዳንድ መሠረታዊ ቃላትን ይጠቀማል፤ ለምሳሌ "በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረጉ" 2፥11(3፥7፡12፤4፥1፤6፥1፤10፥6)፣ "አሳልፎ ሰጣቸው" 2፥4 (6፥1፤13፥1) እና "ሸጣቸው" 2፥14 (3፥8፤4፥2፤ 10፥7)::

የመጽሐፉ ዋና ክፍል በአብዛኛው ስለ አምስቱ ዐበይት መሳፍንት የሚያወሣ ነው፤ ይኸውም:-

1. ከምሥራቅ የመጣውን ወራሪ ኀይል አሸንፎ እስራኤልን ነጻ ያወጣው፣ ከብንያም ነገድ የሆነ ጀግናው ናዖድ (3፥12-30)
2. በሲሣራ መሪነት ከነዓናውያን እስራኤልን በወረሩ ጊዜ በእስራኤል ትፈርድ የነበረችው ከዮሴፍ ነገድ ከኤፍሬም ወገን የሆነችው ዲቦራ (ም6-9)::
3. የዘገባውን ማዕከላዊ ስፍራ የያዙት ጌድዎንና ልጁ አቤሜሌክ (ም6-9)፤ ጌዴዎን በብዙ አቅ ጣጫ የሙሴን መሪነት የሚያስታውስ ዐይነተኛ መሪ ሲሆን፣ ልጁ ግን ኀላፊነት የማይሰማውና የታማኝ መስፍን ተቃራኒ ባሕርይ ነበረው::
4. ከዮሴፍ ነገድ ከምናሴ ወገን የሆነው ከኀብረተ ሰቡ የተገለለው፣ በአሞን ንጉሥ ኀይል ጥቃት በሚደርስባት ዘመን በእስራኤል ይፈርድ የነበረው ዮፍታሔ እና
5. በጀግንነቱ የታወቀው እስራኤልን ከበስተ ምዕራብ ከመጣው ኀይል ነጻ ያወጣው ከዳን ነገድ የሆነው ሳምሶን (ም13-16)፤ የእነዚህ የትረካ ክፍሎች አቀማመጥ ራሱ መልእክት አለው:: የትረካውን ማእከላዊ ስፍራ የያዘው የጌዴዎንና የአቤሜሌክ ትረካ በዲቦራና በዮፍታሔ ትረ ካዎች መካከል የሚገኝ ሲሆን፣ እነዚህም በጀግኖቹ በናዖድና በሳምሶን ታሪክ ታጅበዋል:: በዚህ ሁኔታ የጽሑፉ አወቃቀር በመሳፍንት ዘመን አንገብጋቢ በሆነ ጕዳይ ላይ ትኵረት ያደርጋል፤ ይኸውም ስለ እስራኤል ሕዝብ በከነዓናውያን አማልክት መወሰድና የእግዚአብሔርን በእስራ ኤል ላይ መንገሥ የሚያመለክት ነው (የ 8፥ 23 ማብ ይመ)::

የመጽሐፉ መደምደሚያ ሁለት ንዑሳን ክፍሎች አሉት፤ የመጀመሪያው ንዑስ ክፍል (ም17-18) ሚካ የተባለ ሰው የጣዖትን የአምልኮ ስፍራ እንዳስፋፋና የዳን ነገድ የሚልካን ሃይማኖት ለማስፋፋት ሲል የተሰጠውን ርስት እንደለቀቀ የሚገልጽ ነው:: ሁለተኛው ንዑስ ክፍል (ም19-21) በብንያም ምድር በጊብዓ በአንድ ሌዋዊ ላይ የደረሰውን ክፉ ነገር እና የብንያም ነገድ ይህን ብልሹ ተግባር ለመከላከል የተወሰደውን ርምጃ ያስረዳል፤ ሁለቱ ክፍሎች አያሌ አስደናቂ ትይዩ ገጽታዎች አላቸው:-

1. ሁለቱም ክፍሎች አንድ ሌዋዊ በቤተልሔምና በኤፍሬም መካከል በብንያምና በዳን መተላለፊያ መሻገሩን ይጠቅሳሉ::
2. ሁለቱም 600 ጦረኞችን ጠቅሰዋል፤ እነዚህም የዳንን ነገድ ይመሩ የነበሩና ከብንያም ነገድ የተረፉ ናቸው::
3. ሁለቱም በብንያምና በዳን መካከል ያለውን መተላለፊያ ድንበር ባዶ በማድረግ ያጠቃልላሉ::

የብንያምና የዳን ትይዩ ገጽታዎች በመደምደሚያው ውስጥ ጕልህ ስፍራ የተሰጣቸው ከመሆኑም በላይ፣ ከመጽሐፉ ዋና ክፍል ጋርም ጕልህ ግንኙነት አላቸው:: እስራኤልን የታደገው ናዖድ የተመረጠው ምግባረ ብልሹ ከሆነው ከብንያም ነገድ ነበር (3፥15):: የተሰጠውን ርስት በመተው የባዕድ አምልኮን ከተከተለው ከዳን ነገድም ሳምሶን የተባለው ታዳጊ ወይም ነጻ አውጪ ተነሥቶአል (13፥2፡5):: ስለዚህ በዚህ ክፍል የተጠቀሱት ነገዶች የእስራኤልን የእምነትና የምግባር ብልሹነትን የሚያመለክቱ ሲሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ነጻ አውጪዎች የተመረጡባቸው ነገዶች ናቸው::

ከመግቢያው አንሥቶ እስከ መደምደሚያው ያለው የመጽሐፉ አጠቃላይ አወቃቀር፣ እያንዳንዱ

ክፍል ልዩ በሆነ ሁኔታ ዘመኑን መግለጹና ሃሳቱም ዋና ዋና ክፍሎች መያያዛቸው በእስራኤል ንጉሥ አለመኖሩንና እያንዳንዱም ደስ ያሰኘውን ያደርግ እንደ ነበረ በግልጽ ያሳያሉ (የ17፥6 ማብ ይመ)። በቀጥታ ተጠቅሰው የሚገኙት የተወሰኑ የአገሪቱ ክፍሎች ቢሆኑም፣ መጽሐፉ በአጠቃላይ የእስራኤልን ታሪክ የያዘ ነው። ከኢያሱ በኋላ የነበረው ዘመን እስራኤል ለእግዚአብሔር ያልታመነችበትና ለከነዓን ሽንገላ እጅ የሰጠችበት ጊዜ እንደ ሆነ በመጽሐፉ ተዘግቦአል። ነገር ግን አገሪቱ በዙሪያዋ ባሉ ጣዖት አምላኪ መንግሥታት ሙሉ በሙሉ ያልተዋጠችው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ብቻ ነበር። እንዲ ህም ሆኖ የእግዚአሔር አገልጋይ የዳዊት መምጣትና የእርሱ ሥርወ መንግሥት መመሥረት ከመታደግ ታሪክ አኳያ እንደሚፈጸም የሚጠበቅ ነበር።

**አስተዋፅኦ**

1. መግቢያ፤ ያልተሟላ ውርስና ክህደት (1፥1-3፥6)
   - ሀ. ክፍል አንድ:- እስራኤል ሙሉ ለሙሉ ምድሯን ከከነዓናውያን አለማጥራት (1፥1-2፥5)
   - ለ ክፍል ሁለት:- ለእስራኤል ዐመፀኝነት የእግዚአብሔር ምላሽ (2፥6-3፥6)
2. ጭቆናና ነጻ መውጣት (3፥7-16፥31)

*ታላላቅ መሳፍንት*

ሀ. ጎቶንያል መስጴጦምያን አሸነፈ (3፥7-11)
ለ. ናዖድ ሞዓብን አሸነፈ (3፥12-30)
ሐ. ዲቦራ ከነዓንን አሸነፈች (ም4-5)
መ. ጌዴዎን ምድያምን አሸነፈ(ም6-8)
(አቤሜሌክ፣ ከፉው መስፍን ም9)
ሠ. ዮፍታሔ አሞንን አሸነፈ (10፥6-12)
ረ. ሳምሶን ፍልስጥኤምን ተገዳደረ (ም13-16)

*ታናናሽ መሳፍንት*

1. ሰሜጋር (3፥31)
2. ቶላ (10፥1-2)
3. ኢያዕር (10፥3-5)
4. ኢብጻን (12፥8-10)
5. ኤሎም (12፥11-12)
6. ዓብዶን (12፥13-15)

3. ማጠቃለያ፤ የሃይማኖት ወይም የሥነ ምግባር መበላሸትና መመሳቃቀል (ም17-21)
   - ሀ. ክፍል አንድ (ም17-18፤17፥6፤19፥1 ይመ)
     1) ሚካ ሃይማኖትን ማበላሸቱ (ም 17)
     2) የዳን ነገድ ክርስቱ መነቀሉ (ም 18)
   - ለ. ክፍል ሁለት (ም 19-21፤19፥1 እና 21፥25 ይመ)
     1) የጊብዓ ሰዎች ምግባረ ብልሹነት (ም19)
     2) የብንያማውያን ክርስታቸው መባረር (ም 20-21)

## እስራኤላውያን ከቀሩት ከነዓናውያን ጋር ያደረጉት ውጊያ

1 ኢያሱ ከሞተ በኋላ እስራኤላውያን፣
“ከነዓናውያንን ለመውጋት ማን ቀድሞ
ይውጣልን?” ብለው እግዚአብሔርን ጠየቁ::
2እግዚአብሔርም፣ “ይሁዳ ቀድሞ ይውጣ፤
እነሆ ምድሪቱን በእጁ አሳልፌ ሰጥቼዋለሁ”
በማለት መለሰ::
3የይሁዳም ሰዎች ወንድሞቻቸውን የስም
ዖንን ልጆች፣ “ከነዓናውያንን ለመውጋት
ድርሻችን ወደ ሆነው ምድር አብረን እንውጣ፤
እኛም እንደዚሁ ድርሻችሁ ወደ ሆነው ምድር
አብረናችሁ እንወጣለን” አሏቸው፤ ስለዚህም
የስምዖን ሰዎች አብረዋቸው ሄዱ::
4ይሁዳ በከነዓናውያንና በፌርዛውያን ላይ
ወጣ፤ እግዚአብሔርም በእጃቸው አሳልፎ
ሰጣቸው፤ ቤዜቅ በተባለውም ስፍራ ዐሥር
ሺህ ሰው ገደሉ:: 5በዚህም አዶኒቤዜቅን
አግኝተው ተዋጉት፤ ከነዓናውያንንና ፌርዛ
ውያንን ድል አደረጉ:: 6አዶኒቤዜቅም ከዚያ
ሸሸ፤ እነርሱ ግን አሳደው ያዙት፤ የእጆቹንና
የእግሮቹንም አውራ ጣቶች ቈረጡ::
7ከዚያም አዶኒቤዜቅ፣ “የእጃቸውና የእግ
ራቸው አውራ ጣቶች የተቈረጡባቸው ሰባ
ነገሥታት ከገበታዬ ሥር የወደቀ ፍርፋሪ
ይለቃቅሙ ነበር፤ አሁን ግን እግዚአብሔር
በእነርሱ ላይ የፈጸምሁትን አመጣብኝ” አለ፤
እነርሱም ወደ ኢየሩሳሌም አመጡት፤ በዚ
ያም ሞተ::
8የይሁዳ ሰዎች ኢየሩሳሌምን ወግተው
ያዟት፤ ከተማዪቱንም በሰይፍ ስለት መተው
በእሳት አቃጠሏት::
9ከዚያም በኋላ የይሁዳ ሰዎች በኰረብታ
ማው አገር፣ በኔጌብና በምዕራቡ ኮረብታ
ግርጌ የሚኖሩትን ከነዓናውያንን ለመውጋት
ወረዱ፤ 10ቀድሞ ሲል ቂርያትአርባቅ ተብላ
በምትጠራው በኬብሮን በሚኖሩት ከነዓ
ናውያን ላይ ዘመቱ፤ ሴሲንን፣ አኪመንንና
ተላሚንን ድል አደረጉ::
11ከዚያም ቀድሞ ሲል ቅርያትሤፍር ተብላ
በምትጠራው በዳቤር በሚኖሩት ሰዎች ላይ
ዘመቱ:: 12ካሌብም፣ “ቅርያት ሤፍርን ወግቶ
ለሚይዛት ሰው ልጄን ዓክሳንን እድርለታለሁ”
አለ:: 13በዚህ ጊዜ የካሌብ ወንድም የቄኔዝ
ልጅ ጎቶንያል ከተማዪቱን ያዘ፤ ካሌብም
ልጁን ዓክሳንን ዳረለት::
14እርሷም ወደ ጎቶንያል በመጣች ጊዜ፣
አባቷ የዕርሻ መሬት እንዲሰጠው ይለምነው
ዘንድ አጥብቃ ነገረችው፤ሀ ካሌብም እርሷ
ከአህያዋ ላይ እንደወረደች “ምን እንዳደርግልሽ
ትፈልጊያለሽ?” ሲል ጠየቃት::
15እርሷም፣ “እባክህ አንድ ነገር አድር
ግልኝ፤ በኔጌብ መሬት እንደ ሰጠኸኝ ሁሉ፣
አሁንም የውሃ ምንጭ ስጠኝ” አለችው፤
ካሌብም የላይኛውንና የታችኛውን

ሀ14 ዕብራይስጡ፣ሰብዓ ሊቃናትና ቩልጌት አጥብቆ ነገረው ይላሉ::

1፥1 ቍ27፤ዘፍ10፥18፤ዘኍ2፥3-9፤ ኢሱ24፥29፤ መሳ3፥1-6፤20፥18፤ 1ነገ20፥14፤1፥2 ቍ4፤ዘፍ 49፥10፤ መሳ3፥ 28፤4፥7፡14፤ 7፥9
1፥3 ቍ17
1፥4 ዘፍ13፥7፤ ኢሱ 3፥10፤ 1ሳሙ11፥8
1፥5 ቍ6፡7
1፥7 ዘሌ24፥19፤ ኢሱ 10፥1፤ ኤር25፥12
1፥8 ቍ21፤ ኢሱ 15፥63፤ 2ሳሙ5፥6
1፥9 ዘፍ12፥9፤ ዘኍ13፥17፤21፥1፤ ኢሳ30፥6
1፥10 ቍ20፤ ዘፍ13፥18፤35፥27፤ ዘኍ13፥22፤ ኢሱ 15፥14
1፥11 ኢሱ10፥38
1፥15 ዘኍ13፥6

*1፥3-3፥6፤* መግቢያው በሁለት የተለያዩ ክፍሎች ላይ የተጻፈ ነው፤ ይህም (1) እግዚአብሔር በገባላቸው ቃል መሠረት፣ እስራኤላውያን የተስፋዪቱን ምድር ሙሉ በሙሉ ሊወርሱ አለመቻላቸውን (1፥1-36)፤ እንዲሁም በታማኝነታቸው ጸንተው ባለመገኘታቸው (2፥1-5) ከእርሱ የደረሰባቸውን ተግሣጽ የሚያወሳ ታሪክ ነው:: (2) የመጽሐፉን ዋና ክፍል የሚያሳይ ሲሆን (3፥7-16፥31)፣ ይህም ከኢያሱ ሞት በኋላ ባሉት ምእት ዓመታት የእስ ራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር ላይ እንዳመፀና እግዚአብሔርም እንዴት አድርጎ እንደቀጣው በሚገባ የሚገልጽ ነው (2፥6-3፥6):: ከመግቢያው “ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያቱ” የሚለውን ይመ::

*1፥1-36፤* ምድሪቱን ለመያዝ በሚደረገው ፍልሚያ ውስጥ ይሁዳ መሪነቱን ያዘ (ቍ12፤ እንዲሁም 20፥18 ይመ):: ይህን ከግቡ ለማድረስ የእርሱ ኀይል ብቻ ሳይሆን፣ የስምዖንም ተጨምሮበት የተደረገው ጥረት እንደታሰበው አልተሳካም፤ በመሆኑም የተደረገው ጥረት ድል ሳይሆን ሽንፈት የታየበት አሳዛኝ ታሪክ ነው::

1፥1 ***ኢያሱ ከሞተ በኋላ፤*** እንደ መጽሐፈ ኢያሱ ሁሉ መጽሐፈ መሳፍንትም በድነት ታሪክ ውስጥ አንድ ታዋቂ መሪ ከሞተ በኋላ ስለሚቀጥለው ዘመን ይናገራል (ኢሱ 1፥1 ይመ):: ኢያሱ የሞተው በ1390 ዓ.ቅ.ክ ሳይሆን አይቀርም:: በእርሱ መሪነት የተደረገው ጦርነት የከነዓናውያንን ቅስም ስለ ሰበረው፣ እስራኤላውያንን ከምድሪቱ ለማስወጣት አልቻሉም ነበር:: በዚያ ጊዜ እስራኤላውያን ያጋጠማቸው ችግር የከነዓንን ምድር ሙሉ በሙሉ ለመያዝ አለመቻላቸው ነበር (የ18፥3፤ 21፥43-45 ማብ ይመ):: ***እግዚአብሔርን ጠየቁ፤*** ይህን ያደረጉት በካህናቱ አማካይነት በኡሪምና በቱሚም ሳይሆን አይቀርም (የዘፀ 28፥30፤ የ1ሳሙ 2፥28 ማብ ይመ):: ***ይውጣልን፤*** ዋናው የእስራኤላውያን ሰፈር የሚገኘው በዮርዳኖስ ሸለቆ ከኢያሪኮ አጠገብ ከባሕር ወለል 800 ሜትር በታች ባለው በጌልገላ ሲሆን፣ የከነዓናውያን ከተሞች ግን የሚገኙት ከፍታው ከባሕር በላይ ከ2500-3500 ሜትር በሆነው በመካከለኛው ኰረብታማ አገር ነበር::

1፥2 ***ይሁዳ ቀድሞ ይውጣ፤*** 20፥18 ይመ:: ይሁዳ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምዕራብ ያለው ምድር በመጀመሪያ የተመደበው ለይሁዳ ነበር (ኢሱ 15):: የይሁዳ ነገድ የሚኖረው የመሪነት ድርሻ በያዕቆብ በረከት አስቀድሞ ተነግሮአል (ዘፍ 49፥8-12)::

1፥3 ***የስምዖንን ልጆች፤*** ኢያሱ በይሁዳ ግዛት ያሉትን ከተሞች ለስምዖን መደበለት (ኢሱ 19፥1-9፤ ዘፍ 49፥5-7ይመ)::

1፥4 ***በከነዓናውያንና፤*** የዘፍ10፥6 ማብ ይመ:: ***በፌርዛውያን፤*** የዘፍ 13፥7ማብ ይመ:: ***ቤዜቅ፤*** ይህ ስፍራ የት እንደሚገኝ በውል ለይቶ ማወቅ አይቻልም:: ሳዖል ወደ ኢያቢስ ዘገለዓድ ከመዝመቱ በፊት ሰራዊቱን ያሰባሰበው በዚህ ቦታ ነበር (1ሳሙ11፥8)::

1፥5 ***አዶኒቤዜቅ፤*** የቃሉ ትርጕም ‘የቤዜቅ ጌታ’ ማለት ነው።

1፥6 ***የእጆቹንና የእግሮቹንም አውራ ጣቶች ቈረጡ፤*** በጥንት ጊዜ በቅርብ ምሥራቅ የጦር እስረኞችን አካል መቍረጥ የተለመደ ተግባር ነበር (የ16፥21 ማብ ይመ)፤ ይህም የሚሆነው ለጦርነት ብቁ እንዳይሆኑ ለማድረግ ነው::

1፥7 ***ሰባ ነገሥታት፤*** ከነዓን በራሳቸው የሚተዳደሩ ብዙ ታናናሽ ከተሞች ነበሯት፤ እያንዳንዱ ከተማ የራሱ ንጉሥ ነበረው:: “ሰባ” የሚለው ቃል ትክክለኛውን ቍጥር የሚያመለክት ሳይሆን፣ በማጠጋጋት የተገኘ ቍጥር ሊሆን ይችላል ወይም ደግሞ ብዙ ቍጥር ለማመልከት የቆመ ይሆናል:: ***ከገበታዬ ሥር፣*** አባባሉ ለውሻ እንደሚጣል ቍራሽ በመቍጠር ሌላውን ዝቅ አድርጎ ማየትን ያመለክታል (ማቴ15፥27፤ሉቃ16፥21 ይመ) ***እግዚ አብሔር... አመጣብኝ፤*** የዘፀ 21፥23-25 ማብ ይመ

1፥8 ***ኢየሩሳሌምን ወግተው ፤*** ምንም እንኳ ከተማዪቱ ብትሸነፍም፣ በዚህ ጊዜ በከፊል እንጂ ሙሉ በሙሉ በእስራኤላ ውያን እጅ አልገባችም ነበር (ቍ21፤ ኢሱ15፥63ይመ):: ዳዊት በ 1000 ዓ.ቅ.ክ. ገደማ እስኪይዛት ድረስ (2ሳሙ 5፥6-10)፣ እስራኤላውያን ከተማዪቱን ለመቈጣጠር አልቻሉም ነበር::

1፥10 ***ቂርያትአርባቅ፤*** የኢ.ሱ 14፥15 ማብ ይመ::

1፥11 ***በዳቤር*** የኢሱ 10፥38 ማብ ይመ::

1፥12 ***ካሌብም፤*** ከነዓንን ማሸነፍ እንደሚቻል ተስፋ ያለው ወሬ ይዘው የተመለሱት ካሌብና ኢያሱ ነበሩ (ዘኁ 14፥6-9):: ***ልጄን... እድርለታለሁ፤*** በጦርነት ድል ማድረግ፣ ለሴት ልጅ ከሚቀርቡ የጥሎሽ ዐይነቶች አንዱ ነበር (1ሳሙ 18፥25 ይመ)::

1፥13 ***ጎቶንያል፤*** የመጀመሪያው ታዋቂ መስፍን ነው (3፥7-11 ይመ)።

1፥15 ***የላይኛውንና የታችኛውን ምንጮች፤*** በኬብሮን ያሉት የዕርሻ መሬቶች ውሃ የሚያገኙት ከእነዚሁ ምንጮች ነው።

ምንጮች ሰጣት::
[16]የቄናዊው የሙሴ ዐማት ዘርያዎች
ከዓራድ አጠገብ በኔጌብ ውስጥ በይሁዳ ምድረ
በዳ ካሉት ሕዝቦች ጋር አብረው ለመኖር፣
ከይሁዳ ሰዎች ጋር በመሆን ከባለ ዘንባባዋ
ከተማ ከኢያሪኮ ወጡ::
[17]የይሁዳ ሰዎች ከወንድሞቻቸው ከስም
ዖን ልጆች ጋር ሆነው በጸፋት በሚኖሩት
ከነዓናውያን ላይ ዘመቱ፤ ከተማዪቱንም ፈጽሞ
ደመሰሷት[^a]፤ ስለዚህ ከተማዪቱ ሖርማ[^b] ተብላ
ተጠራች:: [18]ደግሞም የይሁዳ ሰዎች ጋዛ፣
አስቀሎና፣ አቃሮን የተባሉትን ከተሞች
ከነግዛቶቻቸው ያዙ[^c]::
[19]*እግዚአብሔር* ከይሁዳ ሰዎች ጋር
ነበር፤ ስለዚህ ኰረብታማውን አገር ያዙ፤
ነገር ግን በረባዳው ምድር የሚኖሩት ሰዎች
ከብረት የተሠሩ ሠረገሎች ስለ ነበሯቸው
ከዚያ አሳደው ሊያስወጧቸው አልቻሉም::
[20]ሙሴ ባዘዘው መሠረት ኬብሮን ለካሌብ
ተሰጠች፤ እርሱም ሦስቱን የዔናቅ ልጆች
ከውስጧ አሳደደ:: [21]የብንያም ልጆች በኢየሩ
ሳሌም የሚኖሩትን ኢያቡሳውያንን ከዚያ ሊያ
ሰወጧቸው አልቻሉም፤ ስለዚህ ኢያቡሳ
ውያን እስከ ዛሬ ድረስ ከብንያማውያን ጋር

[^a]17 የዕብራይስጡ ቃል አንድን ነገር ወይም ሰው ሙሉ ለሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠትን የሚያሳይ ነው

[^b]17 *ሖርማ* ማለት ጥፋት ማለት ነው

[^c]18 ዕብራይስጡና የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም *አልያዙም* ይላሉ::

1፥16 ዘኍ15፥19፤ ዘኍ10፥29፤21፥1፤ ዘዳ34፥3፤ኢሱ 12፥14፤ መሳ3፥13፤ 2ዜና28፥15
1፥17 ቍ3፤ ዘኍ14፥45
1፥18 ኢሱ11፥22፤ 13፥3
1፥19 ዘኍ13፥17፤14፥43፤ ኢሱ17፥16
1፥20 ቍ10፤ ኢሱ10፥36፤14፥13
1፥21 ቍ8፤ ኢሱ9፥15፤15፥63

1፥16 ***የሙሴ ዐማት፤*** የዘፀ 2፥16 ማብ ይመ::

1፥17 ***የይሁዳ ሰዎች...ከስምዖን ልጆች ጋር፤*** ይሁዳ የሚጠበቅበትን ኀላፊነት እየተወጣ ነው::

1፥18 ***ጋዛን፣ አስቀሎና፣ አቃሮን፤*** እነዚህ፣ ፍልስጥኤማውያን ከሚኖሩባቸው ከአምስቱ ዋና ከተሞች ሦስቱ ናቸው

1፥19 ***ከዚያ አሳደው ሊያስወጧቸው አልቻሉም፤*** እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመቀበል፣ ከነዓናውያንን ከምድሪቱ አሳደው ለማስወጣት አልቻሉም (ዘፀ7፥1-5፤20፥16-18)፤ ማስወጣት ለምን እንዳልቻሉ አምስት ምክንያቶች ተጠቅሰዋል፤ እነዚህም (1) የከነዓናውያን የጦር መሣሪያ በዐይነቱ ብልጫ ነበረው (ቍ19)፣ (2) እስራኤላውያን፣ ከከነዓናውያን ጋር ቃል ኪዳን በማድረግ እግዚአብሔርን ባለመታዘዛቸው (2፥1-3)፣ (3) ከቀደሙት አባቶቻቸው ጋር እግዚአብሔር የገባውን ኪዳን እስራኤላውያን ስላፈረሱ (2፥20-21)፣(4) ትእዛዙን ለመጠበቅ ታማኞች መሆናቸውን ለማወቅ እግዚአብሔር ስለ ፈተናቸው (2፥22-23፤3፥4)፣ (5) እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ሰራዊት ስለ ሆኑ እግዚአብሔርን እንዲያውቁ የውጊያ ስልት ስጥቶአቸዋል (3፥1-2):: ***ከብረት የተሠሩ ሠረገሎች፤*** አብዛኛው የሠረገላ ክፍል ከዕንጨት የተሠራ ሆኖ የእግሮቹ ተሸካሚ ግን ብረት ሊሆን ይችላል::


1፥20 ***ሙሴ ባዘዘው መሠረት፤*** ዘኍ 14፥24፤ ዘዳ 1፥36፤ ኢሱ 14፥9-14 ይመ:: የዔናቅ፤ የዘኍ13፥22 ማብ ይመ::

1፥21 ***የብንያም ልጆች...ከዚያ ሊያስወጧቸው አልቻሉም፤*** የቍ8 ማብ ይመ:: ኢየሩሳሌም የምትገኘው በብንያምና በይሁዳ ወሰን ላይ ሲሆን፣ የተሰጠችው ግን ለብንያም ነበር (ኢሱ 18፥28)::

## አምስቱ የፍልስጥኤም ከተሞች

በሉል እንዳጌጠ ገመድ አምስቱ የፍልስጥኤም ከተሞች በሜድትራንያን ባሕር ዳርቻ ላይ ተሰልፈው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚጠሩብት ስማቸው ቀርበዋል:: እነርሱም ጋዛ፣ አስቀሎና፣አዛጦን፣ አቃሮንና ጌት ናቸው::

እያንዳንዳቸው ዋና ዋና የሆኑ የንግድ ከተሞች ሲሆኑ፣ በጥንታዊው ዘመን የተለያዩ አውራጃዎችን በሚያገናኝ እስከ ግብፅ በሚደርስ አውራ መንገድ ላይ ናቸው:: የፈንቂ፣ የቆጵሮስና የቀርጤስ መርከቦች በዚህ ዘመን የፍልስጥኤም ቤተ ጣዖት የተመሠረተበት ከተማ ቡቴል ቃሲል ድረስ ወደ ፍልስጥኤም የባሕር ወደብ ይመጣሉ::



በዚያ አብረው ይኖራሉ::
22የዮሴፍ ወገን ደግሞ ቤቴልን ወጉ፤
እግዚአብሔርም ከእነርሱ ጋር ነበር::
23እነርሱም ቀደም ሲል ሎዛ ትባል ወደ
ነበረችው ወደ ቤቴል ሰላዮችን በላኩ ጊዜ፣
24ሰላዮቹም አንድ ሰው ከከተማዪቱ ሲወጣ
አይተው፤ "የከተማዪቱን መግቢያ አሳየን፤
እኛም ምሕረት እናደርግልሃለን" አሉት::
25እርሱም አሳያቸው፤ እነርሱም ከሰውየውና
ከቤተ ሰቡ በስተቀር የከተማዪቱን ሕዝብ
በሰይፍ ስለት ፈጁ:: 26ሰውየውም ወደ ኬጢ
ያውያን ምድር ሄዶ ከተማ ሠራ፤ ስሟንም
ሎዛ ብሎ ጠራት፤ እስከ ዛሬም የምትጠራው
በዚሁ ስም ነው::
27የምናሴ ነገድ ግን በቤትሳን፣ በታዕናክ፣
በዶር፣ በይብለዓም፣ በመጊዶንና በየአካባ
ቢያቸው ያሉት መንደሮች ነዋሪውን ሕዝብ
ስላላስወጡ፣ ከነዓናውያን ኑሮአቸውን በዚ
ያው ለማድረግ ወሰኑ:: 28እስራኤላውያን
በበረቱ ጊዜ ግን ከነዓናውያንን የጕልበት
ሥራ እንዲሠሩ አስገደዷቸው እንጂ ፈጽሞ
አላስወጧቸውም:: 29እንደዚሁም የኤፍሬም
ወገኖች በጌዝር የሚኖሩትን ከነዓናውያንን
ማስወጣት አልቻሉም፤ ስለዚህ ከነዓናውያን
በመካከላቸው እዚያው መኖርን ቀጠሉ:: 30ዛብ
ሎንም እንደዚሁ በቂድሮንና በነህሎል የነ
በሩትን በመካከለቸው የቀሩትን ከነዓናው
ያንን አላስወጣም፤ ነገር ግን የጕልበት ሥራ
እንዲሠሩ አስገደዳቸው:: 31አሴርም በዓኮ፣
በሲዶን፣ በአሕላብ፣ በአክዚብ፣ በሒልባ፣
በአፌቅና በረአብ የሚኖሩትን አላስወጣም፤
32በዚህ ምክንያት የአሴር ሕዝብ በምድሪቱ
ካሉት ከነዓናውያን ጋር አብረው ኖሩ::
33ንፍታሌምም በቤትሳሚስና በቤትዓናት
የሚኖሩትን አላስወጣም፤ ስለዚህ የንፍታሌም
ነገድ በምድሪቱ ከሚኖሩት ከነዓናውያን ጋር
አብረው ኖሩ፤ ይሁን እንጂ በቤትሳሚስና
በቤትዓናት የሚኖሩት ለእነርሱ የጕልበት
ሥራ ተገደው ይሠሩ ነበር:: 34የዳን ነገድ
በኰረብታማው ምድር ብቻ እንዲወሰን
እንጂ ወደ ሜዳማው አገር እንዲወርድ አሞ
ራውያን አልፈቀዱለትም:: 35አሞራውያንም
በሔሬስ ተራራ፣ በኤሎንና በሸዓልቢም
ኑሮአቸውን ቀጠሉ፤ ይሁን እንጂ የዮሴፍ
ወገን በበረታ ጊዜ ተገደው የጕልበት ሥራ
ከመሥራት አላመለጡም:: 36የአሞራውያን ድን
በር አቅራቢያም መተላለፊያ እስከ ሴላዕና
ከዚያም የሚያልፍ ነበር::

## የእግዚአብሔር መልአክ በቦኪም

**2** የእግዚአብሔር መልአክ ከጌልገላ ወደ
ቦኪም ወጥቶ እንዲህ አለ፤ "ከግብፅ
ምድር አወጣኋችሁ፤ ለቀደሙትም አባቶ
ቻችሁ ልሰጣቸው ወደ ማልሁላቸው ምድር
አመጣኋችሁ፤ እንዲህም አልሁ፤ ከእናንተ
ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳኔን አላፈርስም፤
2እናንተም ከዚህች ምድር ነዋሪዎች ጋር ቃል
ኪዳን አታድርጉ፤ መሠዊያቸውንም አፍርሱ፤
እናንተ ግን አልታዘዛችሁኝም፤ ይህን ያደ
ረጋችሁት ለምንድነው? 3ስለዚህ አሁንም
ከፊታችሁ አሳድጄ እንደማላስወጣቸው እነ
ግራችኋለሁ፤ ነገር ግን እነርሱ የጐን ውጋት፣
አማልክቶቻቸውም ወጥመድ ይሆኑባችኋል::"
4የእግዚአብሔርም መልአክ ይህን ቃል
ለእስራኤላውያን ሁሉ በተናገረ ጊዜ፣ ሕዝቡ
ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ፤ 5ያንን
ስፍራ ቦኪም" ብለው ጠሩት፤ በዚያም ለእግ
ዚአብሔር መሥዋዕት አቀረቡ::

1፥22 ኢያሱ7፥2፤ መሳ10፥9
1፥23 ዘፍ28፥19
1፥24 ዘፍ47፥29
1፥25 ኢሱ6፥25
1፥26 ዘፍ28፥19፤ ዘዳ7፥1፤ሕዝ16፥3
1፥27 ቍ1፤ኢሱ1 1፥2፤12፥21፤17፥11 ፤1ነገ9፥21
1፥28 ኢሱ17፥12-13
1፥29 ኢሱ10፥33፤ 14፥4፤16፥10፤ መሳ5፥14
1፥31 ዘፍ49፥13 ፤ዘኍ13፥21፤ኢሱ12፥18፤ 15፥44፤17፥7
1፥33 ኢሱ15፥10፤ 19፥38
1፥34 ዘፍ30፥6፤ ዘኍ13፥29፤መሳ10፥11፤18፥1፤1 ሳሙ7፥14
1፥35 ኢሱ19፥42፤ መሳ8፥13፤ 1ነገ4፥9
1፥36 ኢሱ15፥3፤ 2ነገ14፥7፤መዝ106፥34፤ኢሳ16፥1፤42፥11
2፥1 ቍ5፤ ዘፍ16፥7፤ 17፥8፤ዘፀ 20፥2፤ ዘሌ26፥42-44፤ ዘዳ7፥9፤11፥30፤ መሳ6፥8
2፥2 ዘፀ23፥24፤2፡3 4፥12፥13፤ዘዳ7፥2፡5፤ 2ዜና14፥3፤ኤር7፥28
2፥3 ዘፀ10፥7፤ ዘኍ33፥55፤ ኢሱ 23፥13
2፥4 ዘፍ27፥38፤ ዘ25፥6፤2ነገ17፥13
2፥5 ቍ1

"5. ቦኪም ማለት አልቃሽ ማለት ነው::

*ኢያቡሳውያን፤* የዘፍ 10፥16 ማብ ይመ::

1፥22 ***የዮሴፍ ወገን፤*** ኤፍሬምና የምናሴ ምዕራባዊ ክፍል ማለት ነው:: ***ቤቴልን፤*** የዘፍ12፥8 ማብ ይመ:: በ1300ዓ.ቅ.ክ የደረሰውን ጥፋት የሚያመለክት የሥነ ቅርስ ጥናት ማስረጃ ተገኝቶ አል፤ በመሆኑም በዚህ ቍጥር ላይ የተጠቀሰውን ጦርነት ሊያ መለክት ይችላል::

1፥23 ***ሰላዮችን በላኩ፤*** የዘኍ 13፥2 ማብ ይመ::

1፥25 ***ከሰውየውና... በስተቀር፤*** ለረዓብ ከተደረገላት ነገር ጋር ያነጻጽሩ (ኢሱ 6፥25)::

1፥26 ***ወደ ኬጢያውያን ምድር፤*** እስራኤላውያን የተስፋ ዪቱን ምድር በያዙበት ወቅት፣ አራም (ሶርያ) የተባለው አገር ይጠራበት የነበረ ስም ነው (የዘፍ 10፥15 ማብ ይመ)::

*1፥27-29፤* የኢሱ 17፥16-18 ማብ ይመ ::

1፥28 ***የጕልበት ሥራ...*** የ1ነገ 5፥13 ማብ ይመ::

1፥33 ***በቤትሳሚስና፤*** ይህ ቦታ የት እንደሚገኝ አይታ ወቅም:: የስሙ ትርጕም፣ "የፀሐይ አምላክ ቤት" ማለት ነው:: እንደዚሁ በይሁዳም ምድር በቤትሳሚስ የሚባል ነበር (የቍ 35 ማብ ይመ):: ***ቤትዓናት፤*** "ዓናት" ለተባለችው እንስት አምላክ ቤት ማለት ነው (የ3፥31 ማብ ይመ)::

1፥34 ***የዳን ነገድ ... እንዲወሰን፤*** ቀደም ሲል ኢያሱ አሞራውያንን ድል ነሥቶአቸው ነበር (ኢሱ10፥5-11)፤ አሁንም ደግሞ የዳንን ነገድ ለመቋቋም የሚያስችል ኀይልም ብርታትም ነበራቸው፤ ለዚህም ነው አብዛኞቹ የዳን ነገድ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደ ሰሜን ለመሰደድ የበቁት (ም18)::

1፥35 ***በሔሬስ ተራራ፤*** ትርጕሙ "የፀሐይ አምላክ ተራራ" ማለት ነው:: ይህም በይሁዳ ምድር የሚገኘው፣ ሌላ ስሙ ኢር ሳሚስ ማለትም "የፀሐይ አምላክ ከተማ" የተባለው ቤትሳሚስ ሊሆን ይችላል (ኢሱ 19፥41)::

1፥36 ***የአሞራውያን ድንበር፤*** ደቡባዊው ወሰናቸውን ለማለት ነው (ኢሱ 15፥2-3 ይመ)::

*2፥1-5፤* እግዚአብሔር ባዘዛቸው መሠረት እስራኤላውያን በጋለ መንፈስ ተነሣሥተው ምድሪቱን ሙሉ በሙሉ ባለመያዛቸው (1፥27-36 ይመ)፣ እግዚአብሔር ሊረዳቸው የዘረጋውን ክንዱን አጠፈባቸው:: እግዚአብሔር የገሠጸበት ጊዜ በግልጽ ባይጠቀስም በመሳፍንት መጀመሪያ አካባቢ ምናልባትም በኢያሱ ም9 (ወይም ደግሞ እሱ 18፥1-3) ላይ ከተዘገበው ሁኔታ ጋር የተያያዘ ሳይሆን አይቀርም::

2፥1 ***የእግዚአብሔር መልአክ፤*** የዘፍ 16፥17 ማብ ይመ:: በዚህ ክፍል የምናገኘው የእግዚአብሔር መልአክ ተልእኮ፣ በ6፥8-10 ላይ ስሙ ካልተጠቀሰው ነቢይ ተልእኮ ጋርና በ10፥11-14 ላይ እንደ ተገለጸው ሕዝቡን ከወቀሰው ከእግዚ አብሔር ቃል ጋር በተጓዳኝነት የሚሄድ ነው:: ***ጌልገላ፤*** የእስራ ኤል ሕዝብ በኢያሱ መሪነት ምድሪቱን በወረሱ ጊዜ፣ በመጀመሪያ የተቀመጡበት ስፍራ ነው (ኢሱ4፥19-5፥12ይመ):: ***ከግብፅ..... አወጣኋችሁ፤*** የዘፀአት መጽሐፍ መሪ ሐሳብ ሲሆን፣ እግዚአብሔር ከፍቅሩ የተነሣ ሕዝቡን እንደ ተቤዣቸው በማስረጃነት ተደጋግሞ ተጠቅሷል (ዘፀ 20፥2 ይመ):: ***ልሰጣቸው ወደ ማልሁላቸው፤*** ዘፍ15፥18 እንዲሁም የዕብ 6፥13ማብ ይመ::

2፥2 ***ቃል ኪዳን አታድርጉ፤*** ይህን ማድረግ ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን ኪዳን ማፍረስ ነው (ዘፀ 23፥32 ይመ)::

*2፥6-3፥6፤* የመጽሐፉ መግቢያ ሁለተኛው ግማሽ በኢሱ 24፥28-31 ከሚገኘው ትረካ የቀጠለ ነው፤ ይህም መሳ 3፥7-16፥31 ላይ ለቀረበው ትረካ መንደርደሪያ ነው:: የእስራኤል ሕዝብ ቡተስፋዪቱ ምድር ያሳለፉት የመጀመሪያው ምእተ ዓመት ከእምነት

## ያለመታዘዝ ውጤት

6ኢያሱ ሕዝቡን ካሰናበተ በኋላ እያንዳንዱ
የእስራኤል ነገድ ምድሪቱን ለመውረስ ወደ
የርስቱ ሄደ:: 7ኢያሱ በሕይወት በነበረበት
ዘመን ሁሉ እንዲሁም ከእርሱ በኋላ እግዚ
አብሔር ለእስራኤል ያደረገውን ታላላቅ ነገ
ሮች ሁሉ ያዩ አለቆች በነበሩበት ዘመን
ሁሉ ሕዝቡ እግዚአብሔርን አመለከ::
8የእግዚአብሔር አገልጋይ የነዌ ልጅ ኢያሱ
በመቶ ዐሥር ዓመቱ ሞተ:: 9እነርሱም በኩረብ
ታማው በኤፍሬም አገር በምትገኘው ከገዓስ
ተራራ በስተ ሰሜን ባለችው በራሱ ርስት
ላይ በተምናሔሬስ ቀበሩት::
10ያ ሁሉ ትውልድ ወደ አባቶቹ ከተከ
ማቸ በኋላ እግዚአብሔርንም ሆነ እርሱ
ለእስራኤል ሕዝብ ያደረገውን ነገር የማያ
ውቅ ሌላ ትውልድ ተነሣ :: 11ከዚያም እስ
ራኤላውያን በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር
አደረጉ፤ የበአል አማልክትንም አመለኩ::
12ከግብፅ ምድር ያወጣቸውን የአባቶቻቸውን
ስምላክ እግዚአብሔርን ተው፤ በዙሪያቸው
ያሉት ሕዝቦች የሚያመልኳቸውን አማልክት
ተከተሉ፤ ሰገዱላቸውም:: እግዚአብሔርንም
አስቈጡት፤ 13እርሱን ትተው በኣልንና አስ
ታሮትን አምልከዋልና 14እግዚአብሔር በእ
ስራኤል ላይ በመቈጣቱ ለሚዘርፏቸው አሳ
ልፎ ሰጣቸው፤ በዙሪያቸው ላሉ ጠላቶቻቸው
ሸጣቸው:: 15እስራኤላውያን ለውጊያ በሚወጡ
በት ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር አስቀድሞ
በእርሱ ላይ እንደ ተናገረውና እንደ ማለው
ይሸነፉ ዘንድ የእግዚአብሔር እጅ ትከፋ
ባቸው ነበር፤ ከዚህም የተነሣ እጅግ ተጨነቁ::
16እግዚአብሔርም ከእነዚህ ወራሪዎች
የሚያድኗቸውን መሳፍንት[a] አስነሣ፤ 17እስራ
ኤላውያን ግን ሌሎችን አማልክት ተከትለው
አመነዘሩ፤ ሰገዱላቸውም እንጂ መሳፍንታቸውን
አልሰሙም:: አባቶቻቸው እግዚአብሔርን
በመታዘዘ በሄዱበት መንገድ ሳይሆን፣ አባቶ
ቻቸው የእግዚአብሔርን ሕግ በመከተል ከሄ
ዱበት መንገድ ፈጥነው ፈቀቅ አሉ::
18እግዚአብሔር መሳፍንትን ባስነሣላቸው
ቍጥር ከመስፍኑ ጋር ስለሚሆን፣ እርሱ በሕ
ይወት እስካለ ድረስ እግዚአብሔር ከጠላ
ቶቻቸው ያድናቸው ነበር፤ ከጠላቶቻቸው
ሥቃይና መከራ ሲደርስባቸው በሚጮኹበት
ጊዜ እግዚአብሔር ይራራላቸው ነበር:: 19መስ
ፍኑ ከሞተ በኋላ ግን ሕዝቡ ሌሎችን አማ
ልክት በመከተል፣ እነርሱን በማገልገልና በማ
ምለክ ከአባቶቻቸው ይልቅ ወደ ክፉ መን
ገድ ተመለሱ፤ ክፉ ሥራቸውንና የእልኸኝነት
መንገዳቸውንም አይተዉም ነበር::

2፥7 ቍ17
2፥8 ኢሱ1፥1
2፥9 ኢሱ19፥50
2፥10 ዘፀ5፥2፤ ገላ4፥8
2፥11 መሳ3፥7:12፤ 4፥1፤6፥1፤ 8፥33፤ 10፥6፤1ነገ15፥26፤16፥31፤22፥53፤2ነገ10፥18፤17፥16
2፥12 ዘኍ11፥33፤ ዘዳ4፥25፤31፥16፤32፥12፤መሳ10፥6፤መዝ78፥58፤106፥36:40
2፥13 መሳ3፥7፤5፥8፤6፥25፤8፥33፤10፥6፤1ሳሙ7፥3፤31፥10፤1ነገ11፥5:33፤2ነገ23፥13፤ነህ9፥26፤መዝ78፥56፤ኤር11፥10
2፥14 ዘዳ28፥25፤31፥17፤32፥30፤መሳ3፥8፤ነህ9፥27፤መዝ44፥10፤89፥41፤106፥41፤ሕዝ34፥8
2፥15 ዘፍ35፥3፤ሩት1፥13፤2ሳሙ22፥7፤2ዜና15፥4፤ኢዮ5፥5፤19፥21፤20፥22፤መዝ4፥1፤18፥6፤32፥4
2፥16 ሩት1፥1፤ 1ሳሙ4፥18፤7፥6:15፤11፥3፤2ሳሙ7፥11፤1ዜና17፥10፤መዝ106፥46፤ሐሥ13፥20፤ዘዳ9፥12፤ነህ9፥28
2፥17 ቍ7፤ዘፀ34፥15፤ዘኍ15፥39መዝ4፥2፤106፥36
2፥18 ዘፀ2፥23፤ ዘኍ10፥9፤ዘዳ32፥36፤1ሳሙ7፥3፤2ነገ13፥5፤ ኢሳ19፥20፤ 43፥3:11፤45፥15:21፤49፥26፤60፥16፤63፥8
2፥19 ዘፍ6፥11፤ ዘፀ32፥9፤ ዘዳ4፥16፤32፥17፤መሳ4፥1፤8፥33፤ ነህ9፥2፤መዝ78፥57፤ኤር 44፥3:9

[a]16 በዚህም ከ17—19 ባለው ክፍል መሪ ተብሎ ሊተረጐም ይችላል::

ማፈግፈግ፣ ጭቈና፣ ሰቈቃ፣ እንዲሁም የእግዚአብሔር ማዳን በተደጋጋሚ የታዩባቸው ዓመታት እንደ ነበሩ ያመለክታል (ከመ ጽሐፉ መግቢያ "ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርይው" የሚለውን ይመ):: እስራኤል ከእግዚአብሔር በተሰጣት ተስፋ መሠረት፣ በምት ወርሰው ምድር በደስታ መኖር የምትችለው ለእግዚአብሔርና ለኪዳኑ ታማኝ ሆና ስትገኝ ብቻ መሆኑን ጸሓፊው ያስገነዝባል::

2፥6 ***ምድሪቱን ለመውረስ፤*** የ1፥1 ማብ ይመ::

2፥8 ***የእግዚአብሔር አገልጋይ፤*** ኢያሱ እግዚአብሔርን የሚወክል መሆኑን ያመለክታል (የዘፀ 14፥31 ማብ፤ የመዝ 18 ርእስ፤ ኢሳ 41፥8-9፤ 42፥1 ይመ):: ***በመቶ ዐሥር ዓመቱ፤*** ይህን ቍጥር በተመለከተ የዘፍ 50፥26 ማብ ይመ::

*2፥10-15፤* የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን ስለ ተወ፣ እርሱም እስራኤልን አልረዳውም:: "የገዛውን (ዘፀ 15፥16) እና የታደገውን ሕዝብ" (ዘፀ15፥13፤ ከመዝ74፥2 ጋር ያነጻጽሩ) "ይሸጠዋል::"

2፥10 ***ወደ አባቶቹ ከተከማቸ በኋላ፤*** ዘፍ15፥15 እንዲሁም የዘፍ 25፥8ማብ ይመ:: ***እግዚአብሔርንም ሆነ እርሱ ለእስራኤል፤*** እግዚአብሔር ያደረገውን ነገር አላወቁም ነበር (ዘፀ1፥8 ይመ)::

2፥11 ***በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር አደረጉ፤*** ይህን የመሰለ አገላለጽ በ3፥7:12፤ 4፥1፤6፥1፤ 10፥6 ላይ ይገኛል:: ***የበኣል፤*** ከነዓናውያን በልዩ ልዩ መልክ የሚያመልኳቸው የዚያው አገር ጣዖታት ናቸው (የቍ13ማብ ይመ)::

2፥12 ***እግዚአብሔርን አስቈጡት፤*** ዘዳ4፥25 እንዲሁም የዘካ1፥2 ማብ ይመ::

2፥13 ***በኣል፤*** ትርጒሙ "ጌታ" ማለት ነው፤ በከነዓናውያንና በፊንቄያውያን ዘንድ ይመለክ የነበረው ይህ የጣዖት አምላክ የዳጎንና የኤል ልጅ በመባል ይታወቃል፤ በአራም (ሶርያ) ሀዳድ፣ በባቢሎን ደግሞ አዳድ በሚል ስም ይጠራል:: በኣል ማሕፀን እንደሚያለመልም፣ ለምድር ሕይወት የሆነውን ዝናም እንደ ሚሰጥ ይታመን ነበር:: እርሱም የልምላሜና የብርታት ምልክት በሆነ ኮርማ ላይ እንደ ቆመ አድርገው ይቀርጹታል (1ነገ12፥28 ይመ)፤ አስፈሪ ደመና ሠረገላው፣ ነጎድጓድ ድምፁ፣ መብረቅ ጦርና ቀስቱ ነው ይላሉ:: የበኣል አምልኮ በቤተ ጣዖት ውስጥ ዝሙት መፈጸምንና ሕፃናትን መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብን ያካትታል (ኤር19፥5ይመ):: የኤልያስና የኤልሳዕ ታሪክ (1ነገ17-2ነገ13) እንዲሁም ሌሎች የብሉይ ኪዳን ክፍሎች (ለምሳሌ መዝ 29፥3-9፤ 68፥1-4:32-34፤ 93፥1-5፤ 97፥1-5፤ ኤር10፥12-16፤14፥22፤ ሆሴ2፥8:16-17፤ አሞ5፥8) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የበኣልን አምልኮ የሚቃወሙ ናቸው:: ***አስታሮት፤*** የበኣል ሚስት እንደ ሆነችው እንደ አስታሮትና የኤል ሚስት እንደ ሆነችው አሼራ እንስት ጣኦት ናት:: ኤል የከነዓናውያን አማልክት የበላይ አምላክ ነው ተብሎ ይታመን ነበር:: አስታሮት ከምሽት ኮከብ ጋር የምትመሳሰል የተዋበች የጦርነትና የልምላሜ አምላክ እንደ ሆነች ይነገራል:: እርሷም በባቢሎን ኢሽታር፣ በአራም (በሶርያ) ደግሞ አታርት በሚል ስም ትመለክ ነበር:: ግሪኮች አስታርቴ ወይም አፍሮዲት፣ ሮማውያን ደግሞ ቬኑስ ይሏታል፤ የአስታሮት አምልኮ ዘግናኝና አስጸያፊ ከሆነ የዝሙት ተግባር ጋር የተቈራኘ ነው (1ነገ14፥24፤ 2ነገ 23፥7)::

2፥14 ***አሳልፎ ሰጣቸው፤*** ልክ ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አገላለጽ በ6፥1፤13፥1፤10፥7 ላይ ይገኛል:: ***ሸጣቸው፤*** በ3፥8፤4፥2 ላይ ከተጠቀሰው አገላለጽ ጋር ተመሳሳይ ነው::

*2፥16-19፤* እስራኤላውያን መከራ በሚያገኛቸው ጊዜ እግዚአብሔር ከጭቈና አገዛዝ ነጻ በማውጣት የሚታደጓቸውን መሳፍንት እያስነሣ ለሕዝቡ ምሕረቱን ይገልጽላቸው ነበር፤ እነርሱ ግን ቀድሞ በሙሴና በኢያሱ ያደረገውን ነገር እንደረሱት ሁሉ፣ አሁንም ይህን የማዳን ሥራውን አላስተዋሉትም::

2፥16 ***መሳፍንት፤*** በመጽሐፉ መግቢያ ላይ "አሰያየሙ" የሚለውን ይመ:: ዋና ዋናዎቹ መሳፍንት ስድስት ሲሆኑ፣ ስማቸውም ጎቶንያል፣ ናዖድ፣ ዲቦራ፣ ጌዴዎን፣ ዮፍታሔ፣ ሳምሶን ነበር:: ከእነዚህ አነስተኛ ደረጃ የነበራቸው ደግሞ ሰሜጋር፣ ቶላ፣ ኢያዕር፣ ኢብጻን፣ ኤሎም፣ ዓብዶን ይባላሉ:

2፥17 ***አመነዘሩ፤*** በዕብራይስጥ በኣል "ጌታ" ማለት ሲሆን፣ ሴቶችም ባሎቻቸውን ለመጥራት የሚጠቀሙበት ቃል ነው:: በተለዋጭ ዘይቤአዊ አገላለጽ ዝሙትን የሚገልጽ ሲሆን፣ በዚህም የእስራኤል ሕዝብ በኣልን ማምለካቸውን የሚያመለክት የተለመደ አባባል ነው (ሆሴ 2፥2-3:16-17)::

2፥18 ***ሥቃይና መከራ፤*** እስራኤላውያን በግብፅ ባርነት ሥር በነበሩበት ጊዜ የደረሰባቸውን የሚያመለክት ነው (ዘፀ 2፥24፤ 3፥9፤ 6፥5 ይመ)::

[20]ስለዚህ *እግዚአብሔር* በእስራኤል ላይ
እጅግ ተቈጣ፤ እንዲህም አለ፤ “ይህ ሕዝብ
ለቀደሙ አባቶቹ የሰጠሁትን ቃል ኪዳን
ስለተላለፈ፣ እኔንም ስላልሰማ፣ [21]ኢያሱ በሞተ
ጊዜ ከተዋቸው በምድሪቱ ከነበሩት ሕዝቦች
አንዳቸውንም እንኳ በፊታቸው አላስወጣም:: [22]ይህን የሚያደርገውም አባቶ
ቻቸው እንዳደረጉት ሁሉ፣ እስራኤላውያን
*የእግዚአሔርን መንገድ የሚጠብቁ መሆን*
*አለመሆናቸውን ለማወቅ እፈትናቸው ዘንድ*
*እነርሱን መሣሪያ ለማድረግ ነው።”* [23]ስለ
ዚህ *እግዚአብሔር* እነዚያን ሕዝቦች በዚ
ያው እንዲኖሩ አደረገ፤ በኢያሱ እጅ አሳልፎ
በመስጠት ወዲያውኑ አሳዶ አላስወጣቸውም::

3 በዚህ ጊዜ በከነዓን ላይ በተደረጉት
ጦርነቶች ተሳትፈው የማያውቁትን እስ
ራኤላውያን ለመፈተን፣ *እግዚአብሔር*
ባሉበት የተዋቸው ሕዝቦች እነዚህ ናቸው፤
[2]ይህን ማድረጉ ቀደም ሲል በጦር ሜዳ
ውለው የማያውቁትን የእስራኤል ልጆች
የጦርነት ልምድ እንዲያገኙ ለማድረግ ብቻ
ነው፤ [3]እነዚህም አሕዛብ አምስቱ የፍልስ
ጥኤም ገዦች፣ ከነዓናውያን በሙሉ፣ ሲዶና
ውያንና ከበኣል አርሞንዔም ተራራ እስከ
ሐማትስ *መግቢያ* ባሉት የሊባኖስ ተራሮች
የሚኖሩ ኤዊያውያን ነበሩ:: [4]እነዚህ፣ *እግ*
*ዚአብሔር* በሙሴ በኩል ለቀደሙ አባቶቻቸው
የሰጠውን ትእዛዛት ማክበር አለማክበራ
ቸውን ለማወቅ መፈተኛ እንዲሆኑ እዚያው
የቀሩ ነበሩ::

[5]ስለዚህ እስራኤላውያን ከከነዓናውያን፣
ከኬጢያውያን፣ ከአሞራውያን፣ ከፌርዛውያን፣
ከኤዊያውያንና ከኢያቡሳውያን ጋር አብረው
ኖሩ:: [6]እስራኤላውያን የእነዚህን ሴቶች ልጆች
አገቡ፤ የራሳቸውንም ሴቶች ልጆች ለእነርሱ
ወንዶች ልጆች ዳሩ፤ አማልክቶቻቸውንም
አመለኩ::

### ጎቶንያል

[7]እስራኤላውያን *በእግዚአብሔር* ፊት
ክፉ ድርጊት ፈጸሙ፤ *እግዚአብሔር* አምላካ
ቸውንም ረሱ፤ የበኣልንና የአስታሮትን
አማልክት አመለኩ:: [8]*እግዚአብሔር* በእስራ
ኤላውያን ላይ እጅግ ተቈጣ፤ ስለዚህ ለመ
ስጴጦምያ[ሸ] ንጉሥ ለኩስርስቴም አሳልፎ
ሰጣቸው፤ እስራኤላውያንም ስምንት ዓመት
በባርነት ተገዙለት:: [9]እስራኤላውያን ወደ
*እግዚአብሔር* በጮኹ ጊዜ ግን የካሌብን
ታናሽ ወንድም የቄኔዝን ልጅ ጎቶንያልን
ታዳጊ አድርጎ አስነሣላቸው:: [10]*የእግዚ*
*አብሔር* መንፈስ በእርሱ ላይ ወረደ፤ የእስ
ራኤል መስፍን[*] ሆኖ ወደ ጦርነትም
ወጣ:: *እግዚአብሔር* የመስጴጦምያን ንጉሥ
ኩስርስቴምን አሳልፎ ስለ ሰጠው ድል
አደረገ:: [11]የቄኔዝ ልጅ ጎቶንያል እስኪሞ
ተበት ጊዜ ድረስ ምድሪቱ ለአርባ ዓመት
ሰላም አገኘች::

2፥20 ዘጸ31፥17፤ ኢሱ7፥11፤23፥16፤ 2ነገ17፥15
2፥21 ኢሱ23፥5
2፥22 ዘፍ22፥1፤ ዘዐ15፥25
2፥23 መሳ1፥1
3፥1 ዘዐ15፥25
3፥3 ዘፍ 10፥14፡17፤ ዘኍ13፥21፤ ዘዐ፥8፤ ዘሌ13፥21፤ ዘዳ3፥8፤ ኢሱ13፥3
3፥4 ዘዐ15፥25 3፥5 ኢሱ3፥10፤ 11፥3፤ዕዝ9፥1፤ መዝ106፥35
3፥6 ዘዐ34፥16፤ ዘዳ7፥3-4፡16፤ዕዝ10፥18፤ ነህ13፥23፤ሚል2፥11
3፥7 ዘዐ34፥13፤ ዘዳ4፥9፤32፥18፤ መሳ2፥11፡13፤8፥34፤ 1ነገ16፥33፤2ዜና34፥7፤መዝ78፥11፡42፤106፥7፤ኢሳ17፥8፤ ኤር23፥27
3፥8 ቍ 10፤ዘፍ 24፥10፤መሳ2፥14፤ መዝ44፥12፤ኢሳ 50፥1፤52፥3
3፥9 ቍ15፤ ዘጸ 28፥29፤ ኢሱ15፥17፤ መሳ6፥6፡7፤10፥10፤1ሳሙ12፥10፤ነህ9፥27፤ መዝ106፥44፤107፥13
3፥10 ቍ8፤ ዘፍ10፥22፤ዘኍ11፥25፤መሳ6፥34፤11፥29፤13፥25፤14፥6፡19፤15፥14፤1ሳሙ11፥6፤16፥13፤1ነገ18፥46፤ 1ዜና12፥18፤2ዜና24
3፥11 ቍ30፤ዘዐ16፥35፤ኢሱ14፥15፤15፥17፤ መሳ5፥31፤8፥28

[ሀ]3 *ወይም እስከ መግቢያው ድረስ ተብሎ ሊተረጐም ይችላል::*
[ሸ]8 *ስሜን ምዕራብ መሴጴጦንያ ነው::*
[*]10 *ወይም መሪ ተብሎ ሊተረጐም ይችላል::*

*2፥20-23፤* እግዚአብሔር የእስራኤልን *ታማኝነትና ታዛዥ*ነት ለመፈተን ሲል የቀሩት ሕዝቦች እዚያው ባሉበት እንዲቀመጡ ፈቀደ::

*3፥1-6፤* ኢያሱ በሞተበት ዘመን (ቍ1-4) የእስራኤል ሕዝብ ይዞት የነበረውን አገር በምዕራብና በሰሜን የሚያዋስኑትን ሕዝቦች ስም በዚህ ክፍል ተጠቅሰዋል፤ እስራኤላውያን በያዙት ግዛት ውስጥ የአገሬው ተወላጅ የሆኑ ብዙ ሕዝብ ይኖሩ ነበር (ቍ5፤ 1፥27-36 *ይመ*)፤ እስራኤላውያንም የእነዚህን ሕዝብ ሃይ ማኖት እስከሚከተሉ ድረስ ከእነርሱ ጋር ተቀላቅለው ይኖሩ ነበር::

3፥2 ***የጦርነት ልምድ እንዲያገኙ ለማድረግ ብቻ፤*** እስራ ኤላውያን የእግዚአብሔር ኪዳን አገልጋይ እንደ መሆናቸው መጠን፣ በምድሪቱ ላይ ተደላድለው የተቀመጡትን ኀያላን መንግሥታትን የሚወጉ የእግዚአብሔር ሰራዊት ናቸው:: ገና ድል ካላገኘው ጦርነት አንጻር ሲታይ፣ ቀጣዩ የእስራኤል ትውልድ ወደ ፊትም ቢሆን ለጦርነት ብቃት ያለው ብርቱ ሰራ ዊት ሆኖ መገኘት ነበረበት፤ እዚህ ላይ “ብቻ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው “በተለይ” የሚለውን ነው::

3፥3 ***አምስቱ...ገዦች፤*** በዕብራይስጥ “ገዥዎች” የሚለው ቃል አምባ ገነንነትን የሚያመለክት ነው:: (የኢያሱ13፥3 ማብ *ይመ*)፤ በዚህም የሚጠሩት ፍልስጥኤማውያን ገዦች ብቻ ነበሩ:: እነዚህም ገዦች በኮንፌደሬሽን የሚተዳደሩትን አምስት ከተሞች የሚቈጣጠሩ ነበሩ:: በአንድ ወቅት ይሁዳ ከእነዚህ ከተሞች ሦስቱን ድል ቢያደርግም፣ በአገዛዙ ሥር (1፥18) ሊያቈይ አልቻለም:: ***ሲዶናውያን፤*** እዚህ ላይ የተጠቀሰው በጥቅሉ ፊንቄያውያንን ለማመልከት ነው:: ***ኤዊያውያን፤*** እስከ ሐማት የሚዘልቀውን ሰሜኑን የከነዓን ምድር የሚያመለክት ነው (ኢሱ 11፥3 *ይመ*):: ***ከበኣል አርሞንኤም ተራራ፤*** ምናልባትም የአር ሞንኤም ተራራ ሳይሆን አይቀርም (1ዜና 5፥23 *ይመ*)::

3፥6 ***ሴቶች ልጆች አገቡ ... አማልክቶቻቸውንም አመለኩ፤*** የኢሱ 23፥12 ማብ *ይመ*:: እንዲህ ያለው በጋብቻ መቀላቀል ያስከተለው ጠንቅ በሰሎሞን ሕይወት ታይቶአል (1ነገ11፥1-8)::

*3፥7-11፤* ጸሓፊው ስለ ሀበይት መሳፍንት ሲጽፍ የተጠቀመበትን ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ ስለ መስፍኑ ጎቶልያል ለመዘገብም ተጠቅሞበታል:: ከዚህም የተነሳ አጫጭር መግለጫዎች ከእ ምነት ማፈግፈግ፣ ጭቆና፣ መከራ ድነትና ሊታወስ የሚችል ማጠቃለያ አክሉበታል:: ዝርዝር ሁኔታዎችን የሚያቀርበው ግን የተሟላ ዘገባ ለማቅረብ በሚፈልግበት ጊዜ ብቻ ነው (በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ሥነ ጽሑፋዊው ባሕርያቱ ይሚለውን *ይመ*)::

3፥7 ***በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸሙ፤*** በዚያን ዘመን በተከታታይ የተነሡት መሳፍንት የፈጸሙትን በደል ለማ መልከት የተጠቀሰ ተደጋጋሚ አገላለጽ ነው (ቍ12፤4፥1፤6፥1፤ 10፥6፤ 13፥1 *ይመ*):: ***የበኣል....አማልክት፤*** የ12፥13 ማብ *ይመ*:: ***የአስታሮት፤*** የ2፥13፤ የዘፀ34፥13 ማብ *ይመ*::

3፥8 ***ለኩሰርስቴም፤*** የስሙ ትርጒም “በእጥፍ የክፋ ኩሻን” ማለት ሊሆን ይችላል፤ ምናልባትም የስሙ ትርጒም እውነተኛ ስሙንና ባሕርይውን የሚያሳይ ሊሆን ይችላል (ብዔል ዜቡልን በተ መለከተ የ10፥6 ማብ *ይመ*)

3፥9 ***ወደ እግዚአብሔር በጮኹ ጊዜ፤*** ከእያንዳንዱ መስፍን መነሣት በፊት በተደጋጋሚ ከደረሰባቸው መከራ የተነሣ፣ እስራኤላውያን ወደ እግዚአብሔር ያሰሙትን የመከራ ጩኸት ያመለክታል:: ***ጎቶንያል፤*** 1፥13 *ይመ*::

3፥10 ***የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ ወረደ፤*** ለጌዴዎን (6፥34)፣ለዮፍታሔ (11፥29)፣ ለሳምሶን (14፥6፡9) እንዲሁም ለዳዊት (1ሳሙ16፥13) እንዳደረገው ሁሉ፣ ለጎቶንያልም ሕዝቡን ይታደግ ዘንድ የመንፈስ ቅዱስ ኀይል ሰጠው፤ ከዘኍ11፥25-29 ጋር ያነጻጽሩ::

3፥11 ***ምድሪቱም ... ዓመት ሰላም አገኘች፤*** የእያንዳንዱ መስፍን የአገዛዝ ዘመን ሲያበቃ በተደጋጋሚ መደምደሚያ ሆኖ የሚቀርብ ሐሳብ ነው (የተጠቀሰውም እዚህ ላይና፣ ቍ30፤5፥31፤ 8፥28 ላይ ብቻ ነው):: ጌዴዎን መስፍን ሆኖ ከገዛ በኋላ ግን ይህ አባባል ቀርቶ፣ “***እስራኤልን... ዓመት መራቸው***” በሚል ተተክቶአል (12፥7፤15፥20፤16፥31):: ***አርባ ዓመት፤*** የአንድን ትውልድ ዘመን የሚያመለክት የተለመደ አነጋገር ነው::

## ናዖድ

12እስራኤላውያን እንደ ገና በእግዚ
አብሔር ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸሙ፤ ይህን
በማድረጋቸውም እግዚአብሔር የሞዓብ ንጉሥ
ዔግሎን በእስራኤል ላይ እንዲበረታባቸው
አደረገ። 13እርሱም አሞናውያንንና አማሌቃ
ውያንን ካስተባበረ በኋላ እስራኤልን ወግቶ
የዘንባባ ዛፎች[ሀ] ከተማ የሆነችውን ኢያሪኮን
ያዙ። 14እስራኤላውያንም ለሞዓብ ንጉሥ
ለዔግሎን ዐሥራ ስምንት ዓመት ተገዘ
ሉት።

15እስራኤላውያን እንደ ገና ወደ እግዚአ
ብሔር ጮኹ፤ እግዚአብሔርም ብንያማ
ዊውን የጌራን ልጅ ግራኙን ናዖድን ነጻ
እንዲያወጣቸው አስነሣው። እስራኤላውያን
ናዖድን ግብር አስይዘው ወደ ሞዓብ ንጉሥ
ወደ ዔግሎን ላኩት። 16እርሱም በሁለት
በኩል ስለታም የሆነና አንድ ክንድ ተኩል
ርዝመት[+] ያለው ሰይፍ አዘጋጅቶ በልብሱ
ውስጥ በቀኝ ጭኑ ላይ አሰረው። 17ግብሩንም
ወፍራም ለነበረው ለሞዓብ ንጉሥ ለዔግሎን
አቀረበ፤ 18ናዖድም ግብሩን ካቀረበ በኋላ፣
ግብር ተሸክመው የመጡት ሰዎች ተመልሰው
እንዲሄዱ አደረገ። 19እርሱ ራሱ ግን ጌልጌላ
አጠገብ ድንጋዮች[*] ተጠርበው ከሚወጡ
በት አካባቢ ሲደርስ ወደ ኋላ በመመለስ
ወደ ንጉሡ ሄዶ፣ "ንጉሥ ሆይ፤ በምስጢር
የምነግርህ ነገር አለኝ" አለው።

ንጉሡም፣ "ጸጥታ!" ሲል፤ አጠገቡ የነበሩት
አገልጋዮች በሙሉ ትተውት ወጡ። 20ንጉሡ
ሰገነት ላይ ባለው ነፋሻ ዕልፍኝ[1] ውስጥ
ብቻውን ተቀምጦ ሳለ ናዖድ ቀረብ ብሎ፣
"ከእግዚአብሔር ዘንድ ለአንተ ያመጣሁት መልእ
ክት አለኝ" አለው፤ ንጉሡም ከዙፋኑ ተነሣ።
21ናዖድ ግራ እጁን ሰደድ በማድረግ ሰይፉን
ከደበቀበት ከቀኝ ጭኑ መዝዞ በንጉሡ ሆድ
ሻጠው። 22እጀታው ሳይቀር ሰይፉ እንዳለ
ሆዱ ውስጥ ገባ፤ ስለቱም በጀርባው ወጣ፤
ሞራም ስለቱን ሸፈነው፤ ናዖድ ሰይፉን ስላ
ልነቀለው እንጀቱ ተዘረገፈ። 23ከዚያም በኋላ
ናዖድ በዕልፍኙ[2] መግቢያ ወጣ፤ የዕልፍኙንም
በር በንጉሡ ላይ ዘግቶ ቈለፈው። 24ናዖድ
ከሄደ በኋላ የንጉሡ አገልጋዮች ሲመጡ፣ የዕ
ልፍኙ በር ተቈልፎ አገኙት፤ እነርሱም፣
"በውስጠኛው ክፍል እየተጸዳዳ ይሆናል" አሉ፤
25እስኪደክማቸውም ድረስ ጠበቁ፤ ነገር ግን
ንጉሡ የእልፍኙን በሮች ባለመክፈቱ ቍልፍ
ወስደው ከፈቱ፤ በዚያም ጌታቸው ሞቶ፣
በወለሉም ላይ ተዘርግቶ አገኙት። 26የንጉሡ
አገልጋዮች በዕልፍኙ በር ላይ ቆመው ሲጠ
ባበቁ ናዖድ ርቆ ሄደ፤ ድንጋዮች ተጠርበው
በሚወጡበት በኩል ወደ ሴርታይም አመለጠ።
27እዚያም እንደ ደረሰ፣ በኰረብታማው በኤፍሬም
ምድር ቀንደ መለከቱን ነፋ፤ እስራኤላውያንም
በእርሱ መሪነት ከኰረብታው ላይ አብረውት
ወረዱ።

28እርሱም፣ "ጠላታችሁን ሞዓብን እግዚ
አብሔር በእጃችሁ አሳልፎ ስለ ሰጣችሁ
ተከተሉኝ" በማለት አዘዛቸው፤ እነርሱም
ተከትለውት ወረዱ፤ ከዚያም ከዮርዳኖስ
ወደ ሞዓብ የሚያሻግሩትን መልካዎች በመ
ያዝ አንድም ሰው እንዳያልፍ ከለከሉ።
29በዚያን ጊዜ ብርቱና ኀይለኛ የሆኑ ዐሥር
ሺህ ሞዓባውያንን ገደሉ፤ አንድም ሰው
አላመለጠም። 30በዚያን ቀን ሞዓብ በእስራ
ኤል ድል ሆነች፤ ምድሪቱም ለሰማንያ ዓመት
ሰላም አገኘች።

## ሰሜጋር

31ከናዖድ በኋላ ስድስት መቶ ፍልስጥኤ

[ሀ]13 ኢያሪኮ ነች
[+]16 0.5 ሜትር ያህል ነው
[*]19 በዚህና በቍጥር26 ላይ ጣዖት ተብሎ ሊተረጐም ይችላል።
[1]20 የዕብራይስጡ ሐረግ ትርጒም በትክክል አይታወቅም።
[2]23 የዕብራይስጡ ቃል ትርጒም በትክክል አይታወቅም።

፥20፤ኢሳ11፥2
3፥12 መሳ2፥11፤1
ሳሙ12፥9
3፥13 ዘፍ14፥7፤
19፥38፤መሳ1፥16፤1
0፥11
3፥14 ኤር48፥1
3፥15 ቍ9:16:
3፥16 ቍ15
3፥17 ቍ15፤ኢዮ
15፥27፤መዝ73፥417
:18፤መሳ4፥1፤20፥16
፤2ሳሙ8፥2:6፤1ነገ4፥
21፤2ነገ17፥3፤ዜና1
2፥2አስ10፥1፤መዝ6
8፥29፤72፥10፤89፥2
2፤መክ2፥8፤ኢሳ
60፥5፤ ሆሴ10፥6
3፥20 ነህ8፥5፤
አሞ3፥15
3፥21 2ሳሙ2፥16፤
3፥27፤20፥10
3፥24 1ሳሙ24፥3
3፥25 2ነገ2፥17፤
8፥11
3፥27 ዘሌ25፥9፤
መሳ6፥34፤7፥18፤2ሳ
ሙ2፥28፤ኢሳ18፥3፤
ኤር42፥14
3፥28 ዘፍ19፥37፤
ዘኍ13፥29፤ኢ
ሱ2፥7፡ 24፤መሳ1፥2
3፥30 ቍ11፤
ዘፍ36፥35
3፥31 ኢሱ13፥2፤
23፥10፤መሳ5፥6፤10
፥11፤13፥1፤1ሳሙ5፥
1፤31፥1፤2ሳሙ8፥1፤
ኤር25፥20፤47፥1

*3፥12-30፤* ይህ ክፍል ናዖድ በሞዓብ ንጉሥ በዔግሎን ላይ ያገኘውን ድል የሚያወሣ ነው። ግራኙ የብንያም ሰው ናዖድ በእርግጥም የሚደነቅ ጀግና ነበር። ምንም ሰው አብሮት ሳይኖር፣ አንድ ራሱን ብቻ ሆኖ፣ የራሱን ብልሃትና ዘዴ በመጠቀም በከነዓን ምድር በኢያሪኮ አጠገብ ተደላድሎ ይኖር የነበረውን የሞዓብን ንጉሥ መግደል ቻለ። ይህ ታሪክ በመጽሐፈ መሳፍንት ከተወሱት አምስት የተለያዩ ዋና ዋና ትረካዎች ጋር ሲነጻጸር፣ ስለ ሳምሶን ከተጻፈው ጋር ተመሳሳይነት አለው።

3፥12 ***ሞዓብ፤*** የዘፍ 19፥33 ማብ ይመ።

3፥13 ***አሞናውያን፤*** የዘፍ 19፥33 ማብ ይመ። ***አማሌቃውያን፤*** እነዚህ የዔሳው ዘሮች ሲሆኑ (ዘፍ36፥12:16)፣ የኖሩትም በነጌብ ነበር (ዘኍ 13፥29)። የዘፍ 14፥7 ማብ ይመ።

3፥14 ***እስራኤላውያን፤*** እዚህ ላይ በይበልጥ የሚያመለክተው ብንያምንና ኤፍሬምን ነው።

3፥15 ***ግራኙን፤*** ግራኝ መሆን በብንያማውያን ዘንድ አይፈ ለግም ነበር (20፥15-16)። ብንያም ማለት "የቀኝ እጅ ልጅ" ማለት ስለ ሆነ፣ ነገሩ የምጸት አባባልም ነው። ናዖድ ግራኝ ስለ ነበር፣ ሰይፉን ደብቀው እንዳይታይ አድርጎ ሊደብቀው ችሎአል (ቍ21 ይመ)። ***ግብር፤*** ከዕርሻ በሚገኝ ምርት የሚከፈል ዓመታዊ ክፍያ ሊሆን ይችላል (ከ2ነገ 3፥4 ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥16 ***በሁለት በኩል ስለታም የሆነ... ሰይፍ፤*** በመሳፍንት ዘመን እስራኤላውያን ይጠቀሙበት የነበረው የጦር መሣሪያ የሚሰራው በወቅቱ የሚገጥማቸውን አደጋ ለመቋቋም ነበር፤ ከዚህ አንጻር የሰሜጋርን የበሬ መንጃ (ቍ31)፣ የኢያዔልን ካስማ (4፥22)፣ የጌዴዎንን ማሰሮዎችና ችቦዎች (7፥20)፣ የሴትየዋን መጅ (9፥53) እንዲሁም የሳምሶንን የአህያ መንጋጋ (15፥15) መጥቀስ ይቻላል፤ በተጨማሪም 1ሳሙ 13፥19 ይመ።

3፥19 ***ድንጋዮች፤*** የተጠረቡ ምስሎችን ያመለክታል፤ ነገር ግን እዚህ ላይ የዔግሎንን የተጠረበ ምስል ሊሆን ይችላል። ይኸውም ዔግሎን በዚያን ጊዜ ወደ ግዛቱ የጨመረውን የአዲሱን አገር ወሰን ለማመልከት ያቆመው ሐውልት ነው። ይህ ዐይነት ልማድ በቅርብ ምሥራቅ አገሮች የተለመደ ነበር።

3፥20 ***ሰገነት፤*** በዚያን ዘመን በየቤቱ ጣራና (2ነገ 4፥10-11) በቤተ መንግሥት ሰገነት ጣራ (ኤር22፥13-14) ላይ ዕልፍኞች ይሠሩ ነበር፤ የዓይነ ርግብ መስኮት ስላላቸው በበጋው ወራት ለስስ ያለ አየር በማስገባት ቀዝቀዝ ያለ አየር ያስገኙ ነበር።

3፥22 ***በጀርባው ወጣ፤*** ወይም "ሆድ ዕቃው ተዘረገፈ" ማለት ነው።

3፥28 ***የሚያሻግሩትን መልካዎች በመያዝ፤*** መተላለፊያውን አስቀድመው መያዛቸው፣ ሞዓባውያን ደጀን ጦር እንዳይልኩ አገዳቸው፤ እስራኤላውያንም ከኢያሪኮ የሚሸሹትን ሞዓባውያንን በሙሉ እንዲጨርሷቸው ረድቶአቸዋል።

3፥30 ***ሰማንያ ዓመት፤*** በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ቍጥሮች የሚነገሩት በማጠጋጋት ነው (ከመግቢያው "ታሪካዊ ዳራው" የሚለውን ይመ)።

3፥31 ***ሰሜጋር፤*** ከስድስቱ ታናናሽ መሳፍንት አንዱ ሲሆን፣ የኖረውም ዲቦራ በነበረችበት ዘመን ነበር (5፥6-7 ይመ)። ስሙ ለየት ያለ ስለሆነ፣ ይህ ሰው እስራኤላዊ ሳይሆን የሌላ አገ

ማውያንን በበሬ መንጃ የገደለው የዓናት ልጅ
ሰሜጋር ተነሣ፤ እርሱም እንደዚሁ ደግሞ
እስራኤልን አዳነ።

## ዲቦራ

4 ናዖድ ከሞተ በኋላ እስራኤላውያን እንደ
ገና በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸሙ።
2ስለዚህም እግዚአብሔር በሐጾር ሆኖ ይገዛ
ለነበረው ለከነዓን ንጉሥ ለኢያቢስ አሳልፎ
ሰጣቸው። የኢያቢስ ሰራዊት አዛዥ፣ በሐ
ሮሼትሐጎይም የሚኖረው ሲሣራ ነበረ፤
3እርሱም ዘጠኝ መቶ የብረት ሠረገሎች ስለ
ነበሩት እስራኤላውያንን ሃያ ዓመት እጅግ
አስጨንቃቸው፤ እነርሱም ይረዳቸው ዘንድ
ወደ እግዚአብሔር ጮኹ።
4በዚያን ጊዜ የለፊዶት ሚስት ነቢዪቱ
ዲቦራ በእስራኤል ላይ ፈራጅ[a] ነበረች።
5እርሷም በኰረብታማው በኤፍሬም ምድር፣
በራማና በቤቴል መካከል ካለው የዲቦራ
ዘንባባ ዛፍ ሥር ተቀምጣ ትፈርድ ነበር፤
እስራኤላውያንም ለፍርድ ወደ እርሷ ይመጡ
ነበር። 6ዲቦራ፣ በንፍታሌም ውስጥ ቃዴስ
በተባለች ከተማ ይኖር የነበረውን የአቢኒ
ኤምን ልጅ ባራቅን አስጠርታ እንዲህ
አለችው፤ "የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር
እንዲህ ሲል ያዝሃል፤ "ተነሣ፤ ከንፍታሌምና
ከዛብሎን ዐሥር ሺህ ሰዎች ይዘህ ወደ
ታቦር ተራራ ውጣ፤ 7እኔም የኢያቢስን
ሰራዊት አዛዥ ሲሣራን ከሠረገሎቹና ከሰራ
ዊቱ ጋር ቂሶን ወንዝ እንዲመጣ አነሣሣ
ዋለሁ፤ በእጅህም አሳልፌ እሰጥሃለሁ። "
8ባርቅም፣ "አብረሽኝ የምትሄጂ ከሆነ
እሄዳለሁ፤ አብረሽኝ የማትሄጂ ከሆነ ግን
አልሄድም" አላት።
9ዲቦራ መልሳ፣ "ይሁን እሺ፤ መሄዱን
አብሬህ[b] እሄዳለሁ፤ በዚህ ሁኔታ የምትሄድ
ከሆነ ግን ክብሩ ለአንተ አይሆንም፤ እግዚ
አብሔር ሲሣራን ለሴት አሳልፎ ይሰጣልና"
አለችው። ስለዚህ ዲቦራ ከባርቅ ጋር ወደ
ቃዴስ ሄደች፤ 10በዚያም ባርቅ ለዛብሎንና
ለንፍታሌም ሰዎች ጥሪ አስተላለፈ፤ ዐሥር
ሺህ ሰዎች ተከተሉት፤ ዲቦራም አብራው
ሄደች።
11በዚያን ጊዜ ቄናዊው ሔቤር፣ የሙሴ

4፥1 መሳ2፥11፡ 19፤3፥15
4፥2 ዘዳ32፥30፤ ኢሱ11፥1፤ 1ሳሙ12፥9፤ መዝ83፥9
4፥3 ኢሱ17፥16፤ መሳ10፥12፤ መዝ106፥42
4፥4 ዘፀ15፥20፤ መሳ5፥1፡7፡12፡15
4፥5 ኢሱ12፥9፤ 18፥25፤1ሳሙ14፥2፤ 22፥6
4፥6 ዘፍ30፥8፤ ኢሱ12፥22፤ 19፥22፤መሳ5፥1፡12፡ 15፡18፤6፥35፤ 1ሳሙ12፥11፤ ዕብ11፥32
4፥7 ቊ13፤ ኢሱ11፥1፣ መሳ1፥2፤5፥21፣1ነገ 18፥40፤መዝ83፥9
4፥9 ኢሱ12፥22
4፥10 2ዜና 36፥ 23፤ዕዝ1፥2፤ኢሳ4 1፥2፤42፥6፤ 45፥3፤ 46፥11፤48፥15
4፥11 ዘፍ15፥19፤ ዘኁ10፥29፤ኢ ሱ19፥33፤24፥26፤ መሳ9፥6

[a] 4 በትውፊት መሳፍንት ማለት ነው
[b] 9 ወይም፣ ነገር ግን ልትሄድ ወደ ዐቀድከበት ስፍራ

ሰው ሊሆን ይችላል። *የዓናት ልጅ፤* ይህ የሚያሳየው አንድም ሰሜጋር የመጣው ከቤት ዓናት መሆኑን፣ አሊያም ቤተሰቡ ዓናት የምትባለውን ጣዖት አምላክ ማምለኩን ነው። የበአል እኅት የሆነችው ዓናት ለበአል ትዋጋለት ነበር፣ የጦርነት አምላክ ስትሆን፣ "የዓናት ልጅ" የሚለው አባባል የጦርነት ማዕረግ ስም ሊሆን ይችላል፤ ትርጒሙም "ተዋጊ" ማለት ነው። *በበሬ መንጃ፤* ረዘም ያለ ዘንግ ሲሆን፣ አልፎ አልፎም እንስሳትን እያጣደፉ መንዳት እንዲቻል በጫፉ ላይ ሹል ብረት ይኖረዋል፤

*4፥1-5፥31፤* ዲቦራ የከነዓናውያን የጦር አለቃ በሆነው በሲሣራ ላይ የተቀዳጀችው ድል፣ መጀመሪያ በስድ ንባብ (ም 4) ከዚያም ቀጥሎ በቅኔ (ም5) ቀርቦአል። ከነዓናውያን ከበስተ ሰሜን በኩል መምጣታቸው ከፉኛ ያሰጋ በነበረበት ወቅት፣ ዲቦራ የተባለች አንዲት ሴት ወደ እግዚአብሔር ጦርነት እንዲገቡ ጥሪ እስካደረገችበት ጊዜ ድረስ፣ እስራኤላውያን ኀይላቸውን በማስተባበር ጠላቶቻቸውን መቋቋም አልቻሉም ነበር። የእስራኤል ተዋጊዎች ቍርጠው በመነሣት ጠላትን ለመግጠም ድፍረቱ ስላልነበራቸው የድሉን ክብር ያገኘችው ኢያኤል የተባለች አንዲት ሴት ነበረች። ኢያኤል ምናልባትም እስራኤላዊት ላትሆን ትችላለች።

*4፥1-2፤* ከከነዓናውያን በስተቀር የእስራኤል ጠላቶች የሚመጡት ድል አድርጋ ከያዘቻቸው ግዛት ውጭ ነበር። እንደ መስጴጦምያ፣ ሞዓብ፣ ምድያንና አሞን ያሉት ሕዝቦች ዋናው ፍላጎታቸው ምርኮና ብዝበዛ ማካሄድ ሲሆን፣ በም4-5 እንደ ተጻፈው የከነዓናውያን መሻት ግን በሰሜን መልሰው ኀይላቸውን ለማጠናከር ነበር፤ ፍልስጥኤማውያንም ደቡቡንና መካከለኛውን አገር እስከ መጨረሻው ለመቈጣጠር ሲሉ ከእስራኤል ጋር ያለ ማቋረጥ ጦርነት ያካሂዳሉ።

4፥2 *ሐጾር፤* ለኢያቢስ ሥርወ መንግሥት የመጀመሪያዪቱ መናገሻ ከተማ ናት። እስካሁንም እንደ ፈራረሰች ትገኛለች፤ የኢሱ 11፥10 ማብ ይመ። ሲሣራ በሐዖር ነገሥታት ሥር የነበረውን ግዛት ወደ ቀድሞ ቦታው ለመመለስ ፈልጎ ነበር። *ኢያቢስ፤* መዝ 83፥9-10ይመ። ይህ ስም የተጸውዖ ስም ሳይሆን፣ ነገሥታት የሚጠሩበት የማዕረግ ስም ሊሆን ይችላል። (ኢሱ11፥10) *ሲሣራ፤* የሚለው ስም ከነዓናዊ አለመሆኑን የሚጠቍም ነው።

*4፥3 ዘጠኝ መቶ፤* ቍጥሩ ይህን ያህል የሆነ ለጦርነት የተዘጋጀ ሠረገላ የአንዲት ከተማ ብቻ ሳይሆን፣ ምናልባት የእስራኤል ጠላቶች በኅብረት ያሰለፉት ኀይል ሊሆን ይችላል። በ15ኛው ዓ.ቅ.ክ. ገደማ የነበረው ግብጻዊ ፈርዖን ቱትሞስ በመጊዶን ጦርነት ዘጠኝ መቶ ሃያ አራት ሠረገሎች መማረኩን ተናግሮ ነበር። *እስራኤላውያን፤* በይበልጥ ዛብሎንንና ንፍታሌምን ያመለክታል፤ ይሁን እንጂ ምዕራቡን ምናሴን፣ ይሳኮርንና አሴርንም ያካትታል።

4፥4 *ዲቦራ፤* ትርጒሙ "ንብ" ማለት ነው፤ ከዘዳ1፥44 ጋር ያነጻጽሩ። በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ ነቢይ መሆኗ የተነገረላት ሴት ፈራጅ እርስዋ ብቻ ናት። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነቢይነታቸው የተወሣላቸው ሌሎች ሴቶች የሙሴ እኅት ማርያም (ዘፀ15፥20)፣ ሕልዳና (2ነገ22፥14)፣ ኖዓድያ (ነህ 6፥14)፣ እንዲሁም ሐና (ሉቃ2፥36) ናቸው፤ በተጨማሪም የሐሥ 21፥9 ይመ።

4፥6 *በንፍታሌም ውስጥ ቃዴስ፤* በከነዓናውያን ጭቈና ፍዳዋን ያየች ከተማ ናት። *ባርቅ፤* ትርጒሙ "መብረቅ" ማለት ነው። ይህም የሚንቦገቦግ የእግዚአብሔር ሰይፍ (ዘዳ32፥41) እንዲሆን መጠራቱን ያመለክታል። ከእምነት ጀግኖች አንዱ እንደ ሆነ ስሙ በዕብ 11፥32 ላይ ተጠቅሶአል። *ንፍታሌም እና ዛብሎን፤* ለእነዚህ ነገዶች የቅርብ ጎረቤት ናት፤ እዚህ ቍጥር ላይ አልተጠቀሰችም፤ ይሁን እንጂ በም5፥15 ላይ ስለ ጦርነቱ በሚያወሣው ግጥም ውስጥ ስሟ ገብቶአል። ባጠቃላይ ስድስት ነገዶች በጦርነቱ መካፈላቸው ተጠቅሶአል። *ታቦር ተራራ፤* ከፍታው 1300 ጫማ ሲሆን፣ የሚገኘውም ከጦርነቱ ቦታ በስተ ሰሜን ምሥራቅ ነው።

*4፥7፤* እስራኤላውያን የሰፈሩበት የታቦር ተራራ ተረተር በሠረገላ ለሚደረገው ጦርነት አመቺ አልነበረም፤ ሲሣራን እንዲህ ባለው ወጥመድ ውስጥ እንዲገባ ማድረግ የእግዚአብሔርም ዐላማና ዕቅድ ነበር። ሲሣራ ጦርነቱን ለማካሄድ በጥንቃቄ የመረጠው ቦታ በቂሶን ወንዝ አጠገብ የሚገኘውን የኢይዝራኤል ሸለቆ ነበር፤ ቦታውም ሠረገሎቹን በማንኛውም አቅጣጫ ለማንቀሳቀስ፣ ጦርነቱን በተፈለገበት ሁኔታ ለመምራትና ከየትኛውም አቅጣጫ ሆኖ አደጋ ለመጣል ምቹ በመሆኑ ያደረገው ምርጫ ብልኀት የጐደለው አልነበረም፤ ይሁን እንጂ ያደረገው ነገር ተመልሶ ለራሱ መጥፊያ ሆነው፤ እግዚአብሔር በኢያሱ ዘመን እንዳደረገው ሁሉ (ኢሱ10፥11-14) አሁንም ለእስራኤላውያን በኀይለኛ ማዕበልና በጐርፍ ሙላት (5፥20-21) ከሰማይ እንደሚዋጋላቸው አሳወቀም ነበር። በዚህ ዘመንም በቂሶን ወንዝ አካባቢ ባለው ሜዳ ላይ በረዶና ውሽንፍር የቀላቀለ ኀይለኛ ዝናብ በመውረዱ፣ በዚያ አቋርጦ ማለፍ የማይሞከር ነበር፤ በ1799 ዓ.ም. በሚያዝያ ወር ከመጠን በላይ የሞላው የቂሶን ወንዝ ናፖሊዮን በቱርክ ሠራዊት ላይ ድል እንዲቀዳጅ አስችሎታል።

4፥9 *ለሴት፤* የባርቅ ፍርሀት (የሌሎቹም የእስራኤል ጦረኞች ፍርሀት) በእግዚአብሔር ላይ ካለመታመን የተነሣ ስለ ሆነ ተግሣጽ ደርሶበታል (የ9፥54 ማብ ይመ)።

4፥11 *ቄናዊው ሔቤር፤* ሔቤር የሚለው ቃል ትርጒም "ማኅበር"፣ ማለት ነው፤ እንዲሁም ቄናዊ ማለት ከብረት ቀጥቃጭ ጐሣዎች የሆነ ማለት ነው። ይህ ከሕዝቡ አንድ ክፍል የሆነው ጐሣ፣ ከሙሴ ዘመን ጀምሮ ከእስራኤል ጋር ተባብሮአል፤ በዚያ ጊዜ ቍጥሩ ከፍተኛ የሆነ 'የብረት ሠረገላ' ተዋጊ ኀይል ከሚያሰባስበው

ዐማች የአባብ ልጆች ከሆኑት ከሌሎቹ ቄና
ውያን ተለይቶ በቃዴስ አጠገብ ጻዕናይም
ከተባለ ቦታ ከሚገኘው ትልቅ ወርካ ጥግ
ድንኳኑን ተክሎ ነበር።
12የአቢኒዔም ልጅ ባርቅ ወደ ታቦር ተራራ
መሄዱን ሲሣራ በሰማ ጊዜ፣ 13ዘጠኝ መቶ
የብረት ሠረገሎችንና ከአረሶት ሐጎይም እስከ
ቂሶን ወንዝ ያለውን ሰራዊቱን በሙሉ
አሰባሰበ።
14በዚህ ጊዜ ዲቦራ ባርቅን፣ "ተነሣ! እግ
ዚአብሔር ሲሣራን በእጅህ አሳልፎ የሰጠ
ባት ቀን ይህች ናት፤ እነሆ እግዚአብሔር
በፊትህ ቀድሞ ወጥቶአል" አላቸው። ስለዚህ
ባርቅ ዐሥር ሺህ ሰዎችን አስከትሎ ከታቦር
ተራራ ወረደ። 15እግዚአብሔር ሲሣራንና
ሠረገሎቹን ሁሉ በባርቅ ፊት በሰይፍ ስለት
እጅግ ተሸንፈው ወደ ኋላ እንዲያፈገፍጉ
አደረገ፤ ሲሣራም ከሠረገላው ወርዶ በእግሩ
ሸሸ፤ 16ባርቅ ግን የሲሣራን ሠረገሎችና ሰራዊቱን
እስከ አረሶት ሐጎይም ድረስ አሳደዳቸው፤
የሲሣራ ሰራዊት በሙሉ በሰይፍ ወደቀ፤
በሕይወት የተረፈ አንድም ሰው አልነበረም።
17በሐጾር ንጉሥ በኢያቢስና በቄናዊው
በሔበር ጐሣ መካከል መልካም ግንኙነት
ስለ ነበር ሲሣራ በእግሩ ሸሽቶ የቄናዊው
የሔቤር ሚስት ወደ ሆነችው ወደ ኢያዔል
ድንኳን ሮጠ።
18ኢያዔልም ወጥታ ሲሣራን ተቀበ
ለችውና፣ "ጌታዬ፤ ወደ ውስጥ ግባ፤ ፈጽሞ
አትፍራ" አለችው፤ ሲሣራም ወደ ድንኳኗ
ገባ፤ እርሷም በልብስ ሸፍና ደበቀችው።
19ሲሣራም፣ "ጠምቶኛልና እባክሽን ውሃ
አጠጪኝ" አላት፤ እርሷም የውተት ጮጮውን
ከፍታ የሚጠጣውን ሰጠችው፤ እንደ ገናም

4፥12 ኢሱ19፥22
4፥13 ቍ7፤ኢ
ሱ17፥16፤መሳ5፥19
4፥14 ዘዳ9፥3፤
መሳ1፥2፤1ሳሙ8፥20
፤2ሳሙ5፥24፤
መዝ68፥7
4፥15 ዘፀ14፥24፤
መዝ18፥14
4፥16 ዘፀ14፥28፤
መዝ83፥9
4፥17 ቍ18:21:
22፤ ዘፍ15፥19፤
ኢሱ11፥1፤
መሳ5፥6:24
4፥18 ቍ17
4፥19 ዘፍ18፥8
4፥21 ቍ17፤
ዘፍ2፥21፤15፥12፤
መሳ5፥26፤1ሳሙ26፥
12፤ኢሳ29፥10፤
ዮና1፥5
4፥22 ቍ17፤
መሳ5፥27
4፥23 ኢሱ11፥1፤
ነህ9፥24፤መዝ18፥47
፤44፥2፤47፥3፤144፥2
4፥24 መዝ83፥9፤
106፥43
5፥1 ዘፀ15፥1፤
መሳ4፥4:6፤
መዝ32፥7
5፥2 ቍ9፤
2ዜና17፥16፤
መዝ110፥3
5፥3 ዘፀ15፥1፤
መዝ27፥6

ሸፈነችው።
20እርሱም፣ "በድንኳኑ በር ላይ ቁሚ፤
ማንም ሰው መጥቶ፣ 'እዚህ ሰው አለ?' ቢልሽ፣
የለም በይ" አላት።
21የሔቤር ሚስት ኢያዔል ግን ሲሣራ
ደክሞ፣ ከባድ እንቅልፍም ወስዶት ሳለ
የድንኳን ካስማና መዶሻ ይዛ በቀስታ ወደ
እርሱ ቀረበች፤ ከዚያም ካስማውን በመዶሻ
ጆሮ ግንዱ ላይ መትታ ከመሬት ጋር ሰፋችው፤
እርሱም ሞተ።
22ባርቅ ሲሣራን በመከታተል ላይ ስለ
ነበር ከዚያ ሲደርስ፣ ኢያዔል ከድንኳኗ
ወጥታ "ና፤ የምትፈልገውን ሰው አሳይሃ
ለሁ" አለችው፤ ስለዚህ ከእርሷ ጋር ወደ
ድንኳንዋ ገባ፤ ሲሣራም በጆሮ ግንዱ ላይ
ካስማ እንደተመታበት ሞቶ ተዘርሮ ነበረ።
23በዚያች ዕለት እግዚአብሔር የከነዓንን
ንጉሥ ኢያቢስን በእስራኤላውያን ፊት እን
ዲሸነፍ አደረገው፤ 24ከነዓናዊውን ንጉሥ
ኢያቢስን እስኪደመስሱ ድረስ የእስራ
ኤላውያን ክንድ እየበረታ ሄደ።

### የዲቦራ መዝሙር

5 በዚያን ዕለት ዲቦራና የአቢኒኤም
ልጅ ባርቅ ይህን ቅኔ ተቀኙ፤
2"በእስራኤል ያሉ መሳፍንት ሲመሩ፣
ሕዝቡም በፈቃዱ ራሱን ሲያስገዛ፣
እግዚአብሔርን አመስግኑ
3"እናንት ነገሥታት ይህን ስሙ፤
ገዦችም አድምጡ፤
ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ፤ ደግሜም
እዘምራለሁ፤[ሀ]

[ሀ]3 ወይም ከምዘምረው ዝማሬ ጋር ተብሎ ሊተረጐም ይችላል

ከከነዓናዊው ንጉሥ ጋር ለመተባበር (ቍ17) ከያቡስ ወደ ሰሜን መምጣቱ የተረጋገጠ እንደ ሆነ የመጽሐፈ መሳፍንት ጸሓፊ ፍንጭ ሰጥቶአል። ስለ ባርቅ ወታደራዊ ዝግጅትና እንስቃሴ ለሲሣራ ወሬ ያቀበለውም ይኸው ሰው እንደ ነበር የሚያጠራጥር አይደለም። *አባብ፤* ዘኍ10፥29 ይመ። *ከሌሎቹ ቄናውያን፤* በነጌብ ከሚገኘው ከቃዴስ በርኔ እምብዛም ሳይርቁ እዚያው በኔጌብ የተቀመጡ ናቸው (1፥16 ይመ)።

4፥14 *እግዚአብሔር በፊትህ ቀድሞ ወጥቶአል፤* እንደ ንጉሥ ሰራዊቱን እየመራ ማለት ነው (1ሳሙ8፥20 ይመ)፤ እንዲሁም በዘፀ15፥3 ላይ "እግዚአብሔር ተዋጊ ነው" የሚለውን ይመ፤ ኢሱ10፥10-11፤ 2ሳሙ5፥24፤ 2ዜና20፥15-17:2-24። *ባርቅ ... ከታቦር ተራራ ወረደ፤* የእግዚአብሔር "መብረቅ" (የቍ6 ማብ ይመ)፣ የከነዓናውያንን ሰራዊት ለማጥቃት ከተራራው ላይ ወረደ።

4፥15 *እንዲያፈገፍጉ አደረገ፤* የቍ7 ማብ ይመ። ግብፃውያን በቀይ ባሕር (ዘፀ 14፥24) ፍልስጥኤማውያን ደግሞ በምጽጳ (1ሳሙ 7፥10) የደረሰባቸውን ፍርሀትና ድንጋጤ ለመግለጽ የገባ የዕብራይስጥ ቃል ነው።

4፥18 *ወደ ድንኳኗ ገባ፤* በጥንት መካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ባህል፣ ከባል ወይም ከወላጅ አባት በስተቀር ማንም ወንድ ወደ አንዲት ሴት ድንኳን መግባት የተለመደ አይደለም፤ ኢያኤል ለሲሣራ የፈቀደችለት መደበቂያ አስተማማኝነቱ የሚያሰጋ አልነበረም።

4፥19 *ጮጮውን፤* ጮጮ ፈሳሽ ነገር የሚቀመጥበት ዕቃ ሲሆን፣ የሚሠራውም ከፍየል ወይም ከበግ ቆዳ ነው። *ወተት፤* የ5፥25 ማብ ይመ። ኢያኤል የሚለው ስምም "የተራራ ፍየል" የሚል ትርጒም አለው፤ እርሷም ለሲሣራ የሚጠጣው ወተት ሰጠችው፤ ይህ ወተት ምናልባት የፍየል ወተት ሊሆን ይችላል (ዘፀ 23፥19፤ ምሳ 27፥27ይመ)።

4፥21 *ካስማውን ... ጆሮ ግንዱ ላይ መትታ፤* በመሠረቱ እንግዳ በትክክል ተስተናገደ የሚባለው፣ አስተናጋጁ እንግዳውን ተቀብሎ ምንም ዐይነት ችግርና ጒዳት እንዳይገጥመው ኀላፊነቱን ሲወጣ ብቻ ነው (19፥23፤ ዘፍ19፥8 ይመ)። ኢያኤል፣ ቤተሰቧ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር አስቀድሞ ያደረገውን ኅብረት በሚገባ በመጠበቅ ባሏ ሆን ብሎ ያፈረሰው ታማኝነት ወደ ቀደመ ቦታው እንዲመለስ አድርጋለች። ምናልባትም ይህች ሴት እስራኤላዊት ላትሆን ትችላለች። ባርቅ በጣም ፈርቶት የነበረውን ሲሣራን ይህቺ ሴት እቤቷ ውስጥ ያለውን ካስማና መዶሻ ብቻ ተጠቅማ ገደለችው።

4፥22 *ሲሣራም...ሞቶ ተዘርሮ ነበረ፤* ከሲሣራ ሞት በኋላ፣ የኢያቢስ መንግሥት እስራኤልን የሚያሰጋ አልሆነም። "ማርና ወተት የምታፈሰውም" ምድር "በንብ" (የቍ4ማብ ይመ) እና በ"ተራራ ፍየል" (የቍ 19 ማብ ይመ) ደፍረትና ታማኝነት ለመዳን በቃች።

*5፥1-31፤* እስራኤላውያን ቅኔ እየተቀኙ በመዝሙር ያገኙትን ድል የማክበር ልማድ ነበራቸው (ዘፀ15፥1-18፤ ዘኍ21፥27-30፤ ዘዳ32፥1-43፤1ሳሙ 8፥7ይመ)። "የእግዚአብሔር የጦርነት መጽሐፍ " (የዘኍ21፥14 ማብ ይመ)፤ እና "የያሻር መጽሐፍ" (የኢሱ 10፥13ማብ ይመ) የተባሉት ምናልባትም እንደነዚህ ያሉት የቅኔ ወይም የመዝሙር ስብስብ ሳይሆኑ አይቀሩም። ይህን ቅኔ ወይንም መዝሙር የጻፈችው ዲቦራ ወይም በዘመኑ የነበረ ሌላ ሰው ሊሆን ይችላል (ቍ7 እና አማራጭ ትርጒሙን ይመ)፤ ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙት ቀደምት ቅኔዎች አንዱ ሲሆን፣ አንዳንድ የዚህ ትረካ መሪ ሐሳቦችን ይዟል (ከዘፀ15፥1-18፤ከ1ሳሙ2፥1-10፤2ሳሙ22፥23፥1-7፤ ከሉቃ 1፥46-55፡ 68-79 ጋር ያነጻጽሩ)፤ በተለይም የእግዚአብሔርን የጽድቅ ሥራና የእርሱን ሰራዊት ተግባር (ቍ11) በሕዝቡ ፊት(ቍ3) ለማወደስ ይጠቀሙበታል። መዝሙሩን በሚከተለው ሁኔታ መክፈል ይቻላል፤ (1) የመዝሙሩ ዐላማ የሆነው ምስጋናና

ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር
 እቀኛለሁ::
“እግዚአብሔር ሆይ፤ ከሴይር በወጣህ ጊዜ፣
 ከኤዶም ምድርም በተነሣህ ጊዜ፣
ምድር ተንቀጠቀጠች፤ ሰማያትም ዝናብ
 አዘነቡ፤
 ደመናዎችም ውሃ አፈሰሱ::
5ተራሮች በሲና አምላክ በእግዚአብሔር ፊት፣
 በእስራኤልም አምላክ በእግዚአብሔር
 ፊት ተናወጡ::
6“በዓናት ልጅ በሰሜጋር ዘመን፣
 በኢያዔል ጊዜ መንገዶች ባድማ ሆኑ፤
 ተጓዦችም በጠመዝማዛ መንገድ ሄዱ::
7ለእስራኤል እናት ሆኜ
 እኔ ዲቦራ እስክነሣ ድረስ
 በእስራኤል ያለው የከተማ ኑሮ አበቃለት፤
8አዳዲስ አማልክትን በተከተሉ ጊዜ፣
 ጦርነት እስከ ከተማው በር መጣ፤
 ጋሻም ሆነ ጦር፣ በአርባ ሺህ እስራ
 ኤላውያን መካከል አልተገኘም::
9ልቤ ከእስራኤል መሳፍንት፣
 ፈቃደኞችም ከሆኑ ሰዎች ጋር ነው፤
 እግዚአብሔር ይመስገን::
10“እናንት በነጫጭ አህዮች የምትጋልቡ፣
 በባለ ግላስ ኮርቻ ላይ የምትቀመጡ፣
በመንገድ ላይ የምትጓዙ፣
 በውሃ ምንጮች ዙሪያ ያለውን፣
11የዝማሬ ድምፅ[m] ስሙ::
 ይህም የእግዚአብሔር የጽድቅ ሥራ፣
ጦረኞቹም በእስራኤል ያደረጉትን
 ያስታውሳል::
“ከዚያም የእግዚአብሔር ሕዝቦች፣
 ወደ ከተማዪቱ[o] በሮች ወረዱ፤
12‘ዲቦራ ሆይ፤ ንቂ፤ ንቂ፤
 ንቂ፤ ንቂ፤ ቅኔም ተቀኚ፤
የአቢኒኤል ልጅ ባራቅ ሆይ፤ ተነሣ፤
 ምርኮኞችህንም ማርከህ ውሰድ’ አሉ::
13የቀሩትም ሰዎች፣
 ወደ መኳንንቱ ወረዱ፤
የእግዚአብሔር ሕዝብ፣
 እንደ ኃያል ጦረኛ ወደ እኔ መጣ::
14መሠረታቸው ከአማሌቅ የሆነ አንዳንዶች
 ከኤፍሬም መጡ፤
ብንያም አንተን ከተከተሉ ሰዎች ጋር ነበር፤
 የጦር አዛዦች ከማኪር፣
 የሥልጣን በትር የያዙም ከዛብሎን
 ወረዱ::
15የይሳኮር መሳፍንት ከዲቦራ ጋር ነበሩ፤
 ይሳኮርም ራሱ ወደ ሸለቆው ከኋላ
 በመከተል፣ ከባርቅ ጋር ነበረ::
 በሮቤል አውራጃዎች፣ ብዙ የልብ
 ምርምር ነበር::
16በበጎች ጒረኖ[n] መካከል ለምን ተቀመጥህ?
 መንጎችን የሚጠራውን ፉጨት ለመስማት
 ነውን? በሮቤል አውራጃዎች፣
 ብዙ የልብ ምርምር ነበር::
17ገለዓድ ከዮርዳኖስ ማዶ ተቀመጠ፤
 ዳን ለምን በመርከብ ውስጥ ዘገየ?
አሴር በጠረፍ ቀረ፤
 በባሕሩ ዳርቻም ተቀመጠ::

5፥4 ዘፀ13፥21፤ ዘኍ24፥18፤ዘዳ33፥2፤ 2ሳሙ22፥8፤መዝ18፥7፤ 68፥8፤77፥17:1፤ 82፥5፤ኢሳ2፥19: 21፤13፥13፤24፥18፤ 64፥3፤ኤር10፥10፤ 50፥46፤51፥29፤ ኢዩ3፥16፤ ናሆ1፥5፤ዕን3፥6
5፥5 ዘፀ19፥18፤ መዝ29፥6፤46፥3፤ 77፥18፤114፥4፤ ኢሳ64፥3
5፥6 ዘሌ26፥22፤ መሳ3፥31፤4፥17፤ መዝ125፥5፤ ኢሳ33፥8፤59፥8
5፥7 መሳ4፥4
5፥8 ቍ 11፤ዘኍ 25፥7፤ዘዳ32፥17፤ ኢሱ2፥5፤መሳ2፥13
5፥9 ቍ 2
5፥10 ዘፍ49፥11፤ መሳ12፥14
5፥11 ቍ 81ሳሙ 12፥7፤ዳን9፥16፤ሚክ6፥5
5፥12 መሳ4፥4:6፤ መዝ44፥23፤57፥8፤ 68፥18፤ ኢሳ51፥9:17፤ ኤፌ4፥8
5፥14 ዘፍ41፥ 52፤50፥23፤ዘኍ34፥ 21፤ መሳ1፥2 9፤3፥13
5፥15 ዘፍ30፥18፤ መሳ4፥4:6
5፥16 ዘፍ49፥14፤ ዘኍ32፥1
5፥17 ኢሱ12፥2፤ 17፥7፤19፥29

[l]7 ወይም *አንቺ* ተብሎ ሊተረጐም ይችላል::
[m]11 ወይም *ቀስተኞች* ተብሎ ሊተረጐም ይችላል::
[o]11 ወይም *ወደ መንደሮቹ* ተብሎ መተርጐም ይቻላል::
[n]16 ወይም *በኮርቻ ላይ* ተብሎ መተርጐም ይቻላል::

በዓሉ የሚከበርበት ምክንያት (ቍ 2-9)፤ (2) እንዳለፈው የጀግንነት ዘመን ሁሉ ዛሬም እስራኤል ጠንክራ በጀግንነት እንድትዋጋ የሚያነሣሣ (ቍ 10-11)፤ (3)ሕዝቡ ለዲቦራ ያቀረበው ልመና (ቍ 11-12)፤ (4)የጀግኖች በኅብረት መሰብሰብ (ቍ 13-18)፤ (5) ጦርነቱ (ቍ 19-23)፤ (6) ኢያኤል ዘዴ ተጠቅማ በሲሣራ ላይ ያገኘችው ድል (ቍ 24-27)፣ (7) የሲሣራ እናት “ልጄ ከአሁን አሁን በድል ይመለሳል” ብላ በጉጉት መጠባበቋን (ቍ 28-30) እና (8) መደምደሚያው (ቍ 31) ናቸው::

***5፥4-5፤*** እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ በምድረ በዳ መርቶ ወደ ከነዓን ባገባቸው ጊዜ፣ በከባድ ደመና ውስጥ በሚያስፈራና በሚያስደነግጥ ግርማ መገለጡን የሚያስታውስ በግጥም የቀረበ ክፍል ነው (ዘዳ33፥2፤ መዝ 68፥7-8፤ ሚክ 1፥3-4 እንዲሁም መዝ 18፥7-15 ይመ)::

5፥4 ***ሴይር፤*** ኤዶም ማለት ነው፤ በተመሳሳይ ሁኔታም በዘዳ 33፥2 ላይ ሴይር ከሲና ጋር ተጠቅሶአል:: ***ሰማያትም ዝናብ አዘነቡ፤*** መዝ 68፥7-10 ይመ::

5፥5 ***በሲና አምላክ፤*** መዝ 68፥8 ይመ:: እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ በተገለጠ ጊዜ፣ ምድር ተንቀጠቀጠች፤ ከባድ መብረቅና ነጎድጓድም ሆነ (ዘፀ19፥16-18)::

5፥6 ***ሰሜጋር፤*** የ3፥31 ማብ ይመ:: ***መንገዶች ባድማ ሆኑ፤*** ከሰፈረው የጠላት ወራሪ ሰራዊት የተነሣ (የ4፥1-2 ማብ ይመ) በመንገድ ላይ መገኘት የሚያስተማምን አልነበረም::

5፥7 ***የከተማ ኑሮ አበቃለት፤*** ነዋሪዎቹ ራሳቸውን ለማዳን ቅጥር ወዳላቸው ከተሞች ሸሽተዋል ማለት ነው::

5፥8 ***ጋሻም...ሆነ...ጦር...አልተገኘም፤*** ይህ የሆነበት ምክንያት አንድም እስራኤላውያን የአገሪቱ ተወላጆች ከሆኑት ከነዓናውያን ጋር ሰላም ስለመሠረቱ (3፥5-6)፣ አሊያም የጦር መሣሪያ እንዳይኖራቸው ስላደረጉ ነው (1ሳሙ13፥19-22)::

5፥10 ***እናንት በነጫጭ አህዮች የምትጋልቡ፤*** መኳንንቱንና ባለጠጎችን በሚመለከት የተነገረ ነው (10፥4፤12፥14ይመ)::

5፥11 ***የዝማሬ ድምፅ፤*** ዘማሪዎች ውሃ ባለበት ቦታ እየተገኙ እግዚአብሔርና የጦር ሰራዊቱ የፈጸሟቸውን ጀግንነት እያስታወሱ፣ የመሪዎቻቸውን መንፈስ ያነቃቁና ያነሣሱ ነበር::

5፥12 ***ንቂ፤*** አንድ ድርጊት እንዲፈጸም ለማነሣሣት የሚቀርብ ልመና ነው (መዝ44፥23፤ኢሳ51፥9ይመ):: ***ምርኮኞችህንም ማርከህ፤*** በመዝሙር 68፥18 ላይ ስለ እግዚአብሔር፣ በኤፌ4፥8 ላይ ደግሞ ስለ ክርስቶስ በሚናገሩት ንባባት ውስጥ ተመሳሳይ ድርጊት ለመግለጽ የገባ ሐረግ ነው::

***5፥13-18፤*** ለጦርነት የተሰባሰቡትን የእግዚአብሔርን ሰራዊት ያመለክታል፤ የመጡትም ነገዶች ኤፍሬም፣ ብንያም፣ ምናሴ (ምናልባት “ማኪር” ከምናሴ ዕጣ ምሥራቁና ምዕራቡ ክፍል ሳይሆን አይቀርም ዘዳ3፥15፤ ኢሱ13፥29-31፤ 17፥1ይመ) ዛብሎን (ቍ 14:18)፣ ይሳኮር (ቍ 15) እንዲሁም ንፍታሌም (ቍ 8) ናቸው:: በተለይም ቈርጠው ወደ ጦርነቱ የገቡትና የሲሣራን የጭካኔ በትር በመጀመሪያ የቀመሱት የነዛብሎንና የንፍታሌም ነገዶች ናቸው (ቍ 18፤ እንዲሁም 4፥10ይመ):: ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ ያሉት ሮቤል (ቍ 15-16) እና ጋድ (እዚህ ስፍራ በቍ 17 ላይ ገለዓድ ተብሎ ተጠቅሶአል) እንዲሁም በጠረፉ ዳርቻ ያሉት ዳንና አሴር (ቍ 17) ለቀረበላቸው ጥሪ ምላሽ ባለመስጠታቸው ተወቅሰዋል:: ይሁዳና ስምዖን ስማቸው አልተነሣም፤ ይህ የሆነበትም ምክንያት ምናልባት ከፍልስጥኤማውያን ጋር ጦርነቱን ቀደም ብለው ጥመው ይሆናል:: ሌዊ በዚህ የእግዚአብሔር ምድራዊ መንግሥት ሥርዐት ውስጥ የውትድርና ግዴታ ስላልነበረበት ስሙ አልተወሣም::

5፥14 ***መሠረታቸው ከአማሌቅ የሆነ፤*** አንዳንድ አማሌቃውያን በአንድ ወቅት በኰረብታማው የኤፍሬም አገር መኖራቸው ይታወቃል (12፥15ይመ):: ***ማኪር፤*** የምናሴ የበኲር ልጅ ነው (ኢሱ 17፥1 ይመ):: የማኪር ዘሮች ምንም እንኳ በዮርዳኖስ ወንዝ ግራና

18የዛብሎን ሰዎች ሕይወታቸውን አሳልፈው
ሰጡ፤
የንፍታሌም ሰዎች እንደዚሁ በምድሪቱ
ኰረብታዎች አደረጉ።
19"ነገሥታት መጡ፤ ተዋጉም፤
የከነዓን ነገሥታት፣ በመጊዶ ውሆች
አጠገብ በታዕናክ ተዋጉ፤
ብርም ሆነ ሌላ ምርኮ ተሸክመው
አልሄዱም።
20ከሰማያት ከዋክብት ተዋጉ፤
በአካሄዳቸውም ሲሣራን ገጠሙት።
21ጥንታዊው ወንዝ፣ የቂሶን ወንዝ፣
የቂሶን ወንዝ ጠርጐ ወሰዳቸው፤
ነፍሴ ሆይ፤ በኀይል ገሥግሺ!
22የፈረሶች ኰቴ ድምፅ በኀይል ተሰማ፤
ጋለቡ፤ በኀይልም ፈጥነው ጋለቡ።
23*የእግዚአብሔር* መልአክ፣ 'ሜሮዝን
ርገሙ፤'
'ሕዝቧንም አብራችሁ ርገሙ፤
ከኀያላን ሰልፍ *እግዚአብሔርን*
ለመርዳት፣
በእግዚአብሔርም ጐን ለመቆም አልመ
ጡምና' አለ።
24'የቄናዊው የሔቤር ሚስት ኢያዔል፣
ከሴቶች ሁሉ የተባረከች ትሁን፤
በድንኳን ከሚኖሩ ሴቶች ሁሉ፣
የተባረከች ትሁን።
25ውሃ ለመነ፤ ወተት ሰጠችው፤
ለመኳንንት በሚገባ ዕቃ፣ እርጎ
አቀረበችለት።
26እጇ ካስማ ያዘ፤
ቀኝ እጇም የሠራተኛ መዶሻ ጨበጠ፤
ሲሣራን መታችው፤ ራሱንም ተረከከችው፤
ክፉኛ ወጋችው፤ ጆሮ ግንዱን በሳችው።
27በእግሯ ሥር ተደፋ፤ ወደቀ፤
በዚያም ተዘረረ፤ በእግሯ ስር ተደፋ፤
ወደቀ፤ በተደፋበት በዚያ ወደቀ፤
ሞተም።
28"የሲሣራ እናት በመስኮት ተመለከተች፤
በዐይነ ርግቡ ቀዳዳም ጮኻ ተጣራች፤
'ለምን ሠረገላው ሳይመጣ ዘገየ?
የሠረገሎቹስ ድምፅ ለምን ጠፋ?' አለች።
29ብልሃተኞች ወይዛዝርቷም መለሱላት፤
እርሷ ግን ለራሷ እንዲህ አለች፤
30'ምርኮ አግኝተው እየተከፋፈሉ፣
እያንዳንዱም ሰው አንዲት ወይም
ሁለት ልጃገረዶች እየወሰደ
አይደለምን?
ይህ ሁሉ ምርኮ፣ በቀለም ያጌጡ ልብሶች
ለሲሣራ ደርሰውት፣
በጌጣጌጥ የተጠለፉ ልብሶች ለዐንገቴ
ይዞልኝ እየመጣ አይደለምን?'
31"*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ጠላቶችህ ሁሉ ይጥፉ፤
አንተን የሚወዱህ ግን፣ የንጋት ፀሓይ
በኀይል እንደሚወጣ እንዲያ ይሁኑ።"
ከዚያም በኋላ ምድሪቱ ለአርባ ዓመት
ሰላም አገኘች።

## ጌዴዎን

6 እንደ ገና እስራኤላውያን *በእግዚአብሔር*
ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸሙ፤ *እግዚአ
ብሔርም* ለምድያማውያን አሳልፎ ሰጣቸው፤

5፥18 ዘፍ30፥8፤20፤መሳ4፥6፤መዝ68፥27
5፥19 ቍ30፤ ኢሱ11፥5፤12፥21፤መሳ4፥13፤ራእ16፥16
5፥20 ኢሱ10፥11
5፥21 መሳ4፥7፤ ኢሱ1፥6
5፥22 ኤር8፥16
5፥24 ዘፍ15፥19፤ መሳ4፥17፤ሉቃ1፥4
25፥25 ዘፍ18፥8
5፥26 መሳ4፥21
5፥27 መሳ4፥22
5፥28 ኢሱ2፥15፤ ምሳ7፥6
5፥30 ቍ19፤ ዘፀ5፥9፤ 1ሳሙ30፥24፤ 2ሳሙ1፥24፤ መዝ45፥14፤68፥12፤ ሕዝ16፥10
5፥31 ዘኍ10፥35፤ መሳ3፥11፤ 2ሳሙ18፥32፤ 23፥4፤ኢዮ37፥21፤ መዝ19፥4፤89፥36፤ ኢሳ18፥4
6፥1 ዘፍ25፥2፤ መሳ2፥11

ቀኝ ቢሰፍሩም (ዘዳ3፥15፤ ኢሱ13፥29-31፤17፥1፤ 1ዜና 7፥14-19 ይመ) እዚህ ላይ የተጠቀሰው ግን ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ ያሉትን የሚያ መለክት ነው (ቍ17፤ኢሱ17፥5 ይመ)።

5፥18 ***በምድሪቱ ኰረብታዎች*** ከዘፍ49፥21 ጋር ሊገናዘብ የሚችል ሳይሆን አይቀርም። ንፍታሌም "ነጻ እንደተለቀቀች ሚዳቋ ነው"።

5፥19 ***መጊዶ፤*** መጊዶና ታዕናክ ከሳሮን ሜዳ እስከ ኢይዝራ ኤል ሸለቆ ባለው በተራራማው አገር አቋርጦ ወደ ሰሜን ምሥራቅ የሚዘልቀውን ዋና መተላለፊያ የሚቈጣጠሩ ቦታዎች ናቸው። "የመጊዶ ሜዳ" ቍልፍ ቦታ ከመሆኑ የተነሣ (2ዜና 35፥22) ከጥንት ጀምሮ በተደጋጋሚ ጦርነት የተካሄደበት ስፍራ ነው። ግልሳዊ ቱትምስ የተባለው ፈርዖን፣ የተባበረውን የከነዓንን ሰራዊት በ1468 ዓ.ቅ..ክ በዚሁ ቦታ ጦርነት ገጥሞ ድል አድርጎታል። እንዲሁም በ1917 ዓ.ም ታላቋ ብሪታንያ በጄኔራል አለንቢ መሪነት በመጊዶ ትይዩ ባለው በኢይዝራኤል ሸለቆ ከቱርክ ጋር ጦርነት ገጥማ ድል በማድረግ፣ በፓሌስቲና ምድር ተንሰራፍቶ የነበረው የቱርክ አገዛዝ እንዲያከትም አድርጋለች። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ እንደሚገኘው፣ የእስራኤል ሰራዊት በዲቦራና በባርቅ መሪነት የከነዓናውያንን ቅስም የሰበሩት፣ በመጊዶ "...ውሆች አጠገብ ነው" (ቍ19)፤ እንዲሁም መልካሙ የይሁዳ ንጉሥ ኢዮስያስ በ609 ዓ.ቅ.ክ ከዳግማዊ ፈርዖን ኒካው ጋር ጦርነት ገጥሞ በዚሁ ስፍራ ሞቶአል (2ነገ 23፥29)። ደግሞም በራእ 16፥16 ላይ፣ "በዕብራይስጥ አርማጌዶን ተብሎ ስለሚጠራው ስፍራ የተጠቀሰውን ይመ። አርማጌዶን ማለት "የመጊዶን ተራራ" ማለት ሲሆን፣ ይህም ሁሉን ማድረግ በሚችል በእግዚአብሔር ታላቅ ቀን የሚሆነው ጦርነት የሚካሄድበት ሥፍራ ነው (ራእ 16፥14)።

5፥20 ***ከዋክብት ተዋጉ፤*** የሰማይ ኀይላት እስራኤልን ረድተው መዋጋታቸውን ለማመልከት በግጥም መልክ የቀረበ አባባል ነው (የ4፥7 ማብ ይመ)።

5፥21 ***ጠርጐ ወሰዳቸው፤*** የ4፥7 ማብ ይመ።

5፥23 ***ሜሮዝን፤*** ይህች በንፍታሌም የምትገኝ የእስራኤል ከተማ የእግዚአብሔርን ሰራዊት ለመርዳት ስላልፈለገች ተረገመች፤ እንዲሁም ሌሎች ከተሞች በእግዚአብሔር ጦርነት ተካፋይ መሆን ስላልፈለጉ ከባድ ቅጣት ደርሶባቸዋል (8፥15-17፤ 21፥5-10 ይመ)።

5፥25 ***እርጎ፤*** በጮጮ ውስጥ ቀድሞ በነበረው ጥቂት እርጎ ላይ ወተት ጨምሮ በመናጥ የረጋ ነው።

*5፥28፤* በዚህ ሥዕላዊ ገለጻ፣ የሲሣራን እናት ጭንቀት አጕልቶ የሚያሳየው ኢያዔል በከነዓናዊው ኀያል ጀኔራል ላይ የተቀዳጀውን ድል ሲሆን፣ በእስራኤል ያለችው እናት ዲቦራ (ቍ7) ድል በከነዓን ካለችው እናት ጋር የሚነጻጸር ነው።

*5፥31፤* አሁን የተገኘው ድል ወደ ፊትም ከእግዚብሔር ጠላቶች ጋር ለሚደረጉት ጦርነቶች (ዘኍ10፥35፤ መዝ 68፥1-2 ይመ) ምሳሌ ነው፤ መዝሙሩም እዚህ ላይ በጸሎት ይደመድማል። ***ጠላቶችህ ... የሚወዱህ ግን፤*** እግዚአብሔርን ከማምለክ አንጻር ሁለት የተለያየ መሠረታዊ አመለካከት ያላቸውን ሕዝቦች ያሳያል። እግዚአብሔር የኪዳን አምላካቸውና ንጉሣቸው በመሆኑ እንዲወዱት ይፈልጋል (ዘፀ20፥6 ይመ)፤ ይህም በጥንት የመካከለኛ ምሥራቅ አገሮች የነበሩ ነገሥታት የሚገዟቸውን ሕዝቦች ፍቅር ይፈልጉ እንደ ነበር ነው። ***አርባ ዓመት፤*** የአንድን ትውልድ ዘመን የሚያመለክት የተለመደ አባባል ነው።

*6፥1-9፥57፤* የጌዴዎንና የአቤሜሌክ ታሪክ ሲሆን፣ በዲቦራና በዮፍታሔ ታሪክ ታጥሮአል የዲቦራና የዮፍታሔም ታሪክ ደግሞ በብንያማዊው በናዖድና የዳን ወገን በሆነው በሶምሶን ታሪክ ታጥሮአል።

6፥1 ***ለምድያማውያን፤*** የዘፍ37፥25፤ የዘፀ2፥15 ማብ ይመ። ምድያማውያን፣ እስራኤልን ለመውጋት ቍጥራቸው አነስተኛ በመሆኑ፣ ከሞዓባውያንና በዙሪያቸው ከሚኖሩ ሌሎች ሕዝቦች ጋር (ዘኍ2፥4-6፤ 25፥6-18) እንዲሁም በስተ ምሥራቅ በኩል ከሚገኙት ከአማሌቃውያንና ሌሎች ነገዶች ጋር ግምባር ይፈጥሩ ነበር (ቍ3)፤ ሽንፈታቸውም በዕብራውያን ዘንድ ለብዙ ጊዜ ሲታወስ ቈይቶአል (መዝ 83፥9፤ ኢሳ9፥4፤ 10፥26፤ ዕብ 3፥7 ይመ)።

እነርሱም ሰባት ዓመት ገዟቸው:: [2]እስራኤላ
ውያን የምድያማውያን ኀይል ስለበረታባቸው
በየዋሻውና በየምሽጉ፣ በየተራራው ጥግ መሸሸ
ጊያ ስፍራ አበጁ:: [3]እስራኤላውያን ዘር በሚ
ዘሩበት ጊዜ ሁሉ ምድያማውያን፣ አማሌቃ
ውያንና ሌሎች የምሥራቅ ሕዝቦች መጥተው
አገሩን ይወሩ ነበር:: [4]እነርሱም በምድሪቱ ላይ
ሰፍረው እስከ ጋዛ ያለውን ሰብል በማጥፋት
አንዳችም የእህል ዘር አያስተርፉም፣ የበግም
ሆነ የከብት ወይም የአህያ መንጋ አይተዉም
ነበር:: [5]ከብቶቻቸውንና ድንኳኖቻቸውን ይዘው
ሲመጡ ልክ የአንበጣ መንጋ ይመስሉ ነበር፤
ሰዎቹንም ሆነ ግመሎቻቸውን ለመቍጠር አዳ
ጋች ሲሆን፣ የሚመጡትም ምድሪቱን ለማጥ
ፋት ነበር:: [6]ምድያማውያን እስራኤላው
ያንን ችግር ላይ ስለጣሏቸው፣ ይረዳቸው
ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ::
[7]ከምድያማውያን ጥቃት የተነሣ እስራ
ኤላውያን ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፤ [8]እግዚ
አብሔር አንድ ነቢይ ላከላቸው፤ እርሱም
እንዲህ አለ፤ "የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤ ከባርነት ቤት ከግብፅ ምድር
ያወጣኋችሁ እኔ ነኝ:: [9]ከግብፃውያን እጅ
ታደግኋችሁ፤ ከሚያስጨንቋችሁ ሁሉ አዳን
ኋችሁ፤ እነርሱንም ከፊታችሁ አሳድጄ አስ
ወጣኋቸው፤ ምድራቸውንም ሰጠኋችሁ::
[10]እናንተንም፣ 'እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ
ነኝ፤ በምድራቸው ላይ የምትኖሩባቸው የአ
ሞራውያንን አማልክት አታምልኩ' አልኋችሁ፤
እናንተ ግን አላዳመጣችሁኝም::"
[11]የእግዚአብሔር መልአክ ዖፍራ ወደ
ምትባል መንደር መጥቶ፣ በአቢዔዝራዊው
በኢዮአስ ዕርሻ ውስጥ በሚገኝ በአንድ የባ
ሉጥ ዛፍ ሥር ተቀመጠ፤ የኢዮአስም ልጅ
ጌዴዎን፣ ምድያማውያን እንዳያዩበት ደብቆ
በወይን መጭመቂያው ስፍራ ስንዴውን ይወቃ
ነበር:: [12]የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጦ፣
"አንተ ኀያል ጦረኛ! እነሆ፤ እግዚአብሔር
ከአንተ ጋር ነው" አለው::
[13]ጌዴዎን መልሰ፣ "ጌታዬ ሆይ፤ እግዚ

6፥2 1ሳሙ 13፥6፤ ኢዮ 24፥8፤ኢሳ 2፥19፤5፥30፤8፥21፤26፥16፤37፥3፤ኤር 41፥9፤48፥28፤49፥8:30፤ዕብ 11፥38
6፥3 ዘፍ 25፥6፤ ዘኍ 13፥29፤ኢሳ 11፥14፤ ኤር 49፥28
6፥4 ዘፍ 10፥19፤ ዘሌ 26፥16፤ዘዳ 28፥30:51፤ኢሳ 10፥6፤ 39፥6፤ 42፥22
6፥5 ዘዳ 28፥42፤ መሳ 8፥10፤ኢሳ 21፥7፤ 60፥6፤ኤር 49፥32
6፥6 መሳ 3፥9
6፥7 መሳ 3፥9
6፥8 ዘዳ 18፥15፤ ኢሱ 24፥17፤መሳ 2፥1፤1ነገ 20፥13፡22፤2ነገ 17፥13፡23፤ነህ 9፥29፤ኢዮ 36፥10፤ ኤር 25፥5፤ሕዝ 18፥30-31
6፥9 ዘኍ 10፥9፤ መዝ 44፥2፤136፥24
6፥10 ዘፀ 20፥5፤ ኢሱ 24፥15
6፥11 ቊ 29፤ ዘፍ 16፥7፤ዘኍ 26፥30፤ ኢሱ 18፥23፤ መሳ 7፥1፡14፤8፥1፡13:29፤ሩት 2፥17፤3፥2፤ 1ሳሙ 23፥1፤ዜና 21፥20፤ ነህ 13፥15፤ኢሳ 16፥10፤ 63፥3፤ ሰቆ 1፥15፤ ኢል 3፥13፤ዕብ 11፥32
6፥12 ሉ 1፥5፤ መሳ 11፥1፤ሩት 2፥4፤ 1ሳሙ 10፥7፤ መዝ 129፥8
6፥13 ዘዳ 31፥17፤ ኢሱ 3፥5፤ 2ሳሙ 7፥22፤መዝ 44፥1፤ 78፥3
6፥14 ቊ 36፤ መሳ 10፥1፤2ነገ 14፥27፤ዕብ 11፥34
6፥15 1ሳሙ 9፥21፤ኢሳ 60፥22

አብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ይህ ሁሉ እንዴት
ሊደርስብን ቻለ? 'እግዚአብሔር ከግብፅ ምድር
አውጥቶናል' በማለት አባቶቻችን የነገሩን
ታምራት የት አለ? አሁን ግን እግዚአብሔር
ትቶናል፤ በምድያማውያንም እጅ አሳልፎ
ሰጥቶናል" አለው::
[14]በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ወደ እርሱ
ዞወር ብሎ፣ "ሂድ፤ ባለህ ኀይል እስራኤላ
ውያንን ከምድያማውያን እጅ ነጻ እንድታወጣ
የምልክህ እኔ አይደለሁምን? አለው"::
[15]ጌዴዎንም፣ "ጌታ ሆይ፤ የእኔ ጐሣ ከም
ናሴ ነገድ እጅግ ደካማ ነው፤ ከቤተ ሰቤም
እኔ የመጨረሻ ነኝ፤ ታዲያ እንዴት እኔ እስ
ራኤልን ላድን እችላለሁ?" አለ::
[16]እግዚአብሔርም፣ "በእርግጥ እኔ ከአንተ
ጋር እሆናለሁ፤ ምድያማውያንንም እንደ አንድ
ሰው አድርገህ ትመታቸዋለህ" አለው::
[17]ጌድዎን እንዲህ ብሎ መለሰ፤ "አሁን
በፊትህ ሞገስ አግኝቼ ከሆነ፣ በእርግጥ የም
ታነጋግረኝ አንተ ራስህ ለመሆንህ ምል
ክት ስጠኝ፤ [18]ተመልሼ እስክመጣ፣ መሥዋዕ
ቴንም አምጥቼ በፊትህ እስካቀርብ ድረስ
እባክህ አትሂድ::"
እግዚአብሔርም፣ "እስክትመለስ እጠብቅ
ሃለሁ" አለው::
[19]ጌዴዎን ወደ ቤቱ ሄደ፤ የፍየል ጠቦ
ትም ዐረደ፤ አንድ ኢፍ መስፈሪያ* ዱቄት
ወስዶ ዕርሾ ያልገባበት ቂጣ ጋገረ:: ሥጋ
ውን በቅርጫት፣ መረቁን በምንቸት ይዞ
በመምጣት፣ በወርካው ሥር ለተቀመጠው
አቀረበለት::
[20]የእግዚአብሔር መልአክ፣ "ሥጋውንና ዕርሾ
ያልገባበትን ቂጣ ወስደህ በዚያ ዐለት ላይ
አኑር፤ መረቁንም በሥጋውና በቂጣው ላይ
አፍስስ" አለው፤ ጌዴዎንም እንደ ታዘዘው

*19.22 ሊትር ያህል ነው::

6፥16 ዘፀ 3፥12፤ ዘኍ 14፥43፤ኢሱ 1፥5 6፥17 ቊ 36-37፤ ዘፍ 24፥14፤ዘፀ 3፥12፤ 4፥8 6፥19 ዘፍ 18፥7-8፤ ዘሌ 19፥36፤ መሳ 13፥15 6፥20 መሳ 13፥19

6፥3 **አማሌቃውያንና፤** የዘፍ14፥7 ማብ ይመ:: በእርግጥ እነዚህ ሰዎች የኔጌብ ነዋሪዎች ናቸው፤ ነገር ግን ከሞዓብና ከአሞን ምሥራቅ በሚገኘው ምድረ በዳ ከሚኖሩ ዘላኖች ይኸውም ምድያማውያን ከሌሎች የምሥራቅ ሕዝቦች ጋር ግምባር ሲፈጥሩ ይታያሉ::

6፥5 **ልክ የአንበጣ መንጋ፤** ከዳር እስከ ዳር በምድሪቱ ላይ ተሰማርቶ ዝርፊያ በማካሄድ ምድሪቱን ባዶ ያስቀራትን ሰራዊት የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ ነው (7፥12፤ዘፀ 10፥13-15፤ኢዮ1፥4 ይመ):: **ግመሎቻቸውን፤** እነዚህ ግመሎች በጦርነት ጊዜ አገልግሎት እንደ ሰጡ በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው እዚህ ላይ ነው::

6፥7 **ወደ እግዚአብሔር በጮኹ ጊዜ፤** እስራኤላውያን በመሳፍንት አገዛዝ ሥር ሆነው ሳሉ ጭንቅና መከራ ሲበዛባቸው በተደጋጋሚ ወደ እግዚአብሔር የሚያሰሙትን ጩኸት ያመለክታል (ከመግቢያው "ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያት" የሚለውን ይመ) ::

6፥8 **ነቢይ፤** የ2፥1፤ 10፥11 ማብ ይመ:: ከግብጽ ባርነት አውጥቶ ቃል የገባላቸውን ምድር የሰጣቸውን እግዚአብሔርን ስለረሱ አንድ በስም ያልተጠቀሰ ነቢይ ወቀሳቸው (ቊ9-10)::

6፥10 **አሞራውያን፤** ምናልባትም በከነዓን የሚኖሩትን ሁሉ የሚያካትት ሳይሆን አይቀርም (ዘፍ10፥16 ማብ ይመ)::

6፥11 **የእግዚአብሔር መልአክ፤** የዘፍ16፥7 ማብ ይመ:: **ዖፍራ፤** የብንያማውያን ዖፍራ አይደለም (ኢሱ18፥23):: **አቢዔዝራዊው፤** አቢዔዝራውያን (ቊ24) የምናሴ ወገን ነበሩ (ኢሱ17፥2):: **በወይን መጭመቂያው ስፍራ ስንዴውን ይወቃ ነበር፤** ጌዴዎን በተለመደው ዐውድማ ላይ ከመውቃት ይልቅ (የሩት 1፥22 ማብ ይመ) ማንም ሊደርስበት በማይችል ስውርና አስተማማኝ በሆነ ቦታ መውቃትን መረጠ::

6፥12 **ኀያል ጦረኛ፤** በቊ15 ላይ ጌዴዎን ስለ ራሱ ዝቅተኛነት ቢናገርም፣ ከገዥው ወገን መሆኑ በግልጽ ይታወቃል፤ (ቊ27 ይመ)::

6፥14 **እግዚአብሔር...ዞወር ብሎ፤** ቊ22፥23 ይመ:: (ቊ11) በዚህ ስፍራ የታየው የእግዚአብሔር መልአክ የመለኮት መገለጥ (ግህደተ አምላክ) ምሳሌ ሳይሆን አይቀርም:: **ሂድ... የምልክህ እኔ አይደለሁምን?** ጌዴዎን እንደ ሙሴ ሁሉ (ዘፀ3፥7-10) እስራኤልን ከጠላት እጅ እንዲታደግ ኀላፊነት ተሰጠው::

6፥15 **እንዴት እኔ፤** አብዛኛውን ጊዜ እግዚአብሔር ፈቃዱን እንዲፈጽሙ የሚጠራቸው ከኀይለኞች ይልቅ ደካሞችን ነው (የዘፍ 25፥23፤ የ1ሳሙ 9፥21 ማብ ይመ)::

6፥17 **ምልክት ስጠኝ፤** ቊ36-40ይመ:: ሙሴ በሚያደርገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደሚሆን እግዚአብሔር ከሰጠው ምልክቶች ጋር ያነጻጽሩ (ዘፀ3፥12፤ 4፥1-17)::

አደረገ:: 21መልአኩም በያዘው በትር ጫፍ
ሥጋውንና ቂጣውን ነካ፤ ከዐለቱም እሳት
ወጥቶ ሥጋውንና ቂጣውን በላ፤ ከዚያም
የእግዚአብሔር መልአክ ተሰወረ:: 22ጌዴዎን
ያየው የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑን ባወቀ
ጊዜ፣ "ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፤ የእግዚ
አብሔርን መልአክ ፊት ለፊት አይቻለሁና
ወዮልኝ" አለ::
23እግዚአብሔርም፣ "ሰላም ለአንተ
ይሁን፤ አትፍራ፤ አትሞትም" አለው::
24ጌዴዎንም በዚያ ለእግዚአብሔር መሠዊያ
ሠራ፤ ስሙንም "እግዚአብሔር ሰላም ነው"
ብሎ ጠራው፤ ይህ መሠዊያ የአቢዔዝራውያን
ይዞታ በሆነው በዖፍራ ዛሬም ቆሞ ይታያል::
25በዚያች ሌሊት እግዚአብሔር ጌዴዎንን
እንዲህ አለው፤ "ከአባትህ መንጋ ሰባት
ዓመት የሆነውን ሁለተኛውን ወይፈን
ውሰድ፤ አባትህ ለበኣል የሠራውን መሠዊያ
አፍርስ፤ በአጠገቡ የአሼራን ዐምድ[ጸ] ሰባ
ብረህ ጣል:: 26በዚህ ፍርስራሽ ጉብታ ላይ
ስስምባክህ ለእግዚአብሔር የሚገባውን መሠ
ዊያ[ፀ] ሥራ:: ሰባብረህ በጣልኸው የአሼራ
ምስል ዓምድ ሁለተኛውን[ገ] ወይፈን ወስደህ
የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገህ አቅርበው::"
27ጌዴዎን ከአገልጋዮቹ ዐሥር ሰዎች
ወስዶ እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ፤
ቤተ ሰቡንና የከተማውን ሰው ስለ ፈራ ይህን
ያደረገው ቀን ሳይሆን ሌሊት ነበር::
28ሌሊቱ ነግቶ የከተማው ሕዝብ ከመ
ኝታው ሲነሣ፣ የበኣል መሠዊያ ፈርሶ
በአጠገቡ የቆመው የአሼራ ምስል ተሰባ
ብሮ፣ አዲስ በተሠራው መሠዊያ ላይ ሁለ
ተኛው ወይፈን ተሠውቶ ነበር::
29እነርሱም፣ "ይህን ያደረገ ማን ነው?"
በማለት እርስ በርሳቸው ተጠያየቁ::
ነገሩን በጥብቅ ሲከታተሉም፣ "የኢዮአስ
ልጅ ጌዴዎን መሆኑን ደረሱበት::"
30የከተማዪቱም ሰዎች ኢዮአስን፣ "የባ
ኣልን መሠዊያ ያፈረሰና በአጠገቡ የቆመውን
የአሼራን ምስል ዐምድ የሰበረው ልጅህ
በመሆኑ መሞት ስላለበት አውጣልን አሉት"::
31በዚህ ጊዜ ኢዮአስ በቍጣ ለገነፈለውና
በዙሪያው ለነበረው ሕዝብ እንዲህ አለ፤
"ለበኣል ትሟገቱለታላችሁን? ልታድኑትስ
ትሞክራላችሁን? ለእርሱ የሚሟገትለት ቢኖር
እስከ ጠዋት ይሙት! እንግዲህ በኣል በእ
ርግጥ አምላክ ከሆነ መሠዊያውን ሲያፈ
ርሱበት ራሱን ሊከላከል ይችላል::" 32ስለ
ዚህም፣ "መሠዊያውን አፍርሶበታልና ራሱ
በኣል ይሟገተው" ሲሉ በዚያ ዕለት ጌዴዎንን፣
"ይሩበኣል"[ጠ] ብለው ጠሩት::
33በዚህ ጊዜ ምድያማውያን ሁሉ፣ አማ
ሌቃውያንና ሌሎች የምሥራቅ ሕዝቦች
ኀይላቸውን አስተባብረው የዮርዳኖስን ወንዝ
በመሻገር በኢይዝራኤል ሸለቆ ሰፈሩ:: 34ከዚ
ያም የእግዚአብሔር መንፈስ በጌዴዎን ላይ
ወረደ፤ እርሱም መለከት ነፋ፤ አቢዔዝራ
ውያን እንዲከተሉት ጠራቸው:: 35እንዲ
ሁም በመላው የምናሴ ምድር መልእክተ
ኞቹን ልኮ እንዲከተሉት ጥሪ አደረገ፤ ደግሞም
የአሴር፣ የዛብሎንና የንፍታሌም ሰዎች ወጥ
ተው እንዲገጥሟቸው መልእክተኛ ላከባቸው::
36ጌዴዎን እግዚአብሔርን እንዲህ አለው፤
"በተናገርኸው መሠረት እስራኤላውያንን በእጄ
የምታድናቸው ከሆነ፣ 37እነሆ፤ የበግ ጠጕር
ባዘቶ በዐውድማው ላይ አኖራለሁ:: ምድሩ
በሙሉ ደረቅ ሆኖ ባዝቶው ላይ ብቻ ጤዛ
ቢኖር፣ እንዳልኸው እስራኤላውያንን በእኔ
እጅ እንደምታድናቸው ዐውቃለሁ::" 38እን
ደዚሁ ሆነ፤ ጌዴዎን በማግስቱ ጠዋት ማልዶ
ተነሣ፤ ባዘቶውንም ሲጨምቅ የወጣው ውሃ
አንድ ቈሬ ሞላ::
39ከዚያም ጌዴዎን እግዚአብሔርን እንዲህ
አለው፤ "እባክህ አትቈጣኝ፤ አንዲት ጥያቄ
እንደ ገና ልጠይቅ:: በጠጕሩ ባዘቶ ላይ ሌላ
ሙከራ እንዳደርግ ፍቀድልኝ፤ በዚህ ጊዜ
ምድሩ ሁሉ በጤዛ ተሸፍኖ ባዘቶው ደረቅ
ይሁን::" 40በዚያች ሌሊት እግዚአብሔር እንደ
ተጠየቀው አደረገ፤ ምድሩ በሙሉ በጤዛ
ሲሸፈን፣ ባዘቶው ብቻ ደረቅ ሆነ::

6፥21 ዘፀ4፥2፤ ዘሌ9፥24
6፥22 ዘፍ32፥30፤ መሳ13፥16፡21፡22
6፥23 ዘፍ16፥13፤ ዘዳ5፥26፤ዳን10፥19
6፥24 ዘፍ22፥14፤ ኢሱ18፥23
6፥25 ቍ26፡ 28፡30፤ዘፀ34፥13፤ መሳ2፥13
6፥26 ዘፍ8፥20
6፥28 ቍ30፤ 1ነገ16፥32፤ 2ነገ21፥3
6፥29 ቍ11
6፥30 ቍ28
6፥31 ሳሙ24፥15፤ መዝ43፥1፤ ኤር30፥13
6፥32 መሳ7፥1፤ 8፥29፡35፤9፥1፤ 1ሳሙ12፥11
6፥33 ዘፍ25፥6፤ ዘኍ13፥29፤ ኢሱ15፥56፤ ሕዝ25፥4፤ሆሴ1፥5
6፥34 ኢሱ6፥20፤ 17፥2፤መሳ3፥10፡27
6፥35 ኢሱ17፥7፤ መሳ4፥6፤7፥23
6፥36 ቍ14
6፥37 ዘፍ24፥14፤ ዘኍ18፥27፤2ሳሙ6፥6፤24፥16፤ ኢዮ31፥20
6፥39 ዘፍ18፥32
6፥40 ዘፀ4፥3-7፤ ኢሳ38፥7

[ሠ]25 ወይም፣ *ከአባትህ መንጋ በደንብ ያደገውን ኮርማ ውሰድ*
[ጸ]25 በዚህም ሆነ በመጽሐፉ ክፍሎች ሁሉ የአሼራን ምስል ጣዖት የሚያመለክት ነው::
[ፀ]26 ወይም፣ *የድንጋይ ካብ*
[ገ]26 ወይም፣ *የደረሰ*
[ጠ]32 *ይሩበኣል ማለት በኣል ይጋፈጠው ማለት ነው::*

6፥21 ***ሥጋውን ... በላ፤*** ይህ የሚያሳየው የጌዴዎን መሥዋ
ዕት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱን ነው (ዘሌ 9፥24
ይመ)::

6፥23 ***አትሞትም***፤13፥22እንዲሁም የዘፍ16፥13፤32፥30 ማብ ይመ::

6፥25 ***በኣል፤*** የ2፥13 ማብ ይመ:: ***የአሼራን ዐምድ*** እንስት
ጣዖት ናት የ2፥13፤ የዘፀ 34፥13 ማብ ይመ:: ***መሠዊያ አፍርስ፤***
የእግዚአብሔር ታዛዥ ጠረኛ እንደ መሆኑ የጌዴዎን ቀዳሚ ተግ
ባር ለበኣል የቆመውን መሠዊያ ማፍረስ ነበር፤ እስራኤላውያንም
እንዲሁ ያደርጉ ዘንድ ትእዛዝ ተሰጥቶአቸው ነበር (2፥2፤ዘፀ
34፥13፤ ዘዳ7፥5 ይመ)::

6፥26 ***የሚገባውን መሠዊያ፤*** ዘፀ20፥25 ይመ::

6፥30 ***መሞት ስላለበት፤*** እስራኤላውያን የገዛ ወገናቸውን
ለመግደል ቈርጠው እስከሚነሡ ድረስ በበኣል አምልኮ ልባቸው
ክፉኛ ተይዞ ነበር፤ ጣዖት አምላኪዎች በድንጋይ ተወግረው እንዲ
ሞቱ እግዚአብሔር ሙሴን ካዘዘበት ከዘፀ13፥6-10 ጋር ያነጻጽሩ::

6፥32 ***ይሩበኣል፤*** ትርጕሙ ራሱ በኣል ይሟገተው ማለት ነው::

6፥33 ***በኢይዝራኤል ሸለቆ፤*** የ5፥19 ማብ ይመ::

6፥34 ***መንፈስ... ወረደ፤*** ቃል በቃል ሲተረጐም "ጌዴዎን
መንፈስን ለበሰ" ማለት ነው:: ይህ ዘይቤያዊ አባባል ተጠቅሶ
የምናገኘው ሦስት ጊዜ ብቻ ነው (እዚህ፣ ላይ1ዜና 12፥18፤2ዜና
24፥20):: ይህም የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረበት ሰው ኀይል
እንደሚሰጠውና ካለው ኀይል ሥራ እንደሚሠራ ያሳያል (የ3፥10
ማብ ይመ)::

6፥35 ***ምናሴ፤*** ምዕራቡን የምናሴ ድርሻ ማለት ነው:: ***አሴር፤***
ይህ ነገድ ቀደም ብሎ ለጦርነቱ የተደረገለትን ጥሪ ሳይቀበል ቀርቶ
ነበር (5፥17)::

6፥39 ***አንዲት ጥያቄ እንደ ገና ልጠይቅ፤*** በዘፍ 18፥32
ላይ አብርሃም ከተናገረው ጋር ያነጻጽሩ::

*7፥1-8፤* የእስራኤልን ሰራዊት በራሱ ሥልጣንና ኀይል
የሚመራው እግዚአብሔር በመሆኑ ፣ድል የሚገኘው በእነርሱ ኀይል
ሳይሆን በእርሱ ኀይል መሆኑን እንዲያውቁ ስለ ፈለገ የዘማቹን
ሰራዊት ቍጥር ቀነሰ::

## ጌዴዎን ምድያማውያንን ድል አደረገ

**7** ይሩባኣል የተባለው ጌዴዎን፣ ከእርሱም ጋር የነበሩት ሰዎች ሁሉ በጠዋት ተነ
ሥተው በሐሮድ ምንጭ አጠገብ ሰፈሩ።
የምድያማውያንም ሰፈር እስራኤላውያን ከሰ
ፈሩበት በስተ ሰሜን በኩል፣ በሞሬ ኮረ
ብታ አጠገብ በሸለቆው ውስጥ ነበር። [2]እግ
ዚአብሔር ጌዴዎንን እንዲህ አለው፤ ‘ምድ
ያማውያንን በእጃቸው አሳልፌ እንዳልሰጥ
አብረውህ ያሉት ሰዎች በጣም ብዙ ናቸው፤
እስራኤላውያን የገዛ ኀይላቸው እንዳዳናቸው
በመቍጠር እንዳይታበዩብኝ፣ [3]‘ማንም የፈራ
ቢኖር የገለዓድን ተራራ ትቶ ወደ መጣበት
ይመለስ’ ብለህ ለሕዝቡ ዐውጅ።” ስለዚህ
ሃያ ሁለቱ ሺህ ሲመለሱ ዐሥሩ ሺህ ብቻ
ቀሩ።

[4]እግዚአብሔር ጌዴዎንን እንዲህ አለው፤
“አሁንም ሰዎቹ ብዙ ናቸው፤ ወደ ወንዝ
ይዘሃቸው ውረድ፤ በዚያም እለይልሃለሁ።
‘ይህ ከአንተ ጋር ይሂድ’ የምለው፣ ከአንተ
ጋር ይሄዳል፤ ነገር ግን፣ ‘ይህ ከአንተ ጋር
አይሂድ’ የምለው፣ ከአንተ ጋር አይሄድም”።

[5]ስለዚህ ጌዴዎን ሰዎቹን ወደ ወንዝ
ይዞአቸው ወረደ፤ እዚያም እግዚአብሔር፣
“ውሻ በምላሱ እየጨለፈ እንደሚጠጣ ሁሉ፣
በምላሳቸው የሚጠጡትን፣ በጕልበታቸው
ተንበርክከው ከሚጠጡት ለይ” አለው።
[6]ሦስት መቶ ሰዎች ውሃውን በእጃቸው እያ
ፈሱ ጠጡ፤ የቀሩት ሁሉ ግን ለመጠጣት
በጕልበታቸው ተንበረከኩ።

[7]እግዚአብሔርም ጌዴዎንን፣ “ውሃውን
በእጃቸው እያፈሱ በጠጡት ሦስት መቶ
ሰዎች አድናችኋለሁ፤ ምድያማውያንንም
በእጃችሁ አሳልፌ እሰጣችኋለሁ፤ የቀሩት
በሙሉ ወደየመጡበት ይመለሱ” አለው።
[8]ጌዴዎንም የቀሩትን እስራኤላውያን በሙሉ
ወደየድንኳናቸው እንዲመለሱ አደረገ፤ ሦስት
መቶውን ግን አስቀራቸው፤ እነርሱም የሚ
መለሱትን ሰዎች ስንቅና መለከት ወሰዱ።

በዚህ ጊዜ የምድያማውያኑ ሰፈር ከእነ
ርሱ በታች በሸለቆአማው ውስጥ ነበር።
[9]በዚያች ሌሊት እግዚአብሔር ጌዴዎንን
እንዲህ አለው፤ “ተነሥ፤ በሰፈሩም ላይ ውረድ፤

7፥1 ዘፍ12፥6፤ 25፥2፤መሳ6፥11:32 ፤2ሳሙ23፥25
7፥2 ዘዳ8፥17፤ 2ቆሮ4፥7
7፥3 ዘዳ20፥8፤ ኢሱ12፥2
7፥4 1ሳሙ14፥6
7፥6 ዘፍ14፥14
7፥7 ኢሱ8፥7፤ 1ሳሙ14፥6
7፥9 ቍ13-15፤ ኢሱ2፥24፤መሳ1፥2

7፥1 *ሐሮድ፤* የዚህ ቃል ትርጕም “መንቀጥቀጥ” ማለት ነው፤ የሚያመለክተው ጭንቀትን (ቍ3) ወይም ጌዴዎን አደጋ በጣለ ባቸው ጊዜ (ቍ21) በምድያማውያን ላይ የደረሰውን ፍርሀትና ሽብር ነው። *በሞሬ ኮረብታ፤* ይህ ስፍራ የእስራኤል ሰራዊት ከሰፈረበት ስድስት ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ላይ በኢይዝራኤል ሸለቆ ማዶ የሚገኝ ነው።

7፥3 *የገለዓድን ተራራ፤* የጊልቦዓ ተራራ ሌላው ስም ሊሆን ይችላል። *ወደ መጣበት ይመለስ፤* ከእግዚአብሔር ጋር በመሰለፍ በጦርነቱ ላይ ለመካፈል የፈሩ ሰዎች፣ የሌሎቹን ቅስም እንዳይሰብሩ ከሰ ራዊቱ ጋር አብረው እንዳይሰለፉ ተደረገ (ዘዳ20፥8)።

7፥6 *በእጃቸው እያፈሱ፤* የቆሙት ሦስት መቶ ሰዎች የሚደ ርስባቸውን ማንኛውንም አደጋ ለመመልከት ዝግጁ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው ።

*7፥8-14፤* ጌዴዎንን ለማበረታታት ስለ ጠላት ሰራዊት መረጃ ሰጠው።


### የጌዴዎን ጦርነት

የጌዴዎን ታሪክ የሚጀምረው ለም በሆነው መሬት ከአራም በረሃ ወደ ፍልስጥኤም ምድር ወቅት እየጠበቁ በሚሄዱ ዘላኖች ዘመን ነው። በጸደይ ወቅት እነዚህ ከብት አርቢዎች በአንድ አዳር በየኮረብታውና እርሻ ቦታው ተበታትነው ይሰፍራሉ። በእነዚህ ሁለት የኑሮ ዘይቤዎች በሚከተሉ ሰዎች በከብት አርቢዎችና በገበሬዎች መካከል የሚኖረው ግጭት የማይቀር ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የእነዚህ ከብት አርቢ ዘላኖች ቍጥር መበርከትና ጠረኛ ባሕርያቸው በመንደር ሰፍረው የሚኖሩ ሰዎችን ጥገኛ እንዲሆኑ ዳርጓቸዋል ። ለዚህ ችግር የጌዴዎን ምላሽ (1)ከቤተሰቡ ጀምሮ የሃይማኖት ተሐድሶ ማድረግ፣ እና (2) በሰሜን ከሚገኙ የእስራኤል ነገዶች ጋር በመተባበር ወታደራዊ እርምጃ መውሰድ ናቸው። የጌዴዎን ትውልድ አገር ኦፍራ ትክክለኛ ስፍራዋ ባይታወቅም ጥንታዊቷ አፌር (ጽሬራ ሸለቆ የምትገኘዋ) ሳትሆን አትቀርም።

በእግዚአብሔር ረድኤትና ምሪት ጥቂት የሆኑት እስራኤላውያን ለጦርነት ስልታዊ የሆነ ቦታ በመያዝ ታምራዊ ድል በምድያማውያን ላይ ተቀዳጅተዋል።

ዋነኛው ጦርነት የተደረገው ከታቦር ተራራ ሥር ባለው መንደር ነበር። ምድያማውያን የዮርዳኖስ ሸለቆን ተከትለው መሸሻቸውና በቤትሳን የሚያሻግረው መንገድ በኤፍሬም አገር ሰዎች መያዙ ምድያማውያን ወጥመድ ውስጥ እንዲገቡ ምክንያት ሆኖባቸዋል።



በእጅህ አሳልፌ ሰጥቼሃለሁና። 10አደጋ ለመ
ጣል የምትፈራ ከሆነ ግን፣ ፉራ ከተባለው
አገልጋይህ ጋር ወደ ሰፈሩ ውረድ፤ 11የሚ
ሉትንም አድምጥ፤ ከዚያ በኋላ በሰፈሩ ላይ
አደጋ ለመጣል ድፍረት ታገኛለህ።" ስለዚህም
ጌዴዎን አገልጋዩን ፉራን አስከትሎ እስከ
ሰፈሩ ዳርቻ ወረደ። 12ብዛታቸው እንደ
አንበጣ መንጋ የሆነ ምድያማውያን፣ አማ
ሌቃውያንና ሌሎችም የምሥራቅ ሕዝቦች
በሸለቆው ውስጥ ሰፍረው ነበር፤ የግመ
ሎቻቸውም ብዛት በባሕር ዳርቻ እንዳለ
አሸዋ ስፍር ቍጥር አልነበረውም።
13አንድ ሰው ያየውን ሕልም ለጓደኛው
በሚነግርበት ጊዜ ጌዴዎን እዚያ ደረሰ።
ያም ሰው፣ "በሕልሜ ክብ የሆነ አንድ የገብስ
ቂጣ ከላይ ተንከባሎ በምድያማውያን ሰፈር
ላይ ሲወርድ፣ ድንኳኑንም ሲመታው ከአመ
ታቱም ኀይለኛነት የተነሣ ድንኳኑ ተገልብጦ
ሲፈራርስ አየሁ" በማለት ይነግረው ነበር።
14ጓደኛውም መልሶ፣ "ይህ የእስራኤላዊው
የኢዮአስ ልጅ የጌዴዎን ሰይፍ እንጂ፣ ሌላ
ነገር ሊሆን አይችልም፤ እነሆ፤ እግዚአብሔር
ምድያማውያንንና ሰፈሩን በሙሉ በእጁ አሳልፎ
ሰጥቶታልና" አለው።
15ጌዴዎንም ሕልሙንና ፍቺውን በሰማ
ጊዜ ለእግዚአብሔር ሰገደ፤ ከዚያም ወደ እስራ
ኤላውያን ሰፈር ወጥቶ፣ "እግዚአብሔር
የምድያማውያንን ሰፈር በእጃችሁ አሳልፎ
ሰጥቶአልና ተነሡ!" አላቸው። 16ሦስቱን
መቶ ሰዎች በሦስት ቡድን ከፍሎ፣ እያን
ዳንዱን ሰው ቀንደ መለከትና በውስጡ ችቦ
ያለበት ባዶ ማሰሮ በእጁ እንዲይዝ አደረገ።
17ጌዴዎንም እንዲህ አላቸው፤ እኔን ተመልከቱ፤
የማደርገውንም አድርጉ፤ በሰፈሩ ዳርቻ ስደርስ፣
እኔ የማደርገውን አይታችሁ ልክ እንደዚ
ያው አድርጉ። 18እኔና አብረውኝ ያሉት ሁሉ
ቀንደ መለከቶቻችንን በምንነፋበት ጊዜ
እናንተም በሰፈሩ ዙሪያ ሁሉ ቀንደ መለከ
ቶቻችሁን እየነፋችሁ፣ 'ለእግዚአብሔርና
ለጌዴዎን' ብላችሁ ጩኹ።"
19ዘቦቹ ተቀያይረው የእኩለ ሌሊቱን
ጥበቃ በጀመሩበት ጊዜ፣ ጌዴዎንና አብረ
ውት የነበሩት መቶ ሰዎች በሰፈሩ ዳርቻ
ደረሱ፤ እነርሱም ቀንደ መለከቶቻቸውን ነፉ፤
የያዟቸውንም ማሰሮች ሰበሩ። 20በሦስት
ቡድን የተከፈሉት ሰዎች ቀንደ መለከቶ
ቻቸውን ነፉ፤ ማሰሮቻቸውንም ሰበሩ፤
ችቦዎቻቸውን በግራ እጆቻቸው፣ የሚነፏ
ቸውንም ቀንደ መለከቶች በቀኝ እጆቻቸው
ይዘው፣ "የእግዚአብሔርና የጌዴዎን ሰይፍ"
በማለት ጮኹ። 21እያንዳንዱ ሰው በሰፈሩ
ዙሪያ የተመደበበትን ቦታ እንደያዘም፣ ምድ
ያማውያኑ እየጮኹ ሸሹ።
22የሦስት መቶው ቀንደ መለከት ድምፅ
እንደተሰማም፣ እግዚአብሔር በሰፈሩ ውስጥ
ያለው ሰው አንዱ በሌላው ላይ ሰይፉን
እንዲመዝበት አደረገ፤ ሰራዊቱ በጽሬራ
አቅጣጫ ወደ ቤት ሺጣ፣ ከዚያም አልፈው
በጠባት አጠገብ እስካለው እስከ አቤላሞሖላ
ድንበር ድረስ ሸሽተው ሄዱ። 23በንፍታሌም፣
በአሴርና በመላው የምናሴ ምድር የሚገኙ
እስራኤላውያን ተጠርተው ወጡ፤ ምድያ
ማውያንንም አሳደዱ። 24ጌዴዎንም በኤፍሬም
ኰረብታማ አገር ለሚኖሩት ሁሉ፣ "በምድ
ያማውያን ላይ ውረዱ፤ እስከ ቤትባራ ድረስ
ያለውንም የዮርዳኖስ ወንዝ ቀድማችሁ
ያዙ" አላቸው።
ስለዚህ የኤፍሬም ሰዎች ሁሉ ተጠርተው
ወጡ፤ እስከ ቤትባራ ድረስ ያለውንም የዮ
ርዳኖስን ወንዝ ያዙ። 25እንዲሁም ሔሬብና ዜብ
የተባሉትን ሁለቱን የምድያም መሪዎች
ያዙ። ሔሬብን በሔሬብ ዐለት አጠገብ፣
ዜብን ደግሞ በዜብ የወይን መጭመቂያ
ላይ ገደሏቸው፤ ምድያማውያንንም አሳደዱ፤
የሔሬብንና የዜብን ራስ ቈርጠው ጌዴዎን
ወዳለበት ወደ ዮርዳኖስ ይዘው መጡ።

7፥12 ዘኍ13፥29፤ ዘዳ28፥42፤ኢሱ11፥4፤ ኤር46፥23፤ 49፥29
7፥14 መሳ6፥11
7፥15 ቍ9፤ 1ሳሙ15፥31
7፥16 ቍ19፤ ዘፍ14፥15፤15፥17፤ 24፥14፤ዘሌ25፥9፤ መሳ9፥43፤ 1ሳሙ11፥11፤ 2ሳሙ18፥2 ሳ3፥27
7፥19 ቍ16
7፥20 ዘፍ15፥17፤ ዘዳ32፥41
7፥21 2ነገ7፥7
7፥22 ኢሱ6፥20፤ 1ሳሙ14፥20፤ 18፥19፤1ነገ4፥12፤ 19፥16፤2ዜና20፥23 ፤ኢሳ9፥21፤19፥2ሕዝ 8፥21፤ዕን3፥14፤ ሐጌ2፥22፤ዘካ14፥13
7፥23 ኢሱ17፥7፤ መሳ6፥35፤ መዝ83፥9
7፥24 ኢያ2፥7
7፥25 መሳ8፥3፡4፤ መዝ83፥11፤106፥43፤ኢሳ9፥4፤10፥26

*7፥13-14፤* በብሉይ ኪዳን ሕልም ማለም በተደጋጋሚ የተገለጠ ቢሆንም፣ ለየት የሚያደርገው ሕልም ዐላሚውም ሆነ ሕልም ፈቺው እስራኤላዊ አለመሆኑን ነው። በግብፅ የፈርዖንን ሕልም የፈታው ዮሴፍን (ዘፍ40፥1-22፤41፥1-32) እንዲሁም በባቢሎን የናቡከደ ነጾርን ሕልም የፈታው ዳንኤልን (ዳን2፥1-45፤ 4፥4-27) ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ።

7፥13 ***የገብስ ቂጣ፤*** በመሠረቱ ገብስ የታወቀ እህል ቢሆ ንም፣ በዋጋ ረገድ ከስንዴ ጋር ሲነጻጸር በግማሽ ይቀንሳል (2ነገ 7፥1 ይመ)፤ ይህም በቍጥር አነስተኛ የሆነውን የእስራኤልን ሰራዊት የሚያመለክት ነው።

7፥16 ***በሦስት ቡድን ከፍሎ፤*** እስራኤል ከጠላት ጋር ባደ ረገችው ጦርነት፣ ብዙውን ጊዜ የተጠቀመችበት የጦርነት ስልት ነው (9፥43፤ 1ሳሙ1፥11፤ 2ሳሙ18፥2) ***ቀንደ መለከት፤*** የሚሠ ራው ከበግ ቀንድ ነው (ዘፀ19፥13 ይመ)።

7፥19 ***የእኩለ ሌሊቱን ጥበቃ፤*** ዕብራውያን የሌሊቱን ጥበቃ በሦስት ፈረቃ ይከፍሉታል (የማቴ 14፥25 ማብ ይመ)። የእኩለ ሌሊቱ ጥበቃ የሚጀምረው ጠላት እንቅልፍ ከወሰደው በኋላ ነው።

7፥22 ***የሦስት መቶው ቀንደ መለከት፤*** በአንድ ሰራዊት ውስጥ ቀንደ መለከት የሚይዘው የተለመደው የሰው ቍጥር አነ ስተኛ ነበር። ***አንዱ በሌላው ላይ፤*** ይህን የመሰለ ውሉ የጠፋና የተመሰቃቀለ ሁኔታ በአሞናውያን፣ በሞዓባውያንና በኤዶማውያን ላይም ደርሶአል (2ዜና20፥23)። እንደዚሁም ከዚህ መለስ ባለው መልኩ ጊብዓ ላይ በፍልስጥኤማውያን መካከል ይህ ሁኔታ ደርሶአል (1ሳሙ 14፥20፤ ሕዝ38፥21፤ ዘካ14፥13 እንዲሁም የመሳ 4፥15ማብ ይመ)። ***ጽሬራ፤*** በደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ የሚገኝ ቦታ ነው።

7፥23 ***ተጠርተው ወጡ፤*** የጦርነቱ ሁኔታ ተለዋውጦ ስለ ተገኘ ተለይተዋቸው ሄደው የነበሩት እስራኤላውያን ወኔ አግ ኝተው እንደ ገና የጦርነቱ ተካፋይ ሆኑ።

7፥24 ***በኤፍሬም ኰረብታማ አገር፤*** ምድያማውያን ወደ ዮርዳኖስ ሸለቆ ሸሽተው እንዳያመልጡ የኤፍሬም ሰዎች ቀድመው ወርደው በሩን እንዲይዙ ጌዴዎን ርዳታቸውን ጠየቀ። ***የዮርዳኖስ ወንዝ፤*** በቤትሻን በኩል ያለው የወንዙ መልካ ሳይሆን አይቀርም። ይህም እስራኤላውያን የሚሸሹትን ምድያማውያንን እንዳያመልጡ ማገድ የሚችሉት ወንዙን በመቈጣጠር ነበር (የ3፥28ማብ ይመ)። ***ቤትባራ፤*** ቦታው በውል ተለይቶ አይታወቅም፤ ይሁን እንጂ ወንዙን ተከትሎ ቍልቍል ከወረዱ በኋላ፣ ጥቂት ራቅ ብሎ የሚገኝ ስፍራ መሆን አለበት። ጌዴዎን ጠላቶቹን ተከትሎ የዮርዳኖስን ወንዝ ከተሻገረ በኋላ፣ ከያቦቅ ወንዝ አጠገብ ወዳለው ወደ ሱኮት መጣ።

7፥25 ***ሔሬብ፤*** ቍራ ማለት ነው (ኢሳ 10፥26 ይመ)፤ ***ዜብ፤*** ተኩላ ማለት ነው። ***ራስ፤*** በጦርነት ምን ያህል ሰዎች እንደሞቱ ለማወቅ ይረዳ ዘንድ ከሞቱ ሰዎች አካል ላይ ራስ፣ እጅ (8፥6)እና ሸለፈት (1ሳሙ18፥25) ቈርጠው ያመጡ ነበር።

## ዛብሄልና ስልማና

8 በዚህ ጊዜ የኤፍሬም ሰዎች፣ “ምድያ
ማውያንን ለመውጋት ስትሄድ ለምን
አልጠራኸንም? ለምንስ እንዲህ ያለ ነገር
አደረግህ?” በማለት ጌዴዎንን እጅግ ነቀፉት።
2ጌዴዎን ግን፣ “እናንተ ካደረጋችሁት ጋር
ሲነጻጸር የእኔ ከምን ይቈጠራል? የኤፍሬም
የወይን ቃርሚያ ተጠቃሎ ከገባው ከአቢዔ
ዝር የወይን መከር አይበልጥምን? 3እግዚአ
ብሔር የምድያማውያንን መሪዎች ሔሬብንና
ዜብን በእጃችሁ አሳልፎ ሰጣችሁ፤ ታዲያ
እናንተ ከፈጸማችሁት ጋር የሚወዳደር ምን
ማድረግ እችል ነበር?” ይህን ሲሰሙ ቍጣቸው
በረደ።
4ጌዴዎንና ሦስት መቶዎቹ ሰዎች ዮርዳኖ
ስን ተሻገሩ፤ ምንም እንኳ ድካም ቢሰማቸውም
ጠላቶቻቸውን ያሳድዱ ነበር። 5የሱኮትንም
ሰዎች፣ “የምድያምንም ነገሥታት ዛብሄል
ንና ስልማናን በማሳደድ ላይ ስለ ሆንሁ የተ
ከተሉኝም ሰዎች ስለ ደከሙብኝ እባካችሁ
የሚበሉትን እንጀራ ስጧቸው” አላቸው።
6የሱኮት ሹማምንት ግን፣ “ለተከተሉህ
ሰዎች እንጀራ እንሰጥ ዘንድ ዛብሄልና ስል
ማና በእጅህ ገብተዋልን?” አሉት።
7ጌዴዎንም መልሶ፣ “ደህና፤ እግዚብሔር
ዛብሄልንና ስልማናን በእጄ አሳልፎ በሚ
ሰጥበት ጊዜ በምድረ በዳ እሾኽና አሜከላ
ሥጋችሁን እተለትላለሁ” አላቸው።
8ከዚያም ወደ ጵኒኤል ሰዎች ሄዶ ያንኑ
ጥያቄ አቀረበላቸው፤ የእነርሱም መልስ
የሱኮት ሰዎች ከሰጡት መልስ ጋር አንድ ዐይ
ነት ነበር። 9እርሱም የጵኒኤልን ሰዎች፣
“በድል አድራጊነት በሰላም ስመለስ ከተ
ማችሁን የምትጠብቁበትን ይህን ግንብ አፈ
ርሰዋለሁ” አላቸው።
10በዚህ ጊዜ ዛብሄልና ስልማና ዐሥራ
አምስት ሺህ ከሆነ ሰራዊታቸው ጋር ቀርቀር
በተባለ ስፍራ ነበሩ፤ ይህም ከምሥራቅ ሕዝ
ቦች ከተውጣጣውና በጦር ሜዳ ከወደቀው
መቶ ሃያ ሺህ ሰይፍ ታጣቂ ሰራዊት የተረፈው
ነበር። 11ከዚያም ጌዴዎን ተነሣ፤ ከኖባህና
ከዮግብሃ በስተ ምሥራቅ የሚኖሩ ዘላኖች
የሚሄዱበትን መንገድ ተከትሎ በጠላት
ሰራዊት ላይ በድንገት አደጋ ጣለ። 12ሁለቱ

8፥1 ዘፍ25፥2፤
መሳ6፥11፤12፥1፤
2ሳሙ19፥41
8፥2 ዘኍ26፥30
8፥3 መሳ7፥25
8፥4 መሳ7፥25
8፥5 ቍ7:12፤
ዘፍ33፥17፤ኢዮ16፥
7፤መዝ6፥6፤
83፥11፤ ኤር45፥3
8፥6 ቍ14:15፤
1ሳሙ25፥11
8፥7 ቍ5
8፥8 ቍ9:17፤
ዘፍ32፥30፤1ነገ12፥
25
8፥9 ቍ17
8፥10 መሳ6፥5፤
ኢሳ9፥4
8፥11 ዘኍ32፥35፡42
8፥13 መሳ1፥3
5፤6፥11
8፥14 ቍ6፤ዘፀ
3፥16
8፥15 ቍ6
8፥16 ሳሙ14፥12
8፥17 ቍ8:9
8፥18 ኢሱ19፥22
8፥19 ዘኍ14፥21
8፥21 ቍ26፤
ኢሳ3፥18
8፥23 ዘፀ16፥8፤
ዘኍ11፥20፤
1ሳሙ12፥12

የምድያም ነገሥታት ዛብሄልና ስልማና ሸሹ፤
ጌዴዎን ግን አሳዶ ያዛቸው፤ መላ ሰራዊታ
ቸውንም እጅግ በታተነው።
13ከዚህ በኋላ የኢዮአስ ልጅ ጌዴዎን
በሐሬስ መተላለፊያ በኩል አድርጎ ከጦርነቱ
ተመለሰ፤ 14እርሱም የሱኮት ሰው የሆነ አንድ
ወጣት ማረከ፤ መረመረውም፤ ወጣቱም የሰባ
ሰባት የሱኮት ሹማምትና የከተማዪቱንም
አለቆች ስም ጻፈለት። 15ከዚያም ጌዴዎን
ወደ ሱኮት ሰዎች መጥቶ እንዲህ አላቸው፤
“‘ለደከሙት ሰዎችህ እንጀራ እንሰጥ ዘንድ
ዛብሄልና ስልማና በእጅህ ገብተዋልን’ በማለት
ያላገጣችሁብኝ ዛብሄልና ስልማና እነዚሁ
ላችሁ።” 16ጌዴዎን የከተማዪቱን አለቆች
ወሰደ፤ በምድረ በዳ እሾኽና አሜኬላ በመቅጣት
የሱኮትን ሰዎች ትምህርት ሰጣቸው። 17እን
ዲሁም በጵኒኤል ያለውን የከተማ መጠ
በቂያ ግንብ አፈረሰ፤ የከተማዪቱንም ሰዎች
ገደለ።
18ዛብሄልና ስልማናንም፣ “በታቦር ላይ
የገደላችኋቸው ሰዎች እንዴት ያሉ ነበሩ?”
በማለት ጠየቃቸው።
እነርሱም፣ “ሁሉም እንዲህ እንዳንተ ያሉ
የንጉሥ ልጆች የሚመስሉ ናቸው” አሉት።
19ጌዴዎንም፣ “እነርሱ የእናቴ ልጆች
ወንድሞቼ ናቸው፤ ባትገድሏቸው ኖሮ፣
እኔም እንደማልገድላችሁ በሕያው እግዚ
አብሔር ስም አረጋግጥላችሁ ነበር።” ብሎ
መለሰላቸው። 20ከዚያም ወደ በኵር ልጁ
ወደ ዮቴር ዘወር ብሎ፣ “ግደላቸው” አለው፤
ዮቴር ግን ትንሽ ልጅ ነበርና ስለ ፈራ
ሰይፉን አልመዘዘም።
21ዛብሄልና ስልማናም፣ “የሰው ጕልበቱ
እንደ ሰውነቱ መጠን ነውና አንተው ራስህ
ግደለን አሉት፤ ጌዴዎንም ተነሥቶ ገደላቸው፤
በግመሎቻቸው ዐንገት ላይ የነበሩትንም
ጌጦች ወሰደ።

## የጌዴዎን ኤፉድ

22እስራኤላውያንም ጌዴዎንን፣ “ከምድ
ያማውያን እጅ ታድገኸናልና አንተ፣ ልጅህና
የልጅ ልጅህ ግዙን” አሉት።
23ጌዴዎን ግን መልሶ፣ “እኔም ሆንሁ ልጄ
አንገዛችሁም፤ የሚገዛችሁ እግዚአብሔር ነው”

8፥1 ***የኤፍሬም ሰዎች፤*** የዚህን ነገድ ቍጣ ሊያበርድ የቻለውን ጌዴዎንን (ቍ2-3)፣ በዚህ ነገድ ላይ ውርደትንና ሽንፈትንካመጣው ከዮፍታሔ ጋር ያነጻጽሩ (12፥1-6)።

8፥2 ***ቃርሚያ፤*** ዋናው ሰብል ከተሰበሰበ በኋላ የሚቀር እህል ነው፤ (የሩት1፥22 ማብ ይመ)። እዚህ ላይ ጌዴዎንና የእርሱ ኀይል በተካፈለበት ጦርነት ካገኙት ድል ይልቅ፣ የኤፍሬም ሰዎች ባደረጉት ጦርነት ያገኙት ድል እንደሚበልጥ ማውሳቱ ነው። ***አቢዔዝር፤*** የራሱ የጌዴዎን ጐሣ ስም ነው (የ6፥11 ማብ ይመ)፤ ትርጕሙም፣ “አባቴ (አምላኬ) ረዳቴ” ነው ወይም “አባቴ (አምላኬ) ጠንካራ ነው” ማለት ነው።

8፥3 ***ቍጣቸው በረደ፤*** “የለዘበ ምላስ ቍጣን ያበርዳል” (ምሳ15፥1) የተባለው እዚህ ላይ በትክክል ሲፈጸም ይታያል።

8፥5 ***የምድያምንም ነገሥታት፤*** ዛብሄልና ስልማና ከዘላያዊ የምድያም ምድር ነገዶች የተውጣጡ ሊሆኑ ይችላሉ (ዘኍ31፥8 ይመ)።

8፥6 ***እንጀራ እንሰጥ ዘንድ፤*** የሱኮት ሰዎች ይህን ያሉት፣ ጌዴዎን እነዚህን የተባበሩትን የምድያምን ነገሥታት ማሸነፉን ስለተጠራጠሩ አሁን ለሰራዊቱ ምግብ ቢሰጡ ወደ ፊት ነገሥታቱ እንዳይበቀሏቸው ስለፈሩ ነው። ***በእጅህ፤*** የ7፥25 ማብ ይመ።

8፥8 ***ጵኒኤል፤*** ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር የታገለበት ስፍራ ነው (ዘፍ 32፥30-31)።

8፥19 ***የእናቴ ልጆች፤*** አንድ ሰው ብዙ ሚስቶች በሚያገባበት ጊዜ፣ ከአንድ እናት የተወለዱትን ልጆች ብቻ ለይቶ ለመናገር ነው።

8፥21 ***አንተው ራስህ ግደለን፤*** እንደ እነርሱ ያሉ ሰዎች በአንድ ትንሽ ልጅ እጅ መሞትን እንደ ውርደት ቈጥረውት ሊሆን ይችላል (1ሳሙ17፥42)። ***ጌጦች፤*** ግማሽ ጨረቃ የሚመስል የሆነት ጌጥ ነው፤ በኢሳ3፥18 ላይ እንደ ተጠቀሰው ዐይነት ማለት ነው።

8፥23 ***እኔም...አንገዛችሁም፤ የሚገዛችሁ እግዚአብሔር ነው፤*** እንደ ሳሙኤል ሁሉ (1ሳሙ 8፥4-20) ጌዴዎንም ንጉሣዊ አገዛዝን አይፈልግም ነበር፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ንጉሥ መሆኑ በመጽሐፈ መሳፍንት ልዩ ስፍራ የተሰጠው

አላቸው:: 24እርሱም፣ “አንድ የምጠይቃችሁ ነገር አለኝ፤ ይኸውም እያንዳንዳችሁ ከምርኮ ካገኛችሁት ውስጥ የጆሮ ጉትቻችሁን እንድትሰጡኝ ነው” አላቸው፤ የወርቅ ጉትቻ ማድረግ የእስማኤላውያን ባህል ነበርና::

25እነርሱም መልሰው፤ “ደስ እያለን እንሰጥሃለን” አሉት፤ ወዲያው ልብስ አነጠፉ፤ በላዩም ላይ እያንዳንዳቸው ከማረኩት ውስጥ የጆሮ ጉትቻ ጣል ጣል አደረጉለት:: 26ሌሎቹን ገጣ ጌጦች ይኸውም የዐንገት ሐብሉን ከአንጥልጥሉ፣ የምድያም ነገሥታት ይለብሱት የነበረውን ሐምራዊ ልብስ ወይም በግመሎቻቸው ዐንገት ላይ ያሉትን ጌጦች ሳይጨምር ጌዴዎን በጠየቃቸው መሠረት የሰጡት የወርቅ ጉትቻ ክብደት ሺህ ሰባት መቶ ሰቅል[ሠ] ያህል መዘነ:: 27ጌዴዎን በወርቁ ኤፉድ ሠራ፤ በተወለደበትም ከተማ በዖፍራ አኖረው። እስራኤልም በሙሉ ኤፉዱን በማምለክ ስላ መንዘሩ፣ ኤፉዱ ለጌዴዎንና ለቤተ ሰቡ ወጥመድ ሆነ::

## የጌዴዎን መሞት

28ስለዚህ ምድያማውያን በእስራኤላውያን ተሸነፉ፤ ዳግመኛም ራሳቸውን ከፍ ከፍ አላደረጉም:: ጌዴዎን በሕይወት እስካለ ጊዜ ድረስ ምድሪቱ አርባ ዓመት ሰላም አገኘች።

29የኢዮአስ ልጅ ይሩባኣል ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ በዚያም ተቀመጠ፤ 30ብዙ ሚስቶች ስላገባ ሰባ ልጆች ነበሩት፤ 31በሴኬም የምትኖረው ቁባቱም እንደዚሁ ወንድ ልጅ ወለደችለት፤ ስሙንም አቤሜሌክ አለው:: 32የኢዮአስ ልጅ ጌዴዎን ዕድሜ ጠግቦ ሞተ፤ በአቢዔዝራውያን ምድር ባለችው በዖፍራ፣ በአባቱ በኢዮአስ መቃብር ተቀበረ::

33ጌዴዎን ሞቶ ብዙም ሳይቈይ እስራኤላውያን የበኣልን አማልክት በማምለክ አመነዘሩ፤ በኣልብሪትንም አምላካቸው አደረጉ፤ 34በዙሪያቸው ከነበሩት ጠላቶቻቸው እጅ የታደጋቸውን እግዚአብሔርን ስምላካቸውን አላሰቡትም:: 35እንዲሁም ይሩባኣል የተባለው ጌዴዎን ያደረገላቸውን በጎ ነገር ሁሉ አስበው ለቤተ ሰቡ ውለታ መላሽ ሆነው አልተገኙም::

## አቤሜሌክ

9 የይሩባኣል ልጅ አቤሜሌክ ወደ እናቱ ወንድሞች ወደ ሴኬም ሄደ:: እነርሱንና የእናቱን ጐሣዎች በሙሉ እንዲህ አላቸው፤ 2“የሴኬምን ነዋሪዎች ሁሉ እንዲህ ብላችሁ ጠይቋቸው፤ ‘ሰባዎቹ የይሩባኣል ልጆች ቢገዟችሁ ይሻላል ወይስ አንድ ሰው ብቻ?’ የሥጋችሁ ቍራጭ፣ ያጥንታችሁ ፍላጭ መሆኔን ልብ በሉ::”

3የእናቱ ዘመዶች ስለ እርሱ ሆነው እነዚህን ቃሎች ሁሉ ለሴኬም ነዋሪዎች በሙሉ ነገሩ፤ አቤሜሌክንም ለመከተል ልባቸው ዳዳ፤ “እርሱማ ወንድማችን አይደል ብለዋልና”። 4እነርሱም በኣልብሪት ቤተ ጣዖት ሰባ ሰቅል[ጸ] ናስ

8፥24 ዘፍ16፥11፤ 35፥4፤49፥27
8፥26 ቍ21
8፥27 ዘፀ10፥7፤ 25፥7፤32፥2፤ ኢሱ18፥23፤ መሳ17፥5፤18፥14
8፥28 መሳ3፥11፤ መዝ83፥2
8፥29 መሳ6፥ 11:32
8፥30 መሳ9፥2:5፡ 18:24፤12፥14፤2ነገ10፥1፤
8፥31 ዘፍ22፥24፤ መሳ9፥1፤10፥1፤ 2ሳሙ11፥21
8፥32 ዘፍ15፥15
8፥33 መሳ2፥11፡ 13:19፤9፥4:27:46
8፥34 መሳ3፥7፤ ነህ9፥17
8፥35 መሳ6፥32፤ 9፥16
9፥1 መሳ6፥32፤ 8፥31
9፥2 ዘፍ29፥14
9፥4 መሳ8፥33፤ 11፥3፤1ሳሙ25፥25 ፤2ዜና13፥7፤ ኢዮ30፥8

[ሠ]26. 19.5ኪሎ ግራም ያህል ነው::
[ጸ]4. 0.8 ኪሎ ግራም ያህል ነው

ጉዳይ ስለ ነበር፣ ንጉሥ ማንገሥ ማለት የእግዚአብሔርን አገዛዝ እንደ መተካት የሚቈጠር ነው::

8፥24 ***የጆሮ ጉትቻችሁን፤*** ምናልባትም በአፍንጫም ላይ የሚደረግ ጌጥ ሊሆን ይችላል (ዘፍ24፥47፤ ሕዝ16፥12 ይመ):: ***እስማኤላውያን፤*** ከምድያማውያን ጋር ዝምድና ያላቸው ናቸው (ዘፍ25፥1-2)፤ አንዳንድ ጊዜም ከእነዚሁ ጋር አንድ ሆነው ይገኛሉ (ቍ22:24፤ ዘፍ37፥25-28፤ 39፥1)፤ እንዲሁ የዘፍ37፥25 ማብ ይመ::

8፥27 ***ኤፉድ፤*** አንዳንድ ጊዜ ከሥርዐተ ክህነት ጋር የተያያዘ የተቀደሰ ልብስ ነው (ዘፀ28፥6-30፤39፥2-26፤ ዘሌ 8፥7)፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከአረማውያን ጣዖት ጋር ተያይዞአል (17፥5፤ 18፥14:17)::

8፥28 ***አርባ ዓመት፤*** የአንድን ትውልድ ዕድሜን የሚያመለክት የዘመን ቍጥር ነው::

8፥29 ***ይሩበኣል፤*** የ6፥32 ማብ ይመ ::

8፥30 ***ሰባ ልጆች፤*** የኀይልና የብልጽግና ምልክት ነው (12፥14፤ 2ነገ 10፥1 ይመ)::

8፥31 ***ቁባቱም፤*** በመሠረቱ ሴቲቱ ቀደም ሲል የእርሱ የቤት አገልጋይ ነበረች (9፥18 እንዲሁም የዘፍ16፥2 ማብ ይመ):: ***አቤሜሌክ፤*** በሌላ ስፍራ ይህ የማዕረግ ስም ሆኖ ለነገሥታት ተሰጥቶአል (ዘፍ20፥2፤ 26፥1፤ የመዝ 34 ርእስ ይመ)፤ ትርጕሙም “(አምላኬ) አባቴ ንጉሥ ነው” ማለት ነው:: ጌዴዎን ይህን ስም ለልጁ ሲሰጠው፣ “አባት” የተባለው እግዚአብሔር ንጉሥ መሆኑን የሚያስረዳ ነው::

8፥32 ***ዕድሜ ጠግቦ፤*** ይህ ሐረግ በሌላ ቦታ ተጠቅሶ የምናገኘው፣ ለአብርሃምና (ዘፍ15፥15፤ 25፥8)፣ ለዳዊት ብቻ ነው (1ዜና29፥28)::

8፥33 ***የበኣልን አማልክት፤*** የ2፥11:13 ማብ ይመ:: ***በኣልብሪትንም፤*** ትርጕሙ “የኪዳን ጌታ” ማለት ነው፤ ይህ የጣዖት አምላክ በ9፥46 ላይ ኤልብሪት ተብሎ ተጠርቶአል፤ ትርጕሙም “የኪዳን አምላክ” ማለት ነው:: በሴኬም ለእርሱ የተሠራ ቤተ ጣዖት ነበር (9፥4 ይመ)፤ ከስሙ ጋር የተጠቀሰው፣ “ኪዳን” የሚለው ቃል ምናልባትም የከነዓንን ከተሞች ኅብረት አንድ ላይ አስተሳስሮ የሚይዘውን ጠንካራ ስምምነት የሚያመለክት ይሆናል፤ በእነዚህ ከተሞች የሚኖሩ ሕዝቦች ይህን ጣዖት አምላካቸው አድርገው ያመልኩት ነበር:: በአንጻሩ በኤባል አጠገብ ያለው ሴኬም (ቍ31)፣ እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ምድር ከገቡ በኋላ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ያደረገውን ኪዳን ኢያሱ ሁለት ጊዜ ያደሰበት ስፍራ ነበር (ኢሱ 8፥30-35፤ 24፥25-27):: እንዲሁም የ2፥11 ማብ ይመ::

*9፥1-57* የጌዴዎንና የአቤሜሌክ ታሪክ ፣ በመጽሐፈ መሳፍንት ታሪክ ውስጥ የጽሑፉ ማዕከላዊ ክፍል ነው (በመጽሐፉ መግቢያ “ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያቱ” የሚለውን ይመ):: በበኣል ረዳትነት ራሱን የከነዓናውያን ከተሞች ንጉሥ ለማድረግ የሞከረው አቤሜሌክ (ቍ4)፣ የበኣልን አምልኮ ከተቃወመውና እስራኤልን የሚገዛ እግዚአብሔር ነው በሚል እምነቱ ከጸናው ከአባቱ ከጌዴዎን ጋር ሲነጻጸር በሁለቱ መካከል ሰፊ ልዩነት ነበር:: አቤሜሌክ ከነዓናዊነት እንዲያንሠራራ ታላቅ ጥረት ያደረገው፣ እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ያላትን ኪዳን ቀደም ሲል ኢያሱ ባረጋገጠበት ቦታ ላይ ነው (ኢሱ 24፥14-27):: በማንኛውም ረገድ የአቤሜሌክ አድራጎት የእስራኤልን ሕዝብ እንዲመሩ በእግዚአብሔር ከተመረጡት መሳፍንት ጋር የሚቃረን ነበር::

9፥1 ***ሴኬም፤*** የዘፍ 33፥18 ማብ ይመ:: እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ምድር ከመግባታቸው በፊት፣ የከነዓናውያንን ዘመን የሚያመለክቱ ፍርስራሾች እንደሚያስረዱት በዚህ ስፍራ ላይ የበኣልብሪት ወይም የኤልብሪት ቤተ ጣዖት ነበር(ቍ4፥46):: አቤሜሌክ ሴኬምን ካጠፋ በኋላ የሥነ ቅርስ ጥናትም እንደሚስረዳው ያ የአምልኮ ስፍራ እንደ ገና አልተገነባም::

9፥2 ***ነዋሪዎቹ፤*** ይህ ቃል በዕብራይስጥ “በአል” ይባላል፤ ትርጕሙም “ጌታ” ወይም ባለቤት ማለት ሲሆን ምናልባት የገዥውን መደብ ወይም በከተማ የሚኖሩ የመሬት ከበርቴዎችን የሚያመለክት ይሆናል:: ***የሥጋችሁ ቁራጭ ያጥንታችሁ ፍላጭ፤*** አቤሜሌክ ግማሽ ጐኑ ከነዓናዊ ስለ ሆነ፣ ለሰባው የጌዴዎን ልጆች ተገዥ ከሆኑት ይልቅ የገዛ ወገናቸው የሆነውን እርሱን ቢያነግሡት ጥቅሙ ለራሳቸው እንደ ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ መግለጹ ነው:: የእነርሱ ወገን መሆኑን በመግለጽ ከነዓናውያንን እንዲከተሉት ለማድረግ ችሎአል፤ ውጤቱም ለእስራኤል ሕዝብ አደገኛ ነበር::

9፥4 ***ቤተ ጣዖት፤*** በጥንት ዘመን፣ የግል ገንዘብም ሆነ በየጊዜው ከሕዝቡ የሚዋጣውና በስእለትም ሆነ በመቀጫ ወይም

ሰጡት፤ አቤሜሌክም በዚያ ወሮበሎችንና
ምናምንቴዎችን ቀጠረበት፤ እነርሱም ተከ
ተሉት:: 5ከዚያም የፍራ ወደ ሚገኘው
ወደ አባቱ ቤት ሄደ፤ ሰባውን የይሩበኣልን
ልጆች ወንድሞቹን በአንድ ድንጋይ ላይ ዐረ
ዳቸው፤ የይሩበኣል የመጨረሻ ልጅ ኢዮአ
ታም ግን ተሸሽጎ ስለነበር አመለጠ:: 6የሴ
ኬምና የቤትሚሎ ነዋሪዎች በሙሉ አቤሜ
ሌክን ለማንገሥ ሴኬም ውስጥ በዐምዱ
አጠገብ ካለው የባሉጥ ዛፍ ሥር ተሰበሰቡ::
7ኢዮአታም ይህ በተነገረው ጊዜ፣ በገሪዛን
ተራራ ጫፍ ላይ ወጥቶ ድምፁን ከፍ በማ
ድረግ እንዲህ አላቸው፤ የሴኬም ነዋሪዎች
ሆይ፤ እግዚአብሔር ይሰማችሁ ዘንድ እኔን ስሙኝ፤
8ከዕለታት አንድ ቀን ዛፎች የሚያነግሡትን
ለመቀባት ወጡ፤ ወይራንም፣ 'አንተ ንጉሣ
ችን ሁን' አሉት::
9የወይራ ዛፍም፣ "ከዛፎች በላይ ለመወ
ዛወዝ ስል፣ እግዚአብሔርና ሰዎች የሚከበሩ
በትን ዘይቴን መስጠት ልተውን? "አለ::
10"ቀጥሎም ዛፎቹ በለስን፣ 'መጥተህ
ንጉሣችን ሁን' አሉት::
11"በለስ ግን፣ 'ከዛፎች በላይ ለመወ
ዛወዝ ስል፣ እጅግ ጣፋጭና መልካም የሆ
ነውን ፍሬዬን መስጠት ልተውን?' አለ::
12"ከዚያም ዛፎቹ የወይን ተክልን፣ 'መጥ
ተህ ንጉሣችን ሁን' አሉት::
13 "የወይን ተክሉም፣ 'ከዛፎች በላይ
ለመወዛወዝ ስል፣ አማልክትንና ሰዎችን ደስ
የሚያሰኘውን የወይን ጠጄን መስጠት
ልተውን? አለ::
14በመጨረሻም ዛፎቹ በሙሉ የእሾኽ
ቍጥቋጦን፣ 'መጥተህ ንጉሣችን ሁን'
አሉት::

15"የእሾኽ ቍጥቋጠውም ዛፎቹን፣ 'በእ
ርግጥ ቀብታችሁ በላያችሁ የምታነግሡኝ
ከሆነ መጥታችሁ በጥላዬ ሥር ተጠለሉ፤
ይህን ባታደርጉ ግን እሳት ከእሾኽ ቍጥ
ቋጠው ይነሣ! የሊባኖስንም ዝግባዎች ይብላ'
አላቸው::
16"እንግዲህ አቤሜሌክን ስታነግሡት
በቅንነትና በእውነት አድርጋችሁት ከሆነ፣
ይሩበኣልንና ቤተ ሰቡን በበጎ ዐይን ተመል
ክታችሁ ላደረገው የሚገባውን አይታች
ሁለት ከሆነ፣ 17አባቴ ለእናንተ መዋጋቱን፣
ከምድያማውያን እጅ ሊያድናችሁ ሕይ
ወቱን መስጠቱን አስባችሁ ማለት ነው::
18ነገር ግን እናንተ ዛሬ በአባቴ ቤተ ሰብ
ላይ ዐመፃችሁ፤ ሰባ ልጆቹን በአንዲት ድን
ጋይ ላይ ዐረዳችሁ፤ ዘመዳችሁ ስለ ሆነም
አባቴ ከባሪያው የወለደውን ልጅ አቤሜ
ሌክን በሴኬም ነዋሪዎች ላይ አነገሣችሁት::
19እንግዲህ ዛሬ በይሩበኣልና በቤተ ሰቡ ላይ
ያደረጋችሁት በእውነትና በቅንነት ከሆነ
እናንተ በአቤሜሌክ ደስ ይበላችሁ፤ እርሱም
በእናንተ ደስ ይበለው! 20ይህ ካልሆነ ግን
እሳት ከአቤሜሌክ ትውጣና እናንተን፣
የሴኬምንና የቤትሚሎንን ነዋሪዎች ትብላ፤
እንዲሁም እሳት ከእናንተ፣ ከሴኬምና ከቤት
ሚሎን ነዋሪዎች ትውጣና አቤሜሌክን
ትብላ::"
21ከዚህ በኋላ ኢዮአታም ሸሽቶ አመለጠ፤
ብኤር ወደ ተባለች ቦታም መጣ፤ ወንድሙንም
አቤሜሌክን ፈርቶ ስለ ነበር እዚያው ይኖር
ጀመር::
22አቤሜሌክ እስራኤልን ሦስት ዓመት ከገዛ
በኋላ፣ 23እግዚአብሔር በአቤሜሌክና በሴኬም
ነዋሪዎች መካከል ክፉ መንፈስ ሰደደ፤ ስለዚ
ህም የሴኬም ሰዎች አቤሜሌክን ከዱት::

9፥5 ቍ7:21:
57፤መሳ8፥30፤2ነገ11
1፥2፤2ዜና22፥9
9፥6 ቍ20፤
ዘፍ12፥6፤መሳ4፥11
፤2ነገ12፥20
9፥7 ቍ5፤
ዘዳ11፥29፤ዮሐ4፥20
9፥13 ዘፍ14፥18
፤መክ2፥3፤መኃ4፥10
9፥15 ቍ20፤
ዘዳ3፥25፤1ነገ5፥6፤
መዝ29፥5፤92፥12፤
ኢሳ2፥13፤30፥2
9፥17 መሳ12፥3፤
1ሳሙ19፥5፤28፥21
፤ኢዮ13፥14፤
መዝ119፥109
9፥18 መሳ8፥30
9፥19 ቍ16
9፥20 ቍ6:15:45
9፥21 ቍ5፤ዘኍ2
1፥16
9፥23 1ሳሙ16፥14
:23፤18፥10፤19፥9፤1
ነገ22፥22

በስጦታ የሚገባው ገንዘብ በቤተ ጣዖት ውስጥ ይቀመጥ ነበር:: የሥነ ቅርስ ተመራማሪዎች በሴኬም ያገኙት ትልቅ ሕንጻ ምናልባት የበኣልብሪት ቤተ ጣዖት ሊሆን ይችላል:: ወሮበሎች ምናምንቴዎች፤ በጥንቱ ዘመን ፖለቲካም ሆነ የውትድርናን ዐላማን ከግብ ለማድረስ ቅጥረኞችን ማሰባሰብ የተለመደ ነበር:: ዐላማቸውን ከግቡ ለማድረስ በዚህ መንገድ የተጠቀሙ ሌሎች ሰዎችም አሉ፤ እነርሱም ዮፍታሔ (11፥3)፣ ዳዊት (1ሳሙ 2፥1-2)፣ አቤሴሎም (2ሳሙ15፥1)፣ አዶንያስ (1ነገ1፥5)፣ ሬዞን (1ነገ11፥23-24) እና ኢዮርብዓም (2ዜና 13፥6-7) ነበሩ::

9፥5 በአንድ ድንጋይ ላይ፤ የአቤሜሌክ ሰባ ወንድሞች የታረዱት ልክ ለመሥዋዕት እንደሚቀርብ እንስሳ ነበር (13፥19-20፤ 1ሳሙ14፥33-34 ይመ):: እስራኤላውያን ወንድሞቹን መሥዋዕት አድርጎ ካቀረበ በኋላ የንግሥና በዓሉን አከበረ (2ሳሙ 15፥10:12፤ 1ነገ1፥5:9፤ 3፥4 ይመ)::

9፥6 ቤትሚሎ፤ ሚሎ የሚለው ቃል የመጣው መሙላት ከሚለው የዕብራይስጥ ግስ ነው:: ምናልባት ይህ ጥልቅ ሰገነት ወይም ከፍታ ቦታ ለማዘጋጀት በዐፈር ተሞልቶ የተደላደለ ስፍራን የሚያመለክት ቃል ሳይሆን አይቀርም:: ቤት ሚሎም በቍ 46 ላይ ከተመለከተው "ምሽግ" ከሚለው ቃል ጋር አንድ ሳይሆን አይቀርም:: የባሉጥ ዛፍ፤ ኢያ24፥25-26 እንዲሁም የዘፍ12፥6 ማብ ይመ::

9፥7 ጫፍ ምናልባትም ከተማዪቱን ፍንትው አድርጎ ለማየት የሚያስችል ምቹ ስፍራ ሳይሆን አይቀርም::

9፥8 ዛፎች ... ወጡ፤ ግዑዛን ፍጥረታት እንደተናገሩ፣ አንዳንድ ድርጊቶችንም እንደ ፈጸሙ የሚገልጽ እንዲህ ዐይነቱ የፈጠራ ትረካ ማቅረብ በጥንት የምሥራቅ ሰዎች ዘንድ የተለመደ ነበር (2ነገ 14፥9 ይመ)::

9፥9-13፤ ወይራ፣ በለስና ወይን በመካከለኛው ምሥራቅ አስፈላጊ የሆኑ ፍሬዎችን የሚያፈሩ ዛፎች ነበሩ::

9፥13 አማልክትን፤ በዚያን ጊዜ አማልክት ሰዎች እንደ ሚያደርጉት ሁሉ ወይን ይጠጣሉ ተብሎ ይታመን ነበር::

9፥14 የእሾኽ ቍጥቋጦን፤ በፓሌስቲና ኰረብታማ ምድር በብዛት የሚገኝና ብዙ ጊዜ በግብርና ሥራ ላይ ችግር የሚፈጥር ጥቅጥቅ ያለ ቍጥቋጦ ነው፤ ምንም ዐይነት ጥቅም የሚሰጥ ፍሬ ስለማያፈራ ምሳሌው ለአቤሜሌክ መጠቀሱ ተገቢ ነው::

9፥15 በጥላዬ፤ የእሾኽ ቍጥቋጦ ለዛፍ ጥላ ሆነ ማለት ነገሥታት ለሕዝባቸው ከለላ ሆነው የሚጫወቱት ሚና እርኪ እንዳልነበረ የሚገልጽ ምጸታዊ አነጋገር ነው (ኢሳ30፥2-3፤32፥1-2፤ሰቆ4፥20፤ዳን4፥12ይመ):: የሊባኖስንም ዝግባዎች፤ በመካከለኛው ምሥራቅ እጅግ ጠቃሚና ውድ የሆነ ዛፍ ነው፤ እዚህ ላይ ግን ትርጓሜው የሚመለከተው የሴኬምን ዋነኛ ሰዎችን ትምህርት የሚያመለክት ነው (ቍ20 ይመ)::

9፥20 እሳት ...ትውጣና ... ትብላ፤ አቤሜሌክና የሴኬም ሰዎች እርስ በርሳቸው እንደሚተላለቁ የተነገረ አስፈሪ ትንቢት ነው:: ጥቅጥቅ ያለ ጭራሮ ከበዛበት ቍጥቋጦ ውስጥ እሳት ሲነሣ በፍጥነት እየታዛመተ ያገኘውን ሁሉ በማቃጠል ከፍተኛ ጕዳት እንደሚያደርስ የታወቀ ነው (ዘፀ22፥6፤ኢሳ9፥18 ይመ)::

9፥21 ብኤር፤ የተለመደ ስም ሲሆን ፣ትርጕሙም የውሃ ጕድጓድ ማለት ነው::

9፥22 እስራኤልን፤ በሴኬም አካባቢ ያሉ የአቤሜሌክን ሥልጣን የተቀበሉ ናቸው::

9፥23 ክፉ መንፈስ፤ ምናልባትም ያለመተማመንና የጥላቻ መንፈስ ይሆናል:: በዕብራይስጥ "መንፈስ" የሚለው ቃል የአንድን ሰው ትክክለኛ ሁኔታ ወይም ባሕርይ ለመግለጽ የሚያገለግል ቃል ነው:: ከዱት፤ በተንኰል ተነሣሥቶ መንግሥቱን ያቆመ፣ እሱ ራሱ

24እግዚአብሔር ይህን ያደረገውም፣ በሰባው
የይሩበኣል ልጆች ላይ ስለ ተፈጸመው ግፍና
ስለ ፈሰሰው ደማቸው ወንድማቸውን አቤሜ
ሌክና ወንድሞቹን እንዲገድል የረዱትን
የሴኬምን ሰዎች ለመበቀል ነው። 25የሴኬም
ነዋሪዎችም አቤሜሌክን ሸምቀው የሚጠባበ
ቁትን ሰዎች መደቡ፤ ሰዎቹም እርሱን
በመጠባበቅ ላይ ሳሉ በዚያ የሚያልፈውን
ሁሉ ዘረፉ፤ ወሬውም ለአቤሜሌክ ደረሰው።
26በዚህ ጊዜ የአቤድ ልጅ ገዓል ከወን
ድሞቹ ጋር ወደ ሴኬም መጣ፤ የሴኬምም
ሰዎች ተማመኑበት። 27ወደ ዕርሻ ወጥተው
ወይናቸውን ለቅመው ከጨመቁ በኋላ በአ
ምላካቸው ቤት የደስታ በዓል አደረጉ፤ በዚ
ያም እየበሉና እየጠጡ አቤሜሌክን ሰደቡ።
28የአቤድ ልጅ ገዓል እንዲህ አለ፤ "እንገ
ዛለት ዘንድ አቤሜሌክ ማነው? ሴኬምስ
ምንድን ናት? እርሱ የይሩበኣል ልጅ አይደ
ለምን? ዜቡልስ የእርሱ ረዳት ሹም አይደ
ለምን? ለሴኬም አባት ለኤሞር ሰዎች
ተገዙ፤ ለምን ለአቤሜሌክ እንገዛለን?
29ምነው ይህን ሕዝብ የማዘው እኔ በሆንሁ
ኖሮ!" አቤሜሌክን አስወግደው ነበር፤ 'ሰራ
ዊትህን አብዝተህ ውጣ!* እለው ነበር።'"
30የከተማዪቱ ገዥ ዜቡል፣ የአቤድ ልጅ
ገዓል ያለውን በሰማ ጊዜ እጅግ ተቈጣ፤
31ወደ አቤሜልክም መልእክተኞች በምስ
ጢር ልኮ እንዲህ አለ፤ "እነሆ፤ የአቤድ ልጅ
ገዓልና ወንድሞቹ ወደ ሴኬም መጥተው
ከተማዪቱ እንድትሸፍትብህ አድርገዋል።
32ስለዚህ በሌሊት ሰዎችህን ይዘህ ወጥተህ
ሜዳው ላይ ማድፈጥ አለብህ፤ 33ጠዋት
ፀሓይ ስትወጣም ወደ ከተማዪቱ ገሥ
ግሥ፤ ገዓልና ሰዎቹ ሊገጥሙህ በሚወጡበት
ጊዜ እጅህ ማድረግ የሚችለውን ሁሉ አድርግ።
34ስለዚህ አቤሜሌክና ሰዎቹ በሙሉ
በሌሊት ወጡ፤ በአራት ምድብ ሆነውም
በሴኬም አጠገብ አደፈጡ። 35የአቤድ ልጅ
ገዓል ከከተማዪቱ ወጥቶ በመግቢያው በር
ላይ ሲቆም፣ አቤሜሌክና ሰዎቹ ካደፈጡበት ወጡ።
36ገዓል ባያቸው ጊዜ ዜቡልን፣ "ተመ
ልከት፤ ከተራራው ጫፍ ሕዝብ እየወረደ ነው"
አለው። ዜቡልም መልሶ፣ "የተራሮች ጥላ
ሰዎች መስሎ ተሳስተህ" ነው። አለው።
37ገዓልም፣ "ተመልከት እንጂ! ሕዝብ እኮ

9፥24 ቍ56-57፤ ዘፍ9፥6፤ዘሌ35፥33፤ ዘዳ27፥25፤መሳ8፥30፤ 1ነገ2፥32
9፥26 ቍ28:31:41
9፥27 መሳ8፥33፤ኢ ሳ16፥10፤አሞ5፥11፣ 9፥13
9፥28 ቍ26፤ ዘፍ33፥19፤1ሳሙ25 ፥10
9፥29 ቍ38፤ 2ሳሙ15፥4
9፥32 ኢሱ8፥2
9፥33 1ሳሙ10፥7
9፥34 ኢሱ2፥5፤ መዝ32፥7፤ ኢሳ28፥15:17፤ ኤር49፥10
9፥38 ቍ28-29
9፥43 ኢሱ8፥2፤ መሳ7፥16
9፥45 ቍ20፤ ኤር48፥9
9፥46 መሳ8፥33
9፥48 መዝ68፥14

ከተራራው ወገብ ላይ እየደረሰ ነው፤ አንዱ
ክፍልም በቃላተኞች ዛፍ በኩል አድርጎ
እየመጣ ነው" ብሎ እንደ ገና ተናገረ።
38ከዚያም ዜቡል፣ "እንገዛለት ዘንድ
አቤሜልክ ማን ነው?' ብለህ የደነፋኸው
አሁን የት አለ? ያቃለልሃቸውስ ሰዎች እነዚህ
አይደሉምን? በል ውጣና ግጠማቸው" አለው።
39ገዓል የሴኬምን ሰዎች መርቶ በመውጣት
አቤሜሌክን ተዋጋው፤ 40ሆኖም አቤሜሌክ
አሳደደው፤ እስከ መግቢያው በር ድረስ ባለው
መንገድ ሲሸሹም ብዙ ሰዎች ቈስለው ወደቁ።
41አቤሜሌክ በአሩማ ተቀመጠ፤ ዜቡልም ገዓ
ልንና ወንድሞቹን ከሴኬም አስወጣቸው።
42በማግስቱ የሴኬም ሕዝብ ወደ ዕርሻ
ወጡ፤ ይህም ለአቤሜሌክ ተነገረው፤ 43እርሱም
ሰዎቹን አስከትሎ ወጣ፤ ከዚያም ሰዎቹን
ሦስት ቦታ መድቦ በዕርሻዎቹ ውስጥ አድ
ፍጠው እንዲጠባበቁ አደረገ። አቤሜሌክ
የሴኬም ሰዎች ከከተማዪቱ መውጣታቸውን
እንዳየም ካደፈጠበት ሊወጋቸው ተነሣ።
44ከዚያም አቤሜሌክና አብረውት የነበሩ
ምድቦች ቦታ ለመያዝ በፍጥነት ወደ ከተ
ማዪቱ መግቢያ በሚሮጡበት ጊዜ፣ ሌሎቹ
ሁለት ምድቦች ደግሞ እየሮጡ ሄደው በዕ
ርሻው ያሉትን ሁሉ ፈጇቸው። 45በዚያን
ዕለት አቤሜሌክ ቀኑን ሙሉ ከተማዪቱን
ሲወጋ ውሎ በመጨረሻ ያዛት፤ ሕዝቧን ፈጀ፤
ከተማዪቱንም አጠፋ፤ በላይዋም ጨው ዘራባት።
46በሴኬም ግምብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች
ይህን እንደ ሰሙ፤ በኤልበሪት ቤተ መቅደስ
ወዳለው ምሽግ ውስጥ ገቡ። 47አቤሜሌክም
በዚያ መመሸጋቸውን ሲሰማ፣ 48እርሱና
ሰዎቹ ሁሉ ወደ ሰልሞን ተራራ ወጡ፤
አቤሜሌክም መጥረቢያ ወስዶ ጥቂት የዛፍ
ቅርንጫፍ ቈረጠ፤ በትከሻውም ላይ አደረገ።
የተከተሉትንም ሰዎች፣ "ፍጠኑ፤ እኔ ሳደርግ
ያያችሁትን አድርጉ" ሲል አዘዛቸው። 49ሰዎ
ቹም ሁሉ ቅርንጫፎች ቈርጠው አቤሜሌክን
ተከተሉት፤ ቅርንጫፎቹንም ምሽጉ ላይ
አስደግፈው በመከመር ሰዎቹ በውስጡ
እንዳሉ በእሳት አቃጠሏቸው። ስለዚህ በሴኬም
ምሽግ ውስጥ የነበሩት አንድ ሺህ ያህል
ወንዶችና ሴቶች ሞቱ።

*29. ዕብርይስጡ *አቤሜሌክን እንዲህ አለው ሰራዊትህን ሁሉ ጥራ !* ይላል።

በተንኰል ይጠፋል።

9፥26 ***ተማመኑበት፤*** በአንድ ሐሳብ መርጋት የማይሆ
ንለት ሕዝብ፤ አቤሜሌክን ተከትሎ እንደ ነበር ሁሉ፣ እንዲሁም
ገዓል እንዲህ አደርጋለሁ፤ አብሮ እንዲህ እሠራለሁ እያለ
እንደበቱን በማጣፈጥ የነገራቸዉን በመስማት አብረውት ነጐዱ።

9፥27 ***በዓል አደረጉ፤*** የወይን የመከር ወቅት በዓመቱ
ውስጥ እጅግ ከፍ ያለ ደስታ ከሚደረግባቸው ጊዜያት አንዱ ነው
(ኢሳ16፥9-10፤ኤር25፥30ይመ)፤ በአሕዛብ ቤተ ጣዖት የሚደ
ረገው በዓል ግን የሰውን መንፈስ የሚያርክስ ከስካርና፣ ዝሙት
ጋር የተያያዘ ፈንጠዝያ ያለበት ነበር።

9፥28 ***ለኤሞር፤*** የሴኬምን ከተማ የቈረቈረ የኬጢያውያን
ገዥ ነው (ዘፍ33፥19፤34፥2፤ኢሱ24፥32)።

9፥32 ***ማድፈጥ፤*** በብንያም ውስጥ ያለችውን ጊብዓንና
(20፥37) ጋይን ለመያዝ የተደረገው ደፈጣ (ኢሱ8፥2) በድል
ተጠናቀቀ።

9፥34 ***በአራት ምድብ፤*** ብዙ ሆነው ካደፈጡ ሰዎች ይልቅ
ጥቂት ሆነው ያደፈጡ ሰዎችን ፈልጎ ማግኘት አስቸጋሪ ነው።
በአንጻሩ ደግሞ ከየአቅጣጫው አደጋ መጣል ጠላትን ለማጥቃት ያስችላል።

9፥37 ***ከተራራው ወገብ፤*** የሕዝ 38፥12 ማብ ይመ።
***በቃላተኞች ዛፍ፤*** ከበኣልብሪት ጋር በአንድ ዐይነት ሁኔታ የተያያዘ
የአምልኮ ዛፍ ሊሆን ይችላል (የዘፍ12፥6 ማብ ይመ)።

9፥43 ***ሦስት ቦታ መድቦ፤*** የ7፥16 ማብ ይመ።

9፥45 ***በላይዋም ጨው ዘራባት፤*** ይህንም ያደረገው ምድሪቱ
የተረገመችና ለዘላለም ምንም ሳታበቅል ምድረ በዳ ሆና እንድትቀር
ነው (ዘዳ29፥23፤ መዝ107፥33-34፤ ኤር17፥6፤ ሶፎ2፥9 ይመ)።

9፥46 ***ምሽግ፤*** ምናልባትም በቍ6 ላይ የተመለከተው ቤትሚሎ
ሳይሆን አይቀርም።

9፥49 በ***እሳት አቃጠሏቸው ፤*** የኢዮአታም ርግማን ደረሰ

50ከዚያም አቤሜሌክ ወደ ቴቤስ በመሄድ
ከተማዪቱን ከቦ ያዛት። 51ሆኖም በከተማዪቱ
ውስጥ ብርቱ ግንብ ስለ ነበር፣ የከተማዪቱ
ሕዝብ በሙሉ ወንድ ሴት ሳይባል ወደዚያ
ሸሹ፤ ደጁንም በውስጥ ዘግተው ወደ ግንቡ
ጣሪያ ወጡ። 52አቤሜሌክም ተዋግቶ ግን
ቡን ያዘ፤ ይሁን እንጂ እሳት ለመለኮስ
ወደ ግንቡ መግቢያ አጠገብ እንደ ደረሰ፣
53አንዲት ሴት ከላይ የወፍጮ መጅ በራሱ
ላይ ለቀቀችበት፤ ጭንቅላቱንም አፈረሰችው።
54ወዲያውም ጋሻ ጃግሬውን ጠርቶ፣
"'ሴት ገደለችው' እንዳይሉ እባክህ ሰይፍህን
መዘህ ግደለኝ' አለው። ስለዚህ አገልጋዩ
ወጋው፤ እርሱም ሞተ። 55እስራኤላውያንም
አቤሜሌክ መሞቱን ሲያዩ ወደየቤታቸው
ተመለሱ።
56አቤሜሌክ ሰባ ወንድሞቹን በመግደል
በአባቱ ላይ ስላደረሰው በደል እግዚአብሔር
የእጁን ከፈለው። 57በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር
የሴኬምን ሰዎች ክፋት ሁሉ በራሳቸው ላይ
መለሰው፤ የይሩበኣል ልጅ የኢዮአታም ርግ
ማን ደረሰባቸው።

## ቶላ

10 ከአቤሜሌክ በኋላ ከይሳኮር ነገድ
የሆነ የዱዲ ልጅ፣ የፉሐ ልጅ ቶላ
እስራኤልን ለማዳን ተነሣ፤ እርሱም በኰረ
ብታማው በኤፍሬም አገር ሳምር በምትባል
መንደር ይኖር ነበር። 2ቶላ በእስራኤል ላይ
ሃያ ሦስት ዓመት በፈራጅነት ከተቀመጠ
በኋላ ሞተ፤ በሳምርም ተቀበረ።

9፥50 2ሳሙ 11፥21
9፥53 2ሳሙ 11፥21
9፥54 1ሳሙ 31፥4፤ 2ሳሙ 1፥9
9፥57 ቍ 5፥24፤ መዝ 94፥23
10፥1 ዘፍ 30፥18፤ 46፥13፤ ኢሱ 15፥48፤ መሳ 6፥14፤ 8፥31
10፥3 ዘኍ 32፥41
10፥4 ዘፍ 49፥11፤ ዘሌ 32፥41፤ 1ነገ 1፥33
10፥5 ዘኍ 32፥41
10፥6 ዘፍ 10፥15፤ 19፥38፤ 26፥1፤ ዘኍ 21፥29፤ ዘዳ 32፥15፤ መሳ 2፥11፡12፡13፤ ሐዋ 27፥16
10፥7 ዘዳ 31፥17፤ 32፥30
10፥8 ኢሱ 12፥2
10፥9 ቍ 17፤ መሳ 1፥22፤ 11፥4
10፥10 ዘፀ 9፥27፤ መሳ 3፥9፤ መዝ 32፥5፤ ኤር 2፥27፤ 3፥25፤ 8፥14፤ 14፥20
10፥11 ዘፍ 14፥7፤ ዘፀ 14፥30፤ መሳ 3፥13 31
10፥12 ዘፍ 14፥7፤ ኢሱ 15፥55፤

## ኢያዕር

3ከቶላ ቀጥሎ ገለዓዳዊው ኢያዕር ተነሣ፤
እርሱም በእስራኤል ላይ ሃያ ሁለት ዓመት
በፈራጅነት[*] ተቀመጠ። 4ኢያዕር በሠላሳ አህ
ዮች የሚጋልቡ ሠላሳ ወንዶች ልጆች ነበሩት፤
ልጆቹም እስከ ዛሬ ድረስ የኢያዕር መንደ
ሮች ተብለው የሚጠሩ ሠላሳ ከተሞች በገ
ለዓድ ምድር ነበሯቸው። 5ኢያዕር ሞተ፤
በቃሞንም ተቀበረ።

## ዮፍታሔ

6እስራኤላውያን እንደ ገና በእግዚአብሔር
ላይ ክፉ ድርጊት ፈጸሙ፤ በኣልንና አስታ
ሮትን እንዲሁም የሶሪያን፣ የሲዶናን፣
የሞዓብን፣ የአሞንንና የፍልስጥኤማውያንን
አማልክት አመለኩ፤ እስራኤላውያን እግዚ
አብሔርን ስለተወውና ስላላገለገሉት፣ 7ተቈ
ጣቸው፤ በፍልስጤማውያንና በአሞናውያን
እጅ ሸጣቸው፤ 8እነርሱም በዚያን ዓመት
ሰበሯቸው፤ አደቀቋቸውም፤ እስራኤላውያንን
ሁሉ ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ባለው በገለ
ዓድ ምድር፣ 9በአሞራውያን አገር ዐሥራ
ስምንት ዓመት እንዲሁም አሞናውያን ይሁ
ዳን፣ ብንያምንና የኤፍሬምን ቤት ለመ
ውጋት ዮርዳኖስን ስለ ተሻገሩ እስራኤላውያን
እጅግ ተጨነቁ። 10ከዚያም እስራኤላውያን፣
አንተን አምላካችንን በመተው የበኣልን
አማልክት በማምለካችን አንተን በድለናል"
ብለው ወደ እግዚአብሔር ጮኹ።
11እግዚአብሔርም መልሶ እንዲህ አላቸው፤

[*]2 በዚህና በቍጥር 3 ላይ በትውፊት መሳፍንት ይባላል።

ማለት ነው (ቍ20)።

9፥53 ***ሴት፤*** ወንዶች በቀስት፣ በፍላጻና በጦር ሲዋጉ ሴቶች ደግሞ በቅጥሩ አጠገብ ካለው የጠላት ጦር ላይ ከባድ የድንጋይ ናዳ በመልቀቅ ምሽጉ እንዳይያዝ ይረባረቡ ነበር። ***የወፍጮ መጅ፤*** የ3፥16 ማብ ይመ። የወፍጮ መጅ ክብ ሆኖ ከመሀከሉ ቀዳዳ ያለው ሲሆን እህል መፍጨት ለሴቶች ድርሻ በመሆኑ (16፥21 ይመ)፣ ሥራውን የሚሠሩት ሴቶች ነበሩ (ዘፀ11፥5 ይመ)። እንግዲህ አቤሜሌክ በሴት እጅ ተራ በሆነ ነገር ተመቶ የሞተው በዚህ ሁኔታ ነበር (እንዲሁም 4፥21 ይመ)።

9፥54 ***ጋሻ ጃግሬውን፤*** በዚያን ዘመን አንድ የጦር መሪ ጋሻና ጦሩን አንግቦ እንዲከተለው ወጣት የሆነ ሰው መመደቡ የተለመደ ነበር (1ሳሙ14፥6፤31፥4 ይመ)። ***ሴት ገደለችው፤*** የአንድ ወታደር በሴት እጅ መገደል እንደ ውርደት የሚቈጠር ነበር። ከዚህ የተነሣ ነበር የአቤሜሌክ የውርደት አሟሟት ለብዙ ጊዜ ሲወሣ የቈየው (2ሳሙ 11፥21)።

9፥56 ***እግዚአብሔር የእጁን ከፈለው፤*** የአቢሜሌክ ድርጊት ከእግዚአብሔር የተሰወረ አልነበረም፤ እውነተኛ የእስራኤል ንጉሥ እርሱ ስለ ሆነ አቢሜሌክ ባደረገው ክፋትና በደል የእጁን አግኝቶ የውርደት አሟሟት እንዲሞት አደረገው።

9፥57 ***የኢዮአታም ርግማን፤*** ቍ20 ይመ።

10፥1 ***ከይሳኮር ነገድ የሆነ ... የፉሐ ልጅ ቶላ፤*** ቶላና ፉሐ ስማቸውን የወረሱት ከሁለቱ የይሳኮር ልጆች ነው (ዘፍ 46፥13፤ ዘኍ26፥23፤1ዜና 7፥1)።

10፥3 ***ኢያዕር፤*** ኢያዕር የመጣው ከገለዓድና ከምናሴ ምድር ስለ ነበርና ስሙም የምናሴ ዘር ከነበረው ሰው ጋር ሞክሼ ስለሆነ (በዘኍ32፥41፤ዘዳ3፥14፤1ነገ4፥13)፣ እርሱ ራሱም ከምናሴ ነገድ ይመስላል።

10፥4 ***ሠላሳ አህዮች...፤ ሠላሳ ወንዶች ልጆች... ሠላሳ ከተሞች፤*** ሀብታምና የተከበረ ሰው እንደነበር ያመለክታል።

***10፥6-12፥7፤*** በዚህ ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ ፊቱን ወደ ዮፍታሔ አዞረ፤ ዮፍታሔም በማኅበረሰቡ ዘንድ የተጠላና ከእስራኤል ምድረ ርስት የተነቀለ፣ ከአገር ተባርሮም ሸፍቶ የኖረ ሰው ነበር። የዮፍታሔ ታሪክ በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ ከተጻፉት ከሌሎቹ መሪዎች ታሪክ ጋር ሲነጻጸር ከዲቦራ ታሪክ ጋር ብቻ ይመስላል (የ4፥1-5፥31 ማብ ይመ)

10፥6 ***የሶርያን...አማልክት፤*** የሶርያ ዋናዎቹ አማልክት ሐዳድ (በኣል) ፣ ሞት፣ አናትና ሪሞን የሚባሉ ናቸው። ***የሲዶና... አማልክት፤*** ሲዶናውያን ያመልኩ የነበሩት ከነዓናውያን የሚያመልኳቸውን አማልክት ነበር (የ2፥11፡13 ማብ ይመ)። ***የሞዓብን... አማልክት፤*** ዋናው የሞዓብ አምላክ ካሞሽ ይባላል። ***የአሞንን...አማልክት፤*** የአሞናውያን አምላክ ደግሞ ሞሎክ ይባል ነበር (1ነገ11፥7 ይመ)። ለዚህ አምላክ አንዳንድ ጊዜ የሰው ልጆችን መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ ያመልኩት ነበር (ዘሌ 18፥21፤20፥2-5፤2ነገ23፥10)። ይህ አምላክ በዕብራይስጥ ሚልክም በሚል ስም ይታወቃል። ሞሉክ ወይም ሚልክም የሚለው ስም በሴማውያን ቋንቋ "ንጉሥ" ከሚለው ቃል ጋር አንድ ነው። ***የፍልስጥኤማውያንን አማልክት፤*** ፍልስጥኤማውያን አብዛኞቹን የከነዓናውያንን አማልክት ያመልኩ የነበረ ሲሆን፣ ነገር ግን ዳጎንና ብዔልዜቡል ለተባሉት አማልክት ያላቸው ፍቅርና አክብሮት እጅግ ከፍ ያለ ነበር። ዳጎን የሚለው ስም በዕብራይስጥ "እህል" ከሚለው ቃል ጋር አንድ ነው፤ ምናልባት ይህ አምላክ የዕጽዋት አምላክ እንደሆነ ይጠቍማል። ይህ አምላክ ከሁለት ሺህ ዓ.ቅ.. ክ ጀምሮ በባቢሎን ይመለክ ነበር። ብዔልዜቡል የሚመለከው ደግሞ በአቃሮን (2ነገ1፥2-3፡6፡16) ነበር። የዚህ ስም ትርጒምም የዝንብ "ጌታ" ማለት ሲሆን፣ በጥንት የከነዓናውያን ጽሑፎች "የበኣል ልዑል" በመባል የሚታወቀው ብዔልዜቡልን ለማቃለልና ለእርሱ የሚደረገውን አምልኮ በማንኳሰስ (ማቴ 10፥25፡ 12፥24ይመ)፣ የእውነተኛው አምላክ የያህዌ ተከታዮች ይህን ስም ሆን ብለው በመለወጥ በዚህ (የዝንብ ጌታ) እንዲጠራ አደረጉ።

10፥7 ***ፍልስጥኤማውያን፤*** የፍልስጥኤማውያን የጭቈና ታሪክ በ13፥1 ላይ እንደ ገና ሲቀጥል ይታያል።

10፥11 ***እግዚአብሔርም መልሶ እንዲህ አላቸው፤*** የ2፥1 ማብ ይመ። እስራኤላውያን በከነዓን ምድር መከራና ሥቃይ ካሳዩአቸው ጨቋኞች እጅ ነጻ ያወጣቸውን አምላክ ስለ ረሱ እግዚአብሔር ገሠጻቸው የ2፥16-19፤ የ6፥8 ማብ ይመ።

"ግብፃውያን፣ አሞራውያን፣ አሞናውያን፣
ፍልስጥኤማውያን፣ 12ሲዶናውያን፣ አማሌቃው
ያንና ማየናውያን* አሠቃዩአችሁ፤ እናንተም
እንድረዳችሁ ወደ እኔ ጮኻችሁ፤ ታዲያ እኔ
ከእጃቸው አላዳንኋችሁምን? 13እናንተ ግን
እኔን ትታችሁ ሌሎች አማልክትን አመ
ለካችሁ፤ ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲያ አላድ
ናችሁም፤ 14 ሂዱና ወደ መረጣችኋቸው አማ
ልክት ጩኹ፤ መከራ በሚያገኛችሁ ጊዜ
እስቲ ያድኗችሁ!"

15እስራኤላውያንም እግዚአብሔርን፣ "ኀጢ
አት ሠርተናል፤ መልካም መስሎ የታየህን
አድርግብን፤ እባክህን የዛሬን ብቻ አድነን"
አሉት:: 16ከዚያም በመካከላቸው ያሉትን
ባዕዳን አማልክት አስወገዱ፤ እግዚአብሔ
ርንም አመለኩ፤ እግዚአብሔርም የእስራ
ኤልን ጕስቍልና ሊታገሠው የማይቻለው
ሆነ::

17አሞናውያን ለጦርነት ዝግጁ ሆነው
በገለዓድ በሰፈሩ ጊዜ፣ እስራኤላውያንም እን
ደዚሁ ተሰብስበው በምጽጳ ሰፈሩ:: 18የገለዓድ
ሕዝብ አለቆችም እርስ በእርሳቸው፣ "በአሞ
ናውያን ላይ ጦርነቱን የሚጀምር ሰው በገለዓድ
ነዋሪዎች ሁሉ ላይ አለቃ ይሆናል" ተባባሉ::

11 ገለዓዳዊው ዮፍታሔ ኀያል ጦረኛ
ነበረ፤ አባቱ ገለዓድ ነበር፤ እናቱም
ጋለሞታ ነበረች:: 2እንደዚሁም የገለዓድ
ሚስት ለገለዓድ ወንዶች ልጆች ወለደች
ለት፤ እነርሱም ባደጉ ጊዜ ዮፍታሔን "ከሌላ
ሴት ስለ ተወለድህ ከቤተሰባችን ምንም ዐይ
ነት ውርስ አይገባህም" በማለት አሳደዱት::
3ስለዚህም ዮፍታሔ፣ ከወንድሞቹ ሸሽቶ
መኖሪያውን ጦብ በተባለች ምድር አደረገ፤
እዚያም ወሮበሎች ተሰባስበው ተከተሉት::
4ከጥቂት ጊዜ በኋላም አሞናውያን በእስ
ራኤል ላይ ጦርነት ባደረጉ ጊዜ፣ 5የገለዓድ
አለቆች ዮፍታሔን ለማምጣት ወደ ጦብ
ምድር ሄዱ:: 6እነርሱም፣ "ከአሞናውያን
ጋር መዋጋት እንችል ዘንድ መጥተህ
ምራን" አሉት::

7ዮፍታሔም፣ "ምነው ጠልታችሁኝ ከአባቴ
ቤት አሳዳችሁኝ አልነበረምን? ታዲያ አሁን
ችግር ሲገጥማችሁ ነው የምትፈልጉኝ?"
አላቸው::

8የገለዓድ አለቆችም፣ "እንግዲህ አሁን
ወደ አንተ መጥተናል፤ አሞናውያንን እንድ
ንወጋ በል ተነሥና አብረን እንሂድ፤ በገለ
ዓድ በምንኖረው በሁላችንም ላይ አለቃ ትሆ
ናለህ" አሉት::

9ዮፍታሔም፣ "አሞናውያንን ለመውጋት
ወደ አገሬ ብትመልሱኝና እግዚአብሔር በእጄ
አሳልፎ ቢሰጣቸው በእርግጥ አለቃችሁ
እሆናለሁ?" ሲል ጠየቃቸው::

10የገለዓድ አለቆችም፣ "እግዚአብሔር
ምስክራችን ነው፤ ያልከውንም በእርግጥ እናደ
ርጋለን" አሉት:: 11ስለዚህ ዮፍታሔ ከገለዓድ
አለቆች ጋር ሄደ፤ ሕዝቡም በላያቸው ላይ
አለቃና አዛዥ አደረጉት፤ ዮፍታሔም የተና
ገረውን ቃል ሁሉ ምጽጳ ላይ በእግዚአብሔር
ፊት ደገመው::

12ከዚያም ዮፍታሔ ወደ አሞናውያን
ንጉሥ፣ "ከእኔ ጋር ምን ጠብ ቢኖርህ ነው
መጥተህ አገሬን የወጋኸው?" በማለት መል
እክተኞች ላከ::

13የአሞናውያንም ንጉሥ ለዮፍታሔ መልእ
ክተኞች፣ "ይህን ያደረግሁት እስራኤል ከግ
ብፅ በወጣ ጊዜ በአርኖንና በያቦቅ ወንዞች
መካከል ያለውንና እስከ ዮርዳኖስ ያለውን
አገሬን ስለ ወሰዱብኝ ነው፤ አሁንም
በሰላም መልሱልኝ" አላቸው::

14ዮፍታሔም መልእክተኞቹን እንደ ገና

*12. አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች ምድያማውያን ይላሉ::

መሳ4፥3
10፥13 ዘዳ32፥15፤ ኤር11፥10፤13፥10
10፥14 ኢሳ32፥37፤ኢሳ44፥17፥57፥13፤ኤር2፥28፤11፥12፤ዕን2፥18
10፥15 1ሳሙ3፥18፤ 2ሳሙ10፥12፤15፥26፤ኢዮ1፥21፤ኢሳ39፥8
10፥16 ዘዳ32፥36፤ ኢሱ24፥23፤ ኢሳ63፥9፤ኤር18፥8
10፥17 ዘፍ31፥49፤ መሳ11፥29
10፥18 ሳ11፥8:9
11፥1 ዘፍ38፥15፤ ዘኍ26፥29፤መሳ6፥12፤12፥1፤1ሳሙ12፥11፤ዕብ11፥32
11፥3 ቍ5፤ መሳ11፥8:9
11፥4 መሳ10፥9
11፥7 ዘፍ26፥16
11፥8 መሳ10፥18
11፥10 ዘፍ31፥50፤ ኢሳ1፥2
11፥11 ዘፀ19፥9፤ ኢሱ11፥3፤1ሳሙ8፥4፥21፤2ሳሙ3፥17
11፥13 ዘኍ21፥13፡24
11፥15 ዘዳ2፥9፡ 19
11፥16 ዘፍ14፥7፤

10፥12 ***ማየናውያን፤*** አማርኛ ትርጕም ይመ:: ምናልባትም ምዑናውያን ከሚለው ጋር አንድ ሊሆን ይችላል:: እነዚህ ከፍልስጥኤማውያንና ከዐረቦች ጋር ሆነው እስራኤልን የሚቃወሙ ናቸው (2ዜና 26፥7)::

10፥17 ***ምጽጳ፤*** ትርጕሙ፣ "የመጠበቂያ ማማ" ማለት ነው:: በዚህ ስም የሚጠሩ አያሌ ቦታዎች አሉ፤ የዮፍታሔ ዋና የጦር ሰፈር ወይም ምሽግ የሚገኘው በገለዓድ ሲሆን (11፥11)፣ ይህም "የገለዓድ ምጽጳ" በመባል ይጠራል (11፥29)፤ የገለዓድ ምጽጳ፣ ምናልባትም ራማት ምጽጳ ከተባለው ጋር አንድ ሳይሆን አይቀርም (ኢ.ሱ. 13፥26)፤ ይህም የሚገኘው ከቤትሳን 48 ኪ.ሎ ሜትር ያህል ርቆ ነው::

10፥18 ***ሕዝብ፤*** የሚዋጉ ማለት ነው፤ ከአሞናውያን በድንገት የሚጣልባቸውን አደጋ ለመቋቋም ገለዓዳውያን ፈለጉ፤ ይሁን እንጂ ይህን ጉዳይ በልበ ሙሉነት ወደ ፊት የሚገፋ የጦር መሪ ማግኘት አልቻሉም::

11፥1 ***እናቱም ጋለሞታ ነበረች፤*** ዮፍታሔ፣ "ይህ የጋለሞታ ልጅ" እየተባለ በኅብረተ ሰቡ ዘንድ ስፍራ አልነበረውም::

11፥3 ***ጦብ፤*** የጦብ ሰዎች ከጊዜ በኋላ ከአሞናውያን ጋር ተባብረው ዳዊትን ሊወጉ ተነሥተው ነበር (2ሳሙ 10፥6-8):: ***ወሮበሎች፤*** የ9፥4 ማብ ይመ::

11፥8 ***በሁላችንም ላይ አለቃ ትሆናለህ፤*** የገለዓድ ሰዎች ከአሞናውያን ጋር በተደረገው ጦርነት የመሪነቱን ቦታ ለዮፍታሔ በመስጠት ብቻ ሳይወሰኑ (ቍ6) ጦርነቱ ካበቃ በኋላም አለቃቸው ሆኖ እንዲያስተዳድራቸው ጠየቁት::

*11፥11፤* መሪዎቹ ያቀረቡትን ሐሳብ ሕዝቡ አሜን ብሉ ተቀበለው፤ ይህም ሳዖልን (1ሳሙ 11፥15)፣ ሮብዓምን (1ነገ 12፥1) እንዲሁም ኢዮርብዓምን (1ነገ12፥20) ለመምረጥ በተፈጸመው ሂደት መሠረት ተከናወነ::

11፥13 ***አገሬን፤*** እስራኤላውያን በመጀመሪያ ወደ ከነዓን ምድር ለመግባት በተቃረቡበት ጊዜ፣ ምድሪቱ ትገዛ የነበረው በአሞራውያን ንጉሥ በሴዎን ሲሆን እርሱም የወሰደው ከሞዓባውያን ነበር (ዘኍ21፥29):: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አሞናውያን፣ ሞዓብን መቈጣጠር ስለ ቻሉ፣ ቀድሞ የሞዓብ የነበረውንም ግዛት ሁሉ የራሳቸው አድርገው በመቍጠር የይገባኛል ጥያቄ አቀረቡ::

*11፥14-27፤* ዮፍታሔ በዘመኑ በነበረው የመንግሥታት ግንኙነት መመሪያ መሠረት መልስ ሰጠ:: የደብዳቤው ይዘት ሲጤን በጊዜው የነበረው የመንግሥታት መሪዎች የደብዳቤ ልውውጥ ምን ይመስል እንደ ነበር የሚያመለክት ነው:: እንዲሁም በዚያን ጊዜ በሁሉም ዘንድ እንደሚታመነው የአንዱን አገር ዳር ድንበር የሚከልልና የሚጠብቅ የሚነሣውም የወሰን ግጭትና ጥያቄ ሁሉ ተገቢውን ውሳኔ የሚሰጥ በየአገሩ የሚመለከው አምላክ እንደ ነበር፣ ደብዳቤው በሚገባ ያንጸባርቃል:: ዮፍታሔ ምድሩ የእስራኤል መሆኑን ለማሳመን ሦስት የመከራከሪያ ነጥቦች አቅርቦአል፤ እነዚህም (1) እስራኤል ምድሩን የወሰደችው ከአሞራውያን ንጉሥ ከሴዎን እንጂ ከአሞናውያን አለመሆኑን (ቍ15-22)፤ (2) ምድሪቱን ለእስራኤል የሰጣቸው እግዚአብሔር መሆኑን (ቍ23፥25)፤ (3) ምድሪቱ የእስራኤል ይዞታ ሆና ለብዙ ዘመናት መቈየቷን (ቍ26-27) ናቸው::

ወደ አሞናውያን ንጉሥ ላካቸው፤ 15እንዲሁም
አላቸው፤ "ዮፍታሔ እንዲህ ይላል፤ እስራ
ኤል የሞዓብንም ሆነ የአሞናውያንን ምድር
አልወሰደም። 16እስራኤል ከግብፅ በወጣ ጊዜ
በምድረ በዳ አድርጎ ወደ ቀይ ባሕር[T]
ከዚያም ወደ ቃዴስ ሄደ። 17እስራኤልም
ወደ ኤዶም ንጉሥ፣ 'በአገርህ እንዳልፍ እባ
ክህ ፍቀድልኝ' በማለት መልእክተኞችን ላከበት፤
የኤዶም ንጉሥ ግን አልሰማውም። ለሞዓብ
ንጉሥም እንደዚሁ ላከበት፤ እርሱም አልተ
ቀበለውም፤ ስለዚህ እስራኤል በቃዴስ ተቀ
መጠ።

18"ቀጥሎም የኤዶምንና የሞዓብን ምድር
በመዞር፣ በምድረ በዳው ተጕዞ ከሞዓብ
በስተ ምሥራቅ በኩል በማለፍ ከአርኖን
ማዶ ሰፈረ፤ የሞዓብም ድንበር አርኖን ስለ
ነበር ወደ ሞዓብ ክልል አልገባም።

19"ከዚያም እስራኤል በሐሴቦን ወዳለው
ወደ አሞራውያን ንጉሥ ወደ ሴዎን መልእ
ክተኞች ልኮ፣ 'ወደ ገዛ ስፍራችን ለመሄድ
በአገርህ እንዳልፍ ፍቀድልኝ' አለው። 20ሴዎን
ግን በግዛቱ እንዲያልፍ ለመፍቀድ እስራ
ኤልን አላመነውም[ሀ]፤ ሰራዊቱንም ሰብስቦ
በያሃድ ከሰፈረ በኋላ ከእስራኤል ጋር ተዋጋ።

21"ከዚያም የእስራኤል አምላክ *እግዚ
አብሔር* ሴዎንንና ሕዝቡን ሁሉ በእስራኤል
እጅ አሳልፎ ሰጣቸው፤ አሸነፏቸውም፤ እስ
ራኤልም በዚያ አገር የሚኖሩትን የአሞራ
ውያንን ምድር በሙሉ ወረሰ፤ 22ከአርኖን
እስከ ያቦቅ፣ ከምድረ በዳው እስከ ዮርዳኖስ
ድረስ ያለውን ምድር በሙሉ ወረሱ።

23እንግዲህ የእስራኤል አምላክ *እግዚ
አብሔር* አሞራውያንን ከሕዝቡ ከእስራኤል
ፊት አሳዶ ካስወጣቸው፣ አንተ ለመውሰድ
ምን መብት አለህ? 24አምላክህ ካሞሽ የሰጠህን
ይዞ ማቈየቱ ያንተ ፈንታ ነው፤ እኛም እንደዚሁ
አምላካችን *እግዚአብሔር* የሰጠንን ሁሉ
ርስት አድርገን እንወርሳለን። 25አንተ ከሞዓብ
ንጉሥ ከሴፎር ልጅ ከባላቅ ትበልጣለህን?
ለመሆኑ እርሱ ከእስራኤል ጋር ተጣልቶአልን?
ወይስ ተዋግቶአልን? 26እስራኤልም በሐሴቦንና
በመንደሮቿ፣ በአሮዔርና[‘] በመንደሮቿ፣ በአ
ርኖንም አቅራቢያ ባሉት ከተሞች ሁሉ ሦስት
መቶ ዓመት ተቀምጦ በነበረበት በዚያን ጊዜ
ስለ ምን አልወሰዳችኋቸውም ነበር? 27እኔ
አልበደልሁህም፤ አንተ ግን በእኔ ላይ ዘም
ተህ በድለኸኛል፤ እንግዲህማ ፈራጁ[^] *እግዚ
አብሔር* በእስራኤላውያንና በአሞናውያን
መካከል ዛሬ ይፍረድ።"

28የአሞን ንጉሥ ግን ዮፍታሔ የላከውን
መልእክት ከምንም አልቈጠረውም።

29ከዚያም *የእግዚአብሔር* መንፈስ በዮፍ
ታሔ ላይ ወረደ፤ ተነሥቶም ገለዓድንና
ምናሴን አቋርጦ ሄደ፤ ገለዓድ ባለችው በምጽጳ
በኩል አድርጎም በአሞናውያን ላይ ዘመተ
ባቸው። 30ዮፍታሔም እንዲህ ሲል *ለእግዚ
አብሔር* ተሳለ፤ "አሞናውያንን በእጄ አሳል
ፈህ ብትሰጠኝ፣ 31አሞናውያንን ድል አድርጌ
በምመለስበት ጊዜ በመጀመሪያ ሊቀበለኝ
ከቤቴ ደጅ የሚወጣው ማንኛውም ሰው
*ለእግዚአብሔር* ይሆናል፤ እኔም የሚቃጠል
መሥዋዕት አድርጌ አቀርበዋለሁ።"

32ከዚያም ዮፍታሔ አሞናውያንን ለመ
ውጋት ወጣ፤ እግዚአብሔርም እርሱን በእጁ
አሳልፎ ሰጠው። 33ከአሮዔር አንሥቶ እስከ
ሚኒት አካባቢ ከዚያም አልፎ እስከ ክራ
ሚም የሚገኙትን ሃያ ከተሞች ፈጽሞ አጠ
ፋቸው፤ አሞናውያንም ለእስራኤል ተገዙ።

34ዮፍታሔ ምጽጳ ወዳለው ቤቱ ተመለሰ፤
እነሆ፤ ልጁ አታሞ እየደለቀች በመዝፈን
ልትቀበለው ወጣች፤ እርሷም አንዲት ልጁ
ብቻ ነበረች፤ ከእርሷ በቀር ወንድም ሆነ
ሴት ልጅ አልነበረውም። 35ባያትም ጊዜ
ልብሱን በመቅደድ፣ "ወይኔ ልጄ ጉድ አደ
ረግሽኝ! ጭንቅም ላይ ጣልሽኝ፤ ማስቀረት የማ
ልችለውን ስእለት *ለእግዚአብሔር* ተስያለሁና"
ብሎ በሐዘን ጮኸ።

ዘኁ14፥25፤ዘዳ1፥40
11፥17 ቍ19፤ ዘፍ32፥3፤ዘኁ20፥14:17፤ኢሱ24፥9፤ ኤር48፥1
11፥18 ዘኁ20፥21፤ 21፥13፤ዘዳ2፥8
11፥19 ቍ17፤ ዘኁ21፥21-22፤ ኢሱ12፥2
11፥20 ዘኁ21፥23
11፥22 ዘኁ21፥21-26፤ዘዳ2፥26
11፥24 ዘዳ2፥36፤ ኢሱ3፥10፤ ዘኁ21፥29
11፥25 ዘኁ22፥2፤ ኢሱ24፥9
11፥26 ዘኁ21፥25፤ 32፥34፤ኢሱ13፥9
11፥27 ዘፍ16፥5፤ 18፥25፤ 2ዜና20፥12
11፥29 ዘፍ31፥49፤ መሳ3፥10፤ መሳ10፥17
11፥30 ዘፍ28፥20፤ ዘኁ30፥10፤1ሳሙ1፥21፤ምሳ31፥2
11፥31 ዘፍ8፥20፤ 28፥21፤ዘሌ1፥3፤ መሳ13፥16
11፥33 ሕዝ27፥17
11፥34 ዘፍ31፥27፤ ዘፀ15፥20፤ኤካ12፥10
11፥35 ዘኁ14፥6፤ 30፥2፤ዘዳ23፥21፤ መክ5፥2:4:5

[T]16. ዕብራይስጡ *ያም ሱፍ* ይላል ይህም የደንገል ባሕር ማለት ነው።
[ሀ]20. ወይም ከእስራኤል ጋር አልተስማማም ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።
[^]27. ወይም *መሪው* ተብሎ ሊተረጉም ይችላል።

11፥16 ***ቃዴስ፤*** ቃዴስ በርኔ ለማለት ነው፤ የዘኁ20፥1ማብ ይመ።

11፥21 ***የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር፤*** ጦርነት፣ በጦር ሜዳ የሚደረገውን ፍልሚያ ብቻ የሚያመለክት ሳይሆን፣ በአማልክትም መካከል የትኛው አሸናፊ እንደሚሆን የሚለይበት ነበር (ቍ 24፤ዘፀ12፥12፤ ዘኁ33፥4 ይመ)።

11፥24 ***ካሞሽ፤*** የሞዓባውያን ዋናው አምላክ መጠቀሱ፣ በዚያን ጊዜ የአሞን ንጉሥ ሞዓብንም ጨምሮ መግዛቱን አለያም በሁለቱ ሕዝቦች መካከል የጋራ የጦር ቃል ኪዳን ስምምነት መኖሩን ያመለክታል።

11፥25 ***ባላቅ፤*** ዘኁ ም 22-24 ይመ።

11፥26 ***ሦስት መቶ ዓመት፤*** በመጽሐፈ መሳፍንት ለተ ወሣው ነገር ትክክለኛውን ጊዜ ለመመልከት፣ ይህ ሐረግ አስ ፈላጊ እንደ ሆነ ለመገንዘብ የመግቢያን "ታሪካዊ ዳራ" የሚለ ውን ይመ።

11፥27 ***ፈራጁ፤*** 1ሳሙ24፥15 ይመ። እግዚአብሔር እውነ ተኛ ፈራጅ እንደ መሆኑ መጠን የመጨረሻውን ፍርድ የሚሰጥ እውነተኛ ዳኛ እርሱ ብቻ ነው። በመሠረቱ ለዚህ መጽሐፍ የተሰጠው "መሳፍንት" የሚለው ስም ከግእዝ የተወረሰ እንጂ የአማርኛ ቃል አይደለም፤ ይህ ቃል በቀጥታ ወደ አማርኛ ቢመለስ "ፈራጆች" ማለት ነው። በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ በነጠላ ቍጥር "ፈራጅ" ተብሎ የተነገረ ቃል ቢኖር እዚህ ቦታ ላይ ብቻ ነው፤ ይህም የእስራኤል ሕዝብ እውነተኛ ፈራጅ ለሆነው ለእግዚአብሔር የተነገረ ነው።

11፥29 ***የእግዚአብሔር መንፈስ፤*** የ3፥10 ማብ ይመ። በብሉይ ኪዳን አንድ ሰው ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ተልእኮ በሚገባ መወጣት እንዲችል አስቀድሞ ልዩ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ኀይል ይሰጠው ነበር።

11፥30 ***ተሳለ፤*** እንዲህ ማድረግ በእስራኤላውያን ዘንድ የተለመደ ነበር (ዘፍ28፥20፤1ሳሙ1፥11፤ 2ሳሙ 15፥8)፤ የስእለ ቱን ዐይነት በተመለከተ የተለያዩ አስተያየቶች ይሰጣሉ፤ ይሁን እንጂ ቍ31 ስእለቱ የሚቃጠል መሥዋዕት መሆኑን ያመለክታል። ይህም ዮፍታሔ ምናልባት ልጁን የሚቃጠል የሰው መሥዋዕት አድርጎ አቅርቦአል ከሚል መደምደሚያ ላይ ያደርሳል (ቍ39)። ከአፍ የወጣ አፋፍ፣ ደግሞም የተተፋ ምራቅ ተመልሶ አይዋጥም እንደሚባለው ምሳሌ፣ አፍ የተናገረው ስእለት በምንም ዐይነት መቅረት ስለማይችል መፈጸም ነበረበት (ዘኁ30፥2፤ ዘዳ23፥21-23 እንዲሁም መክ 5፥4-5 ይመ)።

11፥34 ***በመዝፈን፤*** ሰዎችን ድል አድርጎ የሚመለሰውን ሠራዊት ሴቶች በዚህ ሁኔታ መቀበላቸው የተለመደ ነበር (ዘፀ15፥20፤ 1ሳሙ18፥6 ይመ)።

11፥35 ***ልብሱን በመቅደድ፤*** ከባድ ሐዘን የሚገለጥበት

[36]እርሷም እንዲህ አለች፤ "አባቴ ሆይ፤
መቼም አንዴ ለእግዚአብሔር ቃል ገብተሃል፤
ጠላቶችህን አሞናውያንን አሁን እግዚአብሔር
ተበቅሎልሃልና ቃል የገባኸውን ፈጽምብኝ::
[37]ነገር ግን አንድ ነገር ብቻ እንድትፈቅድልኝ
እለምንሃለሁ፤ ከእንግዲህ ባል ስለማላገባ
ከባልንጀሮቼ ጋር ወደ ተራሮች ወጥቼ እየ
ዞርሁ ሁለት ወር እንዳለቅስ አሰናብተኝ::"
[38]እርሱም፣ "በይ ሂጂ" ብሎ ለሁለት
ወር አሰናበታት፤ እርሷም ከእንግዲህ ባል
ስለማታገባ ከልጃገረድ ጓደኞቿ ጋር ወደ
ተራሮች ሄደው አለቀሱ:: [39]ከሁለት ወር
በኋላ ወደ አባቷ ተመለሰች፤ እርሱም የተሳ
ለውን አደረገ፤ ድንግልም ነበረች::
ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ በእስራኤል
ልማድ ሆኖ፣ [40]የእስራኤል ወጣት ሴቶች
የገለዓዳዊውን የዮፍታሔን ልጅ በማሰብ በየዓ
መቱ እየወጡ የአራት ቀን ሐዘን ያደርጉ
ላታል::

## የዮፍታሔና ኤፍሬም

12 የኤፍሬም ሰዎች ኀይላቸውን አሰባ
ስበው ወደ ጻፎን በመሻገር ዮፍ
ታሔን፣ አሞናውያንን ለመውጋት ስትወጣ
አብረንህ እንድንሄድ ያልጠራኸን ለምንድን
ነው? ቤትህን በላይህ ላይ እናቃጥለዋለን አሉት::"
[2]ዮፍታሔም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
"እኔና ሕዝቤ ከአሞናውያን ጋር ከፍተኛ
ትግል ገጥመን በነበረበት ጊዜ ጠርቼያችሁ
ከእጃቸው አላዳናችሁኝም፤ [3]እኔም እንደ
ማትረዱኝ በተረዳሁ ጊዜ በሕይወቴ ቈርጬ
አሞናውያንን ለመውጋት ተሻገርሁ፤ እግዚ
አብሔርም ድሉን ሰጠኝ፤ ታዲያ ዛሬ እኔን
ለመውጋት የመጣችሁት ለምንድን ነው?"
[4]ከዚያም ዮፍታሔ የገለዓድን ሰዎች አሰ
ባስቦ ከኤፍሬም ጋር ተዋጋ:: ኤፍሬማውያን
ገለዓዳውያንን፣ "እናንተ ገለዓዳውያን ከኤፍ
ሬምና ከምናሴ የከዳችሁ ናችሁ" ይሏቸው
ስለ ነበር በብርቱ መቷቸው:: [5]ገለዓዳውያን
ወደ ኤፍሬም የሚያሻግሩትን የዮርዳኖስን
መልካዎች ያዙ፤ ታድያ አምልጦ የሚሸሽ
አንድ ኤፍሬማዊ ለመሻገር በሚጠይቃቸው
ጊዜ፣ የገለዓድ ሰዎች "አንተ ኤፍሬማዊ
ነህ?" ብለው ይጠይቁታል፤ ያም ሰው፣ "አይ
ደለሁም" ብሎ ከመለሰላቸው፣ [6]እስቲ
"ሺቦሌት" በል ይሉታል፤ ታዲያ ቃሉን በት
ክክል ማለት ሳይችል ቀርቶ "ሲቦሊት" ካለ
ይዘው እዚያው እመልካው ላይ ይገድሉታል፤
በዚያ ጊዜም አርባ ሁለት ሺህ ኤፍሬማውያን
ተገደሉ:: [7]ዮፍታሔ በእስራኤል ላይ ለስድ
ስት ዓመት ፈራጅ[ሐ] ሆነ:: ገለዓዳዊው ዮፍ
ታሔ ሞተ፤ ከገለዓድም ከተሞች በአንዲቱ
ተቀበረ::

## ኢብጻን፣ ኤሎም፣ ዓብዶን

[8]ከዮፍታሔ ቀጥሎ የቤተ ልሔሙ ኢብ
ጻን በእስራኤል ላይ ፈራጅ ሆነ:: [9]እርሱም
ሠላሳ ወንዶችና ሠላሳ ሴቶች ልጆች
ነበሩት:: ሴቶች ልጆቹንም ከጐሣው ውጭ
ለሆኑ ሰዎች ዳራቸው፤ ከጐሣው ውጭ የሆኑ
ሠላሳ ልጃገረዶች አምጥቶ ከወንዶች ልጆቹ
ጋር አጋባቸው:: ኢብጻን በእስራኤል ላይ
ሰባት ዓመት ፈራጅ ሆነ:: [10]ኢብጻን ሞተ፤
በቤተ ልሔምም ተቀበረ::
[11]ከእርሱም በኋላ ዛብሎናዊው ኤሎም
በእስራኤል ላይ ዐሥር ዓመት ፈራጅ ሆነ::
[12]ከዚያም ኤሎም ሞተ፤ በዛብሎን ምድር
በኢያሎን ተቀበረ::
[13]ከኤሎም ቀጥሎ የጲርዓቶናዊው የሂ
ሌል ልጅ ዓብዶን በእስራኤል ፈራጅ ሆነ::
[14]እርሱም በሰባ አህዮች ላይ የሚቀመጡ
አርባ ወንዶች ልጆችና ሠላሳ ወንዶች የልጅ
ልጆች ነበሩት፤ በእስራኤልም ላይ ስም
ንት ዓመት ፈራጅ ሆነ:: [15]ከዚያም የሂሌል
ልጅ ዓብዶን ሞተ፤ ኰረብታማ በሆነው
በአማሌቃውያን አገር በኤፍሬም ምድር
በጲርዓቶን ተቀበረ::

ሐ7. በዚህ እንዲሁም በቍጥር 8-14 ላይ ባለው ክፍል በትውፊት *መሳፍንት* ይባላል::

11፥36 ዘኍ31፥3፤ 2ሳሙ18፥19፤ሉቃ1፥38
12፥1 ኢሱ13፥27፤ መሳ8፥1፤11፥1
12፥3 ዘጸ20፥4፤ መሳ9፥17
12፥4 ዘፍ46፥20፤ 1ነገ17፥1፤ኢሳ9፥21፤ 19፥2
12፥5 ኢሱ2፥7
12፥8 ዘፍ35፥19
12፥12 ኢሱ10፥12
12፥13 ቍ15፤ 2ሳሙ23፥30፤1ዜና1 1፥31፤27፥14
12፥14 መሳ5፥10፤ 8፥30
12፥15 መሳ5፥14

የተለመደ ሁኔታ ነው (ዘፍ 37፥34፡ እና ማብ ይመ)::

11፥37 ***ከእንግዲህ ባል ስለማላገባ፤*** አለማግባትና ልጅ አለ መውለድ ለአንዲት እስራኤላዊ ሴት እጅግ አሳዛኝ ነው::

11፥39 ***ይህ በእስራኤል ልማድ ሆኖ፤*** ምናልባትም ይህን በተመለከተ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ በሌላ ስፍራ የተጠቀሰ ባለመሆኑ፣ ነገሩ የአንድ አካባቢ ልማድ ሊሆን ይችላል::

12፥1 ***ቤትህን...እናቃጥለዋለን፤*** ፍልስጥኤማውያንም የሳምሶንን ሚስት ደሊላን ያስፈራሯት በዚሁ ዐይነት ነው (14፥15) እንዲሁም 20፥48 ይመ::

12፥2 ***መልሶ፤*** ዮፍታሔ እንደ ገና በዘዴ ማነጋገሩን በማስ ቀደም ሊያግባባቸው ሞከረ 11፥12፥14 እንዲሁም የ8፥1 ማብ ይመ :: ***ጠርቼአችሁ፤*** በፊት ያልታወቀ፣ ግን በድርጊቱ ሂደት ውስጥ የተከሰተ አዲስ ነገር ነው::

12፥6 ***ሺቦሌት፤*** በምጸታዊ አነጋገር የቃሉ ትርጒም "ጐርፍ" ማለት ነው፤ ለምሳሌ መዝ 69፥2:15 ይመ:: ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ የሚገኙ እስራኤላውያን የዚህን ቃል መነሻ ሆኖ ጠበቅ አድርገው በመጫን "ሺ" ብለው የሚጠሩት ሲሆን፣ በከነዓን ያሉት ግን ላላ አድርገው "ሲ" በማለት ይጠሩት ነበር:: ጴጥሮስም የገሊላ ሰው መሆኑ የተጋለጠው በአነጋገር ዘዬው ነበር፤ ማቴ26፥73 ይመ::

12፥7 ***በእስራኤል...ዓመት ፈራጅ ሆነ፤*** የአንድን መስፍን ታሪክ ለመደምደም የቀረበ አዲስ ዐይነት አገላለጥ ነው (የ3፥11 ማብ ይመ፤ እንዲሁም በመጽሐፉ መግቢያ ሥር "ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያቱ" የሚለውን ይመ)::

12፥8 ***ቤተ ልሔም፤*** ምናልባት በምዕራብ ዛብሎን የምትገኘውን ቤተ ልሔም ማለት ይሆናል::

12፥9 ***ሠላሳ ወንዶችና ሠላሳ ሴቶች ልጆች፤*** የ10፥4ማብ ይመ::

12፥11 ***ኤሎም፤*** በዛብሎን ነገድ ውስጥ የአንድ ጐሣ ስም ነው (ዘፍ 46፥14፤ ዘኍ26፥26)::

12፥14 ***አርባ ወንዶች ልጆችና ሠላሳ ወንዶች የልጅ ልጆች፤*** በጠቅላላ ሰባ ናቸው (የ8፥30፤ 10፥4 ማብ ይመ)::

12፥15 ***ኰረብታማ በሆነው በአማሌቃውያን አገር፤*** የ5፥14 ማብ ይመ:: የዚህ ምንጭ ዳራ አይታወቅም፤ ምክንያቱም አማሌ ቃውያን ከነጌብ ጋር በተያያዘ መልኩ ብቻ ስለሚገለጡ ነው::

*13፥1-16፥31፤* ከዳን ወገን የሆነው ሳምሶን፣ ከብንያም ወገን እንደ ሆነው እንደ ናዖድ ሁሉ ምንም ረዳት ሳይፈልግ ብኀይለኞች ጠላቶቹ ላይ ታላቅ ድል የተጐናጸፈ ጀግና ነው፤ ከዚህ የተነሣም የዚህ ጀግና ታሪክ ከናዖድ ታሪክ ጋር ተመሳሳይ ነው (3፥12-30)፡ የሳምሶን ታሪክ የእስራኤልን ሕዝብ ሁኔታ የሚገልጽ ጕልህ ምሳሌ ነው:: ይኸውም የተወለደው በእግዚአብሔር ፈቃድ ሲሆን፣ ከሕፃንነቱ ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየና ከወገኖቹም መካከል ተመርጦ ልዩ ኀይል ስለ ተሰጠው ነው:: ይህ መመሳሰል ይበልጥ ጐልቶ የሚታየው፣ ሳምሶን በመጨረሻ በጠላቶቹ ወጥመድ እስኪ ገባ ድረስ የባዕድ አገር ሴቶችን ተከትሎ በመሄዱ ነው:: እስራኤል

## የሳምሶን መወለድ

13 እስራኤላውያን እንደ ገና በእግዚ
አብሔር ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸሙ፤
ስለዚህም እግዚአብሔር በፍልስጥኤማውያን
እጅ አርባ ዓመት እንዲገዙ አሳልፎ ሰጣቸው::
2ማኑሄ የተባለ ከዳን ወገን የተወለደ አንድ
የጸርዓ ሰው ነበረ፤ ሚስቱ መካን ስለ
ነበረች ልጅ አልወለደችም:: 3የእግዚአ
ብሔርም መልአክ ለሴቲቱ ተገልጦ እንዲህ
አላት፤ "እነሆ፤ አንቺ መካን ነሽ፤ ልጅም
አልወለድሽም፤ ነገር ግን ትፀንሻለሽ ወንድ
ልጅም ትወልጃለሽ:: 4እንግዲህ ተጠንቀቂ፤
የወይን ጠጅም ሆነ ሌላ የሚያሰክር መጠጥ
አትጠጪ፤ ርኩስ ነገርም አትብዪ፤ 5ምክን
ያቱም ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅም ትወልጃ
ለሽ:: በራሱ ላይ ምላጭ አይድረስበት፤
ልጁ ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ ናዝራዊ በመሆን
ለእግዚአብሔር የተለየ ይሆናልና፤ እስራኤል
ንም ከፍልስጥኤማውያን እጅ መታደግ ይጀም
ራል::"

6ከዚያም ሴቲቱ ወደ ባሏ ሄዳ እንዲህ አለ
ችው፤ "የእግዚአብሔር ሰው ወደ እኔ መጣ፤
የእግዚአብሔር መልአክ የሚመስልና እጅግ
የሚያስደነግጥ ነበር:: ከየት እንደ መጣ
አልጠየቅሁትም፤ እርሱም ስሙን አልነገረኝም፤
7ነገር ግን፣ 'ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅም ትወልጃ
ለሽ፤ ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲያ የወይን ጠጅም
ሆነ ሌላ የሚያሰክር መጠጥ አትጠጪ፤
ርኩስ ነገር አትብዪ፤ ልጁም ከእናቱ ማሕፀን
ጀምሮ እስኪሞት ድረስ ናዝራዊ በመሆን
ለእግዚአብሔር የተለየ ይሆናልና' ብሎኛል::"

8ከዚያም ማኑሄ፣ "ጌታ ሆይ፤ የሚወለደውን
ልጅ እንዴት አድርገን ማሳደግ እንዳለብን
እንዲያስተምረን ያ ወደ እኛ የላክኸው የእ
ግዚአብሔር ሰው እንደ ገና እንዲመጣ ታደርግ
ዘንድ እለምንሃለሁ":: ብሎ ወደ እግዚአብሔር
ጸለየ::

9እግዚአብሔርም የማኑሄን ጸሎት ሰማ፤ የእግዚ
አብሔርም መልአክ ሴቲቱ በዕርሻ ውስጥ ሳለች
ተገለጠላት፤ በዚህ ጊዜ ግን ባሏ ማኑሄ
አብሮአት አልነበረም:: 10እርሷም ለባሏ ለመ
ንገር ፈጥና በመሄድ፣ "ባለፈው ጊዜ የተገ
ለጠልኝ ሰው ዛሬም ተገለጠልኝ" አለችው::

11ማኑሄም ተነሥቶ ሚስቱን ተከተላት፤
ሰውየው እንደ ደረሰም፣ "ከሚስቴ ጋር ተነጋ
ግረህ የነበርኸው አንተ ነህ?" ሲል ጠየቀው::

እርሱም፤ "አዎን እኔ ነኝ" አለው::

12ማኑሄም፣ "ያልኸው በሚፈጸምበት ጊዜ
የልጁ ሕይወት የሚመራው እንዴት ነው?
እኛስ ምን ማድረግ አለብን?" ሲል ጠየ
ቀው::

13የእግዚአብሔርም መልአክ እንዲህ አለው፤
"ሚስትህ የነገርኋትን ሁሉ ታድርግ:: 14ከወይን
ተክል የሚገኝ ማንኛቸውንም ነገር አትብላ፤
የወይን ጠጅም ሆነ ሌላ የሚያሰክር መጠጥ
አትጠጣ፤ ርኩስ ነገር አትብላ፤ ያዘዝኋት
ንም ሁሉ ታድርግ::"

15ከዚያም ማኑሄ የእግዚአብሔርን መል
አክ፣ "የፍየል ጠቦት ዐርደን እስክናዘጋጅልህ
ድረስ እባክህ ቈይ" አለው::

16የእግዚአብሔርም መልአክ፣ "የግድ
ብታቈየኝ እንኳ የምታቀርበውን ማንኛውንም
ምግብ አልበላም፤ ነገር ግን የሚቃጠል መሥ
ዋዕት የምታዘጋጅ ከሆነ እርሱን ለእግዚአብሔር
አቅርበው" አለው:: የሚያነጋግረው የእግዚአ
ብሔር መልአክ መሆኑን አላወቀም ነበር::

17ማኑሄ የእግዚአብሔርን መልአክ፣ "የተና
ገርኸው ሲፈጸም እንድናከብርህ ስምህ ማን
ነው" በማለት ጠየቀው::

18እርሱም፣ "ስሜ ድንቅ* ስለ ሆነ ለምን
ትጠይቀኛለህ?" አለው::

19ማኑሄም የፍየሉን ጠቦት ከእህል ቍርባኑ
ጋር ወስዶ በዐለት ላይ ለእግዚአብሔር

13፥1 መሳ3፥31፤ 14፥4
13፥2 ቍ8፤ ዘፍ11፥30፤30፥6፤ ኢሱ15፥33፤ መሳ16፥31
13፥3 ቍ10፤ ዘፍ16፥7፤ ኢሳ7፥14፤ ሉቃ1፥13
13፥4 ቍ14፤ ዘሌ10፥9፤ዘኍ6፥2-4፤ሉቃ1፥15
13፥5 ዘፍ3፥15፤ ዘኍ6፥2 ፡13፤1 ሳሙ1፥11፤7፥13፤ አሞ2፥11 ፡12
13፥6 ቍ8፤ ዘኍ22፥22፤1ሳሙ2፥27፤9፥6፤1ነገ13፥1፤17፥18፤መዝ66፥5
13፥7 ዘሌ10፥9፤ 1ሳሙ1፥11 ፡28፤ኤር35፥6
13፥8 ቍ2፡6
13፥10 ቍ3
13፥14 ቍ4፤ ዘሌ10፥9
13፥15 መሳ6፥19
13፥16 መሳ6፥22፤ 11፥31
13፥17 ዘፍ32፥29
13፥18 ዘፍ32፥29
13፥19 መሳ6፥20

*18 ወይም ድንቁ

በዘመነ መሳፍንት ለጋዛ ራሷ ጥፋት ከከነዓን አማልክት ጋር ያመነዘረ ችበትን ሁኔታ ሳምሶን በትክክል ያሳያል::

13፥1 ***በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸሙ፤*** የ3፥7 ማብ ይመ::

13፥2 ***ከዳን ወገን፤*** 1፥34 እና ማብ ይመ:: ***ጸርዓ፤*** በመጀመሪያ ለይሁዳ በርስትነት የተደለደለች ከተማ ስትሆን (ኢሱ 15፥33)፣ በኋላ ግን ለዳን ነገድ ተሰጥታለች (ኢሱ19፥41)፤ ይህም የዳን ልጆች ወደ ሰሜን እንዲፈልሱ ምክንያት ሆኖአቸዋል (18፥2፡8፡ 11):: ***መካን ስለ ነበረች ልጅ አልወለደችም፤*** ሣራ ይስሐቅን (ዘፍ11፥30፤16፥1)፣ ርብቃ ያዕቆብን (ዘፍ 25፥21) ሐና ሳሙኤልን (1ሳሙ 1፥2)፣ ኤል ሳቤጥ መጥምቁ ዮሐንስን (ሉቃ1፥7) ሳይወልዱና በእግዚአብሔር ሳይጐበኙ የነበሩበትን ሁኔታ ይመስላል::

***13፥3 የእግዚአብሔር መልአክ፤*** የዘፍ 16፥7 ማብ ይመ:: ***ነገር ግን...ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፤*** ስለ እስማኤል (ዘፍ 16፥11)፣ ስለ ይስሐቅ (ዘፍ 18፥10)፣ ስለ አማኑኤል (ኢሳ 7፥14)፣ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ (ሉቃ1፥13) እንዲሁም ስለ ኢየሱስ (ሉቃ1፥31) መወለድ አስቀድሞ ከተነገረው ጋር ያነጻጽሩ::

13፥5 ***ናዝራዊ፤*** በዕብራይስጥ የቃሉ ትርጕም የተለየ ወይም የተሰጠ ማለት ነው:: ናዝራዊ ለመሆን ስእለት የተሳለ ሰው መፈ ጸም ስለሚገባው ነገር ዘኍ6፥1-21 እና ማብ ይመ:: የሳምሶን ስእለት ግን የውዴታ ሳይሆን በእግዚአብሔር ውሳኔና የዕድሜ ልክ ነበር (ቍ7)፤ የሳሙኤል (1ሳሙ1፥11) እንዲሁም የመጥምቁ ዮሐንስ (ሉቃ 1፥15) ሕይወትም ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ ነበር:: ***ከፍልስጥኤማውያን እጅ መታደግ ይጀምራል፤*** ይህ መታደግ በሳሙኤል ዘመንም ቀጥሎ (1ሳሙ 7፥10-14) በዳዊት ዘመን ተጠናቋል (2ሳሙ 5፥17-25፤ 8፥1)::

13፥6 ***የእግዚአብሔር ሰው፤*** ይህ አባባል ብዙውን ጊዜ ነቢይን የሚያመለክት ሲሆን (ዘዳ 33፥1፤1ሳሙ 2፥27፤ 9፥6-10፤ 1ነገ12፥22 ይመ)፣ እዚህ ላይ ግን መልእክተኛው ነቢይ ሳይሆን የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑ በቍ3:21 ላይ በግልጽ ተቀምጦአል::

13፥8 ***እንዲያስተምረን፤*** በተለምዶ ወላጆች ለልጆቻቸው የሚያደርጉትን መልካም አስተዳደግ ሳይሆን ሕፃኑ ለተጠራበት ተልእኮ ብቁ የሚያደርገውን ማለት ነው::

13፥12 ***ያልኸው በሚፈጸምበት ጊዜ፤*** ማኑሄን ያሳሰበው ከእ ግዚአብሔር መልአክ የሰማው ቃል መፈጸም ወይም አለመፈጸሙ ሳይሆን፣ የሚፈጸምበት ጊዜ መቼ ነው? የሚለው ጕዳይ ነበር (ቍ17)::

13፥15 ***የፍየል ጠቦት ዐርደን እስክናዘጋጅልህ ድረስ እባክህ ቈይ፤*** ይህ ዐይነት ምግብ ባሕሙ ልዩ እንደሆነ ይነገራል:: የዚህ ዐይነቱ መስተንግዶ በጥንት የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች የተለመደ ነበር (6፥18-19፤ ዘፍ18፥1-8)::

13፥17 ***የተናገርኸው ሲፈጸም፤*** የተነገረ ትንቢት መፈጸም የተናጋሪውን ነቢይ ትክክለኛነት ያረጋግጣል (ዘዳ 18፥21-22፤ 1ሳሙ 9፥6):: ***ስምህ ማን ነው?፤*** ለመልእክቱ ክብደት ለመስጠት የተላከውን ማንነት ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ ነው::

13፥18 ***ስሜ ድንቅ ስለ ሆነ ፤*** በኢሳ 9፥6 ላይ ይህ ሐረግ የሚያመለክተው የዕብራይስጡ ቃል "ድንቅ" ማለት ሲሆን፣ ስለ ሚመጣው "ኀያል አምላክ" ይናገራል::

ሠዋው:: ማኑሄና ሚስቱ እያዩ እግዚአብሔር
አስደናቂ ነገር አደረገ፤ 20ይኸውም የእሳቱ
ነበልባል ከመሠዊያው ወደ ሰማይ ሲወጣ
የእግዚአብሔር መልአክ በነበልባሉ ውስጥ
ዐረገ:: ማኑሄና ሚስቱ ይህን ሲመለከቱ
በግንባራቸው መሬት ላይ ተደፉ:: 21የእግዚ
አብሔርም መልአክ ለማኑሄና ለሚስቱ ዳግ
መኛ ባለመገለጡ ቀደም ሲል የተገለጠላቸው
የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑን ማኑሄ ዐወቀ::
22ሚስቱንም፣ "እግዚአብሔርን ስላየን ያለ
ጥርጥር እንሞታለን" አላት::
23ሚስቱ ግን መልሳ እንዲህ አለችው፣
"እግዚአብሔር ሊገድለን ቢፈልግ ኖሮ የሚ
ቃጠለውን መሥዋትና የእህል ቍርባኑን
ከእጃችን ባልተቀበለን፤ ደግሞም ይህን ነገር
ሁሉ ባላሳየንና እንዲህ ያለውንም ነገር በዚህ
ጊዜ ባልነገረን ነበር::"
24ሴቲቱ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙንም
ሳምሶን ብላ ጠራችው፤ ልጁ አደገ፤ እግዚ
አብሔርም ባረከው፤ 25የእግዚአብሔርም መን
ፈስ በጾርዓና በኤሽታኦል መካከል ባለው
በዳን ሰፈር ሳለ ያነቃቃው ጀመር::

## የሳምሶን ጋብቻ

14 ሳምሶን ወደ ተምና ወረደ፤ እዚያም
አንዲት ወጣት ፍልስጥኤማዊት አየ::
2እንደ ተመለሰም አባቱንና እናቱን፣ "በተምና
አንዲት ወጣት ፍልስጥኤማዊት አይቻለሁና
አሁኑኑ አጋቡኝ" አላቸው::
3አባቱና እናቱም፣ "ከዘመዶችህ ወይም
ከሕዝባችን ሁሉ መካከል ለአንተ የምትሆን
ሴት መቸ ታጣችና ነው ወደ ያልተገረዘች
አሕዛብ ዘንድ ሚስት ፍለጋ የሄድኸው?"
አሉት::
ሳምሶንም አባቱን፣ "ልቤን የማረከችው
እርሷ ናትና እርሷን አጋባኝ" አለው:: 4በዚ
ያን ጊዜ በእስራኤል ላይ ገዦቹ ፍልስጥ
ኤማውያን ስለ ነበሩ፣ ከፍልስጥኤማውያን
ጋር ጠብ እንዲፈጠር እግዚአብሔር ሆን
ብሎ ያደረገው ነገር መሆኑን አባቱና እናቱ
አላወቁም ነበር:: 5ከዚያም ሳምሶን ከአባቱና
ከእናንቱ ጋር ወደ ተምና ወረደ፤ በዚያም
ከአንድ የወይን አትክልት ቦታ እንደ ደረሱ
ድንገት አንድ የአንበሳ ደቦል እያገሣ መጣ
በት:: 6በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ
በኀይል ወረደበት፤ ስለዚህ የፍየል ጠቦት
እንደሚገነጣጠል አንበሳውን ያለ ምንም መሣ
ሪያ በባዶ እጁ ገነጣጠለው፤ ያደረገውን ግን
ለአባቱም ሆነ ለእናቱ አልነገራቸውም ነበር::
7ወደ ሴቲቱም ወረደ፤ ከእርሷም ጋር ተነ
ጋገረ፤ እጅግም ወደዳት::
8ከጥቂት ቀን በኋላም ሊያገባት ተመ
ለሰ፤ የአንበሳውንም በድን ለማየት ከመን
ገድ ዘወር አለ፤ በበድኑም ውስጥ የንብ
መንጋ ሰፍሮ ተመለከተ፤ ማርም ነበረበት፤
9በእጁ ወስዶም መንገድ ለመንገድ እየበላ
ሄደ፤ ከወላጆቹም ጋር እንደ ተገናኘም ከማሩ
ሰጣቸው፤ እነርሱም በሉ:: ነገር ግን ማሩን
የወሰደው ከአንበሳ በድን መሆኑን አልነገራ
ቸውም ነበር::
10የሳምሶን አባት ልጅቱን ሊያይ ወረደ፤
ሳምሶንም በነበረው የሙሽራ ወግ መሠረት
በዚያ ግብዣ አደረገ:: 11እርሱም ለፍልስጥኤማ
ውያን በታየ ጊዜ ሠላሳ አጃቢዎች ሰጡት::
12ሳምሶን እንዲህ አላቸው፤ አንድ እን
ቈቅልሽ እነግራችኋለሁ፤ ታዲያ ፍቺውን
በሰርጉ በዓል ሰባት ቀኖች ውስጥ ከሰጣ
ችሁኝ፣ ሠላሳ የቀጭን ፈትል በፍታ ቀሚ
ስና ሠላሳ የክት ልብስ እሰጣችኋለሁ::
13እንቈቅልሹን ካልፈታችሁልኝ ግን ሠላሳ
የቀጭኔ ፈትል በፍታ ቀሚስና ሠላሳውን
የክት ልብስ እናንተ ትሰጡኛላችሁ::" እነር

13፥20 ዘፍ17፥3፤ ዘሌ9፥24
13፥21 መሳ6፥22
13፥22 ዘፍ16፥13፤ ዘፀ3፥6፤24፥10፤ ዘኍ17፥12፤ዘዳ5፥26
13፥23 መዝ25፥14
13፥24 መሳ14፥1፤ 15፥1፤ 16፥1ሳሙ-2፥21፡ 26፥3፥19፤ ሉቃ1፥80፤ ዕብ11፥32
13፥25 መሳ3፥10፤ 18፥12
14፥1 ዘፍ38፥12 ፤መሳ13፥24
14፥2 ዘፍ21፥21
14፥3 ዘፍ24፥4፤ 34፥14፤ዘፀ 34፥16፤1ሳሙ-14፥6
14፥4 ዘዳ2፥30፤ ኢሱ11፥20፤ መሳ13፥1፤15፥11
14፥6 መሳ3፥10፤ 1ሳሙ-17፥35
14፥10 ዘፍ29፥22
14፥12 ዘፍ29፥27፤ 45፥22፤ዘኍ12፥8፤2 ነገ5፥5ሕዝ17፥2፤ 20፥49፤24፥3፤ሆሴ12፥1

13፥22 ***ያለ ጥርጥር እንሞታለን፤*** 6፥23 እና የዘፍ 16፥13፤32፥30 ማብ ይመ::

13፥24 ***ሳምሶን፤*** ይህ ስም የተገኘው "ፀሐይ" ወይም "ብሩኅነት" ከሚለው ከዕብራይስጡ ቃል ነው፤ ምናልባትም ይህ ስም ሊወጣለት የቻለው፣ አንድም በልጁ መወለድ የተገኘውን ደስታ ለመግለጽ አለያም በአጠገባቸው በምትገኘው በቤትሳሚስ ከተማ ውስጥ ያለውን "የፀሐይ አምላክ ቤት" ለማመልከት ይሆናል፤ ***ልጁ አደገ፤ እግዚአብሔርም ባረከው፤*** ከ1ሳሙ 2፥26፤ እና ከሉቃ 2፥52 ጋር ያነጻጽሩ::

13፥25 ***ያነቃቃው ጀመር፤*** የ3፥10፤ 11፥29 ማብ ይመ::

14፥1 ***ተምና፤*** ከቤትሳሚስ በስተ ምዕራብ ባለው በሶሬቅ ሸለቆ ውስጥ የምትገኝ ስትሆን ፣ ቴል ባታሽ በሚል መጠሪያም ትታወቃለች:: የሥነ ቅርስ ጥናት ሊቃውንት ከመሬት ውስጥ የነበረ አንድ የፍልስጥኤማውያን ከተማ ፍርስራሽ አግኝተዋል:: ***አንዲት ወጣት ፍልስጥኤማዊት፤*** እስራኤላውያን ከከነዓናውያን ጋር እንዳይጋቡ የሚከለከል ሕግ በመኖሩ (ዘፀ34፥11፡16፤ዘዳ 7፥1፡ 3፤መሳፍ3፥5-6 ይመ)፣ የሳምሶን ወላጆች በዚህ አድራጎቱ እንዳልተደሰቱ ግልጽ ነው (ቍ3 ይመ፣ በዘፍ 26፥35፤27፥46፤ 28፥1 ላይ ስለ ኤሳው ከተጠቀሰው ጋር ያነጻጽሩ)::

14፥2 ***አጋቡኝ፤*** ዘፍ 34፥4 ይመ:: አባት የቤተ ሰቡ ራስ እንደ መሆኑ ለወንዶች ልጆቹ ሚስት በመምረጥ ረገድ ሙሉ ሥልጣንና መብት አለው (12፥9፤ ዘፍ24፥3-9፤ ነህ10፥30 ይመ)::

14፥3 ***ወዳልተገረዙት፤*** ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ውጭ የሆኑትን በተለይም ፍልስጥኤማውያንን የሚመለከት ሲሆን፣ ጠንከር ያለ ጥላቻ የሚገለጥበት ቃል ነው (የ1ሳሙ 14፥6 ማብ ይመ):: ***እርሷን አጋባኝ፤*** የዕብራይስጡ አገላለጽ በ17፥6፤21፥25 ላይ ከተጠቀሰው "መልካም መስሎ የታየውን" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው:: ይህን መሪ ሐሳብ ጸሐፊው በም 17-21 ላይ እንደ ገና ያነሣዋል::

14፥4 ***እግዚአብሔር ሆን ብሎ ያደረገው፤*** ኢሱ 11፥20፤ 1ነገ12፥15 ይመ:: እግዚአብሔር የሰዎችን ደካማ ጐን ለዐላማው መፈጸሚያ፣ ለስሙ ክብርና ምስጋና እንዲውል ማድረግ ይችላል (ዘፍ45፥8፣ 50፥20፤ 2ዜና25፥20፤ ሐሥ2፥23፤4፥28፤ሮሜ8፥28-29 ይመ)::

14፥5 ***ተምና... የወይን አትክልት ቦታ፤*** የተምና ከተማ ያለችበት የሶሬቅ ሸለቆና አካባቢው የታወቀ የወይን ተክል ቦታ ነበር:: ***የአንበሳ ደቦል፤*** በዚያን ዘመን በደቡቡ የከነዓን ምድር አንበሳ ይገኝ ነበር 1ሳሙ 17፥34፤ 2ሳሙ23፥20፤ 1ነገ13፥24፤ 20፥36)::

14፥6 ***የእግዚአብሔር መንፈስ ... ወረደበት፤*** 13፥25፤ 14፥19፤ 15፥14 እንዲሁም የ3፥10፤11፥29 ማብ ይመ:: ***አንበሳውን... ገነጣጠለው፤*** በኋላም ዳዊት (1ሳሙ17፥34-37) እና በናያስ (2ሳሙ 23፥20) ይህንኑ የመሰለ ተግባር ፈጽመዋል::

14፥10 ***ግብዣ፤*** ይህን ዐይነት ግብዣ ማድረግ በጥንት የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች የተለመደ ነበር (ዘፍ 29፥22 ይመ):: ያም ግብዣ ሰባት ቀን ያህል ቈይቶአል (ቍ12 እንዲሁም ዘፍ 29፥27 ይመ):: በግብዣውም ላይ የወይን ጠጅ ስለ ነበር፣ ምናልባት ሳምሶን የናዝራዊነት ስእለቱን ሳያፈርስ አልቀረም (13፥4፡7 ይመ)::

14፥11 ***አጃቢዎች፤*** ሙሽራውን የተከተሉ እንግዶች ሲሆኑ (ከማቴ9፥15ጋር ያነጻጽሩ) ምናልባት ወንበዴዎች በሙሽሮቹ ላይ አደጋ እንዳያደርሱባቸው ለመጠበቅ አብረው የሄዱ ሊሆኑ ይችላሉ::

14፥12 ***እንቆቅልሽ፤*** በጥንት ዘመን በግብዣም ሆነ በሌላ ልዩ ዝግጅት ላይ የእንቈቅልሽ ጥያቄ ማቅረብና ፍችውን መመለስ የተለመደ ነበር:: ***የክት ልብስ፤*** ከሀብር ጋር እንደ ስጦታ የሚቀርብ፣ ከፍ

ሱም፣ “በል እንቄቅልሽህን ንገረንና እንስ
ማው” አሉት::

[14]ሳምሶንም፣
“ከበላተኛው መብል፣
ከብርቱም ጣፋጭ ነገር ወጣ” አላቸው::
እነርሱም እስከ ሦስት ቀን ድረስ እንቈ
ቅልሹን መፍታት አልቻሉም ነበር::

[15]በአራተኛው[w] ቀን የሳምሶንን ሚስት፣
“የእንቈቅልሹን ፍች እንዲነግረን ባልሽን እስቲ
አግባቢልን፤ ያለዚያ አንቺንም የአባትሽ
ንም ቤተ ሰብ በእሳት እናቃጥላችኋለን፤ ጠር
ታችሁ የጋበዛችሁን ልትዘርፉን ነው?” አሏት::
[16]ከዚያ የሳምሶን ሚስት ተንሰቅስቃ
እያለቀሰች ከፊቱ በመቅረብ፣ “ለካስ ትጠላ
ኛለህ! በእርግጥ አትወደኝም” አለችው::
እርሱም፣ “ይህን ለአባቴም ሆነ ለእናቴ
አልነገርኋቸውም፤ ታዲያ ለአንቺ ለምን እነ
ግርሻለሁ?” አላት:: [17]ሚስቱም በሰርጉ በዓል
ሰባት ቀን ሙሉ እያለቀሰች ጨቀጨቀችው፤
አጥብቃ ስለ ነዘነዘችውም በመጨረሻ በሰ
ባተኛው ቀን ነገራት፤ እርሷም በበኩሏ የእ
ንቈቅልሹን ፍች ለሕዝቧ ነገረች::
[18]በሰባተኛው ቀን ፀሓይ ከመጥለቋ በፊት
የከተማው ሰዎች፣

“ከማር የጣፈጠ ምን ተገኝቶ?
ከአንበሳስ ወዲያ ብርቱ ከየት መጥቶ!”
አሉት::
ሳምሶንም መልሶ፣
“በጊደሬ ባላረሳችሁ፣
እንቈቅልሼንም ባልፈታችሁ”አላቸው::

[19]ከዚያም የእግዚአብሔር መንፈስ በሳ
ምሶን ላይ በኀይል ወረደበት፤ ወደ አስቀ
ሎናም ወርዶ ከሰዎቻቸው መካከል ሠላሳውን
ገደለ፤ ያላቸውንም ከገፈፈ በኋላ ልብሶቻ
ቸውን አምጥቶ እንቈቅልሹን ለፈቱት ሰዎች
ሰጣቸው:: በቍጣ እንደነደደም ተነሥቶ
ወደ አባቱ ቤት ወጣ:: [20]የሳምሶንም ሚስት
ለሚዜው ተዳረች::

14፥14 ቍ18
14፥15 ዘሌ20፥14፤ መሳ15፥6፤16፥5፤ መክ7፥26
14፥16 መሳ16፥15
14፥17 አስ1፥5
14፥18 ቍ14
14፥19 ኢሱ13፥3፤ መሳ3፥10፤ 1ሳሙ11፥6
14፥20 መሳ15፥2 :6፤ዮሐ3፥35
15፥1 ዘፍ29፥21፤ 30፥14፤38፥17፤ መሳ13፥24
15፥2 መሳ14፥20
15፥4 ዘፍ15፥17፤ መኃ2፥15
15፥5 ዘፍ15፥17፤ ዘፀ22፥6፤ 2ሳሙ14፥30-31
15፥6 ዘፍ38፥24፤ መሳ14፥5 :20
15፥8 ቍ11፤ ኢሳ2፥21
15፥9 ቍ14 : 17:19

## ሳምሶን ፍልስጥኤማውያንን ተበቀለ

15 ከጥቂት ጊዜ በኋላ [a]በስንዴ መከር
ወራት ሳምሶን አንድ የፍየል ጠቦት
ይዞ ሚስቱን ለማየት ሄደ፤ እርሱም፣
“ሚስቴ ወዳለችበት ጫጉላው ቤት ልግባ”
አለ፤ አባቷ ግን እንዲገባ አልፈቀደለትም::
[2]አባትየውም፣ ፈጽሞ የጠላሃት መሆ
ንህን ስለ ተረዳሁ ለሚዜህ ድሬለታለሁ፤ ታናሽ
እኅቷ ከእርሷ ይልቅ ውብ አይደለችምን?
እርሷን አግባት” አለው::
[3]ሳምሶንም መልሶ፣ “ከእንግዲህ በፍልስ
ጥኤማውያን ላይ በሚደርሰው ጕዳት ተጠ
ያቂ አልሆንም” አላቸው:: [4]ከዚያም ወጥቶ
በመሄድ ሦስት መቶ ቀበሮች ያዘ፤ የሁለት
ሁለቱን ጭራ አንድ ላይ ካሰረ በኋላ ችቦ ወስዶ
ጥንድ ሆኖ ከተያያዘው ጭራ ጋር አሰረው::
[5]ችቦውን በእሳት አቀጣጥሎ ቀበሮቹን
በፍልስጥኤማውያን የእህል አዝመራ ላይ ለቀ
ቃቸው፤ ነዶውንና የቆመውን አዝመራ እንዲ
ሁም የወይኑንና የወይራውን ተክል አቃጠለ::
[6]ፍልስጥኤማውያን፣ “ይህን ያደረገው ማን
ነው?” ብለው ሲጠይቁ፣ “ሚስቱ ለሚዜው
ስለ ተሰጠችበት የተምናዊው ዐማች ሳምሶን
ነው” የሚል መልስ አገኙ::
ስለዚህም ፍልስጥኤማውያን ወጥተው ሴቲ
ቱንና አባቷን በእሳት አቃጥለው ገደሏቸው::
[7]ሳምሶንም፣ “እንግዲህ እናንተ ይህን ካደ
ረጋችሁ እኔ ደግሞ ሳልበቀላችሁ አልመለስም”
አለ:: [8]ክፉኛ መታቸው፤ ከነርሱም ብዙዎችን
ገደለ፤ ከዚያም ወርዶ በኢታም ዐለት ዋሻ
ተቀመጠ::
[9]ፍልስጥኤማውያን ወጥተው በይሁዳ ሰፈሩ፤
ከዚያም በሌሒ አጠገብ ተበታትነው አደፈጡ::
[10]የይሁዳም ሰዎች፣ “ልትወጉን የመጣችሁት
ለምንድን ነው?” ሲሉ ጠየቋቸው::
እነርሱም “እኛ የመጣነው ሳምሶንን ልናስ
ርና ያደረገብንን ልናደርግበት ነው” ብለው
መለሱላቸው::

[w]15. አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞችና የሱርስቱ ትርጒም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን ሰባተኛ ይላል::

ያለ ዋጋ ያለው መሆኑ በዘፍ 45፥22፤ 2ነገ 5፥22 ላይ ተመልክቶአል፤ እንዲሁም ዘካ14፥14 ይመ::

14፥16 *በእርግጥ አትወደኝም፤* ደሊላ እንዲህ ያለውን የብልጠት ጥያቄ ደጋግማ ታቀርብለታለች (18፥15)::

14፥18 *በጊደሬ፤* የሳምሶንን ሚስት ለማለት ነው (ቍ 15 ይመ)፤ በዚያን ዘመን በጊደር ስለማይታረስ በዚህ መንገድ መምጣታቸው ትክክል ስላልሆነ በወቀሳ መልክ ነገራቸው::

14፥19 *የእግዚአብሔር መንፈስ...ወረደበት፤* ሳምሶን እንዲያከናውነው እግዚአብሔር ካዘጋጀለት ዕቅድ ውስጥ አንዱ ፍልስጥኤማውያንን ማዋረድ ነበር:: *አስቀሎና፤* ከፍልስጥኤማውያን አምስት ዋና ዋና ከተሞች አንዷ ነች::

14፥20 *ለሚዜው፤* 15፥2 ይመ፤ ምናልባትም ሳምሶንን ካጀቡት ከሠላሳዎቹ ሰዎች መካከል አንዱ ሊሆን ይችላል (ከዮሐ 3፥29 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም ቍ 11 ይመ)::

15፥1 *በስንዴ መከር ወራት፤* በግንቦት ወር መጨረሻ ወይም በሰኔ ወር መግቢያ አካባቢ ማለት ነው (የሩት1፥22 ማብ ይመ):: *የፍየል ጠቦት፤* በተመሳሳይ ሁኔታም፣ ይሁዳ ለትዕማር ይህን ዐይነት የተለመደ ስጦታ አቅርቦ ነበር (ዘፍ38፥17)::

15፥2 *ታናሽ እኅቷ፤* የሳምሶን ዐማት የማጫ ገንዘብ ተቀብሎት ስለ ነበር በእኅቷ ለማካካስ ፈለገ:: በላባና በያዕቆብ (ዘፍ29፥16-28)፣ በሳኦልና በዳዊት (1ሳሙ18፥19-21) መካከል ይህንኑ የመሰለ ድርድር ተፈጽሞ ነበር::

15፥4 *ቀበሮዎች፤* የዕብራይስጡ ቃል ቀበሮን ወይም ተኵላን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል:: እነዚህ ሁለቱ እንስሳት ዛሬም በእስራኤል አገር ይገኛሉ::

15፥5 *አቃጥሉ፤* የስንዴ መከር (ቍ 1) የሚደርሰው በበጋ ወቅት ስለ ሆነ ዕርሻው በቀላሉ እሳት ሊያይዝ ይችላል::

15፥7 *ሳልበቀላችሁ፤* በጥንት የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች መበቀል የተለመደ ነበር:: የማያቋርጥ የእርስ በርስ መገዳደልን ለማስቀረት እግዚአብሔርም ስድስት የመማጠኛ ከተሞች እንዲኖሩ አድርጎአል (ኢሱ 20፥1-9)::

15፥9 *በሌሒ፤* ትርጒሙ የመንጋጋ ዐጥንት ማለት ነው:: እዚህ ላይ የተወሣው ድርጊት እስከ ተፈጸመ ድረስ፣ ምናልባትም ይህ ቦታ በዚህ ስም አልተጠራ ይሆናል፤ ጸሓፊው ይህንን ስም የተጠቀመው ከሚፈጸመው ጋር በተያያዘ መልኩ ነው፤ ይህም በዕብራውያን የትረካ አጻጻፍ ስልት የተለመደ ነበር:: ሌሒ የነበረች ትክክለኛ ቦታ እስከ ዛሬ ድረስ በውል ተለይቶ አልታወቀም::

11ከዚያም ሦስት ሺህ ሰዎች ከይሁዳ ተነ
ሥተው በኤታም ዐለት ወዳለው ዋሻ ወርደው
ሳምሶንን፣ "ፍልስጥኤማውያን ገዦቻችን መሆ
ናቸውን አታውቅምን? ያደረግህብንስ ነገር ምን
ድን ነው?" ብለው ጠየቁት።
ሳምሶንም፣ "ያደረግሁት እነርሱ ያደረ
ጉብኝን ነው" በማለት መለሰላቸው።
12እነርሱም፣ "አስረን ለፍልስጥኤማውያን
ልንሰጥህ ይኸው መጥተናል" አሉት።
ሳምሶንም፣ "እናንተ ራሳችሁ ላትገድሉኝ
ማሉልኝ" አላቸው።
13እነርሱም፣ "አስረን ብቻ ለእነርሱ አሳ
ልፈን እንሰጥሃለን እንጂ ራሳችን አንገድል
ህም" አሉት፤ ከዚያ በሁለት አዳዲስ ገመድ
አስረው ከዐለቱ ዋሻ አወጡት። 14ሳምሶን
ሌሒ እንደ ደረሰም ፍልስጥኤማውያን እየ
ጮኹ ወደ እርሱ መጡ፤ በዚህ ጊዜ የእግዚ
አብሔር መንፈስ በሳምሶን ላይ በኀይል
ወረደበት። እጆቹ የታሰሩበትም ገመድ እሳት
ውስጥ እንደ ገባ የተልባ እግር ፈትል ሆኖ
ከእጆቹ ላይ ወደቀ። 15ከዚያም በቅርቡ
የሞተ የአንድ የአህያ መንጋጋ አይቶ ከመሬት
አነሣ፤ በዚያም አንድ ሺህ ሰው ገደለ።

16ሳምሶንም፣

"በአንድ የአህያ መንጋጋ፣
ሺህ ሰው ዘራራ፤
በአንድ የአህያ መንጋጋ፣
ሺህ ሬሳ አነባባርሁ[ሐ]፡ ብሎ ፎከረ።

17ይህን ተናግሮ እንዳበቃ የአህያውን
መንጋጋ ከእጁ ወዲያ ወረወረው፤ የዚያም
ቦታ ስም ራማት ሌሒ[ሰ] ተብሎ ተጠራ።
18እጅግ ተጠምቶ ስለ ነበር፤ "እነሆ፤ ለአገ
ልጋይህ ይህን ታላቅ ድል አጐናጽፈሃል፤ ታዲያ
አሁን በውሃ ጥም ልሙት? እንዴትስ በእነ
ዚህ ባልተገረዙ ፍልስጥኤማውያን እጅ
ልውደቅ? በማለት ወደ እግዚአብሔር ጮኸ።

19እግዚአብሔርም በሌሒ ዐለት ሰነጠቀለት፤
ከዚያም ውሃ ወጣ፤ ሳምሶንም ያን ሲጠጣ
በረታ፤ መንፈሱም ታደሰ። ስለዚህ ያ ምንጭ
ዓይንሀቆሬ[ኸ] ተባለ፤ እስከ ዛሬም ድረስ በዚ
ያው በሌሒ ይገኛል።
20ሳምሶንም በፍልስጥኤማውያን ዘመን
በእስራኤል ላይ ለሃያ ዓመት ፈራጅ[+] ሆነ።

## ሳምሶንና ደሊላ

16 አንድ ቀን ሳምሶን ወደ ጋዛ ሄደ፤
እዚያም አንዲት ዘሙት አዳሪ አየ፤
አብሮአት ለማደርም ገባ። 2የጋዛ ሰዎች፣
"ሳምሶን እዚህነው!" የሚል ወሬ ደረሳቸው፤
ስለዚህም ሰዎቹ ቦታውን ከበው፤ ሌሊቱን
በሙሉ በከተማዪቱ ቅጥር በር ላይ አድ
ፍጠው ጠበቁት፤ "በማለዳ እንገድለዋለን"
በማለትም ሌሊቱን በሙሉ እንዳደፈጡ አደሩ።
3ነገር ግን ሳምሶን እዚያ የተኛው እስከ
እኩለ ሌሊት ብቻ ነበር፤ ተነሥቶም የከተ
ማዪቱን ቅጥር በር ከሁለት መቃኖቹ ጋር
መወርወሪያውንና ማያያዣውን ጭምር በሙሉ
ነቅሎ በትከሻው ላይ ካደረገ በኋላ፣ በኬብሮን
ፊት ለፊት እስካለው ኰረብታ ጫፍ ድረስ
ተሸክሞት ወጣ።
4ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሳምሶን በሶሬቅ
ሸለቆ የምትኖር ደሊላ የምትባል አንዲት
ሴት ወደደ። 5የፍልስጥኤማውያን ገዦች
ወደ እርሷ ሄደው፣ "እርሱን አስረን በቍጥ
ጥራችን ሥር በማዋል ልናሸንፈው እንዴት
እንደምንችልና የብርታቱ ታላቅነት ምስጢር
ምን እንደ ሆነ እንዲያሳይሽ እስቲ አባብ
ዪው፤ ይህን ካደረግሽ እያንዳንዳችን አንድ
ሺህ አንድ መቶ ሰቅል[በ] ጥሬ ብር እንሰጥ
ሻለን" አሏት።

15፥11 መሳ14፥4፤ መዝ106፥40-42
15፥12 ዘፍ47፥31
15፥13 መሳ16፥11 ፡12
15፥14 ቍ9፤ ኢሱ2፥6፤መሳ3፥10
15፥15 ዘሌ26፥8
15፥16 ኤር22፥9
15፥17 ቍ9
15፥18 ዘጸ20፥4፤ መሳ16፥28
15፥19 ዘፍ45፥27፤ ዘፀ17፥6፤ 1ሳሙ30፥12፤ ኢሳ40፥29
15፥20 መሳ16፥31
16፥1 ዘፍ10፥19፤ 38፥15፤መሳ13፥24
16፥2 ኢሱ2፥5፤ 1ሳሙ19፥11
16፥3 ኢሱ10፥36
16፥4 ቍ6፤ ዘፍ24፥67፤34፥3
16፥5 ቍ6 ፡15 ፡18፤ዘፀ10፥7፤ ኢሱ13፥3፤ መሳ14፥15

[ሐ]16. በዕብራይስጡ አህያ የሚለው ቃል ፍም ከመረ ወይም አነባበረ ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው።
[ሰ]17.ራማት ሌሒ ማለት የመንጋጋ ኰረብታ ከምር ማለት ነው።
[ኸ]19.ዓይንሀቆሬ ማለት የጠሪዎች ምንጭ ማለት ነው
[+]20. በትውፊት መሳፍንት ይባላል።
[በ]5. 13 ኪሎ ግራም ያህል ነው።

15፥11 *ሦስት ሺህ ሰዎች ከይሁዳ፤* ከመሳፍንቱ ታሪክ ጋር በተያያዘ፣ ከይሁዳ ለጦርነት የወጣው የሰራዊት ብዛት ግልጽ ሆኖ በቍጥር ሲቀርብ ይህ የመጀመሪያ መሆኑ ነው (የ1፥2 ማብ ይመ)። የይሁዳ ሰዎች የሳምሶንን ማንነት በሚገባ ያውቁ ስለ ነበር፣ ምንም እንኳ ያን ያህል ብዛት ያለው የሰው ኀይል ቢይዙም እርሱ ራሱ ሳይፈቅድላቸው ሊያስሩት አልደፈሩም (ቍ12-13)። *ፍልስጥኤማውያን ገዦቻችን መሆናቸውን፤* አብዛኛው የይሁዳ ክፍል በፍልስጥኤማውያን አገዛዝ ሥር ቢወድቅም ሕዝቡ እነሱን መቃወም እንደማይፈልግ የታወቀ ነበር። ይህን ኀይል ያሰባሰቡትም ሳምሶንን ለመርዳት ሳይሆን፣ እጁን ይዞ ለፍልስጥኤማውያን አሳልፎ ለመስጠት ነበር።

15፥14 *እየጮኹ፤* የቀከራ ቃል ማሰማታቸውን ያመለክታል (1ሳሙ17፥52)፤ ፍልስጥኤማውያን ወደ በሳምሶን የመጡት፣ አንበሳ ሊውጠው የመጣበትን ሁኔታ ይመስል ነበር ፣ (14፥5)። *የእግዚአብሔር መንፈስ፤* የ3፥10፤ 11፥29፤14፥19 ማብ ይመ።

15፥15 *አንድ ሺህ ሰው ገደለ፤* ሰሚጋር በጀግንነት ስድስት መቶውን ፍልስጥኤማውያን በበሬ መንጃ እንዴት እንደፈጀቸው ከሚያወሳው ታሪክ ጋር ያነጻጽሩ (3፥31)።

15፥18 *ታዲያ አሁን በውሃ ጥም ልሙት?* ሳምሶን ምንም እንኳ ኀያልና ጀግና ቢሆንም፣ ሟች ሰው በመሆኑ ክፉኛ ተጠማ።

*15፥19፤ ከዚያም፣ ውሃ ወጣ፤* እግዚአብሔር ለእስራኤል በምድረ በዳ ሲጓዙ በማሳና በመሪባ (ዘፀ 17፥1-7፤ ዘኍ 20፥2-13) እንዳደረገላቸው ሁሉ እንደዚሁ ለሳምሶን አደረገለት።

15፥20 *በእስራኤል...ዓመት፤* የ12፥7 ማብ ይመ። *ሃያ ዓመት፤* በመጽሐፈ መሳፍንት ቍጥሩን እያጠጋጉ በሙሉ ቍጥር መጻፍ የተለመደ ነው (በመጽሐፉ መግቢያ "ታሪካዊ ዳራ" የሚለውን ይመ)።

16፥1 *ጋዛ፤* በደቡብ ምዕራብ ፓሌስቲና በሜድትራንያን ዳርቻ የሚገኝ ዋና የፍልስጥኤም የባሕር ወደብ ነው። *ዘሙት አዳሪ፤* ምንም እንኳ ሳምሶን ብርቱና ጠንካራ ሰውነት ቢኖረውም፣ መንፈሰ ጠንካራ ስላልነበር ለውድቀቱ ምክንያት ሆነው።

16፥2 *ማለዳ፤* ይህን ጊዜ የመረጡት ሳምሶን ከመድከሙ የተነሣ ከባድ እንቅልፍ ላይ ሊሆን እንደሚችል በመገመታቸው ነው።

16፥3 *መወርወሪያ፤* ምናልባትም ከናስ (1ነገ4፥13) ወይም ከብረት (መዝ 107፥16፤ ኢሳ 45፥2) የተሠራ ይሆናል። *በኬብሮንም ፊት ለፊት፤* በኬብሮን ትይዩ 61ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ በኰረብታማው አገር የሚገኝ ስፍራ ነው። ኬብሮን የይሁዳ ምድር ዋና ከተማ ስለሆነች፣ የይሁዳ ሰዎች ስለፈጸሙበት ድርጊት ሳምሶን ሆን ብሎ ይህን አደረገ(15፥11-13)።

16፥5 *የፍልስጥኤማውያን ገዦች፤* የ3፥3 ማብ ይመ። *ልናሸንፈው፤* ፍልስጥኤማውያን ሳምሶንን ወዲያውኑ ለመግደል ይኸን ያህል ጕጕት አልነበራቸውም፤ ፍላጐታቸው ረዘም ላለ ጊዜ በማሠቃየት ለመበቀል ነበር። *አንድ ሺህ አንድ መቶ ሰቅል ብር፤* በ17፥10 ላይ ከተጠቀሰው ጋር ሲነጻጸር ክፍያው እጅግ ከፍ ያለ ነው (በዚያ የተጠቀሰውን ማብ ይመ)፤ በአጠቃላይ ከአምስቱ የፍልስጥኤም መኳንንት የቀረበው ይህ ክፍያ ከምእተ ዓመት በፊት ዮሴፍ በተሸጠበት ዋጋ ሲሰላ (ዘፍ37፥28)፣ የሁለት መቶ ሰባ አምስት ባሮች ዋጋ ነበር። ሚካ ከእናቱ የሰረቀውም ብር ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ ነበር (17፥2)።

6ስለዚህም ደሊላ ሳምሶንን፣ "ዋብርታትህን
ታላቅነት ምስጢርና ታስረህ በቍጥጥር ሥር
የምትውለው እንዴት እንደ ሆነ እባክህ ንገረኝ"
አለችው::
7ሳምሶንም፣ "ማንም ባልደረቀ ሰባት እርጥብ
ጠፍሮች+ ቢያስረኝ እንደ ማንኛውም ሰው
ደካማ እሆናለሁ" አላት::
8ከዚያም የፍልስጥኤማውያን ገዦች ያል
ደረቁ ሰባት እርጥብ ጠፍሮች አመጡላት፤
እርሷም አሰረችው:: 9ሰዎች በጓዳ ውስጥ ተደ
ብቀው ነበር፤ እርሷም፣ "ሳምሶን! ፍልስጥኤ
ማውያን መጡብህ" አለችው፤ ሳምሶን ግን
ፈትል እሳት ሲነካው እንደሚበጣጠስ ጠፍሮ
ቹን በቀላሉ በጣጠሳቸው፤ ስለዚህ የብርታቱ
ምስጢር ምን እንደ ሆነ ሊታወቅ አልቻለም::
10ደሊላም ሳምሶንን፣ "አሞኘተኸኛል፤
ዋሽተኸኛል፤ እባክህ አሁንም አንተን እን
ዴት ማሰር እንደሚቻል ንገረኝ" አለችው::
11እርሱም፣ ሥራ ላይ ባልዋሉ አዳዲስ
ገመዶች ቢያስሩኝ እንደ ማንኛውም ሰው
ደካማ እሆናለሁ" አላት::
12ደሊላም አዳዲስ ገመዶች ወስዳ አሰረ
ችው፤ ሰዎች በጓዳ ውስጥ ተደብቀው ነበር፤
እርሷም፣ "ሳምሶን! ፍልስጥኤማውያን መጡ
ብህ" አለችው:: እርሱ ግን ክንዱ የታሰረባ
ቸውን ገመዶች እንደ ፈትል ክር በጣጠሳቸው::
13ደግሞም ደሊላ ሳምሶንን፣ "እስካሁን
አሞኘተኸኛል፤ ዋሽተኸኛል:: እባክህን አን
ተን ማሰር የሚቻለው እንዴት እንደ ሆነ
ንገረኝ" አለችው::
እርሱም መልሶ፣ "የራስ ጠጕሬን ሰባት
ቈንዳላዎች ከድር ጋር ጐንጕነሽ በችካል
ብትቸክዪው፣ እንደ ማንኛውም ሰው ደካማ
እሆናለሁ" አላት:: ደሊላም መተኛቱን አይታ
ሰባቱን ቈንዳላዎቹን ከድር ጋር ጐነጐነችው፤
14ከችካልም ጋር ቸከለችው::
እንደ ገናም፣ "ሳምሶን! ፍልስጥኤማውያን
መጡብህ" አለችው:: ሳምሶን ከእንቅልፉ
ነቃ፤ ችካሉን ከነድሩ፣ ከነቈንዳላው ነቀለው::
15ከዚያም፣ "ሳታምነኝ እንዴት 'እወድሻ
ለሁ' ትለኛለህ? ስታታልለኝና የኀይልህንም
ታላቅነት ምስጢር ስትደብቀኝ ይህ ሦስተኛ
ጊዜህ ነው" አለችው:: 16በሕይወት መኖሩን
እስኪጠላ ድረስ ዕለት ዕለት በመጨቅጨቅ
አስለቸችው::
17ስለዚህ ሁሉንም ነገር ነገራት፤ እንዲ
ህም አለ፤ "ከተወለድሁ ጀምሮ ናዝራዊ
በመሆን ለእግዚአብሔር የተለየሁ ስለ ሆንሁ
ራሴን ምላጭ ነክቶት አያውቅም፤ የራሴ
ጠጕር ቢላጭ ግን ኀይሌ ተለይቶኝ እንደማ
ንኛውም ሰው ደካማ እሆናለሁ" አላት::
18ደሊላ ሁሉንም ነገር እንደ ነገራት
በተረዳች ጊዜ፣ ለፍልስጥኤማውያን ገዦች
"ሁሉንም ነገር ነግሮኛልና ተመልሳችሁ ኑ"
ብላ ላከችባቸው፤ የፍልስጥኤማውያን ገዦችም
ብሩን ይዘው ተመልሰው መጡ:: 19ደሊላ፣
ሳምሶንን በጭኗ ላይ አስተኝታ እንቅልፍ
እንዲወስደው ካደረገች በኋላ አንድ ሰው
ጠርታ ሰባቱን የጠጕር ቈንዳላዎቹን አስላ
ጨቻቸው፤ እርሷም ታስጨንቀው+ ጀመር፤
ኀይሉም ተለየው::
20እርሷም፣ "ሳምሶን፤ ፍልስጥኤማውያን
መጡብህ!" አለችው::
ሳምሶን ከእንቅልፉ ነቅቶ፣ "እንደ ወትሮው
አደርጋለሁ" አለ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር
እንደ ተወው አላወቀም ነበር::
21ከዚያም ፍልስጥኤማውያን ያዙት፤
ዐይኖቹን አውጥተው ወደ ጋዛ ይዘውት ወረዱ፤
በናስ ሰንሰለት አስረውም እስር ቤት ውስጥ
እህል እንዲፈጭ አደረጉት፤ 22ነገር ግን
ከተላጨ በኋላ ጠጕሩ እንደ ገና ማደግ ጀመረ::

### የሳምሶን አሟሟት

23በዚህ ጊዜ የፍልስጥኤማውያን ገዦች፣
"አምላካችን ዳጎን ጠላታችን ሳምሶንን በእ
ጃችን አሳልፎ ሰጥቶናል" ብለው በመደሰት
ለአምላካቸው ለዳጎን ታላቅ መሥዋዕት ለማ
ቅረብ ተሰበሰቡ::
24ሕዝቡም ሳምሶንን ባዩት ጊዜ፣ አምላ
ካቸውን ዳጎንን በማመስገን፣

"ምድራችንን ያጠፋውን፣
 ብዙ ሰው የገደለብንን፣ ጠላታችንን፣
 አምላካችን በእጃችን አሳልፎ ሰጠን" አሉ::

16፥6 ቍ4
16፥9 ቍ12፤ቍ14
16፥10 ቍ13
16፥11 መሳ15፥13
16፥12 ቍ14
16፥14 ቍ9 ፡20
16፥15 ቍ5፤ ዘኍ24፥10፤ መሳ14፥16
16፥17 ቍ18፤ ዘኍ6፥2፤ ሚክ7፥5
16፥18 ቍ5፤ ኢሱ13፥3፤1ሳሙ5፥8
16፥19 ምሳ7፥26-27
16፥20 ቍ14፤ዘኍ 14፥42፤ ኢሱ7፥12፤ 1ሳሙ16፥14፤18፥12 ፤28፥15
16፥21 ዘፍ10፥19፤ ዘኍ16፥14፤ ኢዮ31፥10፤ ኢሳ47፥2፤ኤር47፥1
16፥23 1ሳሙ5፥2፤ 1ዜና10፥10
16፥24 1ሳሙ 31፥9፤ ዜና10፥9፤ ዳን5፥4

+7. ወይም በዚህ እንዲሁም በቍጥር 8 እና 9 ላይ *የቀስት አውታር*
+19. ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ሲስማማ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች ግን *ታዳከመው ጀመር* ይላሉ

16፥7 ***ባልደረቀ ሰባት እርጥብ ጠፍሮች፤*** ሰባት የፍጹምነት ወይም የሙሉነት ትእምርት ነው ተብሎ ስለሚታሰብ፣ በጥንት ሕዝቦች ዘንድ ከፍ ያለ ግምት የሚሰጠው ቍጥር ነበር:: የሳምሶን ጠጕር ሰባት ቦታ ተከፍሎ የተጐነጐነ ነበር (በቍ 13)::

16፥11 ***አዳዲስ ገመዶች፤*** ይህን ዘዴ ከዚህ በፊት ተሞክሮ ሳይሠራ መቅረቱን ፍልስጥኤማውያን እንዳላስተዋሉ ግልጽ ነው (15፥13-14)::

*16፥13፤* ፍልስጥኤማውያን ጠላቶቹን ከምንም ባለመቍጠር ሳምሶን በተለያየ መንገድ ያፌዝባቸው ነበር:: ***በችካል ብትቸክዪው፤*** በዚህ ቦታ የተጠቀሰው ችካል አንድን ነገር እንዳይንቀሳቀስ ከመሬት ጋር ግጥም አድርጐ ለመያዝ የሚያገለግል ነው፤ ከዚህም የተነሣ የሳምሶን ረጅም ጠጕር ከድር ጋር ተጐንጕኖ ከመሬት ጋር መቸከሉ ፍልስጥኤማውያን በቀላሉ ለመያዝ እንዲያመቻቸው ነው::

16፥19-20 ***ኀይሉም ተለየው... እግዚአብሔር እንደ ተወው፤*** ለሳምሶን የጕልበት ምንጭ ሙሉ በሙሉ እግዚአብሔር ብቻ ነበር::

16፥20 ***አላወቀም ነበር፤*** በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከተወሰኑ እጅግ አሳዛኝ ሁኔታዎች አንዱ ይህ ነው:: ሳምሶን የተደረገለትን ጥሪ እንዳቃለለ አላወቀም ነበር:: ለእግዚአብሔር የተለየ መሆኑን የሚገልጸውን ልዩ ምልክት ለአንዲት ፍልስጥኤማዊት ሴት በቀላሉ አስረከበ፤ ይህ እግዚአብሔር መርጦት የነበረ ጀግና በወደዳት ሴት ክንድ ላይ አሳቡን ጥሎ ለመተኛት በቃ::

16፥21 ***ዐይኖቹን አውጥተው፤*** ለማዋረድና ዐቅም ለማሳጣት በጦር እስረኞች ላይ ይፈጸም የነበረ እንዲህ ዐይነቱ ጭካኔ የተሞላበት አድራጎት የተለመደ ነበር (1ሳሙ 11፥2፤ 2ነገ25፥7፤ እንዲሁም የመሳ 1፥6 ማብ ይመ):: ***ወደ ጋዛ፤*** ሳምሶን ቀድሞ ታላቅ ኀይሉን (ቍ 1-3) ወደ አሳየበት ወደ ጋዛ አዋርደውና አቃለው ወሰዱት:: ***እህል እንዲፈጭ አደረጉት፤*** የ9፥53 ማብ ይመ::

16፥23 ***ዳጎን፤*** ፍልስጥኤማውያን የሚያመልኩት የእህል ወይም የተክል አምላክ ነው (የ10፥6 ማብ ይመ):: ***አምላካችን... አሳልፎ ሰጥቶናል፤*** ድል ሲገኝ ሕዝቡ በሚያመልካቸው አማልክት ርዳታ እንደ ተገኘ መናገር የተለመደ ነበር::

25እጅግ ደስ ባላቸው ጊዜ፣ “እንዲያዝ
ናናን ሳምሶንን አምጡት” አሉ፤ ስለዚህ
ሳምሶንን ከእስር ቤት ጠርተው አስመጡት፤
በፊታቸውም ተጫወተ።
በምሰሶዎቹ መካከል ባቆሙት ጊዜ፣
26ሳምሶን እጁን ይዞ የሚመራውን ልጅ፣
“ቤተ ጣዖቱን ደግፈው ወደ ያዙት ምሰሶዎች
አስጠጋኝና ልደገፋቸው” አለው። 27በዚህ ጊዜ
ወንዶችና ሴቶች ቤተ ጣዖቱን ሞልተውት
ነበር፤ የፍልስጥኤማውያን ገዦችም በሙሉ
በዚያ ነበሩ፤ ሳምሶን ሲጫወት ለማየት
ሦስት ሺህ ያህል ወንዶችና ሴቶች በሰገነቱ
ላይ ነበሩ። 28ሳምሶንም ወደ *እግዚአብሔር*
እንዲህ ሲል ጸለየ፤ “ልዑል *እግዚአብሔር*
ሆይ፤ አስበኝ፤ አምላክ ሆይ፤ እባክህን አንድ
ጊዜ ብቻ ብርታት ስጠኝና ስለ ጠፉት ዐይ
ኖቼ፣ ፍልስጥኤማውያንን አንዴ ልበቀላ
ቸው።” 29ከዚያም ቤተ ጣዖቱን መካከል
ላይ ደግፈው የያዙትን ሁለት ምሰሶዎች
አንዱን በቀኙ፣ አንዱን በግራ እጁ አቅፎ
በመያዝ፣ 30“ከፍልስጥኤማውያን ጋር አብሬ
ልሙት” በማለት ባለ ኀይሉ ሲገፋው፣ ቤተ
ጣዖቱ በገዦቹና በውስጡ በነበሩት በሌሎቹ
ሰዎች ሁሉ ላይ ወደቀባቸው፤ ስለዚህ በሕ
ይወት ከኖረበት ጊዜ ይልቅ በሞቱ ጊዜ
ብዙ ሰው ገደለ።
31ወንድሞቹና መላው የአባቱ ቤተ ሰብ
ሬሳውን ለማምጣት ወደዚያ ወረዱ፤ አም
ጥተውም የአባቱ የማኑሄ መቃብር ባለበት
በጸርዓና በኤሽታኦል መካከል ቀበሩት።
ሳምሶን በእስራኤል ላይ ሃያ ዓመት ፈራጅ
ሆነ ።

16፥25 መሳ9፥27፤ 19፥6፡9፡22፤ ሩት3፥7፤ አስ1፥10
16፥27 ኢሱ2፥8
16፥28 ዕብ15፥18፤ ኤር15፥15
16፥31 መሳ13፥2፤ 15፥20፤ሩት1፥1፤1 ሳሙ4፥18፤7፥6
17፥1 መሳ18፥2፡13
17፥2 ሩት2፥20፤ 3፥10፤1ሳሙ15፥13፤ 23፥21፤2ሳሙ2፥5
17፥3 ዘፀ20፥4
17፥4 ዘፀ32፥4፤ ኢሳ17፥8
17፥5 ዘፍ31፥19፤ ዘፀ29፥9፤ ዘኍ16፥10፤ መሳ8፥27፤ ኢሳ44፥13፤ ሕዝ8፥ 10
17፥6 ዘዳ12፥8፤ መሳ18፥1፤ 19፥1፤21፥25

## ሚካ ያሠራቸው ጣዖታት

17 ሚካ የተባለ በኰረብታማው በኤ
ፍሬም አገር የሚኖር ሰው ነበር።
2እናቱን፣ “አንድ ሺህ አንድ መቶ ሰቅል[1]
ብር ተሰርቆብሽ፣ የሰረቀውን ሰው ስትራ
ገሚ ሰምቼሽ ነበር፤ ብሩ ከእኔ ዘንድ
ይገኛል፤ የወሰድሁት እኔ ነኝ” አላት።
ከዚያም እናቱ፣ “ልጄ *እግዚአብሔር*
ይባርክህ” አለችው።
3አንድ ሺህ አንድ መቶውን ሰቅል ብር
በመለሰላት ጊዜ፣ እናቱ “ብሬን የተቀረጸ
ምስልና ቀልጦ የተሠራ ጣዖት ለማበጀት
ስለ ልጄን *ለእግዚአብሔር* እቀድሰዋለሁ፤ አሁ
ንም ለአንተው መልሼ እሰጥሃለሁ” አለችው።
4ስለዚህ ብሩን ለእናቱ መለሰላት፤ እና
ቱም ከላዩ ሁለት መቶ[2] ጥሬ ብር ወስዳ
ለብር አንጥረኛ ሰጠች፤ አንጥረኛውም የተ
ቀረጸ ምስልና ቀልጦ የተሠራ ጣዖት አደ
ረገው፤ ምስሎቹም በሚካ ቤት ተቀመጡ።
5ሚካ የተባለው ይህ ሰው የአምልኮ ስፍራ
ነበረው፤ አንድ ኤፉድና ተራፊም ሠርቶ
ከልጆቹ አንዱን ካህን ሆኖ እንዲያገለግለው
አደረገ። 6በዚያን ዘመን በእስራኤል ንጉሥ
አልነበረም፤ እያንዳንዱ ሰው ለራሱ መልካም
መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር። 7በይሁዳ
ምድር፣ በይሁዳ ነገድ መካከል በቤተልሔም
የሚኖር አንድ ሌዋዊ ወጣት ነበር።
8ይህም ሰው ሌላ መኖሪያ ስፍራ ለመ
ፈለግ ከተማዪቱን ለቆ ሄደ። በሚጓዝበትም
ጊዜ[3] በኰረብታማው በኤፍሬም አገር ወዳለው
ወደ ሚካ ቤት መጣ።

31. በትውፊት *መሳፍንት* ይላል። 2. 13 ኪሎ ግራም ያህል ነው።
4 2.3 ኪሎ ግራም ያህል ነው፡
8. *ወይም የዕለት ምግቡ ሊያገኝ ሲል*

16፥27 *በጣሪያው ላይ!* የቤተ ጣዖቱ ሕንፃ ጣራ ክፍት ስለሆነ፣ በጣሪያው ዙሪያ ሰዎች ቆመው ወይም ተቀምጠው ሳምሶንን ቍልቍል ለመመልከት ያመች ነበር።

16፥30 *ሲገፋው!* ሳምሶን የዕንጨት ምሰሶዎች በመያዝ ከመሠረቱ ለማላቀቅ ገፋው፤ የሥነ ቅርስ አጥኚዎች የምሰሶ መሠረት ያሉትን አንድ የፍልስጥኤማውያን ቤተ ጣዖት አግኝተዋል። *ብዙ ሰው ገደለ!* ቀደም ሲል ሳምሶን ከአንድ ሺህ ሰው በላይ ገድሎ ነበር 15፥15 ይመ፤ እንዲሁም 14፥19፡15፥8 ይመ።

16፥31 *ለማምጣት ወደዚያ ወረዱ!* ቤተ ሰቦቹ አስከሬኑን ወስደው ለመቅበር አለመከልከላቸው በሳምሶን ራስ ላይ ፍልስጥኤማውያን ማላገጥ እንደፈለጉ ያሳያል (ከሳዖል አሟሟት ጋር ያነጻጽሩ 1ሳሙ 31፥9-10)። *በእስራኤል ላይ...ዓመት ፈራጅ ሆነ!* የ12፥7 ማብ ይመ። *ሃያ ዓመት፣* በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ቍጥርን እየጠጋጉ መጻፍ የተለመደ ነው (ከመግቢያው “ታሪካዊ ዳራው” የሚለውን ይመ)።

*17፥1-21፥25!* በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የሚገኙት ሁለት ትረካዎች፣ ለመጽሐፈ መሳፍንት መደምደሚያ ናቸው። (በመጽሐፉ መግቢያ ሥር “ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያቱ” የሚለውን ይመ)። እነዚህ ድርጊቶች ከዘመነ መሳፍንት ቀደም ብለው የተፈጸሙ ናቸው (የ18፥30 ፣20፥1፡28 ማብ ይመ)። ይህ ትረካ እስራኤላውያን ንጉሥ ባልነበራቸው ጊዜና እያንዳንዱ ሰው ለራሱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ በነበረበት ዘመን የነበረው የሃይማኖትና የምግባር ብልሹነት የቱን ያህል አስከፊ ደረጃ ላይ እንደ ደረሰ ይገልጻል (17፥6፤21፥25)።

*17፥1-18፥31!* ይህ የመጀመሪያ ትረካ የሙሴ ዘር ነኝ በሚለው ሌዋዊ ሰው አማካይነት በኤፍሬም ምድር ባዕድ አምልኮ ማቆሙንና ይህም እስራኤላውያን ወደ ጥፋት እንዲያመሩ እንዳደረጋቸው ይናገራል፤ የዳን ነገድም ርስቱን ትቶ ወደ ሰሜን እስራኤል በሄደ ጊዜ በሕዝብ ልማድ ያደርግ የነበረውን አምልኮ እንዳለ ይዞ ሄዶአል።

17፥2 *አንድ ሺህ አንድ መቶ ሰቅል!* የ16፥5 ማብ ይመ። *ስትራገሚ! ሰምቼሽ ነበር!* ገንዘቡን የመለሰው የእናቱን ርግማን በመፍራት ነበር። *እግዚአብሔር ይባርክህ!* ርግማኑን የሚሽር ምርቃት ነው።

17፥3 *እናቱ... ልጄ!* እናትና ልጅ የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን ያዩት፣ አሕዛብ አምላኮቻቸውን እንደሚያዩአቸው ነበር፤ ሕጉ የሚያዝዘውን ባለመፈጸም ሁለቱም ጣዖት አምላኪዎች ነበሩ (ዘፀ20፥4፡23፤ ዘዳ4፥16)፤ ከዚህም የተነሣ ሁለቱም ባዕድ አምልኮ ፈጽመዋል። *የተቀረጸ ምስልና ቀልጦ የተሠራ ጣዖት!* ምናልባትም ምስሉ ከዕንጨት የተሠራ ሆኖ በብር የተለበጠ፣ ጣዖቱም ከነጠረ ብር ወይም ከመናኛ ብረት የተሠራና በብር የተለበጠ ሳይሆን አይቀርም።

17፥4 *ብር አንጥረኛ!* በሐሥ19፥24 ላይ እንደ ተመለከተው ማለት ነው (ከኢሳ40፥19 እና ከኤር10፥9 ጋር ያነጻጽሩ፤ ይህንም ቃል የዕብራይስጡ ወርቅ ሠሪ ይለዋል)።

17፥5 *ኤፉድ!* 8፥27 እና የዘፀ 28፥6 ማብ ይመ። *ተራፊም!* የቤተ ሰብ አምላክ ነው፤ እዚህ ላይ የተጠቀሰው ለጥንቈላ ተግባር ነው (ከሕዝ21፥21፤እና ከዘካ 10፥2 ጋር ያነጻጽሩ)።

17፥6 *ንጉሥ አልነበረም!*18፥1፤19፥1፡21፡25 ይመ፤ መጽሐፈ መሳፍንት የተጻፈው እስራኤላውያን በንጉሥ መግዛት ከጀመሩ ወዲህ እንደ ሆነ የሚጠቍም ነው (ከመጽሐፉ መግቢያ፤ “ጸሐፊውና የተጻፈበት ጊዜ” የሚለውን ይመ)። *ለራሱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር።* እስራኤላውያን በሕጉ መጽሐፍ (ዘዳ12፥8) ከተሰጣቸው ቃል ኪዳን የራቁ መሆናቸውን ይገልጻል።

17፥7 *በይሁዳ ምድር ቤተ ልሔም!* ለሌዋውያን ከተመደቡት አርባ ስምንት ከተሞች አንዷ አይደለችም።

17፥8 *ከተማዪቱን ለቆ ሄደ!* እስራኤላውያን ለተሰጣቸው ሕግ አለመታዘዛቸው ሌዋውያኑ ተገቢውን ርዳታ እንዳያገኙ ሳያደርጋቸው አልቀረም፤ ሌዋዊው የተሻለ ነገር ለመፈለግ ሲል፣ የሚኖርበትን ከተማ ለቆ የሄደው በዚህ ምክንያት ነው።

9ሚካም፣ “የየት አገር ሰው ነህ?” ሲል
ጠየቀው::
እርሱም፣ “እኔ በይሁዳ ምድር ከምትገኝ
ከቤተ ልሔም የመጣሁ ሌዋዊ ነኝ፤
መኖሪያ ስፍራ እፈልጋለሁ” አለው::
10ሚካም፣ “እንግዲያውስ” አብረኸኝ ተቀ
መጥ፤ አባትም ካህንም ሁነኝ፤ እኔም በዓመት
ዐሥር ሰቅል[ሀ] ብር እንዲሁም ልብስና ምግብ
እሰጥሃለሁ”አለው:: 11ስለዚህ ሌዋዊው አብ
ሮት ለመኖር ተስማማ፤ ወጣቱም ለሚካ
ከልጆቹ እንደ አንዱ ሆነለት:: 12ሚካም
ሌዋዊውን ካህን አድርጎ አስቀመጠው፤
ወጣቱም ካህኑ ሆነ፤ በቤቱም ኖረ:: 13ሚካም፤
“ይህ ሌዋዊ ካህን ስለ ሆነልኝ እግዚአብሔር
በጎ ነገር እንደሚያደርግልኝ አሁን ተረዳሁ” አለ።

## ዳናውያን ሰዎች በላይሽ ሰፈሩ

18 በዚያን ዘመን በእስራኤል ንጉሥ
አልነበረም፣ የዳን ነገድም በእስራ
ኤል ነገዶች መካከል ርስተ ድርሻውን ገና
ስላልወሰደ፣ የሚሰፍርበትን የራሱን ርስት
ይፈልግ ነበር:: 2ስለዚህ ዳናውያን ምድሪ
ቱን እንዲሰልሉና እንዲመረምሩ አምስት
ኀያላን ሰዎች ከጾርዓና ከኤሽታኦል ከተ
ሞች ወደዚያ ላኩ፤ እነዚህም ነገዶቻቸውን
ሁሉ የሚወክሉ ነበሩ:: የላኳቸውም ሰዎች፣
“ሂዱ፤ ምድሪቱን ሰልሉ” አሏቸው::
መልእክተኞቹም ወደ ኰረብታማው
የኤፍሬም አገር ገቡ፤ ወደሚያድሩበትም ወደ
ሚካ ቤት መጡ:: 3በሚካ ቤት አጠገብ እንደ
ደረሱም የወጣቱን ሌዋዊ ድምፅ ዐወቁ፤
ስለዚህ ወደዚያ ጐራ ብለው፣ “ወደዚህ ያመ
ጣህ ማን ነው? እዚህ ምን ትሠራለህ? የመ
ጣኸውስ ለምንድን ነው?”:: ሲሉ ጠየቁት::
4እርሱም፣ “ሚካ ይህን ይህን አደረገልኝ፤
ቀጠረኝ፤ ካህኑም ሆንሁ” አላቸው::
5እነርሱም፣ “መንገዳችን መቃናት አለ
መቃናቱን እንድናውቅ እባክህ እግዚአብሔርን
ጠይቅልን” አሉት::
6ካህኑም፣ “በሰላም ሂዱ፤ መንገዳችሁን
እግዚአብሔር አቃንቶላችኋል” ብሎ መለሰላቸው::
7ስለዚህ አምስቱ ሰዎች ከዚያ ተነሥተው
ወደ ላይሽ መጡ፤ ሲዶናውያን ያለ ስጋት
በጸጥታ[ለ] እንደሚኖሩ ሁሉ፣ በዚያም የሚ
ኖረው ሕዝብ በሰላም እንደሚኖር አዩ::
ምድሪቱ አንዳች የሚጐድላት ነገር ባለ
መኖሩ ሕዝቡ ባለጸጋ ነበር:: እንዲሁም
ከሲዶናውያን ርቆ የሚኖር ሲሆን፣ ከማን
ኛቸውም ሕዝብ ጋር[መ] ግንኙነት አልነበረውም።
8ወደ ጾርዓና ወደ ኤሽታኦል እንደ
ተመለሱ ወገኖቻቸው፣ “የሄዳችሁበት ጕዳይ
እንዴት ሆነ?” በማለት ጠየቋቸው::
9መልእክተኞቹም እንዲህ አሏቸው፤ “ምድ
ሪቱ እጅግ መልካም መሆኗን አይተናል፤
እንግዲህ ተነሡ! ሄደን እንዋጋቸው፤ ተነሡ
እንጂ ዝም ትላላችሁን? ወደዚያው ሄዳችሁ
ምድሪቱን ለመያዝ አታመንቱ 10እዚያ
ስትደርሱም ያለ ሥጋት የሚኖር ሕዝብ፣
እግዚአብሔር በእጃችሁ የሚሰጣችሁን አንዳች
ነገር ያልጐደላትን ሰፊ ምድር ታገኛላችሁ::”
11ከዚያ በኋላም ከዳን ወገን ለጦርነት
ዝግጁ የሆኑ ስድስት መቶ ሰዎች ከጾርዓና
ከኤሽታኦል ተነሡ:: 12ወጥተውም በይሁዳ
ምድር ባለችው በቂርያትይዓሪም ሰፈሩ፤

17፥7 ዘፍ35፥19፤ መሳ18፥3፤ማቴ2፥1
17፥9 ሩት1፥1
17፥10 ዘፍ45፥8፤ መሳ18፥19
17፥12 ‘ኍ16፥10፤ መሳ18፥4
17፥13 ዘኍ18፥7
18፥1 ኢሱ19፥47፤ መሳ1፥34፤17፥6
18፥2 ቍ17፤ ዘፍ30፥6፤ዘኍ21፥32 ፤ኢሱ2፥1፤መሳ17፥1
18፥3 መሳ17፥7
18፥4 መሳ17፥12
18፥5 ዘፍ25፥22፤ መሳ20፥18 ፡23 ፡27፤1ሳሙ14፥18፤ 2ሳሙ5፥19፤ 2ነገ1፥2፤8፥8
18፥6 1ነገ22፥6
18፥7 ቍ17፡28፤ ዘፍ34፥25፤ ኢሱ11፥8፤19፥47
18፥9 ዘኍ13፥30፤ 1ነገ22፥3
18፥10 ዘዳ8፥9፤ 1ዜና4፥40
18፥11 ቍ16፡17፤ መሳ13፥2
18፥12 ኢሱ9፥17፤ መሳ13፥25

[ሀ]10. 110 ግራም ያህል ነው::
[ለ]7. በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጒም በትክክል አይታወቅም
[መ]7. ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ሲስማማ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ግን ከአራም ሰዎች ጋር ይላል::

17፥10 *አባትም፤* የአክብሮት መግለጫ ነው፤ ለኤልያስና (2ነገ 2፥12) ለኤልሳዕ አክብሮትን ለመግለጥ ጥቅም ላይ ውሏል (2ነገ 6፥21፤13፥14)፤ ዘፍ 45፥8፤ ማቴ 23፥9 ይመ:: *ዐሥር ሰቅል፤* አማራጭ ትርጒሙን ይመ:: ለአንድ ዓመት አገልግሎት የሚሰጠው ይህ ክፍያ ከ16፥5 እና ከ17፥2 ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ ክፍያ ነበር:: ሌዋዊው በዓመት እንዲከፈለው የቀረበለት የደመወዝ፣ የልብስና የምግብ ክፍያ የማያልፈው መልካም አጋጣሚ ስለነበር፣ እንዲህ በቀላሉ አልተመለከተውም (ቍ 11)፤ ከተወሰነ ጊዜም በኋላ ሌላ የተሻለ ክፍያ በቀረበለት ጊዜ መቀበሉ (18፥19-20) የሰው ውሳኔ የተመሠረተው ለኑሮ በሚያስፈልገው ነገር ላይ እንደ ሆነ ያመለክታል::

17፥12 *ሚካም ሌዋዊውን ካህን አድርጐ አስቀመጠው፤* ሚካ፣ እቤቱ ያለው ተራፊም ዕውቅና እንዲያገኝለትና እንዲከበርለት ጥረት ማድረጉ ነበር:: በዚህ ጊዜ ሚካ ልጁን ከክህነት አገልግሎት ሳያስወግደው አይቀርም (ቍ 5 ይመ)::

18፥1 *ርስት ይፈልግ ነበር ፤* ለዳን ነገድ የተደለደለለት ርስት በይሁዳና በኤፍሬም መካከል ያለው ወሸመጥ መሰል ቆላማ መሬት ነው (ኢሱ 19፥41-46)፤ ይሁን እንጂ ከአሞራውያንና (መሳ1፥34) ከፍልስጥኤማውያን ተቃውሞ የተነሣ፣ ይህን ምድር ለመያዝ አልቻሉም (የ13፥2 ማብ ይመ)::

18፥2 *እንዲሰልሉ፤* 1፥23 እና የዘኍ 13፥2 ማብ ይመ::

18፥3 *ድምፅ ዐወቁ፤* የድምፁን ቅላጼ በመለየት ሊሆን ይችላል::

18፥5 *እግዚአብሔርን ጠይቅልን፤* ጥያቄው የቀረበው ከእግዚአብሔር ንግር ለማግኘት ነው፤ ምናልባትም የሚጠየቀው በኤፉድና በቤተ ሰቡ አማልክት አማካይነት ሳይሆን አይቀርም (የ17፥5ማብ ይመ):: እግዚአብሔርም ምድሪቱ ለተለያዩ ነገዶች እንድትከፋፈል ባደረገ ጊዜ፣ ፈቃዱን ገልጾአል (ኢሱ 14፥20):: እነርሱ ለማግኘት የፈለጉት ንግር ጕዞአቸው የተቃና እንዲሆን የሚያረጋግጥ የእግዚአብሔር ቃል ነው::

18፥6 *በሰላም ሂዱ፤* ሌዋዊውም የነገራቸው መልእክት፣ እነርሱ ሊሰሙ የፈለጉትን ነበር:: መልእክቱ የሚታመንና ክብደት ያለው እንዲሆን በእግዚአብሔር ስም ተናገራቸው::

18፥7 *ላይሽ፤* ወደ ሰሜን የተደረገው ጕዞ ከጾርዓና ከኤሽታኦል አንድ መቶ ስድሳ ኪሎ ሜትር ያህል ይርቅ ነበር (ቍ 2)፤ ይህች ከተማ በመጽሐፈ ኢያሱ ሌሼም ተብላ ተጠራች (ኢሱ 19፥47)፤ ከተማዪቱ በዳን ነገድ ከተያዘች በኋላ የቀድሞ ስሟ ተለውጦ ዳን ተብላለች (ቍ 29)፤ በስተ ሰሜን ላለው የእስራኤል ምድር የመጨረሻዋ የጠረፍ ከተማ ናት (20፥1፤1ሳሙ3፥20፤2ሳሙ3፥10 ይመ):: የሥነ ቅርስ ጥናት ሊቃውንት ባደረጉት ቁፋሮ የተገኘው መረጃ እንደሚገልጸው፣ ቀደምት እስራኤላውያን ይህን ቦታ በመጀመሪያ የያዙት አንድ ሺህ ሁለት መቶ ዓ.ቅ.ክ. ገደማ ሲሆን የመጀመሪያው ነዋሪ በድንኳን ወይም በጊዜያዊ መጠለያ ውስጥ እንደሆነ ነው:: ይህ ቦታ እስከ አሦራውያን ዘመን ድረስ እንደተያዘ የቈየ ሲሆን፣ ከተማዪቱ በተደጋጋሚ ስትፈርስና ስትሠራ ቈይታለች:: ከከተማዪቱ ወጣ ብሎ ያለ አንድ ከፍ ያለና ያማረ ቦታ በተደጋጋሚ ሲገነቡ የፈረሰውንም ሲያድሱ እስከ ግሪኮች ዘመን ድረስ ሲጠቀሙበት ቈይተዋል:: *ሲዶናውያን፤* በሜድትራኒያን አገሮች ሁሉ በንግድ ሥራ የሚታወቁ በሳ ማውያን የፊንቄ ሰዎች ናቸው:: *ግንኙነት አልነበረውም፤* ሕዝቡ ከሌሎች መንግሥታት ጥቃት ይደርስብኛል የሚል ሥጋት ስላል ነበረው የጋራ መከላከያ ስምምነት አልነበረቻቸውም::

18፥11 *ስድስት መቶ ሰዎች፤* የዳን ነገድ መሪዎች እንደ መሆናቸው መጠን፣ መላው የዳን ነገድ በሰሜን ወዳለው ወደ አዲሱ ምድር ለሚያደርገው ፍልሰት የሚወክሉ ናቸው:: የብንያምን ነገድ ቅሬታ ከሚያዋቅሩት ስድስት መቶ ሰዎች ጋር ያነጻጽሩ (20፥47)::

እንግዲህ ከቂርያትይዓሪም በስተ ምዕራብ
ያለው ስፍራ እስከ ዛሬ ድረስ የዳን ሰፈር
መባሉ ከዚሁ የተነሣ ነው:: 13ከዚያም ተጕ
ዘው ወደ ኰረብታማው የኤፍሬም አገር
በመሄድ ወደ ሚካ ቤት መጡ::
14የላይሽን ምድር ሰልለው የነበሩት አም
ስቱ ሰዎች ለወንድሞቻቸው፣ "ከእነዚሁ
ቤቶች በአንዱ ኤፉድ፣ ተራፊም፣ የተቀረጸ
ምስልና ቀልጦ የተሠራ ጣዖት እንዳለ
ታውቃላችሁን? እንግዲህ ምን ማድረግ
እንዳለባችሁ ዕወቁበት" አሏቸው:: 15ስለዚህ
ወጣቱ ሌዋዊ ወደሚኖርበት ወደ ሚካ ቤት
ጎራ ብለው ሰላምታ አቀረቡለት :: 16ለጦ
ርነት ተዘጋጅተው የመጡት ስድስት መቶ
የዳን ሰዎች በቅጥሩ በር መግቢያ ላይ
ቆመው ነበር:: 17ካህኑ ለጦርነት ከተዘጋጁት
ስድስት መቶ ሰዎች ጋር በቅጥሩ በር ላይ
ቆሞ ሳለ፣ ምድሪቱን ለመሰለል መጥተው
የነበሩትን አምስት ሰዎች ወደ ቤቱ ውስጥ
በመግባት የተቀረጸውን ምስልና ኤፉዱን፣
ተራፊሙንና ቀልጦ የተሠራውን ምስል
ወሰዱ::
18እነዚህ ሰዎች ወደ ሚካ ቤት ገብተው
የተቀረጸውን ምስልና ኤፉዱን፣ ተራፊሙንና
ቀልጦ የተሠራውን ምስል በሚወስዱበት
ጊዜ ካህኑ፣ "ምን ማድረጋችሁ ነው?" አላቸው::
19እነርሱም፣ "ዝም በል! አንዲት ቃል እን
ዳትተነፍስ፤ ከእኛ ጋር ሁን፤ አባትም ካህንም
ሁነን፤ ለአንተስ የአንድ ቤተ ሰብ ካህን
ከመሆን ይልቅ በእስራኤል የአንዱ ነገድና
ጐሣ ካህን ሆነህ ማገልገሉ አይሻልህምን?"
አሉት:: 20ይህም ካህኑን ደስ አሰኘው፤ እርሱም
ኤፉዱን፣ ተራፊሙንና የተቀረጸውን ምስል
ይዞ ከሕዝቡ ጋር ሄደ:: 21እነርሱም ሕፃናታ
ቸውን፣ የከብቶቻቸውን መንጋና ሀብታ
ቸውን ሁሉ ወደ ፊት በማስቀደም ተመል
ሰው ሄዱ::
22ከሚካ ቤት ጥቂት ራቅ እንዳሉም፣
የሚካ ጎረቤቶች ለርዳታ ተጠርተው ተሰ
በሰቡ፤ የዳን ሰዎችንም ተከታትለው ደረሱ
ባቸው:: 23ከበስተ ኋላቸው ሆነው ሲጮኹባ
ቸውም፣ የዳን ሰዎች ወደ ኋላቸው ዞረው
ሚካን፣ "ሰዎችህን ለውጊያ አሰባስበህ መም
ጣትህ ምን ሆንህና ነው?" አሉት::
24እርሱም፣ "እንዴት፣ 'ምን ሆንህ' ብላችሁ
ትጠይቁኛላችሁ? የሠራኋቸውን አማልክቴንና
ካህኔን ወስዳችሁ ሄዳችኋል፤ ምን የቀረኝ
ነገር አለ?" አላቸው::
25የዳን ሰዎች፣ "አትሚገተን፤ ያለዚያ
የተቈጡ ሰዎች ጉዳት ላይ ይጥሉሃል፤ አንተም
ቤተ ሰብህም ሕይወታችሁን ታጣላችሁ"
አሉት:: 26የዳን ሰዎች ይህን ብለው መንገ
ዳቸውን ቀጠሉ፤ ሚካም የማይችላቸው
መሆኑን በማየት ተመልሶ ወደ ቤቱ ሄደ::
27ከዚያም ሚካ የሠራውን ጣዖትና ካህኑን
ወስደው ወደ ላይሽ በመሄድ፣ በሰላምና ያለ
ስጋት ይኖር የነበረውን ሕዝብ በሰይፍ
መቱት፤ ከተማዪቱንም በእሳት አቃጠ
ሏት:: 28የሚኖሩት ከሲዶና በጣም ርቀው
ስለነበርና ከማንም ጋር ግንኙነት ስላልነበራ
ቸው የሚታደጋቸው አንድም አልነበረም፤
ከተማዪቱም የምትገኘው በቤትሮዓብ አጠ
ገብ ነበረ::
የዳንም ሰዎች ከተማዪቱን እንደ ገና
ሠርተው መኖሪያቸው አደረጓት:: 29ከተ
ማዪቱንም ከእስራኤል በተወለደው በአባታ
ቸው በዳን ስም ዳን ብለው ጠሯት፤ ቀድሞ
ግን ስሟ ላይሽ ይባል ነበር:: 30እዚያም የዳን
ሰዎች ለራሳቸው ጣዖታት አቆሙ፤ የሙሴ
ልጅ፣° የጌርሳም ልጅ ዮናታንና የእርሱም
ልጆች ምድሪቱ እስከ ተማረከችበት ጊዜ
ድረስ ለዳን ነገድ ካህናት ሆኗቸው፤ 31ስለዚ
ህም ሚካ የሠራቸውን ጣዖታት፣ የእግዚአብሔር
ቤት በሴሎ በነበረበት ጊዜ ሁሉ ባለማቋረጥ
አመለኳቸው::

18፥13 መሳ17፥1
18፥14 ዘፍ31፥19፤ ኢሱ19፥47፤ መሳ8፥27
18፥16 ቍ11
18፥17 ቍ11፤ ዘፍ31፥19፤ሚክ5፥13
18፥18 ቍ24፤ ዘፍ31፥19፤ ኢሳ46፥2፤ ኤር43፥11፤48፥7፤49፥3፤ሆሴ10፥5
18፥19 ዘኍ26፥42፤ መሳ17፥10፤ ኢዮ13፥5፤ 21፥5፤29፥9፤40፥4፤ ኢሳ52፥15፤ ሚክ7፥16
18፥24 ቍ17-18
18፥26 2ሳሙ3፥39 ፤ መዝ18፥17፤ 35፥10
18፥27 ዘፍ34፥25፤ 49፥47፤ዘኍ31፥10፤ ኢሱ19፥47
18፥28 ቍ7፤ ዘፍ10፥19፤ ዘኍ13፥21
18፥29 ዘፍ14፥14፤ ኢሱ19፥47፤ 1ነገ15፥20
18፥30 ዘፀ2፥22
18፥31 ቍ17፤ ኢሱ18፥1፤ መሳ19፥18፤ 20፥18፤ኤር7፥14

°30 ጥንታዊው የዕብራውያን ጸሓፍት ትውፊት፣ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም እንዲሁም የቩልጌት ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የማሶሬቱ ቅጅ ግን ምናሴ ይላል::

18፥19 ***አባትም፤*** የ17፥10 ማብ ይመ:: ***ነገድና ጐሣ፤*** ከዳን ነገድ ስሙ የተጠራ አንድ ጐሣ ብቻ ነው፤ ይኸውም ሹሐም የተባለው ነበር (ዘኍ26፥42)፤ ይህም በዘፍ46፥23 ላይ ሑሺም ተብሎአል:: የዳን ነገድ ሰዎች ሌዋውያን የማይጠቅማቸውና ከንቱ የሆነ ቍሳ ቍስ ጠየቁ::

18፥21 ***ወደፊት በማስቀደም፤*** ድንገት አደጋ ቢገጥማቸው ለመከላከል እንዲያመች ነው:: ስለ ያዕቆብና ኤሳው በዘፍ33፥2-3 የተጻፈውን ይመ::

18፥24 ***አማልክቴን... ወስዳችሁ፤*** ሚካን ያሳሰበው ራሳቸውን እንኳ ማዳን የማይችሉት ጣዖታት ስለ ተወሰዱበት ነው:: ***ምን የቀረኝ ነገር አለ?*** ይህ ተስፋ የመቍረጥ አነጋገር ሊጠቅሙ በማይችሉ ከንቱ አማልክት የሚታመን ሰው የሚያሰማው ሮሮ ነው::

18፥28 ***በቤትሮዖብ፤*** ምናልባት በዘኍ13፥21 ላይ ረአብ ተብሎ ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይ ሳይሆን አይቀርም::

18፥30 ***ዮናታን፤*** እዚህ ላይ ሌዋዊው፣ የጌርሳም ልጅ የሆነው የሙሴ ልጅ ዮናታን እንደ ሆነ ተጠቅሶአል (ዘፀ 2፥22፤ 18፥3፤1ዜና23፥14-15):: የሙሴን ስም እንዳያጐድፍ በማለት በኋለኛው ዘመን የተነሡ ጸሓፊዎች ይህን ስም ለውጠው "ምናሴ" ብለውታል:: ዮናታን የሙሴ የልጅ ልጅ ከሆነ በዚህ ምዕራፍ ላይ የተወሳው ታሪክ ቀደም ባለው በመሳፍንት ዘመን ተፈጽሞአል ማለት ነው (የ20፥1፡28ማብ ይመ):: ***ምድሪቱ እስከ ተማረከችበት ጊዜ ድረስ፤*** ይህ የምርኮ ዘመን መቼ እንደነበር በውል ተለይቶ የሚታወቅ ነገር የለም (ላይሽን በተመለከተ የቍ7 ማብ ይመ)::

18፥31 ***የእግዚአብሔር ቤት በሴሎ በነበረበት ጊዜ ሁሉ፤*** ኢሱ18፥1 ይመ:: ስለ ሴሎ መጥፋት መዝ 78፥60፤ ኤር 7፥21፡14፤ 26፥6 ይመ:: በሴሎ የተደረገው የሥነ ቅርስ ጥናት ምርምር ሴሎ በ1050 ዓ.ቅ..ክ መጥፋቷንና ለብዙ ምእተ ዓመታት ሰው አልባ ምድር እንደ ነበረች አረጋግጦአል::

*19፥1-21-25፤* ይህ የመጽሐፉ መደምደሚያ ሁለተኛው ትረካ ነው (የ17፥1-18፥31ማብ ይመ)፤ ይኸውም የጊብዓ ሰዎች የፈጸሙት ድርጊት እስራኤላውያን በሥነ ምግባር ረገድ ምን ያህል እንደወደቁ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው:: ከምእተ ዓመታት በኋላ እንኳ ሳይረሳ ቈይቶአል (ሆሴ9፥9፤10፥9):: የከተማዪቱ ክፋት ከሌሎቹ የከነዓን ከተሞች አንሶ ባይገኝም እግዚአብሔር በእስራኤላውያን አማካይነት ሊያጠፋቸው ፈልጐ ሳለ፣ የብንያም ነገድ ልጆች ግን የገዛ ወገኖችው እስኪያልቁ ድረስ ለጊብዓ ሰዎች በመርዳት ተዋጉ::

*19፥1-30፤* የሰዶም ሰዎች ክፉ ሥራ በአንድ የእስራኤል ከተማ እንደገና ተደገመ (ዘፍ 19 ይመ)::

## አንድ ሌዋዊና ቁባቱ

19 በዚያን ዘመን በእስራኤል ንጉሥ
አልነበረም፤ በዚሁ ጊዜም በኰረብ
ታማው በኤፍሬም አገር የሚኖር አንድ ሌዋዊ
ከይሁዳ ምድር ከቤተልሔም አንዲቱን ሴት
ቁባት አድርጎ ወሰዳት።
2ሴቲቱ ግን በታማኝነት አልጸናችም፤ ትታ
ውም በይሁዳ ምድር ወደሚገኘው ወደ
አባቷ ቤት ወደ ቤተልሔም ሄደች፤ እዚ
ያም አራት ወር ከቈየች በኋላ፣ 3ባሏ ታርቆ
ሊመልሳት ወደ እርሷ ሄደ፤ ሲሄድም አሽ
ከሩንና ሁለት አህዮችን ይዞ ነበር፤ ሴቲቱም
ወደ አባቷ ቤት አስገባችው፤ አባቷም ባየው
ጊዜ በደስታ ተቀበለው። 4የልጂቱ አባትም
እዚያው እንዲቈይ አጥብቆ ለመነው፤ ስለዚህ
እየበላ እየጠጣ ሦስት ቀን አብሮት ተቀመጠ።
5በአራተኛው ቀን ማልደው ተነሡ፤ እን
ግዳውም ለመሄድ ተዘጋጀ፤ የልጂቱ አባት
ግን፣ "እንድትበረታ እህል ቅመስ፤ ከዚያም
መሄድ ትችላለህ" አለው። 6ስለዚህ ሁለቱ
ለመብላትና ለመጠጣት አብረው ተቀመጡ።
የልጅቷም አባት፣ "እባክህ ዛሬም እዚሁ አድ
ረህ ተደሰት" አለው። 7ሰውየው ለመሄድ ሲን
ሣም ዐማቱ እንዲያድር ለመነውና እዚያው
አደረ። 8በአምስተኛውም ቀን ጠዋት ሌዋ
ዊው ለመሄድ ሲነሣ፣ የልጅቱ አባት
"ሰውነትህን አበርታ፤ ጥላው እስኪበርድም
ድረስ በዚሁ ቈይ" አለው፤ ስለዚህ ሁለቱም
አብረው በሉ።
9ሰውየውም ከቁባቱና ከአገልጋዩ ጋር
ለመሄድ በተነሣ ጊዜ፣ የልጅቱ አባት ዐማቱ
"እነሆ፣ ጊዜው እየመሸ ነው፤ እዚሁ እደሩ፤
ቀኑ እየተገባደደ ነው፤ እዚሁ አድራችሁ
ተደሰቱ፤ ነገ ጠዋት ማልዳችሁ በመነሣት
መንገዳችሁን ትሄዳላችሁ" አለው። 10ሌዋ
ዊው ግን በዚያች ሌሊት በዚያ ለማደር
ስላልፈለገ ተነሥቶ የተጫኑትን ሁለቱን
አህዮቹንና ቁባቱን ይዞ ኢየሩሳሌም ወደ
ተባለችው ወደ ኢያቡስ ሄደ።
11ወደ ኢያቡስ እንደ ቀረቡም ጊዜው
እየመሸ ስለ ነበር አገልጋዩ ጌታውን
"እንግዲህ ወደዚህች ወደ ኢያቡሳውያን ከተማ
ጐራ ብለን እንደር" አለው።
12ጌታውም፣ "አይሆንም፤ ሕዝቧ እስራ
ኤላዊ ወዳልሆነ ወደ ባዕድ ከተማ አንገባም፤
ወደ ጊብዓ አልፈን እንሂድ" አለው። 13ቀጥ
ሎም፣ "ብል ና፤ ወደ ጊብዓ ወይም ወደ ራማ
ለመድረስ እንሞክርና ከዚያ በአንዱ ስፍራ
እናድራለን" አለው። 14ስለዚህም መንገዳቸውን
ቀጠሉ፤ የብንያም ነገድ ወደ ሆነችው ወደ
ጊብዓ እንደ ደረሱም ፀሓይ ጠለቀች። 15ለማ
ደርም ወደዚያው ጎራ አሉ፤ ሄደውም በከተ
ማዪቱ አደባባይ ተቀመጡ፤ ሆኖም በቤቱ ለማ
ሳደር ማንም አልተቀበላቸውም ነበር።
16በዚያች ምሽት ከኰረብታማው ከኤ
ፍሬም አገር መጥቶ በጊብዓ የሚኖር አንድ
መጻተኛ ሽማግሌ ከዕርሻ ሥራው መጣ፤
የዚያ አገር ሰዎች ግን ብንያማውያን ነበሩ።
17ሽማግሌው ቀና ብሎ መንገደኛውን በከተ
ማዪቱ አደባባይ ላይ ባየው ጊዜ፣ "ከወዴት
መጣህ? ወዴትስ ትሄዳለህ?" ሲል ጠየቀው።
18ሰውየውም እንዲህ ሲል መለሰ፤ "እኛ
የመጣነው ከይሁዳ ቤተልሔም ርቆ ከሚገኘው
ከኰረብታማው ከኤፍሬም አገር ነው፤
ከይሁዳ ቤተልሔም ነበርሁ፤ አሁን ወደ
*እግዚአብሔር* ቤት እሄዳለሁ፤ ወደ ቤቱ
የሚወስደኝ ሰው አላገኘሁም። 19ለአህዮቻችን
ገለባና ገፈራ አለን፤ እኛ ባሮችህ ለእኔም
ሆነ ለገረድህ፣ አብሮን ላለውም ወጣት
እንጀራና የወይን ጠጅ ይዘናል፤ ሌላ ምንም
ነገር አያስፈልገንም።"
20ሽማግሌውም፣ "ኑ ግቡ በቤቴም እደሩ፤
የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አቀርባለሁ፤ በዐደ
ባባይ ግን አትደሩ" አለው። 21ስለዚህ ወደ
ቤቱ አስገብቶት ለአህዮቹ ገፈራ ሰጣቸው፤
እንግዶቹም እግራቸውን ታጠቡ፤ በሉ፤ ጠጡም።
22በግብዣው ላይ እየተደሰቱ ሳለ፣ ጥቂት
የከተማዪቱ ወስላቶች ቤቱን ከበቡ፤ በሩንም
እየደበደቡ፣ "ዝሙት እንድንፈጽምበት
ቤትህ የገባውን ሰው አውጣው" በማለት

19፥1 ቊ16፡18፤ሩት1፥1
19፥4 ቊ6፡8፤ ዘፀ32፥6
19፥5 ቊ8፤ ዘፍ18፥5
19፥6 መሳ16፥25
19፥10 ዘፍ10፥16፤ ኢሱ15፥8
19፥11 ዘፍ10፥16፤ ኢሱ3፥10
19፥13 ኢሱ18፥25
19፥14 ኢሱ 15፥57፤ 1ሳሙ 10፥29
19፥15 ዘፍ19፥2፤ 24፥23
19፥16 ቊ1፤ መዝ104፥23
19፥17 ዘፍ29፥4
19፥18 መሳ18፥31
19፥19 ዘፍ14፥18፤ 24፥25፤42፥27
19፥21 ዘፍ24፥32-33፤ሉቃ7፥44
19፥22 ዘፍ19፥4-5፤ዘዳ13፥13፤መሳ16፥25፤20፥5፤ ሮሜ1፥26-27

19፥1 ***ሌዋዊ፤*** በም17-18 ላይ ያለው "ሌዋዊ" ስሙ የተጠቀሰ ስለሆነ፣ የዚህኛው ሌዋዊ ስም ግን አልተጠቀሰም። ***ቁባት፤*** የዘፍ 25፥6 ማብ ይመ።

19፥3 ***በደስታ ተቀበለው፤*** ቁባቱ ትታው ወደ አባቷ ቤት መሄዷ ለቤተ ሰቡ ኀፍረት ሳይሆን አይቀርም፤ ሆኖም ሌዋዊው በመጣ ጊዜ በሰላም አብረው መኖር ይችላሉ ብሎ በማሰብ አባቷ ደስ አለው ማለት ነው።

19፥10 ***ኢያቡስ፤***1፥21 ይመ፤ እንዲሁም የዘፍ10፥16 ማብ ይመ።

19፥12 ***ወደ ባዕድ ከተማ፤*** ከተማዪቱን የሚቈጣጠሯት ኢያቡሳውያን በመሆናቸው፣ በእንግድነት እንደማይቀበሏትና ምናልባትም በሕይወታቸው ላይ አደጋ ሊደርስ እንደሚችል ሥጋት ሳያድርበት አልቀረም።

19፥14 ***የብንያም ነገድ ወደ ሆነችው ጊብዓ፤*** ይህች ጊ ብዓ በይሁዳ ካለችው ጊብዓ (ኢሱ15፥20:57) እንዲሁም በተራራ ማው የኤፍሬም ምድር ካለችው ጊብዓ (ኢሱ 24፥33) ጋር አንድ አይደ ለችም። የሳኦል መንግሥት ዋና ከተማ ስለነበረች፣ የሳኦል ጊብዓ ትባል ነበር (1ሳሙ11፥4፤13፥15) ይመ።

19፥15 ***በቤቱ...ማንም አልተቀበላቸውም፤*** የ13፥15 እንዲ ሁም የዘፍ 18፥2ማብ ይመ ።

19፥18 ***ወደ እግዚአብሔር ቤት፤*** በመሠረቱ ሌዋዊው ያሰበው፣ ለእግዚአብሔር የምስጋና መሥዋዕት ለማቅረብ ወይም ስለ ራሱና ስለ ቁባቱ የኀጢአት መሥዋዕት ለማቅረብ ወደ ሴሎ ለመሄድ ነበር (18፥31፤ኢሱ 18፥1 ይመ)።

19፥21 ***እግራቸውን ታጠቡ፤*** በጥንት መካከለኛ ምሥራቅ አገሮች፣ መንገደኛ ነጠላ ጫማ አድርጎ ይጓዝ ስለ ነበር በእግሩ ላይም አቧራ ስለሚኖር የመንገደኛውን እግር ማጠብ የተለመደ ነበር (ዘፍ18፥4፤24፥32፤43፥24፤ሉቃ 7፥44፤ዮሐ 13፥5-14ይመ)።

19፥22 ***ወስላቶች፤*** በዕብራይስጥ ቀጥታ ትርጒሙ መጋጦች ማለት ነው። ይህ ቃል ጣዖት ማምለክን (የዘዳ13፥13)፣ ስካርን (1ሳሙ1፥16) እና ዐመፅን (1ሳሙ2፥12) የሚገልጽ ነው፤ እዚህ ላይ ግን የሚያመለክተው ግብረ ሰዶማዊነትን ለመግለጽ ነው። ***የገባውን ሰው አውጣው፤*** የእነዚህ ወስላቶች ግብረ ሥጋ ፍላ ጐት፣ "እያንዳንዱ ሰው ለራሱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር" ለሚለው ሀረፍተ ነገር ጥሩ ማስረጃ ነው (17፥6፡21፥25)፤ የሰዶም ሰዎችም ይህን የመሰለ ጥያቄ አቅርበው ነበር (ዘፍ19፥5)። ግብረ ሰዶማዊነት በከነዓናውያን ዘንድ የተለመደ ነበር።

የቤቱ ባለቤት በሆነው ሽማግሌ ላይ ጮኹበት።
23የቤቱም ባለቤት ወደ ውጭ ወጥቶ
እንዲህ አላቸው፤ "የለም ወዳጆቼ፤ እንዲህ
አትሁኑ፤ ሰውየው እንግዳዬ ስለ ሆነ ይህን
አሳፋሪ ድርጊት አትፈጽሙ። 24እነሆ
ድንግል የሆነች ልጄና የሰውየው ቁባት
አሉ፤ እነርሱን አሁኑኑ ላውጣላችሁና አስነ
ውሯቸው፤ ያሻችሁንም አድርጉባቸው፤ በዚህ
ሰው ላይ ግን እንዲህ ያለውን አሳፋሪ ድርጊት
አትፈጽሙበት።"
25ሆኖም ሰዎቹ ሊሰሙት አልፈለጉም፤
ስለዚህ ሌዋዊው ቁባቱን ወደ ውጭ አወጣ
ላቸው፤ ሰዎቹም አመነዘሩባት፤ ሌሊቱን ሙሉ
ሲፈራረቁባት አድረው ጐሕ ሲቀድ ለቀቋት።
26በነጋም ጊዜ ሴቲቱ ጌታዋ ወዳለበት ቤት
ተመልሳ ሄደች። ደጃፉ ላይ ወድቃ ፀሐይ
እስክትወጣ ድረስ እዚያው ተዘረረች።
27ጌታዋ በጠዋት ተነሥቶ በሩን በመክፈት
መንገዱን ለመቀጠል ሲወጣ፣ ቁባቱ እጆዋን
ከደጃፉ መድረክ ላይ እንደ ዘረጋች ከቤቱ
በራፍ ላይ ተዘርራ ወድቃ አገኛት። 28ሌዋ
ዊውም፣ "በል ተነሺና እንሂድ" አላት፤ ነገር
ግን መልስ አልነበረም። ከዚያም በአህያው ላይ
ከጫናት በኋላ ወደ ቤቱ ጕዞውን ቀጠለ።
29ቤቱ እንደ ደረሰም ቢላዋ አንሥቶ ቁባ
ቱን ዐሥራ ሁለት ቦታ በመቈራረጥ ወደ
እስራኤል ምድር ሁሉ ሰደደ። 30ያየም
ሁሉ፣ "እስራኤላውያን ከግብፅ ከወጡ ጀምሮ
እንዲህ ያለ ነገር ከቶ አልታየም፤ አልተደ
ረገም፤ ምን ማድረግ እንዳለብንም በነገሩ
አስቡበት፤ ተመካከሩበት" ተባባሉ።

## እስራኤላውያን ከብንያማውያን ጋር ተዋጉ

20 ከዚያም ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ያሉ
እንዲሁም በገለዓድ ምድር የሚገኙ
እስራኤላውያን ሁሉ እንደ አንድ ሰው ሆነው
ወጡ፤ በምጽጳም በእግዚአብሔር ፊት ተሰበ
ሰቡ። 2የእስራኤል ሕዝብ ነገዶች ሁሉ
ቍጥራቸው አራት መቶ ሺህ በሚሆን፣

19፥23 ዘፍ19፥6፤ 34፥7፤ዘሌ19፥29፤ ኢሱ7፥15፤ መሳ20፥6፤ሮሜ1፥27
19፥24 ዘፍ19፥8
19፥25 መሳ20፥5፤ 1ሳሙ31፥4
19፥29 ዘፍ22፥6፤ መሳ20፥6፤ 1ሳሙ11፥7
19፥30 መሳ20፥7፤ ምሳ13፥10፤ ሆሴ9፥9
20፥1 ቍ11፤ ዘፍ21፥14፤ኢሱ11፥3፤መሳ21፥5፤1ሳሙ3፥20፤7፥5፤ 11፥7፤ 2ሳሙ3፥10፤17፥11፤ 24፥15፤1ነገ4፥25፤ 2ዜና30፥5
20፥2 1ሳሙ11፥8
20፥4 ዘፍ24፥23፤ ኢሱ15፥57
20፥5 መሳ19፥22፡ 25-26
20፥6 መሳ19፥23፡ 29፤2ሳሙ13፥12
20፥7 መሳ19፥30
20፥9 ዘሌ16፥8
20፥11 ቍ1
20፥12 ዘዳ13፥14
20፥13ዘዳ13፥5፡13 ፤1ቆሮ5፥13

ሰይፍ በሚመዙ እግረኞች ወታደሮች በሆኑ
በእግዚአብሔር ሕዝብ ጉባኤ መካከል አለቆች
ተገኙ። 3በዚህ ጊዜ ብንያማውያን፣ እስራ
ኤላውያን ወደ ምጽጳ መውጣታቸውን ሰሙ፤
ከዚያም እስራኤላውያን፣ "ይህ ክፉ ድርጊት
እንዴት እንደ ተፈጸመ እስቲ ንገሩን" ተባባሉ።
4ስለዚህ የተገደለችው ሴት ባል ሌዋዊ
እንዲህ ሲል መለሰ፤ "እኔና ቍባቴ በዚያ
ለማደር በብንያም ወደምትገኘው ወደ ጊብዓ
መጣን። 5የጊብዓም ሰዎች በሌሊት ሊገ
ድሉኝ ያደርኩበትን ቤት ከበቡት፤ ከዚያም
በቁባቴ ላይ ስለ አመነዘሩባት ሞተች። 6የቀ
ባቴንም ሬሳ ከቈራረጥሁ በኋላ እያንዳንዱን
ቍራጭ፣ እያንዳንዱ የእስራኤል ርስት
ወዳለበት አገር ሰደድሁ፤ ይህን ያደረጉትም
ሰዎቹ በእስራኤል ዘንድ አሠቃቂና አስነዋሪ
ድርጊት ስለ ፈጸሙ ነው። 7አሁንም እናንተ
እስራኤላውያን ሁሉ በጕዳዩ ላይ ተወያ
ዩበት፤ ፍርዳችሁንም ስጡ።"
8ከዚያም ሕዝቡ እንደ አንድ ሰው ሆነው
በመነሣት እንዲህ አሉ፤ "ከእኛ ማንም ሰው
ወደ ድንኳኑ አይሄድም፤ ማንኛችንም ወደ
ቤታችን አንመለስም። 9ነገር ግን በጊብዓ
ላይ የምናደርገው ይህ ነው፤ በዕጣው መሠ
ረት እንዘምትበታለን። 10ከመላው የእስራ
ኤል ነገዶችም ለሰራዊቱ ስንቅ እንዲይዙ
ከመቶው ዐሥር፣ ከሺው አንድ መቶ፣ ከዐ
ሥር ሺው ደግሞ አንድ ሺህ ሰው እንወ
ስዳለን። ከዚያም ሰራዊቱ በብንያም ወደም
ትገኘው ጊብዓ በሚደርስበት ጊዜ፣ ነዋሪዎችዋ
በእስራኤል ላይ ለፈጸሙት አስነዋሪ ድርጊት
ተገቢውን ቅጣት ይሰጣቸዋል።" 11ስለዚህ
የእስራኤል ሰዎች ሁሉ እንደ አንድ ሰው
ሆነው በመተባበር በከተማዪቱ ላይ ዘመቱባት።
12የእስራኤል ነገዶች ለመላው የብንያም
ነገድ እንዲህ በማለት መልእክተኞች ላኩ፣
"በመካከላችሁ የተፈጸመው ይህ ክፉ ድርጊት
ምንድነው? 13አሁንም እነርሱን ገድለን ይህን

19፥23 *እንዲህ አትሁኑ፤* ያልተለመደና አስነዋሪ ድርጊትን ለመግለጽ የሚነገር ኀይለ ቃል ነው (ዘፍ19፥7፤2ሳሙ 13፥12 እንዲሁም ሮሜ1፥27 ይመ)።

19፥24 *ድንግል የሆነች ልጄና የሰውየው ቁባት፤* የዚህ ታሪክ አስከፊ ገጽታ፣ ራሳቸውን መከላከል የማይችሉትን እነዚህን ሴቶች ሌሊቱን ሙሉ አስነዋሪ ድርጊት እንዲፈጽሙባቸው ለጨካኝ ወንዶች አሳልፎ መስጠታቸው ነው። ይህንም ሎጥ ለሰዶም ሰዎች አሳልፎ የሰጠበትን ሁኔታ ከዘፍ19፥8 ጋር ያነጻጽሩ።

19፥25 *አወጣላቸው፤* ግሡ፣ በዕብራይስጥ ማስገደድን የሚያ መለክት ነው።

19፥29 *የቁባቱን ሬሳ... በመቈራረጥ ፤* የቁባቱን አካል ቈራርጦ ለዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች መላኩ "ጉበዝ ተነሣ እንጂ! እንዲህ ያለ ጕድ ሲሠራ እንዴት ዝም ትላለህ" ማለቱ ነው (ከ1ሳሙ11፥7 ጋር ያነጻጽሩ)።

*20፥1-48፤* የጊብዓ ሰዎች እንዲህ ያለውን አሰቃቂ ድርጊት ስለ ፈጸሙ ከኢያቢስ ገላዓድ በስተቀር እስራኤላውያን በሙሉ በጊብዓ ሰዎች ላይ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለመመካከር በእግዚአብሔር ፊት ተሰበሰቡ፤ በመጀመሪያ የእግዚአብሔር ፈቃድ በመጠየቅ እርሱንም እንደ ንጉሣቸው አድርገው በመከተል የእግ ዚአብሔርን የቅጣት በትር ለማቅመስ በጊብዓ ሰዎችና በብንያማዎያን ላይ ዘመቱባቸው (ኢሳ 22፥11-34 ይመ)።

20፥1 *ከዳን እስከ ቤርሳቤህ፤* ከሰሜን (ዳን) እስከ ደቡብ (ቤርሳቤህ )ያሉትን እስራኤላውያን በሙሉ ለመግለጽ በተለምዶ የሚነገር አባባል ነው፤ (1ሳሙ 3፥20፤ 2ሳሙ 3፥10፤24፥2፤ 1ዜና 21፥2፤ 2ዜና 30፥5 ይመ)። ሆኖም ይህ አገላለጽ በዚህ ምዕራፍ ያለው ትረካ የተከናወነው የዳን ነገድ ወደ ሰሜን ከተጓዘ በኋላ ነው ማለት አይደለም (18፥27-29)፤ እንዲያውም ጸሐፊው ይህን መጽሐፍ የጻፈው፣ የዳዊት ሥርወ መንግሥት ከተጸፈ በኋላ ስለሆነ፣ በእርሱ ዘመን ያለውን አባባል በመጠቀሙ ብቻ ነው (ከመጽሐፉ መግቢያ፣ "ጸሐፊውና የተጻፈበት ዘመን" የሚለውን ይመ)። ስለዚህም አባባሉ ከኢያቡ ገላዓድ በስተቀር፣ እስራ ኤላውያን በሙሉ ከብንያም ወገን የቀሩትንና በጊብዓ ሰዎች ላይ ያደረሱትን ቅጣት ያመለክታል። ይህ ርምጃ የተወሰደው በቅድመ መሳፍንት ዘመን ሲሆን፣ የእስራኤል ምድር በተለያዩ ጐረቤቶቻቸው መገዛት ከመጀመሩ ጥቂት ቀደም ብሎ ነው (2፥8-9 ይመ)። *እንደ አንድ ሰው፤* ከቍ8፡11፤1ሳሙ7 ጋር ያነጻጽሩ። *በምጽጳ... ተሰበሰቡ፤* በሳኦል ዘመን የእስራኤል ነገዶች የሚሰበሰቡበት ቦታ ነው (1ሳሙ 7፥5-17)።

20፥9 *በዕጣ፤* የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ዕጣ መጣል የተለመደ ልማድ ነበረ፤ የዘፀ 28፥30፤ ዮሐ 1፥7፤ የሐሥ 1፥26 ማብ ይመ።

20፥10 *ዐሥር ... ሰው፤* ብዙ ቍጥር ላለው ሰራዊት የሚ ደረገው ድጋፍ በሚገባ የተደራጀ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ ነበር። አንዱ ሰው በግምባር ለሚሰለፉ ዘጠኝ ሰዎች ምግብ የማ ቅረብ ግዴታ ነበረበት።

ክፉ ድርጊት ከእስራኤል እንድናስወግድ፣
እነዚያን የጊብዓን ወስላቶች አሳልፋችሁ
ስጡን።”
ብንያማውያን ግን ወገኖቻቸውን እስራኤላው
ያንን አልሰሟቸውም ነበር፤ 14ስለዚህ እስራ
ኤላውያንን ለመውጋት ከየከተሞቻቸው
በአንድነት ወደ ጊብዓ መጡ። 15ብንያማው
ያንም ከመላው የጊብዓ ነዋሪዎች መካከል
ከተመረጡት ሰባት መቶ ሰዎች ሌላ፣
ሰይፍ የታጠቁ ሃያ ስድስት ሺህ ሰዎች በአንድ
አፍታ ከየከተሞቻቸው በተጨማሪ አሰባሰቡ።
16በእነዚህም ሁሉ መካከል እያንዳንዳቸው
ድንጋይ ወንጭፈው ጠጒር እንኳ የማይስቱ
ሰባት መቶ ምርጥ ግራኞች ነበሩ።
17እስራኤላውያን፣ ብንያማውያንን ሳይ
ጨምር ሰይፍ የታጠቁ አራት መቶ ሺህ
ተዋጊዎች አሰባሰቡ ።
18እስራኤላውያን ወደ ቤቴል" ወጡ፤
እግዚአብሔርንም፣ “ብንያማውያንን ለመውጋት
ከመካከላችን ማን ቀድሞ ይውጣ?” ሲሉ
ጠየቁ።
እግዚአብሔርም፣ “ይሁዳ ቀድሞ ይውጣ”
ብሎ መለሰ።
19በማግሥቱ ጠዋት እስራኤላዋያን ተነሥተው
በጊብዓ አጠገብ ሰፈሩ፤ 20የእስራኤል ሰዎች
ብንያማውያንን ለመውጋት ሄዱ፤ በጊብዓ
ለሚያደርጉትም ውጊያ ቦታ ቦታቸውን ያዙ።
21ብንያማውያን ከጊብዓ ወጡ፤ በዚያችም
ዕለት ከእስራኤላውያን ሃያ ሁለት ሺህ
ሰዎች ገደሉ። 22ይሁን እንጂ እስራኤላውያን
እርስ በርሳቸው ተበረታትተው በመጀመሪያው
ቀን ተሰልፈው በነበረበት ስፍራ ላይ እንደ
ገና ቦታ ቦታቸውን ያዙ። 23እስራኤላውያን
ወጥተው እስኪመሽ ድረስ በእግዚአብሔር ፊት
አለቀሱ፤ “ወንድሞቻችንን ብንያማውያንን
ለመግጠም እንደ ገና እንውጣን?” ብለው እግ
ዚአብሔርን ጠየቁ።
እግዚአብሔርም፣ “አዎን፤ ውጡና ግጠ
ሟቸው” ብሎ መለሰላቸው።
24በሁለተኛው ቀን እስራኤላውያን ወደ
ብንያማውያን ተጠጉ። 25በዚሁ ጊዜም ብንያ
ማውያን፣ እስራኤላውያንን ሊወጉ ከጊብዓ
ወጡ፤ እንደ ገናም በሙሉ ሰይፍ የታ
ጠቁ ዐሥራ ስምንት ሺህ ሰዎች ገደሉ።
26የእስራኤልም ሕዝብ ሁሉ ወደ ቤቴል
ወጡ፤ እዚያም እያለቀሱ በእግዚአብሔር
ፊት ተቀመጡ፤ በዚያን ቀን እስኪመሽ ድረስ
ጾሙ፤ በእግዚአብሔር ፊት የሚቃጠል
መሥዋትና የኅብረት መሥዋዕት" አቀረቡ።
27እስራኤላውያንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ
ጠየቁ፤ በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር የኪዳኑ
ታቦት እዚያው ነበር፤ 28የአሮን ልጅ፤ የአ
ልዓዛር ልጅ ፊንሐስም በፊቱ ይቆም ነበር።
እስራኤላውያንም፣ “ወንድሞቻችንን ብንያ
ማውያንን እንደ ገና ሄደን ጦርነት እንግጠ
ማቸው ወይስ ይቅር?” ሲሉ ጠየቁ።
እግዚአብሔርም፣ “ሂዱ፤ በነገው ዕለት በእ
ጃችሁ አሳልፌ እሰጣችኋለሁ” አላቸው።
29ከዚያም እስራኤላውያን በጊብዓ ዙሪያ
ድብቅ ጦር አኖሩ። 30በሦስተኛውም ቀን
ብንያማውያንን ለመውጋት ወጡ፤ ከዚህ በፊት
እንዳደረጉት ሁሉ ጊብዓን ለመውጋት ቦታ
ቦታቸውን ያዙ። 31ብንያማውያንም ሊገ
ጥሟቸው ወጡ፤ ከከተማዪቱም ርቀው እንዲ
ሄዱ ተደረጉ፤ እንደ በፊቱም እስራኤላው
ያንን ይገድሉ ጀመር። ከዚህ የተነሣም በሜ
ዳው እንዲሁም ወደ ቤቴልና ወደ ጊብዓ
በሚወስደው መንገዶች ላይ ሠላሳ ያህል
ሰዎች ወድቀው ነበር።
32ብንያማውያኑ፣ “እንደ በፊቱ ይኸው
ድል እያደረግናቸው ነው” አሉ፤ እስራኤላው
ያንም በበኩላቸው፣ “ወደ ኋላ እያፈገፈግን
ከከተማዪቱ ወደ መንገዶቹ እንዲርቁ እናድ
ርጋቸው” ይሉ ነበር።
33የእስራኤል ሰዎች በሙሉ ከነበሩበት
ቦታ አፈግፍገው በበኣልታማር ስፍራ ስፍራ
ቸውን ያዙ። ሽምቆ ይጠባበቅ የነበረው
የእስራኤል ጦር ደግሞ ካደፈጠበት ከጊብዓ
በስተ ምዕራብ' ካለው ቦታ ወጣ። 34ከዚያም
ከመላው እስራኤል የተውጣጣው ዐሥር ሺህ
ጦር በጊብዓ ላይ ፊት ለፊት አደጋ ጣለ።
ውጊያው ከመበርታቱ የተነሣም ብንያማው
ያን መጥፊያቸው እየቀረበ መምጣቱን ገና አላ
ወቁም ነበር። 35እግዚአብሔር ብንያምን በእ
ስራኤል ፊት መታው፤ በዚያችም ዕለት
እስራኤላውያን በሙሉ ሰይፍ የታጠቁ ሃያ
አምስት ሺህ አንድ መቶ ብንያማውያንን

"18 ወይም ወደ እግዚአብሔር ቤት "26 በትውፊት የሰላም መስዋዕት ይባላል። '33. አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች ቩልጌት ከዚህ ጋር ይስማማሉ ነገር ግን የዕብራይስጡ ቃል ትርጒም በትክክል አይታወቅም።

20፥16 መሳ3፥15
20፥18 ቍ23:28፤ ዘፍ49፥10፤ኢ ሱ12፥9፤መሳ1፥1፤18፥5:31
20፥23 ቍ18፤ ዘኍ14፥1፤ ኢሱ7፥6፤መሳ18፥5
20፥25 ቍ21
20፥26 ዘፀ32፥6፤ ዘሌ1፥3፤ዘኍ14፥1፤ መሳ21፥4፤ 2ሳሙ12፥21
20፥27 ዘኍ10፥33፤ መሳ18፥5
20፥28 ዘኍ25፥7፤ ዘዳ18፥5፤ ኢሱ2፥24
20፥29 ኢሱ8፥2
20፥31 ኢሱ8፥16፤ 16፥1
20፥32 ቍ39
20፥33 ኢሱ8፥19
20፥34 ቍ41፤ ኢሱ8፥14
20፥35 1ሳሙ9፥21

20፥13 ***እነዚያን...ወስላቶች አሳልፋችሁ ስጡን፤*** በመሠረቱ እስራኤላውያን ያቀረቡት ጥያቄ ትክክል ነበር፤ ፍላጐታቸውም ይህን አስነዋሪ ተግባር የፈጸሙትን ሰዎች ብቻ ለይቶ ለመቅጣት ነበር። ***ወስላቶች፤*** የዘዳ13፥13 ማብ ይመ። ***እንርሱን ገድለን፤*** የጊ ብዓ ሰዎች ኀጢአት የሞት ቅጣት የሚያስከትል በመሆኑ፣ ይህንንም በደል ለማስወገድ ራሷ እስራኤል ቅጣቱን በገዛ እጇ መፈጸም ይገባታል (ዘዳ13፥5፤17፥7፤ 19፥19-20 ይመ)።

20፥16 ***ግራኞች፤*** ብናያማዊው ናዖድ ግራኝ ነበር (3፥15)። ***ድንጋይ ወንጭፈው፤*** በዘመኑ የልብ የሚያደርስ መሣሪያ ነበር (1ሳሙ 17፥19)።

20፥18 ***ቤቴል፤*** በዚህ ጊዜ፣ የቃል ኪዳኑ ታቦትና ሊቀ ካህኑ ፊንሐስ በቤቴል ነበሩ (ቍ 26-28 ይመ)። ***እግዚአብ ሔርንም... ጠየቁ፤*** ካህናት በሚጠቀሙበት በኡሪምና በቱሚም ሊሆን ይችላል (የዘፀ 28፥30፤ የ1ሳሙ 2፥28 ማብ ይመ)። ***ማን ቀድሞ ይውጣ፤*** 1፥1-36 ይመ። ***ይሁዳ፤*** የ1፥2 ማብ ይመ።

20፥21 ***ከእስራኤላውያን ሃያ ሁለት ሺህ፤*** ቍጥራቸው ሃያ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ለሆነው ብንያማውያን ይህ ታላቅ ድል ነበር። ባጠቃላይ ሲታይ እያንዳንዱ ሰው አንዳንድ እስራ ኤላዊ ገድሎአል ለማለት ይቻላል።

20፥27 ***ታቦት፤*** በመጽሐፈ መሳፍንት ላይ ታቦት ተጠቅሶ የምናገኘው እዚህ ቦታ ብቻ ነው።

20፥28 ***ፊንሐስ፤*** በኢያሱ ዘመን በመገናኛው ድንኳን የሚ ያገለግል ካህን ነበር (ኢሱ22፥13)፤ ይህ ሰው እስካሁን በሕይወት ኖሮ ማገልገሉ፣ ይህ ድርጊት በዘመነ መሳፍንት መጀመሪያ ላይ የተፈጸመ ለመሆኑ ተጨማሪ ማረጋገጫ ነው (የቍ 1፥18፥30 ማብ ይመ)።

20፥29 ***ድብቅ ጦር አኖሩ፤*** 9፥32፤ ኢሱ 8፥2 ይመ።

20፥33 ***በዓል ትማር፤*** ቦታው የት እንደሚገኝ አይታወቅም።

ገደሉ:: 36ከዚህ የተነሣ ብንያማውያን ድል
መሆናቸውን ተረዱ::
በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን ጊብዓ ላይ
ባኖሩት ድብቅ ጦር ስለ ተማመኑ የተሸነፉ
በመምሰል ለብንያማውያን ቦታ ለቀቁ::
37ከዚያም ሸምቀው የነበሩት ሰዎች በድ
ንገት እየተወረወሩ ወደ ጊብዓ ገቡ፤ በየቦታው
ተሰራጭተውም መላዉቱን ከተማ በሰይፍ መቱ::
38የእስራኤል ሰዎች ያሸመቀው ጦር በከተ
ማዪቱ ውስጥ ከባድ የጢስ ደመና ምልክት
እንዲያሳዩ ተስማሙ፤ 39እስራኤላውያንም
ወዲያውኑ እንዲያፈገፍጉ ነበር::
ብንያማውያንን ማጥቃት እንደ ጀመሩ
ሠላሳ እስራኤላውያንን ስለ ገደሉ፣ "እንደ
መጀመሪያው የጦርነት ጊዜ እያሸነፍናቸው
ነው" አሉ:: 40ነገር ግን የጢሱ ዐምድ
ከከተማዪቱ መነሣት በጀመረ ጊዜ፣ ብንያማውያን
ወደ ኋላቸው ዞረው የመላዪቱ ከተማ ጢስ
ወደ ሰማይ ሲወጣ አዩ:: 41ከዚያም እስራ
ኤላውያን ዞረው አጠቋቸው፤ በዚህ ጊዜ
ብንያማውያን ጥፋት እንደ ደረሰባቸው ስላ
ወቁ እጅግ ደነገጡ:: 42ስለዚህም ጀርባ
ቸውን አዙረው ከእስራኤላውያን ፊት ወደ
ምድረ በዳው ሸሹ፤ ሆኖም ከጦርነት ማምለጥ
አልቻሉም፤ ከየከተሞቹ የወጡ እስራኤላ
ውያንም በዚያው ገደሏቸው:: 43ብንያማውያን
ንም ከበቧቸው፤ አሳደዷቸው፤ ከጊብዓ በስተ
ምሥራቅ ትይዩ ባለውም ስፍራ በቀላሉ[x]
አሸነፏቸው፤ 44በጦርነቱም ላይ ዐሥራ ስምንት
ሺህ ብንያማውያን ወደቁ፤ ሁሉም ምርጥ
ተዋጊዎች ነበሩ:: 45ብንያማውያን ጀርባ
ቸውን አዙረው በምድረ በዳው በኩል ወደ
ሬሞን ዐለት በሚሸሹበት ጊዜ፣ እስራኤላ
ውያን በመንገድ ላይ አምስት ሺህ ሰው ገደ
ሉባቸው፤ እስከ ጊድአምም ድረስ ተከታት
ለው ሁለት ሺህ ሰዎች በተጨማሪ ገደሉ::
46በዚያች ዕለት ሰይፍ የታጠቁ ሃያ
አምስት ሺህ ብንያማውያን በጦር ሜዳ
ወደቁ፤ ሁሉም ምርጥ ተዋጊዎች ነበሩ::
47ነገር ግን ስድስት መቶ ሰዎች ጀርባቸውን
አዙረው በምድረ በዳው ውስጥ ወዳለው
ወደ ሬሞን ዐለት ሸሹ፤ በዚያም አራት ወር
ተቀመጡ:: 48ከዚያም እስራኤላውያን ወደ
ብንያም ምድር ተመልሰው ከተሞቻቸውን
በሙሉ እንዲሁም እንስሳቱንና በዚያ ያገኙትን
ሁሉ በሰይፍ መቱ፤ በመንገዳቸው ያገኙትን
ከተማ ሁሉ በእሳት አቃጠሉ::

**ለብንያማውያን ሚስት ስለ ማግኘት**

21 እስራኤላውያን በምጽጳ፣ "ከእኛ አን
ድም ሰው ሴት ልጁን ቢጋብቻ ለብንያ
ማውያን መዳር የለበትም" በማለት ተማም
ለው ነበር::
2ሕዝቡ ወደ ቤቴል[ፀ] ሄደው በዚያም
እስከ ማታ ድረስ በእግዚአብሔር ፊት ተቀ
መጡ፤ ድምፃቸውንም ከፍ በማድረግ አም
ርረው አለቀሱ፤ 3እንዲህም አሉ፤ "የእስራ
ኤል አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤ ይህ ለምን
በእስራኤል ላይ ሆነ? ዛሬ ከእስራኤል አንድ
ነገድ እንዴት ይታጣ?"
4በማግሥቱ ጠዋት ሕዝቡ መሠዊያ ሠሩ፤
የሚቃጠል መሥዋዕትና የኅብረት መሥዋዕት[1]
አቀረቡ::
5በምጽጳ፣ በእግዚአብሔር ጉባኤ ፊት
ያልተገኘ ማንኛውም ሰው መገደል አለበት
ብለው እስራኤላውያን ተማምለው ስለ ነበር፣
"ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ በእግዚአብሔር
ፊት ሳይወጣ የቀረ ማን አለ?" ሲሉ ጠየቁ::
6በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን ስለ ወንድ
ሞቻቸው ስለ ብንያማውያን በማዘን እንዲህ
አሉ፤ "ዛሬ ከእስራኤል ነገዶች አንዱ ታጥቷል፤
7ሴቶች ልጆቻችንን ለእነዚህ ብንያማውያን
በጋብቻ ሳንሰጥ በእግዚአብሔር ስለ ማልን
ለተረፉት እንዴት ሚስት ልናገኝላቸው እን
ችላለን?" 8ከዚያም፣ "ከእስራኤል ነገዶች
ምጽጳ ላይ በእግዚአብሔር ጉባኤ ፊት ሳይ
ወጣ የቀረ ማን ነው" ሲሉ ጠየቁ፤ ታዲያ
ከኢያቢስ ገለዓድ አንድም ሰው ለጉባኤው
ወደ ሰፈሩ አለመምጣቱን ተረዱ፤ 9ሕዝቡን
ሲቈጥሩም ከኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች አንድም
ሰው አልነበረምና::
10ስለዚህ ዐሥራ ሁለት ሺህ ተዋጊዎች
ወደ ኢያቢስ ገለዓድ ሄደው በዚያ የሚኖሩትን

20፥36 ኢሱ8፥2:15
20፥37 ኢሱ8፥19
20፥38 ኢሱ8፥4-8:20
20፥39 ቍ32፤ መዝ78፥9
20፥40 ኢሱ8፥20
20፥41 ቍ34፤ ኢሱ8፥21
20፥44 1ሳሙ10፥26፤ መዝ76፥5
20፥45 ኢሱ15፥32
20፥46 1ሳሙ9፥21
20፥48 መሳ21፥23
21፥1 ቍ18:22፤ ኢሱ9፥18፤11፥3
21፥2 ቍ6፥17
21፥4 መሳ20፥26
21፥5 መሳ20፥1
21፥7 ኢሱ9፥18
21፥8 1ሳሙ11፥1፤31፥11፤2ሳሙ2፥4፤21፥12፤1ዜና10፥11

[x]43. የዕብራይስጡ ቃል ትርጕም በትክክል አይታወቅም::
[ፀ]2. ወይም *ወደ እግዚአብሔር ቤት*
[1]4. በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል::

*20፥36-45* በቍ 29-36 የተነገረው ታሪክ በዚህ ላይ በዝርዝር ቀርቧል::

20፥46 ***ሃያ አምስት ሺህ፤*** ይህ ቍጥር የተጻፈው ተጠጋግቶ ነው፤ ትክክለኛ ቁጥሩ ሃያ አምስት ሺህ አንድ መቶ ነው (ቍ35)::

20፥47 ***ስድስት መቶ ሰዎች፤*** እነዚህ ባያመልጡ ኖሮ ከብንያም ነገድ ሰው ፈጽሞ ይጠፋ ነበር:: ብዛታቸው ይህንኑ የሚህል የዳን ወገን ሰዎች ወደ ላይሽ ሄደዋል (18፥11)::

*21፥1-25፤* ብንያማውያን ወንድሞቻቸው በጦርነት አልቀው፣ የተረፉት ጥቂት ወንዶች ብቻ ስለ ነበሩ እስራኤላውያን አዘኑላቸው:: ከዚህም የተነሣ፣ የብንያም ነገድ ጨርሶ ከምድር ገጽ እንዳይጠፋ፣ እስራኤላውያን ከገለዓድ ሰዎች አራት መቶ ልጃገረዶችን ነጥቀው በማምጣት ለአራት መቶ ብንያማውያን ወንዶች ሚስቶች እንዲሆኗቸው ሰጧቸው::

21፥1 ***ተማምለው ነበር፤*** ምናልባትም ይህ በእግዚአብሔር ስም የተደረገ መሐላ እንጂ ተራ መሓላ ስላልሆነ፣ መሐላውን ባፈረሰ ሰው ላይ ርግማን የሚያስከትል ሳይሆን አይቀርም (ቍ18፤ እንዲሁም ሐሥ 23፥12-15 ይመ)::

21፥2 ***ቤቴል፤*** 20፥18:26-27 ይመ:: ***አምርረው አለቀሱ፤*** ቀደም ሲል እስራኤላውያን በብንያም ነገድ ሰዎች በመሸነፋቸው አልቅሰው ነበር (20፥23:26):: አሁን ደግሞ በብንያማውያን ላይ የፈጸመው ቅጣት ከእስራኤል ነገዶች አንዱ የሆነውን የብንያም ነገድ ጨርሶ ሊጠፋ በመቃረቡ አለቀሱ (ቍ3 ይመ)::

21፥5 ***ሳይወጣ የቀረ፤*** ወደ ጦርነት ለመዝመት አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ፣ እያንዳንዱ ነገድ በጦርነቱ የመካፈል ግዴታ ነበረበት (የ5፥13-18ማብ ይመ):: በጦርነቱ ሳይካፈሉ የቀሩትን ለይቶ በማውጣት እንዲቀጡ ይደረጋል፤ (5፥15-17:23):: ***ተማምለው ስለ ነበር፤*** እስራኤላውያን በጦርነቱ ላይ ያልተገኘ እንዲገደል ብለው የተማማሉት በዚህ ሁኔታ ግራ ስለተጋቡ ነበር::

21፥10 ***ዐሥራ ሁለት ሺህ፤*** ከየነገዱ አንዳንድ ሺህ ማለት ሲሆን (ዘኍ31፥6ይመ)፣ ይህም የብንያምን ነገድ ለመተካት የተደረገ ነው::

በሙሉ ሴቶቹንና ሕፃናቱን ጭምር በሰይፍ
እንዲፈጇቸው ጉባኤው መመሪያ ሰጥቶ ላካ
ቸው:: [11]እነርሱም፣ “እንግዲህ የምታደር
ጉት ይህ ነው፤ ወንዱን በሙሉ እንዲሁም
ድንግል ያልሆኑትን ሴቶች ሁሉ ግደሉ”
አሏቸው:: [12]በኢያቢስ ገለዓድ ከሚኖረው
ሕዝብ መካከል ወንድ ያልደረሰባቸው አራት
መቶ ደናግል አገኙ፤ በከነዓን ምድር በሴሎ
ወደሚገኘውም ሰፈር አመጧቸው::
[13]ከዚያም ጉባኤው በሙሉ በሬሞን
ዐለት ወዳሉት ብንያማውያን የሰላም ጥሪ
አስተላለፈ:: [14]ስለዚህ በዚህን ጊዜ ብንያ
ማውያን ተመለሱ፤ ከመገደል የተረፉትንም
የኢያቢስ ገለዓድ ሴቶች ሰጧቸው፤ ይሁን
እንጂ የሴቶቹ ቍጥር ለሁሉም የሚበቃ
አልነበረም:: [15]*እግዚአብሔር* በእስራኤል
ነገዶች መካከል አስደንጋጭ ስብራት ስላ
ደረገ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለብንያማውያን
አዘነ:: [16]የጉባኤውም መሪዎች እንዲህ አሉ፤
“እነሆ፤ የብንያም ሴቶች አልቀዋል፤ ታዲያ
ለቀሩት ወንዶች ሚስት የምናገኝላቸው
እንዴት ነው? [17]ከእስራኤል ነገዶች አንዱ
የሆነው እንዳይጠፋ አሁን በሕይወት ያሉት
ብንያማውያን ወራሽ የሚሆን ዘር ሊኖ
ራቸው ይገባል:: [18]‘ልጁን ለብንያማዊ
የሚድር ርጉም ይሁን’ ብለን እኛ እስራኤላ
ውያን ስለ ተማማልን እንግዲህ ልጆቻች
ንን ልንድርላቸው አንችልም፤ [19]ይሁን እንጂ
ከቤቴል በስተ ሰሜንና ከቤቴል ወደ ሴኬም
በሚወስደው መንገድ በስተ ምሥራቅ እንዲ
ሁም ከለቦና በስተ ደቡብ ባለችው በሴሎ
የእግዚአብሔር በዓል በየዓመቱ ይከበራል::”
[20]ስለዚህም ለብንያማውያን እንዲህ ሲሉ
መመሪያ ሰጧቸው፤ “ሂዳችሁ በወይኑ የአ
ትክልት ስፍራ ተደበቁ፤ [21]አድፍጣችሁ
ተጠባበቁ:: የሴሎ ልጃገረዶች ለጭፈራ ወደ
ዚያ በሚወጡበት ጊዜ፣ ከወይኑ አትክልት
ቦታ ወጥታችሁ ከልጃገረዶቹ ለየራሳችሁ
ሚስት ጥለፉ፤ ወደ ብንያምም ምድር ሂዱ::
[22]አባቶቻቸውም ሆኑ ወንድሞቻቸው ቢቃወሙ፣
‘በጦርነት ጊዜ ለእያንዳንዳቸው የሚሆኑ
ሚስቶች ስላላገኘን ነውና እነርሱን በመርዳት
ምሕረት አድርጉልን፤ እናንተም ደግሞ
ልጆቻችሁን ፈቅዳችሁ ያልዳራችሁ በመሆናችሁ
በደለኞች አትሆኑም’ እንላቸዋለን::”
[23]ብንያማውያን እንደ ተባሉት አደረጉ፤
ልጃገረዶቹ በሚጨፍሩበትም ጊዜ እያንዳንዱ
ሰው አንዳንድ እየጠለፈ ሚስት እንድትሆነው
ይዞ ሄደ፤ ከዚያም ወደ ርስታቸው ተመለሱ፤
ከተሞቻቸውንም አድሰው በዚያ ኖሩ::
[24]በዚያን ጊዜ እስራኤላውያን ያን ቦታ
ትተው ወደየቤታቸው፣ ወደየርስታቸው፣ ወደ
የጐሣቸውና ወደየነገዳቸው ሄዱ::
[25]በዚያን ዘመን በእስራኤል ንጉሥ
አልነበረም፤ እያንዳንዱም ሰው መልካም
መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር::

21፥11 ዘኍ31፥7፡ 17-18
21፥12 ኢሱ18፥1
21፥13 ዘዳ2፥26፤ ኢሱ15፥32
21፥15 ቍ6
21፥17 ቍ3
21፥18 ቍ1፤ ኢሱ9፥18
21፥19 ኢሱ16፥1፤ 17፥7፤18፥1
21፥21 ዘፀ15፥20
21፥22 ቍ1
21፥23 ቍ21፤ ኢሱ24፥28፤ መሳ20፥48
21፥25 ዘዳ12፥8

21፥11 ***ወንዱን በሙሉ...ግደሉ፤*** በኢያቢስ ገለዓድ ላይ የተፈጸመው ቅጣት ዘግናኝ ቢሆንም፣ ይህን ቅጣት በፈጸሙት ነገዶች መካከል የነበረው የቃል ኪዳን ትስስር ግን እጅግ አስፈላጊ ነበር፤ ምንም እንኳ ሕገወጥ ድርጊት ቸል እየተባለ ቅጣት ሳይፈጸም ቢቀርም (5፥15-17)፣ እዚህ ላይ የተፈጸመው ድርጊት ብንያ ማውያን ወንጀለኞቹን አሳልፎ ለመስጠት ፈቃደኞች ካለመሆና ቸው የተነሣ እስራኤላውያን ይህን መሐላ ለመማል ተገደው ነበር (ቍ 5)::

21፥12 ***በከነዓን፤*** ልጃገረዶቹን ያመጧቸው ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ ካለው አገር መሆኑን በአጽንዖት ይገልጻል::

21፥19 ***የእግዚአብሔር በዓል፤*** የወይን ተክል ስፍራ ከመጠቀሱ አንጻር (ቍ 20) ምናልባት ጊዜው የዳስ በዓል የሚከበርበት ወቅት መሆኑን ሊያመለክት ይችላል (የ1ሳሙ 1፥3 ማብ ይመ):: ***ከቤቴል በስተ ሰሜን ... ከለቦና በስተ ደቡብ፤*** የሴሎ ከተማ ስለ ነበረችው ስለዚህ ስፍራ የተሰጠው ይህ ዝርዝር መግለጫ፣ ይህ መጽሐፍ የተጻፈው ሴሎ በፈረሰችበት ዘመን ምናልባትም በአፌቅ ጦርነት ከተካሄደና ሴሎ ከተደመሰሰች በኋላ መሆኑን ይጠቍማል (1ሳሙ 4፥1-11)::

21፥21 ***ሚስት ጥለፉ፤*** ብንያማውያኑ በዚህ ሁኔታ ሚስት ለማግኘት ቢችሉም፣ ሌሎቹ ነገዶች ግን ልጆቻቸውን ሊያጋቧቸው አልፈለጉም ነበር (የቍ 22 ማብ ይመ)::

21፥22 ***አባቶቻቸው ሆኑ ወንድሞቻቸው ቢቃወሙ፤*** አንዲት ልጃገረድ ተገዳ ከተወሰደች ወንድሞቿ መበቀላቸው የተለመደም ነበር (ዘፍ34፥7-31፤ 2ሳሙ13፥20-38 ይመ)፤ ስለዚህም ሽማግሌዎቹ የልጃገረዶቹን ወላጆች የሚሰጡትን መልስ ከወዲሁ ማዘጋጀት ነበረባቸው::

21፥24 ***ወደየቤታቸው፤*** ምናልባት እነዚህ ወታደሮች ከቤታቸው ከወጡ አምስት ወር ገደማ ሳይሆናቸው አይቀርም (20፥47 ይመ)::

21፥25 ***በእስራኤል ንጉሥ አልነበረም፤*** የ17፥6 ማብ ይመ::